www.zeyeneta.com

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

<<የተወደዳችሁ የልዑል እግዚአብሔር ቤተ ሰቦች÷
የቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ወዳጆች ሁላችሁም>>

የጥንታዊው ታሪክና የሥልጣኔ ዋና ምንጭ የሆነችው
አርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ከጥንት
ጀምራ እምነቷ እንዲስፋፋና እንዲጠናከር፣

የእምነቷ ተከታዮች ሕዝበ ክርስቲያንም በሥጋዊውም ሆነ
በመንፈሳዊው ትምህርትና ዕውቀት እየተኩተኩቱ፣ እንዲያድጉና
በመልካም ስነ ምግባር እንዲኰትቱ ከፍተኛውን ጥረት
ስታደርግ ኖራለች።

አሁንም የእምነቷ ተከታይ ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ መንፈሳዊውንና
ሀገራዊውን ታሪኩ ከመሠረቱ በማወቅ ሃይማኖቱን፣ ሥርዓቱንና
ባህሉን እንዲጠብቅ፣ በሰላም፣ በፍቅርና በአንድነት ሆኖ እየተረዳዳ
እንዲኖር በመጻሕፍትም ሆነ በአባቶች፣ በካህናትና በምሁራን
ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አማካይነት እያስተማረች፣ እየመከረች
ትገኛለች።

ተከታዮቿም ከጊዜ ወደ ጊዜ በዕውቀት እየበለፀጉ፣ በጥበብና
በአመለካከት እያደጉ፣ በቍጥርም እየበዙ በመሔድ ላይ እንደሆኑ
ግልጽ ነው።

ይሁን እንጂ አብዛኛው ኅብረተሰብ÷ በተለይም በውጭ ሀገር
የሚገኘው ወጣቱ ትውልድ የራሱን እምነት፣ ታሪኩን፣ ቋንቋውንና
ባህሉን እንዳያውቅ የሚኖርበት አካባቢና ሁኔታው ሁሉ ተፅዕኖ

www.zeyeneta.com

ስለሚያደርግበት የሃይማኖቱና የሀገሩ ጉዳይ ብዙውንም የሚያስፈልገውና የሚያሳስበው መስሎ አይታይም።

ቀደም ብሎ በግእዝ ቋንቋ የተጻፈው ማንነቱን የሚያስረዳው ጥንታዊው የሀገሩ ታሪክም የሚመለከተው አይመስልም።

በመሆኑም ሁሉም ጎብረተሰብ፥ በተለይም ደግሞ የተሟላ ዕውቀት ያላችሁ ወገኖችና ወላጆች፥ የሃይማኖትና የሀገር ተረካቢዎች የሆኑ ልጆቻችሁ መንፈሳዊውንና ሀገራዊውን ታሪካቸው በውል እንዲገነዘቡ፥

ምን ጊዜም የማይነዋወጠውን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖታቸውንና ሥርዓቱን ሁሉ ከመሠረቱ በመረዳት በእምነታቸው እንዲፀኑ፥

ስለ ቤተ ክርስቲያናቸውና ስለሀገራቸው ታሪክ፣ ስለ ባህሉና ስለ ሥርዓቱም ሁሉ አመች በሆነ ጊዜና ቦታ እየተገኙ በሀገራቸው ቋንቋ፥ ከተቻለ የግእዝንም ቋንቋ በመማር በግእዝ ቋንቋም ጭምር እርስ በእርሳቸው እንዲወያዩ ታደርጉ ዘንድ በታላቅ ትሕትና ሆኜ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ስም አሳስባለሁ።

ከዋና አዘጋጁ መምህር ሰሎሞን ገብሩ።

1998 (2006)

Po.box 41435
Arlington, VA, 22204።

U.S

ይህ ፍሬ ሕይወት (የሕይወት ፍሬ) የተሰኘው የኦርቶዶስ ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እምነትንና ሥርዓተ ሃይማኖትን የጠበቀ መጽሐፍ፥ ምግበ ነፍስ (ለነፍስ ምግብ) የሚሆን፣ ፍጹም ሕይወትን የሚሰጥ መንፈሳዊ ሲሳይ (ልዩ ምግብ) ያለበት ሲሆን፥

<<ሀ>> ስለ ልደት፣ ጥምቀት፣ ግዝረትና የመሳሰለውም፣

<<ለ>> ስለ ቃና ዘገሊላና መሠረታዊ ምሥጢሩ፣

<<ሐ>> ስለ ጠቅላላ ጸምና ሰብዓቱ (7ቱ) አጽዋማት፣

<<መ>> ስለ ንስሓና አፈጻጸሙ ሁሉ፣

<<ሠ>> ስለ ሰንበት ትርጉም፣ ስለ ቀዳሚት ሰንበትና ሰንበተ ክርስቲያን፣ በዐቢይ ጸም ውስጥ ስለሚገኙ ሰንበታትና ሥርዓታቸው፣ መሠረታዊ ሥጢራቸውም ሁሉ፥

<<ረ>> ስለ ሆሳዕና፣ ስለ ዕለታት፣ ስለ ሰሙነ ሕማማት፣ ስለ ጸሎተ ሐሙስ፣ ዓርብ ስቅለት፣ ቅዳሜ ሥዑርና ትንሣኤ (ፋሲካ)

<<ሰ>> ስለ ዕርገትና ስለ ጰራቅሊጦስ (በዐለ መንፈስ ቅዱስ)

በአጠቃላይ ስለ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከትስብእቱ (ከጽንሰቱ) ጀምሮ እስከ ዕርገቱ ያለው ሒደትና ምሥጢር፣

<<ሸ>> ስለ እምነትና አፈጻጸሙ ሁሉ፥

<<ቀ>> ስለ እምነት፣ ጥምቀተ ክርስትና እና ጠቅላላ ሥርዓቱ፥

<<በ>> ስለ ታቦትና መሠረታዊ ሥርዓቱ፥

<<ተ>> ስለ መናፍቃንና የሃይማኖት ክፍፍል ምክንያት

<<ቸ>> ስለ ክርስትና እና እስልምና ልዩነት፣

<<ኀ>> እኛ ሕዝበ ክርስቲያን ማድረግ ስለሚገባን፥

<<ነ>> ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፣ ወላዲተ አምላክ ፍጹም ንጽሕና፣ ቅድስና እና መመረጥ፥ እንዲሁም የውርስ ኃጢአትና ነውር፣ በዘመናችን ጥንተ አብሶ

www.zeyeneta.com

የሚባለውም አለመኖር፥ ስለ ቅዱሳን አማላጅነት፣ የሚመለከትንና ሌሎች ንዑሳን ከፍሎችንም የያዘ ሆኖ፥ ከብሉያትና ከሐዲሳት ቅዱሳት መጻሕፍት ተቀነባብሮ፥ አስፈላጊ የሆኑትን ምሥጢራት እያስገባ አንዱን ከሌሌላው ጽሑፍ ጋር እያገናዘበ፣ በአበው (በአባቶች) ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ የሚነገረውንና በመሠረታዊው ትርጓሜ የሚኘውን ምሥጢር እያብራራ፣ ለተጠቃሚው ጎብረተሰብ በሚያመች መንገድ እየገለጸ የሚሔድ፥ ለጠያቂዎችም ሆነ ለመናፍቃን ትክክለኛውን መልስ በተገቢው መንገድ የሚነግርና የሚያስረዳም ነው።

እም ይህ ፍሬ ሕይወት (የሕይወት ፍሬ) የተሰኘ መንፈሳዊ መጽሐፍ በብሉያትና በሐዲሳት ቅዱሳት መጻሕፍት ያሉትን፣ ከአሁን ቀደም በልዩ ልዩ አባቶችና ምሁራን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የተጻፉትንም በጥቅስና በመሠረታዊ ታሪክ መልክ አስገብቷል፣ ማብራሪያቸውንም ሰጥቷል።

ይኸውም ጎብረተሰቡ ቀደም ብለው የተጻፉትንም አፈላልጎ እንዲመለከታቸው ለማስታወስና በተለይም ደግሞ ጸሓፊዎች፣ ባለውለታዎቻችን አባቶቻችንና ምሁራን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን ለማዘከርም ጭምር ነው።

መጽሐፉ ሁሉም መንፈሳዊ ጎብረተሰብ እንዲገለገልበት ታስቦ ብዙ ጥረት ተደርጎበት በእግዚአብሔር መልካም ፈቃድ የተዘጋጀ ሲሆን፥ በብዙኃን (በብዙ) ምሁራንና ሕዝበ ክርስቲያን ዘንድ መልካም ተወዳጅነትና ፈጣን ተቀባይነት በማግኘቱ ሁለተኛ እንዲታተም ከአያሌዎች ወገኖች ተደጋጋሚ አስተያየት በቀረበው መሠረት ይኸውና አንዳንድ የፊደላት ግድፈቶችና ጥቃቅን ጒድለቶች ተስተካክለው፣ ታርመው፣ አስፈላጊ የሆነም ታክሎበት ለሁለተኛ ጊዜ ታትሞ በመንፈሳዊ ስርጭትና አገልግሎት ላይ ይገኛል።

የመጽሐፉ ተጠቃሚዎች ሁሉ ያልገባን ካለ እየጠየቅን፣ በማውጫ ገጹ መሠረት እየተመራን እንድንመለከተው፥ እንደዚሁም ደግሞ የኮምፒዩተር (የፊደል) ግድፈት፣ የቃላት ስሕተትና ግልፅ ያልሆነ ካለውም ወደፊት በሚቀጥለው ሦስተኛ ኅትመቱ በበለጠ ተስተካክሎና ታርሞ እንዲዘጋጅ ለማድረግ ያመች ዘንድ ጠቃሚ የሆነውን ሐሳባችሁ ከዚሁ በተጠቀሰው አድርሻ እንድትልኩልኝ በፍጹም ትሕትና እና በታላቅ አክብሮት በእግዚአብሔር ስም አሳስባለሁ።

ከዋና አዘጋጁ መምህር ሰሎሞን ገብሩ።

ማውጫ፥

መክሥተ አርእስት፥

<<ገጽ>>

<<ማሳሰቢያ>> >> 1

<<መግቢያ>> >> 3

መክሥተ አርእስት፥ (ማውጫ) >> 5

መቅድም፥ ልዩ መግለጫና ማብራሪያ >>>9

ምዕራፍ 1 <<<ልዩ ከፍል ስለ ልደት>>>15

ምዕራፍ 2 ስለ ጌታችን ልደትና ምሥጢሩ>>>>16

ክፍል 1 <ሀ> ከጌታችን ልደት በፊት የነበረው ሁኔታ >> 16
ክፍል 2 <ለ> ከልደቱ በፊት ከተነገሩት መካከል>>>> 19
ክፍል 3 <ሐ>የቅዱስ ገብርኤል ብሥራትና ምሥጢሩ >> 22
ክፍል 4 <መ> <<የልደቱ ምሥጢርና ፍጻሜው>> >> 26
ክፍል 5 <ሠ> <<እኛ ልናደርገው የሚገባን>>>>>> 32
ክፍል 6 <ረ> <<የጌታችን ዘመነ ልደት ሲተነተን >> 37

ምዕራፍ 3፥ <<<<<ጥምቀት>>>>>> 40

ክፍል 7 <ሀ> << የጥምቀት ትርጉምና ምሥጢሩ>>>>> 41
ክፍል 8 <ለ> ስለ ጥምቀት በብሉይ ከተነገሩት መካከል>> 41
ክፍል 9 <ሐ><< ጥምቀትና ጥቅሙ በሐዲስ ኪዳን>>>> 43
ክፍል 10 <መ> ወንድ በ40 + ሴት በ80 ቀን መጠመቃቸው>> 45
ክፍል 11 <ሠ> <<ስለ ግዝረት አመጣጥና ጥቅሙ >>> 45

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ 4 ክፍል 12 <ረ> የጌታችን ጥምቀት>> 46

ክፍል 13 <ሰ> የታቦታት ወደ ባሕረ ጥምቀት መውረድ>> 47
ክፍል 14 <ሸ> ጥምቀቱን በዮርዳኖስ ያደረገበት ምሥጢር>> 47

ምዕራፍ 5÷ <<<<ቃና ዘገሊላ>>>>>> 53

ክፍል 16÷ <<ቃና ዘገሊላና የቃና ዘገሊላ ምሥጢር >> 55

ምዕራፍ 6÷ <<<<<ጸምና ጸሎት>>>>> 59

ክፍል 17÷ <ሀ> ጸም ማለት ምን ማለት ነው ? >> 60
ክፍል 18÷ <ለ> አፈጻጸሙስ ? <ሐ> ጸሎትስ? >> 61
ክፍል 19÷ <መ> ጸም, ጸሎት ለምን ይጠቅማል? >> 64
ክፍል 20÷ <ሠ> << ጸም በብሉይ ኪዳን>> >> 65
ክፍል 21÷ <ረ> << ጸም በሐዲስ ኪዳን>> >> 67
ክፍል 22÷ <ሰ> <<በቀኖናችን የተመደቡት አጽዋማት>> 69
ክፍል 23÷ <ሸ> <<ዐቢይ ጸም÷ ዐቢይ ጸም ማለት >> 71
ክፍል 24÷ <ቀ> <<ዘወረደ>> ዘወረደ ማለት÷ >> 72
ክፍል 25÷ <በ> <<የዘወረደ ጸም>> >> 73
ክፍል 26÷ <ተ> << ጸም እስከ ስንት ሰዓት ነው ? >> 76

ምዕራፍ 7÷ ቸ <<<<<<ንስሓ>>>>>>>78

ክፍል 27÷ <<ንስሓ በብሉይ ኪዳን>> >> 79
ክፍል 28÷ <<ንስሓ በሐዲስ ኪዳን>> >> 80

ምዕራፍ 8÷ ኀ <<ሰንበትና ምሥጢሩ>>>84

ክፍል 29÷ ቅዳሜና መሠረታዊ ምሥጢሩ >> 85
ክፍል 30÷ ሰንበተ ክርስቲያን (እሑድ) እና ምሥጢሩ >> 86

ምዕራፍ 9÷<<የዐቢይ ጸም ሰንበታት>>>> 88

ክፍል 31÷ <<ዘወረደ>> የዐቢይ ጸም 1ኛ <<እሑድ>>>>> 90
ክፍል 32÷ <<ቅድስት>> >>>> 2ኛ <<እሑድ>>>>> 90
ክፍል 33 <<ምኵራብ>> >>>> 3ኛ <<እሑድ>>>>> 96
ክፍል 34÷ <<መፃጉዕ>> >>>> 4ኛ <<እሑድ>>>>> 98
ክፍል 35÷ <<ደብረ ዘይት>> >>>> 5ኛ <<እሑድ>>>>> 99
ክፍል 36÷ <<ገብር ኄር>> >>>> 6ኛ <<እሑድ>>>>>112
ክፍል 37÷ <<ኒቆዲሞስ>> >>>> 7ኛ <<እሑድ>>>>>118

ምዕራፍ 10÷ <<<ሆሳዕና በአርያም>>>>>120

ምዕራፍ 11÷ ሕማማት፤ ሰሙነ ሕማማት>>123

ክፍል 38÷ <<የሳምንት ዕለታት ምሥጢር>> >>124
ክፍል 39÷ << ሐሙስ፤ ጸሎተ ሐሙስ >> 125
ክፍል 40÷ << በሰሙነ ሕማማት ውስጥ ዓርብ ስቅለት >> 127
ክፍል 41÷ << የዓርብ ስቅለት ጥብጣቤ፤ ንስሓና ስግደቱ >> 128

ምዕራፍ 12÷<<የቅዳሜ ሥዑር ምሥጢር>>133

ምዕራፍ 13÷ የትንሣኤ (ፋሲካ) ምሥጢር>> 136

ክፍል 42÷ <ሀ> የጌታችን ሞትና ትንሣኤ >>>> 138
ክፍል 43÷ <ለ> <<የፍጡራን ሞትና ትንሣኤ >>>> 140
ክፍል 44÷ <ሐ> <<ጽድቅና ኃጢኣት፤ ጻድቅና ኃጥአ>>> 142
ክፍል 45÷ <መ> <<የእኛ የሕያዋን ሞትና ትንሣኤ >> >> 143

ምዕራፍ 14÷ <<<<ዕርገተ ክርስቶስ>>>> 147

ምዕራፍ 15÷<<<<በዐለ ጰራቅሊጦስ>>>> 149

ምዕራፍ 16÷ <<<እምነት÷ (ሃይማኖት)>>>153

ክፍል 46÷ << የእምነትና የቃል ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት>> 157
ክፍል 47÷ <<<እምነትና መልካም ምግባር>>>>>>>>>> 163

ምዕራፍ 17÷ የእምነትና የክርስትና መነሻ>> 169

ክፍል 48÷ <<እምነት (ሃይማኖት) በኢትዮጵያ >>>>>>>>170

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ 18÷ <<<ጥምቀተ ክርስትና>>>>> 171

ክፍል 49÷ ክርስትና (ጥምቀተ ክርስትና) በኢትዮጵያ>>>> 172

ምዕራፍ 19÷ <<ክርስትና እና እስልምና>> 174

ምዕራፍ 20÷ <<<<የእምነት ክፍፍል>>>> 175

ክፍል 50÷ <<ጉባኤ ኒቅያ ስለ አርዮስ÷ ማብራሪያ >> >> 175
ክፍል 51÷ <<ጉባኤ ቊስጥንጥንያና መቅዶንዮስ >> >> 176
ክፍል 52÷ <<ጉባኤ ኤፌሶን ስለ ንስጥሮስ >> >> 176
ክፍል 53÷ <<ስለ ልዮን >> >> 177
ክፍል 54÷ << ስለ ማርቲን ሉተር >> >> 178
ክፍል 55÷ << ስለ ሔንሪ ስምንተኛ >> >> 179
ክፍል 56÷ << ስለ አድቨንቲስት >> >> 180
ክፍል 57÷ << ስለ ጀሆቫ ዊትነስ >> >> 180
ክፍል 58÷ << ስለ በሐሁላ >> >> 181

ምዕራፍ 21÷ <<ሃይማኖት,እምነት (ዶግማ)>>183

ክፍል 59÷ <<ስለ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን>>>>>>> 184

ምዕራፍ 22÷ <<<ስለ ታቦትና ምሥጢሩ>>> 186

ምዕራፍ 23÷ <<እመቤታችን ድ.ማርያም>>> 191

ክፍል 60÷ <<<የእመቤታችን ሥርወ ልደት>>>>>>>>>> 196
ክፍል 61÷ <<<የእመቤታችን ዕረፍትና ትንሣኤ>>>>>>>>199
ክፍል 62÷ <<<<ስለ ቀብሯ፣ ትንሣኤዋና ዕርገቷ >>>>>199
ክፍል 63÷ <<<ስለ ፍልሰትና ፍልሰታ ለማርያም >>> 201

ክፍል 64÷ <<<<<ማጠቃለያ>>>>>>>>>>> 202

ምዕራፍ 24÷ ስለ ባሕረ ሓሳብ ዐሞር መግለጫ÷

<<መቅድም ከልዩ መግለጫና ማብራሪያው ጋር>>

መናፍቃንና የመናፍቃን ደቀ መዛሙርት በእምነታችንም ሆነ በሥርዓታችን፤ እንዲሁም በቃል ኪዳን እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክና በቅዳሳን አማላጅነት ላይ በየጊዜው የሚያቀጣጥሉት እሳት አደገኛ መሆኑን ስለምንገነዘበው በዝምታ ልናልፈው አንችልም።

ነገር ግን ልሳነ መናፍቃን (የመናፍቃን አንደበት) እንከን ይኖረው እንደሆነ እንጂ እምነታችንስ ምንም እንከን የሌለው ንጹሕ እምነት ነው፤ ሃይማኖታዊ ሥርዓታችንም ቅዳሳት መጻሕፍትንና መንፈሳዊ ታሪካችንን መሠረት ያደረገ ማንም ሊነቅፈው የማይችል ተደናቂ ሥርዓት ነው።

እንዲሁም በሐዋርያት መሠረት የታነጸች፣ በክርስቶስ ደም የጸናች ኦርቶዶክሳዊት፣ ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ፈጽማ አትነዋወጥም።

<<ሀገራችን ኢትዮጵያም በዚህች ኦርቶዶክሳዊት፣ ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መካከል የቆመች የብሪት ምሰሶ ናት ማለት ይቻላል>>።

ምክንያቱም ኢትዮጵያ ሀገራችን ማንም አስተማሪና ምንም ጽሕፈት ባልነበረበት ዘመን እንኳ እግዚአብሔርን በሕገ ልቡና የምታመልክ የእምነት ሀገር ነበረች እንጂ ከእግዚአብሔር እምነት ውጭ የሆነችበት ጊዜ የለም።

በዘመነ ኦሪት÷ (ከልደተ ክርስቶስ በፊትም)

እግዚአብሔርን ያመለከች፣ ብሉይ ኪዳንንና ሐዲስ ኪዳንን ተቀብላ፣ የእምነት ሀገር በመሆን ቀዳሚነት እንዳላት በቅዳሳት መጻሕፍት የሚነገርላት፣ በልዩ ልዩ ምሁራንም በየጊዜው፣ በየክፍሉ የተዘገበላት፤ የክርስትና ደሴት በመባል የምትታወቀው ኢትዮጵያ ሀገራችን÷ የክርስትና እምነቷና ሥርዓቱ በመላው ዓለም እንደ ዕንቊ እያበራ የሚገኝ በተመልካቹ ሁሉ ልዩ አድናቆት ያለው ሲሆን÷ እኛ የእምነቱና የሥርዓቱ ተከታዮች የሆን ሕዝበ ክርስቲያንም በየዓውደ ዓመቱና በየበዐላቱ በልዩ ልዩ ሃይማኖታዊ ምስጋና እና መንፈሳዊ ባህል ስለምንገልጸው መላውን ዓለም በመልካም ገጽታ እያንፀባረቀ ይኖራል።

www.zeyeneta.com

ይኸውም ቅዳሳን ሐዋርያት ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀጥታ ተረክበው ያስተላለፉልን የክርስትና እምነትና ሥርዓቱ ሁሉ በሐዋርያት ተከታዮች አርድእትና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አባቶቻችን እየተመራ ትክክለኛውን ትምህርቱንና ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን፥ እንዲሁም መንፈሳዊ ባህሉንም ጠብቆ በአንድ መሥመር እየሔደ እንደሚገኝ ይታወቃል።

<u>(ሙሉውን ዝርዝሩ በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ ምዕራፍ 16፥ በገጽ 153 እና 157 ይመልከቱ)</u>

እኛ እያንዳንዳችን የክርስቶስ ወገኖች እውነተኞች ሕዝበ ክርስቲያን ነን የምንለውም ከዚህ በላይ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው በትክክለኛው እምነታችን በመጽናት፣ በቀደምት አበውና በቅዳሳን ሐዋርያት አማካይነት ከጌታችን የተሰጠንን፣ በቅዳሳት መጻሕፍትና በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አባቶቻችን በትውፊት (በቅብብሎሽ) የተረከብነውን ሃይማኖታችንን፣ ምንም ሳንበርዝና ከሌላውም ጋር ሳንቀላቅል፣ ጥንታዊውንና ታሪካዊ ሥርዓቱን በመጠበቅ መልካም ምግባር ሠናይ ሥራ በሚባለው በጾም፣ በጸሎት፣ በርኅራኄ፣ በምጽዋት፣ በትሕትና፣ በሰላምና በእውነተኛ ፍቅር አንድ በመሆን በመንፈሳዊ ባህላችን ስለምንገልጸው ነው።

ትክክለኛ የሃይማኖት ትርጉምና ሃይማኖትን ከመልካም ምግባር ጋር መያዝ፣ ሃይማኖታዊ ሥርዓትንም መጠበቅ ማለት ደግሞ ይህ እንደሆነ እውነትን ለሚቀበል ሁሉ ግልጽ ነው።

ቅዳሳን አባቶቻችን ብራና ፍቀው፣ ቀለም አውጥተው፣ ብዕር ቀርፀው፣ ጥሬ እየቆረጠሙ፣ ውሃ እየጠጡ፣ በሱባኤ ተወስነው ጽፈው ያስተላለፉልን ምንም ያልተቀላቀለበት፣ ያልተበረዘውና ያልተከለሰው፣ ቋንቋው ግእዝ የሆነ፥ በተቀደሱ መንፈሳውያን መነኮናትና የታሪክ ሥፍራዎች የሚገኝ ትክክለኛውን ሃይማኖታችንንና ሥርዓቱን ሁሉ ለዘለዓለም እየነገረን የሚኖር ቅዱስ መጽሐፋችን ትርጉሙና ምሥጢሩ ለመናፍቃን በቀላሉ ሊገባቸው ስለማይችልና በየጊዜው የሚለዋወጠውን የስሕተት ጉዟአቸውንም ስለማይደግፉላቸው ለማደናገሪያ የሚያመቹዋቸውን አንድ አንድ ጽሑፎች አዘጋጅተው እያባዙ የማሰናከያ ምዕራፍንና ቊጥርን ብቻ ቊነፃፅለው እየያዙ በመቅረብ የዋሁን ሕዝብ ለማደናገር ይሞክሩ ይሆናል።

ሆኖም ግን ቅዱስ መጽሐፍን፣ ጥሬ ንባቡን፣ ትርጉሙንና መሠረታዊ ምሥጢሩንም ጠንቅቆ በሚያውቅ ላይ ሊራመዱ አይችሉም።

ቅዱስ መጽሐፍን በመልካም ምግባር የሚተረጉም እውነተኛ ክርስቲያንንም ከቶ አያታልሉም።

ይኸውም እውነተኛ ክርስቲያን ቅዱስ መጽሐፍን በወረቀት ብቻ ሳይሆን በተግባርም ጭምር ነውና የሚያነበው ምሥጢሩንም በሥራ ነው የሚተረጉመው።

<u>በሉቃስ ወንጌል 10፥38፣ እንደተዘገበው፥ እንደዚሁም በትርጓሜ ቅዳሴ ማርያም <<በግእዙ>> <<ናጥሪ እንከ አርምሞ ወትዕግሥተ ከመ ማርያም እኅቱ ማርታ>> እንደ ማርያም እኅቱ ማርታ</u> አርምሞንና ትዕግሥትን ገንዘብ እናድርግ ከሚለው ቀጥሎ ያለውንም ታሪክ እንደምንመለከተው፥<u>ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመነ ሥጋዌው ማርታና</u> ማርያም የተባሉትን ሁለት እኅት (እትማማኞች) ለመንፈሳዊ ተግባር ሲያሠማራ እንጂ (ማርታን) በረድእነት (በሥራ ላይ) መድቦ፥ ሌላኛዋን (ማርያምን) ደግሞ ለትምህርት እንዳዘጋጃ ሁሉ፥ የእግዚአብሔር አገልጋዮችና እውነተኞች ክርስቲያኖችም እግዚአብሔር በፈቀደላቸው መሠረት፥ በገዳም ይሁን በደብር፥ በሱባኤ ተወስነው ወይም በበረኻ ወድቀው ወይም ደግሞ ማንም ተራ ሰው መስለው በመካከላችን እየተገኙ ስለ ሰው ሰርዖተ ኃጢኣት፣ ስለ ዓለም ሁሉ ሰላምና ደኅንነት የሚጸልዩ አሉ።

ወንበር ተክለው፣ ጉባኤ አስፍተውም ሆነ በተለያየ ሥፍራ እየተዘዋወሩ ምንም ያልተቀላቀለበትን፣ ያልተበረዘውንና ያልተከለሰውን እውነተኛውን የክርስቶስ ቃል ንባቡን፣ ትርጉሙንና ምሥጢሩን ጠንቅቀው በመማር የሚያስተምሩም አሉ።

እንደየችሎታቸው በልዩ ልዩ ደረጃ ተመድበው መንፈሳዊውን አገልግሎት የሚሰጡም አሉ።

በልዩ ልዩ ሥራ ላይ ተሠማርተው በጉልበታቸው ሠርተው አብያተ ክርስቲያናትን የሚያሠሩ፣ አስፈላጊ የሆነውን ንዋየ ቅድሳት (የማመሰገኛ ንብረት) ሁሉ እያሟሉ ቤተ ክርስቲያን እንድትኖር የሚያደርጉ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን አባቶች፣ ሊቃውንቷንና አገልጋዮቿ ካህናትን የሚንከባከቡ፣ የተቸገሩትንም ሁሉ ባላቸው ዓቅም የሚረዱም አሉ።

ክርስቲያናዊ ግዴታቸውን በተግባር የሚወጡ፣ ቅዱስ መጽሐፍን በመልካም ሥራ የሚተረጉሙ፣ ሃይማኖትን ከመልካም ምግባር ጋር የያዙ፣ ሃይማኖታዊ ሥርዓታቸውንና መንፈሳዊ ታሪካቸውን የጠበቁ እውነተኞች ሕዝበ ክርስቲያን የሚባሉ እነዚህ ናቸው።

www.zeyeneta.com

አዎ ሃይማኖታቸውን በመልካም ሥራ ገልጸዋል፣ ሃይማኖታዊ ሥርዓታቸውንና መንፈሳዊ ታሪካቸውንም ጠብቀዋል ሊባሉ የሚችሉ ይህን ያደረጉ ሰዎች ናቸው።

ታዲያ እነዚህ ይመሰገናሉ እንጂ ማንም ሊነቅፋቸው አይገባም።

ስለሆነም እውነተኛ ሕዝበ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ ወገን ነኝ የሚል ሁሉ እንደ እነዚህ የእግዚአብሔር ወዳጆች በመሆን መልካሙን የጽድቅ ሥራ መሥራት ይገባዋል።

ሆኖም ግን እንደዚህ አሁን እንደተጠቀሰው ያለውን መልካም ሥራ መሥራት ተገቢ መሆኑ እየታወቀ እውነትን ወደ ጎን እየተው፣ ያልሆነውንም ሆነ እያሉ የሚያደናግሩ፣ ሃይማኖታዊ ሥርዓታችንና ጥንታዊ ታሪካችን እያቃለሉ አፈጻጸሙን የሚለዋውጡ፣ መንፈሳዊውና ሀገራዊው አንድነታችንን የሚለያዩ እንደበታቸው የክፋት ምላጭ የሆነ፣ መሠረታዊ እውቀትና በእውነት ላይ የተመሠረተ ልባዊ ትሕትና የሌላቸው፣ በተለያየ ምክንያት የሚደራጁ ቡድኖችም ሊኖሩ እንደሚችሉ በመገመት በሰላማዊት፣ የተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንና በሕዝበ ክርስቲያኗ መካከል አለመግባባትና ቅሬታ እንዳይኖር አስቀድመን በማሰብ ጥንቃቄን ማድረግ፣ ስለ እምነታችንና መሠረታዊ ሥርዓቱ ሁሉ ግልፅ ያልሆነልን ካለ ሳንቸኩል፣ ልባዊና እውነተኛ በሆነ መንፈሳዊ ትሕትና ከአበውና ከምሁራን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ልሳን (አንደበት) በተገቢው መንገድ መማር፣ መጠየቅ፣ መረዳትና ማስረዳት ይገባናል እንጂ አንድ አንድ ነገሮች በተከሠቱ ቍጥር <<ሆን>> ማለትና መጨበጫ በሌለበት አሉባልታ መነዳት አደገኛ በመሆኑ ሃይማኖታዊ ሥራችን ሊሆን አይገባውም።

መንፈሳዊ ባህላችንም አይደለም፣ ሕጋዊ ተግባራችንም ሊሆን አይችልም።

የሃይማኖት ምሥጢር ቀላል አለመሆኑን መገንዘብ አለብን፣ ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን (ከሥርዓተ ሃይማኖት) ውጭ እንዳንሆንም ማስተዋል ያስፈልጋል።

ምክንያቱም ለሁሉ ሥርዓት አለውና በትዕግሥት መወያየት፣ በእውነተኛ ፍቅር መጠያየቅ፣ በትሕትና መተራረም ቀዳሚ ተግባራችን ሊሆን ይገባል።

ሙሉ ምሥጢሩን በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ ምዕራፍ 21 በገጽ 183 እና 184 እንመልከት።

አመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፥

<<ኩላንታኪ ሠናይት እንተ እምኀቤየ አልብኪ ነውር ወኢምንትኒ ላዕሌኪ>>

(ወዳጄ ሆይ ሁለንተናሽ ውብ ነው፥ ነውርም የለብሽም)
መሐልየ (መኃልየ) ሰሎሞን 3 (4) ፥7

አስቀድሞ በአምላክ ጎሊና ታስባ የኖረች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፥ ለአምላክ እናትነት የተመረጠችው ገና ሳትወለድ ሲሆን፥ ከእናቷ ማኅፀን ሳለች ጀምራ መንፈስ ቅዱስ ከነውርና ከውርስ ኃጢአት ሁሉ የጠበቃት ፍጽምት፣ ንጽሕት፥ ቅድስትና ቡርክት ናት።

በሊቃውንት አባቶቻችን ጉባኤ ተብሎ የማያውቅ በዘመናችን አንድ አንድ ሰዎች ጥንተ አብሶ እያሉ የሚጠሩትም አሳማኝትም፣ ፈጽሞም የለባትም።

አዎ ሰማይን ያለ ምሰሶ ያቆመ፣ ምድርንም ያለ መሠረት ያፀና፥ እነአብርሃምን፣ እነኤርምያስንና እነዳዊትን ገና ሳይወለዱ ከእናታቸው ማኅፀን ሳሉ ጀምሮ ለመልካም ሥራ ያዘጋጀ እግዚአብሔር፥ ሁሉን ማድረግ ስለሚችል፥ ለእርሱ እንዳችም የሚሳነው ነገር የለምና እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ከተመረጡት የተመረጠች፣ ከከበሩት የከበረች ልዩ፣ ንጽሕት፣ ቅድስትና ቡርክት አድርጎ ፈጥሯታል።

መዝ 21፥1, 57፥3, 135፥5, ኤር 1፥4፥ማቴ 1፥18

ይህን እውነት እየተቃወሙ ከዚህ ውጭ በሆነ መንገድ የሚንቀሳቀሱ ካሉ የእግዚአብሔርን ከሃሊነትንና የባሕርይ አምላክነትን እየተቃወሙ እንደሆኑ፥ ማለትም እግዚአብሔርን ሁሉን ማድረግ አይችልም በማለት ላይ እንዳሉ በመረዳት ከስሕተታቸው ተመልሰው ንስሓ ሊገቡ ይገባቸዋል።

ምክንያቱም ይህን ያደረገ እግዚአብሔር ስለ ሆነ እግዚአብሔር ለእመቤታችንም ሆነ ለሌሎች ቅዱሳን የሰጠውን የማይሻር የአማላጅነት፣ የረድኤት፣ የበረከትና የምሕረት ቃለ ኪዳንን (ቃል ኪዳንን) እንደናቁ፣ የእግዚአብሔርን ዘለዓለማዊ ስጦታ እንዳቃለሉ፣ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ አማላጅነት፣ ፍጹም ቅድስና እና ፍጹም ንጽሕና ላይ እንደቀለዱ፥ በአጠቃላይ በማቴዎስ ወንጌል ያለውን ሰማይ ከምድር ጋር

www.zeyeneta.com

(ሰማይና ምድር) ያልፋል ቃሌ ግን አያልፍም የሚለውን የማይሻር የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል ወደ ጎን እንደተው ይቆጠራል። ዘፍጥ.48÷16 ዘጎልቁ 20÷16 መጽሐ.ጥበብ 4÷16÷ ማቴ.24÷35 እንመልከት

አም ይህን የሚቃወሙ ካሉ <<አንቺ ከሴቶች መካከል>> ተለይ ተሸ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለብሽ÷ በረከተ ሥጋን፣ በ ረከተ
ነፍስን ከልጅሽ ከኢየሱስ ክርስቶስ እያማለድሽ የምታሰጪ ነሽ የሚለውን የቅዱስ ወንጌሉን መሠረት አድርጎ በበቁ አበው ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ሲነገር የሚኖረውን ምሥጢረ መለኮት ስላልተቀበሉ በእምነታቸውም ሆነ በሥርዓታቸው ከኦርቶዶ ክሳዊት ተዋሕዶ
ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን እምነትና ሥርዓተ አምልኮ ውጭ በሆነ መንገድ እየተጓዙ ናቸው ማለት ነው።

ሙሉ ምሥጢሩን ከእነማስረጃው በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ በምዕራፍ 23 ከገጽ 191 ጀምሮ ይመልከቱ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት÷ በሊቃውንት ጉባኤ መምሪያ አዲስ አበባ ብፁዓን አባቶች ሊቃነ ጳጳሳትን ጨምሮ 22 ምሁራን አባላትን ባቀፈ የሊቃውንት ጉባኤ ተዘጋጅቶ ቀርቦ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ታይቶ ከጸደቀ በኋላ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠሙር 1988 ዓ ም (1996) ታትሞ በአገልግሎት ላይ እንዲውል ለመላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት የተሰራጨው እምነት፣ ሥርዓተ አምልኮና የውጭ ግንኙነት የሚል መጽሐፍም በገጽ 49 በምዕራፍ 7 ከብረ ቅድስት ድንግል ማርያም በሚል ርእስ ቅድስና ከሚለው ክፍል የሚገኘው ቃል÷ <<አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና የወለደች ድንግል ማርያም ከአዳም ዘር የተላለፈ ኃጢኣት (ጥንተ አብሶ የሚባለው) ያላገኛት፣ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት፣ ገና ከመወለዷ አስቀድሞ በእምላክ ጎሊና ታስባ ትኖር የነበረች፣ በሰው ልማድና ጠባይ ከሚደርሰው ሥጋዊ ሐሳብና ፈቃድ ሁሉ የተጠበቀች፣ ከተለዩ የተለየች ቅድስተ ቅዱሳን ናት>> በማለት ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ÷ ድንግልና፣ ንጽሕና÷ ቅድስና እና መመረጥ÷ በዘመናችን ጥንተ አብሶም የሚባለውም አለመኖር በተጨማሪ አረጋግጧል።

<<እምነት፣ ሥርዓተ አምልኮና የውጭ ግንኙነት ገጽ 49 ምዕራፍ 7>>

ምዕራፍ <<1>> <<ልደት>>

ልዩ ክፍል÷ ስለ ልደት ምሥጢር መግለጫና ዐጭር ማብራሪያ÷

እነሆ ፈጣሪአችን ልውል እግዚአብሔር ፍጹም የባሕርይ አምላክ ሲሆን÷ በፍጥረቱ የማይጨክን ርኅሩኅ እንደመሆኑ መጠን ሊያድነን ስለ ፈቀደ ፍጹም ሰው ሆኖ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ።

በልደቱ ጊዜም ሰውና መላእክት በአንድነት ሆነው ስለአመሰገኑት የአንድነትና የሰላም አምላክ መሆኑ በግልጽ ታየ።

<< ተፈሥሑ በእግዚአብሔር ዘረድእነ>>

ስለዚህ በረድኤቱ፣ በቸርነቱ ፍጹም የሆነውን ሕይወት ባደለን፣ (በሰጠን) ፍጹም ደስታን በሰጠን በእግዚአብሔር ዘንድ ደስ ይበላችሁ። ከመዝ 80÷1 የተመሰደ።

ልደት ብዙ ምሥጢር ያለበት ሲሆን ቀጥተኛ ትርጉሙ ከማኅፀን መወለድ ከጨለማ ወደ ብርሃን መውጣት ማለት ነው።

ምሥጢራዊ ትርጉሙም÷ ካለመኖር ወደ መኖር መምጣት መሸነት ተገልጸ መታየት ነው

ልደት በምሥጢራዊ የግእዝ ቋንቋ ተመሥርቶ ሲብራራ÷ ስለመኖር ለማለት÷

<<ዘእንበለ ህላዌ÷ ኢህልው፣ አልቦ፣ ኢምንት>> ሲል÷

መኖር ለማለት ደግሞ÷

<<ህላዌ÷ ህልው፣ እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ፣ ምንት>> ይላል።

www.zeyeneta.com

ዘኢንበለ ህላዌ÷ ኢሀልዎ፣ አልቦ፣ ኢምንት ማለት÷

አለመኖር፣ ከፅንሰ በፊት በምንም ተገልጾ ያለመታየት፣ አለመፀነስ፣ አለመወለድ ሲሆን÷

ህላዌ፡÷ ሀልዎ፣ እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ፣ ምንት ግን÷

መኖር፣ መፀነስ፣ መወለድ፣ ከእናት ኾድ ወደ ብርሃን መውጣት፣ መኘት፣ ተገልጾ መታየት ነው።

ልደት የሚለው ዘርና ዋና ግንዱ <<ወለደ>> ከሚል የግዕዝ ግስ ስለሚወጣ በዐቢይ አንቀጹ ወለደ በማለት ልደት ብሎ ይገኛል።

ምዕራፍ <<2>>

ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደትና መሠረታዊም ሥጢሩ÷

<<ሀ>> ከጌታችን ልደት በፊት የነበረው ሁኔታና የመወለዱ ዋና ምክንያት÷

<<ለ>> ከልደቱ በፊት የተነገሩት ትንቢታት÷

<<ሐ>> የመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ብሥራትና ምሥጢሩ÷

<<መ>> የልደቱ ፍጻሜና ምሥጢሩ÷

<<ሠ>> እኛ ልናደርገው የሚገባን÷

<<ረ>> የጌታችን ዘመነ ልደት በቅደም ተከተል ሲተነተን የሚሉት ከዚህ ቀጥለው በየክፍላቸው ይብራራሉ።

ክፍል<<1>>

<<ሀ>> ከጌታችን ልደት በፊት የነበረው ሁኔታና የመወለዱ ዋና ምክንያት÷

በኦሪት ዘፍጥረት ከምዕራፍ 1 ጀምሮ በተከታታይ ምዕራፎች እንደምንመለከተው ልዑል እግዚአብሔር ፍጥረቱን ሁሉ ሲፈጥር ሰውን በአርአያውና በምሳሌው ፈጥሮ ከሁሉም ፍጥረት አልቆ አክብሮ በገነት አኑሮት ነበር። ዘፍጥረት 1÷26 2÷7።

ከዚህም ጋር ሕግንና መመሪያን ሰጥቶ ሕጉን እንዲያከብር አዞት ነበር።

አዎ ይህን ዕፀ በለስ የበላህ እንደሆነ የኃጢኣትን ሞት ትሞታለህና ዕፀ በለስን አትብላ ብሎታል።

ይኸውም የፈጣሪና የፍጡር መለያ÷ የአዛዥና የተአዛዥ ልዩ ምልክት መሆኑ ነው። በፈጣሪና በፍጡር መካከል ሕግና መመሪያ መኖሩንም የሚያስገነዝብ ነው። ዘፍጥ 2÷16።

ይሁን እንጂ ሰው (አዳም) የፈጣሪውን ሕግና መመሪያን ጠብቆ በተፈቀደለት መሠረት መኖር ሲገባው የፈጣሪውን ሕግና መመሪያ ጥሶ፣ የታዘዘውን አፍርሶ ያልታዘዘውን ሲፈጽም፣ በልቡ አስቦ ያልተፈቀደለትን ያውም ከዐቅሙ በላይ የሆነውን የባሕርይ አምላክነትን ሲሻ (ሲፈልግ) በመኘቱ ከፈጣሪው ጋር ተጣልቶ ከገነት ወጥቶ ከክብር ወደ ሐሣር ተለውጦ መርገም ወድቆበት ከሕይወት ወደ ሞት ተባረረ። ዘፍጥ 3÷1።

በመሆኑም በአዳምና በሔዋን ላይ የወደቀው መርገም ባለመነሣቱ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የነበረው 5500 ዘመን ሁሉ÷ መርገሙን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በመስቀል ተሰቅሎ እስከ ደመሰሰው ድረስ የመርገም፣ የፍዳ፣ የጨለማ፣ የችግርና የጭንቀት ዘመን ስለ ሆነ ሰው መልካምም ይሥራ ክፉ ኑሮው በሲኦል በችግር ውስጥ ነበር ማለት ነው።

ነገር ግን በፍጥረቱ የማይጨክን የርኅራኄና የጽድቅ ባለቤት ልዑል እግዚአብሔር በአምስት ቀን ተኩል (ከመንፈቅ) ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ ብሎ ለአዳም በሰጠው አምላካዊ ተስፋ መሠረት ትንቢት ተነግሮ ሱባኤ ተቆጥሮ ካበቃ÷ ጊዜው ሲደርስ÷ ማለትም በነቢያቱ እንደበት ትንቢትን አናግሮ ከጨረሰ በኋላ 5500 ዓመተ ዓለም ሲፈጸም ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ።

ዘመኑም አምስት ቀን ያለው አምስት ሺህ ዓመት ሲሆን÷ እኩለ ቀን (መንፈቀ ዕለት) ያለው ደግሞ አምስት መቶ ዓመት ነው።

www.zeyeneta.com

ጠቅላላው አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ይሆናል ማለት ነው።

ይኸውም ነቢየ እግዚአብሔር ንጉሥ ዳዊት በመዝ 89÷4÷

<<እስመ ዐሠርቱ ምዕት ዓመት በቅድሜከ ከመ ዕለት እንተ ትማልም ኀለፈት>>

አንድ ሺህ ዓመት በአንተ ፊት (ዘንድ) ትናንትና እንዳለፈች አንዲት ቀን ናት እንዳለው፤

(ሺህ ዓመት በፊትህ እንዳለፈች እንደ ትናንት ቀን ይላል።
(የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ)

ትርጓሜው ደግሞ÷ <<በሰው ዘንድ ሺህ ዘመን÷ ባንተ ዘንድ ትናንት እንዳለፈች ዕለት ናትና>> ይላል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም÷ ወዳጆች ሆይ በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት፤ ሺህ ዓመትም እንደ አንድ ቀን እንደ ሆነ ይህን አንድ ነገር አትርሱ።

ለአንዳንዶቹ የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሓ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል በማለት እንደጠቀሰው÷

በእግዚአብሔር ዘንድ ብዙ ጥቂት ጥቂትም ብዙ ሊሆን ይችላል ማለት ነው። 2ኛ ጴጥ 3÷8

እንዲሁም ስንበድል የሚታገሠን፤ ጊዜውንም የሚሰጠን የርኅራኄ አምላክ እግዚአብሔር ፍጥረቱ በክንቱ እንዲጠፋ ስለማይፈልግ÷

እኛም ከክፋት÷ ከተንኰል÷ ከቂምና ከበቀል÷ ከኃጢአት መንገድ ሁሉ ተመልሰን፤ በኃጢአታችን ተፀፅተን በንስሓ ወደ እርሱ እንድንቀርብና ከእርሱ ምሕረትንና ይቅርታን አግኝተን መንግሥቱንና ጽድቁን እንድንወርስ ሰፊ ዕድል እየሰጠን እደሆነ÷

ይህንን ተገንዝበን ንስሓ እየገባን ከኃጢአታችን ሁሉ ነጻ ልንሆን እንደሚጋብንም እየነገረን ነው ማለት ነው።

<< ክፍል 2 >>

<<ለ>> ከልደቱ በፊት ከተነገሩት ትንቢታት መካከል÷

ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደትና ስለ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ብዙ ምሳሌና ትንቢት ተነግሯል፤ ብዙ ምሥጢርም ተመሥጥሯል።

ከእነዚህም መካከል ጥቂቶቹን ለምሳሌ ያህል ብንጠቅስ÷ ነቢዩ ኢሳይያስ በትንቢቱ÷

<<እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅንም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች>> በማለት አስቀድሞ ተናግሯል።

ይኸውም ምሥጢሩ ስለ ተገለጸለት <<ድንግል ትፀንሳለች>> ብሎ ስለ እመቤታችን ፍጹም ድንግልና እና ፍጹም ንጽሕና÷ ማለትም አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና መውለዷን፤ አምላክን ከመውለዷ በፊት፤ በምትወልድበት ጊዜም ሆነ ከወለደችው በኋላ፤ ድንግል፤ ንጽሕት፤ ፍጽምት መሆኗን÷ እንዲሁም ከፍጥረት ሁሉ በተለየ መልኩ መመረጧን÷

<<ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች>> ብሎም ስለ ጌታችን ስመ ሥጋዌ ወይም ስለ ጌታችን የሥጋዌ ስም አስቀድሞ በትንቢቱ የተናገረ ሲሆን÷ ኢሳ 7÷14።

ነቢዩ ዳንኤልም÷ <<በሌሊት ራዕይ አየሁ፤ እነሆም የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ፤ በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ ወደ ፊቱም አቀረቡት፤ ወገኖችና አሕዛብ÷ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው፤ ግዛቱም የማያልፍ የዘለዓለም ግዛት ነው፤ መንግሥቱም የማይጠፋ ነው>> በማለት÷ ስለ ጌታችን መምጣትና ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለድ÷ እንዲሁም ስለ ዘለዓለማዊ መንግሥቱና ስለ ዘለዓለማዊ አምላክነቱ አመሥጥሮ ተናግሮአል። ዳን 7÷13።

www.zeyeneta.com

በሌሎች ነቢያትም ብዙ ምሳሌና ትንቢት ተነግሯል።

በተለይም <<በምሥጢር አፍላቂነቱና በአስደናቂ ትንቢቱ ልበ አምላክ>> (የአምላክ ልብ) እየተባለ የሚጠራው፣ አምላካዊ ሥራን ከመሆኑ በፊት በመዝሙሩ አስተካክሎ የሚናገር፥

ስለ ጌታችንና ስለ እመቤታችን መሠረታዊ ምሥጢር አስቀድሞ የተገለጸለት ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት በመዝሙሩ በየክፍሉ ትንቢቱንና ምሳሌውን ደጋግሞ አመሥጥሮታል።

ለምሳሌም፥

1ኛ በግእዙ፥

ኖላዊሆሙ ለእስራኤል አፅምዕ፥
ዘይርእዮሙ ከመ አባግዓ ዮሴፍ፥
ዘይነብር ላዕለ ኪርቤል አስተርአየ።

ቀጥተኛ ትርጉሙ፥

የእስራኤል ጠባቂ ሆይ አድምጥ፣
ወይም ደግሞ በትርጓሜው ተስተካክሎ ሲገለጥ፥
እስራኤልን እንደ ዮሴፍ በጎች የምትመራ፣ በኪሩቤል ላይ
የምትቀመጥ ተገለጥ ይላል። መዝሙረ ዳዊት 79፥1።

በመሠረታዊ ትርጓሜው ምሥጢሩ ሲተነተንም፥

እስራኤል ዘነፍስን የምትጠብቅ አምላካችን ሆይ አድምጥ፣
በረድኤት ተገለጥ፥ ሥልጣንህንና ረድኤትህን በሥጋ ገልፀህ፣
ሰው ሆነህ ተወልደህ አድነን፣

አቤቱ ከሲኦል ወደ ገነት መልሰን፣ ከገሃነምም ወደ መንግሥተ ሰማያት አግባን ማለት ነው።

2ኛ ግእዙ፥

ምስሌከ ቀዳማዊ በዕለተ ኃይል፥
በብርሃነሙ ለቅዱሳን፥
ወለድኩከ እምከርሥ እምቅድመ ኮከበ ጽባሕ።

ቀጥተኛ ትርጉሙ፥

ከአንተ ጋር ቀድሞ በኃይልህ ቀን በቅዱሳን ብርሃን ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድኩህ ይላል።

(ከጥንተ ፍጥረት በፊት ከአንተ ጋር ነበርሁ፣ ከመላእክት መፈጠር በፊት ወለድኩህ ሲል ነው) መዝሙረ ዳዊት 109፥3

ይህ መዝሙር፥ አንድነቱን ሲገልፅ በፍጥረት ጊዜ ከአንተ ጋር ነበርኩ፣ ቅድመ ዓለም ያለ እናት መወለዱን ሲገልፅም ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ እካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ ወለድኩህ የሚል ሲሆን፥ ድኅረ ዓለም ያለ አባት ያለ ዘርዐ ብእሲ ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን ሲገልጽ ደግሞ የነቢያት ትንቢት በተፈጸመበት፥ መላእክት <<ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ >> ብለው ባመሰገኑበት ቀን ወለድኩህ የሚል ምሥጢር ይገኝበታል።

በውስጡ የአንድነትንና የሦስትነትን ምሥጢር የያዘ እንደመሆኑ መጠንም፥ የእግዚአብሔር አንድነትንና ሦስትነትን በሰፊው ያመሠጥራል።

አም ጌታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በመወለዱ በመላእክትና በልሳነ ሰብእ (በሰው አንደበት) በፍጥረቱም ሁሉ እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ተብሉ ተመሰገነ፥ አብ ወላዲ፣ ወልድ ተወላዲ፣ መንፈስ ቅዱስ ሠራፂ እንደሆነም በፍጥረቱ በግልፅ ታወቀ።

የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት ምንም እንኳ ቀድሞም በነቢያት አንደበት ሲነገር፣ በብሉያት ቅዱሳት መጻሕፍትም ሲመሠጠር እንደነበረ ቢታመንም በልደቱ ምሥጢር ደግሞ በሥራ ተገለጠ፣ ጎልቶ ታየ።

ከዚህ ቀጥሎም በሐዲሳት ቅዱሳት መጻሕፍት ተጻፈ፣ በጉባኤም በትርጓሜ ተመሠጠረ፣ በሥፋት ለሁሉ ተነገረ ማለት ነው።

ስለሆነም ጌታችን በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ ሰማያት ተከፍተዋል።

መላእክትም <<ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ>> እያሉ እግዚአብሔርን እያመሰገን ከሰማይ ጌታችን ወደ ተወለደባት ወደቤተ ልሔም ሲወርዱ፣ ከምድርም ወደ ሰማይ ሲወጡ ስለነበር ትንቢት በተፈጸመበት መላእክት ባመሰገኑበት ቀን ወለድኩህ ይላል።

www.zeyeneta.com

ክፍል <<3>>

<<ሐ>> የመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ብሥራትና ምሥጢሩ፥

<<ወበሳድስ ወርኀ ተፈነወ ገብርኤል መልአክ>> ሉቃስ 1፥26።

አም በሉቃስ ወንጌል 1፥26 ጀምሮ እንደምንረዳው መልአክ ብሥራት ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል፥ የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆነው ካህነ አሮት ዘካርያስን ወደሚያገለግልበት ቤተ መቅደስ ሔዶ፥ ዘካርያስ ሆይ ጸሎትህ ከእግዚአብሔር ፊት ደርሷል፣ መካን የምትባለው ኤልሳቤጥ ሚስትህም ወንድ ልጅን ትወልድልሃለች ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ።

ይኸውም ፍጹም ደስታ ማለት ነው ብሎ ካበሠረው በኋላ፥ በስድስተኛው ወሩ ናዝሬት ገሊላ ወደ ነበረችው ወደ ቅድስት ድንግል (ማርያም) ከእግዚአብሔር ተላከ።

የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ መልአኩም ወደ እርሷ ገብቶ <<ደስ ይበልሽ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፣ አንቺ ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ>> አላት።

አም ምሥጢሩ በትርጓሜው መሠረት ሲብራራም፥ እግዚአብሔር ከሥጋሽ ሥጋን፣ ከነፍስሽም ነፍስን ነሥቶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ይሆናልና (ከአንቺ ይወለዳልና) በክቢያት ትንቢት በመላእክት ተልእኮ ደስ ያለሽ ምልዕተ ክብር ሆይ (ተፈሥሒ) ደስ ይበልሽ ማለት ነው።

ይህ <<በአበው ትርጓሜ መሠረት ሲብራራ>>

ከሴቶች መካከል፥ ማለትም ከሁሉም ሴቶች ተለይተሽ አንቺ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለብሽ፣ በረከተ ሥጋን በረከተ ነፍስን ከልጅሽ ከኢየሱስ ክርስቶስ እያማለድሽ የምታሰጪ ነሽ፣

የማኅፀንሽ ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስም መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለበት፣ በረከተ ሥጋን በረከተ ነፍስን የሚያድል ወይም የሚሰጥ ነው የሚል ምሥጢር ይገኝበታል።

ይኸውም፥ <<ከሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አባቶቻችን መደበኛ የጥባኤ ትርጓሜና ከቅዱሳት መጻሕፍት ትክክለኛ ምሥጢር እንደምንገነዘበው>>

ከሴቶች መካከል ተለይተሽ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለብሽ ነሽ ብሎ በአዳምና በሔዋን ላይ የወደቀው ከፈጣሪያቸው እንዲርቁ የሚያደርግ መርገም፥ በተለይም ደግሞ በሔዋን ላይ የነበረው ፃዕረ ወሊድና አስቸጋሪ የሆነ ሥጋዊ ጠባይዕ (ሥጋዊ ሐሳብም ሆነ ሥጋዊ ባሕርይ) ሁሉ በእመቤታችን ላይ ግን እንደሌለ፥ (እንደዘመናችን አነጋገር ጥንተ አብሶ የሚባለውም እንዳላገኛት፣ ፈጽሞም እንደሌለባት)

በረከተ ሥጋን በረከተ ነፍስን እያማለድሽ የምታሰጪ ነሽ ብሎም አማላጅነቷን በሚገባ ያስረዳናል።

አም ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር ስለሌለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ገና ሳትወለድ ከእናቷ ማኅፀን ሳለች ከማንኛውም ነውርና የውርስ ኃጢኣት ጠብቆ፥ ከሌሎች ንጹሓን የተለየች ንጽሕት፣ ፍጽምት፥ ሆና እንድትወለድ አድርጓታል።

መዝ 131፥13, ኤር 1፥4፥

የአሊታ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሰዋስውንም ከመትደሙ፥ ክፍል 3፥ ገጽ 25 እንመልከት።

ይህ በፍጡር ሊለካ የማይቻል የማይመረመር የእግዚአብሔር አምላካዊ ጥበብና አምላካዊ ሥራ ነው።

ሌላ ፍጡር ሁሉ ምንም እንኳ ኃጢኣትን ከመሥራት የታቀበ ከገቢር ንጹሕ ቢሆንም፥ ከተፈጥሯዊ ጎልዮ (ሓሳብ) ፈጽሞ ንጹሕ ሊሆን አይችልም እመቤታችን ግን ከጎልዮም፣ ከገቢርም፥ ማለትም ከማሰብም ሆነ በተግባር ከመፈጸም ሁሉ ንጽሕት፣ ፍጽምት ናት።

እንደዚሁም ደግሞ፥ <<የማኅፀንሽ ፍሬ የተባረከ ነው የተባለው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ>> ሁሉ በእጁ የሆነ፣ ሰሞ የሚያድል፣ ተማላጅ (የሚሰማን) እንጂ አማላጅ እንዳልሆነ ከዚሁ ምሥጢርም በሚገባ መረዳት እንችላለን።

www.zeyeneta.com

ድንግል ማርያምም ከሐዲስ ንግግሩና እንግዳ ከመሆኑ የተነሣ ለጊዜው ደንግጣ እንደነበር ቅዱስ መጽሐፋችን ይናገራል።

አቡ ድንግል ማርያም መልአኩ ባበሠራት ጊዜ÷

ሊቁ ኢትዮጵያዊ ቅዱስ ያሬድ በግእዝ ቋንቋ÷
<<እምአይቴ ዘመጽአ ዝ እንግዳ ዘይዜንወኒ ፍሥሓ>>
በማለት በጣዕመ ዜማው እንዳመሠጠረው÷
(የመጋቢት በዐለ እግዚአብሔር ድጓ)

ይህ ደስታን የሚነግረኝ ዕንግዳ ከየት የመጣ ነውን?
ቀድሞ አባቴ አዳምንና እናቴ ሔዋንን ያታለለ ያ ጥንተ ጠላታችን ሰይጣን ይሆንን? ወይስ እውነት መልአክ እግዚአብሔር ነውን? ብላ ነበር ማለት ነው።

ፍርሃትን ማስወገድ ልማዱ የሆነው መልአክ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤልም በእግዚአብሔር ፊት ጸጋን (ባለሟልነትን) አግኝተሻልና አትፍሪ አላት።

አያይዞም እነሆ ትፀንሻለሽ፤ ወንድ ልጅንም ትወልጃለሽ፤ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ። እርሱ ታላቅ ነው፤ የልዑል ልጅም ይባላል፤ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊት ዙፋን ይሰጠዋል፤ በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘለዓለም ይነግሣል፤ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም አላት።

መሠረታዊ ትርጉሙ <<እነሆ ትፀንሻለሽ፤ ወንድ ልጅንም ትወልጃለሽ>> ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ፤ »እርሱ ዐቢይ ነው።

የልዑል እግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ ነው፤ በያዕቆብ ቤት ለዘለዓለም ይነግሣል፤ ለመንግሥቱም <<ለባሕርይ አምላክነቱ>> ጎልፈት ሽረት የለውም ማለት ነው። ዳን 7÷13, ሉቃ 1÷31, ዕብ. 1÷1 ጀምሮ በሰፊው እንመልከት።

ማርያምም ወንድን ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል አለችው።

አቡ ቅድስት ማርያም ግን በጎሊናም በሥጋም ማለትም በሐሳብም ሆነ በግብር ድንግል፤ ንጽሕት፤ ፍጽምት ናትና እኔ እንኪንስ የግቢር የጎልዮም የለብኝም፤ ይህ የምትለው ነገር እንዴት ሊሆን ይችላል።

ለመሆኑ መፈት ያለዘር ስታበቅል ሴት ያለውንድ ስትፀንስ የት አየህና ነው እንደዚህ የምትለኝ ብላ መለሰችለት ማለት ነው።

መልአኩም መንፈስ ቅዱስ ወደ አንቺ ይመጣል፤ በአንቺ ላይ ያድራል፤ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል÷

ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል አላት።

አቡ መልአኩ÷ መንፈስ ቅዱስ ወደ አንቺ ይመጣል፤ በአንቺ ላይም ያድራል፤ ኃይለ ልዑል ወልድም ይፀልልሻል÷

ማለትም ሥጋሽን ይሰብሳል፤ ከአንቺ ይወለዳል።

ከአንቺ የሚወለደውም ተራ ፍጡር÷ (ዕሩቅ ብእሲ) ሳይሆን <<ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ>> ተብለው ከሚመሰገኑት ከሦስቱ አካላት÷

(ከሥላሴ) አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ ነው፤

ከአንቺ የሚወለደው ሁሉን የፈጠረ፤ የፍጥረታት ባለቤት የሆነ እግዚአብሔር አምላክ ነው አላት።

አያይዞም መልአኩ እነሆ መካን ትባል የነበረችው ኤልሳቤጥ ዘመድሽ እንኳ ከአረጀች በኋላ ወንድ ልጅን ፀንሳለች ይኸውም ስድስት ወር ሆኖታል።

ስለዚህ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና ይህ የምነግርሽ ሁሉ ይሆናል አላት።

ቅድስት ድንግል ማርያምም እንደቃልህ ይሁንልኝ ይደረግልኝ አለችው።

ከዚህ በኋላ አምላክ ከሥጋዋ ሥጋን፤ ከነፍሷም ነፍስን ነሥቶ (ተዋሕዶ) ሰው ሆነ፤ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ ማለት ነው።

ሚቴ 1÷1,ዮሐ 1÷1, 1ኛ የዮሐንስ መልእክት 5÷1። በሰፊው እንመልከት

አቡ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም።

www.zeyeneta.com

ክፍል <<4>>

<<መ>> <<የልደቱ ምሥጢርና ፍጻሜው>>

የልደቱ ምሥጢር እንዴት እንደነበረ ሲተነተንም÷

በሉቃስ ወንጌል ም 2÷1 ጀምሮ እንደምንረዳው ሰው ሁሉ በየሀገሩ ከግብር ገብቶ ይቆጠር ዘንድ÷ ማለትም ዛሬም የሕዝብ ቆጠራ እንደሚደረገው መላው ሕዝብ በየአከባቢው እየተሸ እንዲቆጠር፣ እንዲመዘገብ በዘመኑ ከነበረው ገዥ ከአውግስጦስ ቄሣር ትእዛዝ ወጣ።

በመሆኑም የዳዊት ወገን የሆነው ዮሴፍም ከድንግል ማርያም ጋር በመሆን እንዲጻፍ (እንዲመዘገብ) ከናዝሬት ከገሊላ የዳዊት ሀገር ወደምትሆን ወደ ይሁዳ ወደ ቤተ ልሔም ሔደ ይላል ቅዱስ መጽሐፉ።

በነገራችን ላይ ይህች ቤተ ልሔም የምትባል ቦታ÷ ቀደም ሲል ትንቢት የተነገረላት ናት።

ይኸውም የቅዱስ መጽሐፋችን ታሪክ እንደሚያስረዳን÷ ሚክያስ የተባለ ነቢየ እግዚአብሔር በሴላው ክፍል ሲያስተምር ውሉ ወደ ማታ አካባቢ በቤተ ልሔም በኩል ሲያልፍ <<ቤተ ልሔምን>> ተፈታ ወይም ጠፍ ቦታ፣ ዑና ሆና ቋያ በቅሎባት እንዳያትና÷

አዝኖ ተክዞ አንቺ የኤፍራታ ዕጣ የምትሆኝ <<ቤተ ልሔም>> የይሁዳ ነገሥታት ከነገሡባቸው ሀገሮች ብትበልጪ እንጂ ከቶ አታንሽም÷

እንዲህ ጠፍ እንደሆንሽ አትቀሪም።

ንጉሥ ይነግሥብሻል፣ አስራኤል ደጅ ይጠኑብሻል፣ ነጋሪት ይሰማብሻል፣ ድንኳን ይተከልብሻል፣ አሕዛብም ግብርን ይገብሩብሻል ብሎ÷ አስቀድሞ ትንቢት ተናግሮባት

እንደ ነበር ይታወቃል። ሚክ 5÷2, ማቴ 2÷6።

ትንቢቱ አልቀረም ሆኗል፣ ሁሉም ተፈጽሞአል።

ለጊዜው ዘሩባቤል ነግሦባታል፣ ነጋሪት ተሰምቶባታል፣ ድንኳን ተተክሎባታል፣ እስራኤል ደጅ ጠንተውባታል አሕዛብም ገብረውባታል።

ዋናው ትንቢቱና ፍጻሜው ደግሞ÷ ለእየሱስ ክርስቶስ ስለ ሆነ ጌታችን በተወለደ ጊዜ የብርሃን ድንኳን ተተክሎባታል፣ እስራኤል ዘነፍስን የሚጠብቅ ጌታ ተወልዶባታል።

አዎ ጌታችን በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ ቤተ ልሔም የመላእክት ምስጋና ተሰምቶባታል፣ ነገደ መላእክት ደጅ ጠንተውባታል÷ ሰብአ ሰገልም ወርቅን፣ ዕጣንንና ከርቤን ገብረውባታል።

በመዝሙረ ዳዊት መዝ 71÷10። እንደምንረዳው ጌታችን በእርሷ በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ ሰብአ ሰገል ወርቅን÷ ዕጣንንና ከርቤን አምጥተውለታል ለማለት ነው።

የዚህ ምሥጢር ወደፊት በዝርዝር ይብራራል።

እንዲሁም ይህ ሁሉ በርሷም ላይ ስለተፈጸመ ምሳሌው ለድንግል ማርያምም ይሆናል።

ወደዋናው ርእሳችን እንመለስና ዮሴፍና ቅድስት ድንግል ማርያም ወደ ዳዊት ሀገር ወደ ይሁዳ ቤተ ልሔም በወጡበት ጊዜ ድንግል ማርያም ጌታን ፀንሳ ስለነበር የምትወልድበት ሰዓት ደረሰ።

የሚያድሩበትንም ሥፍራ ባለማግኘታቸው ድንግል ማርያም ጌታችንን በጎል (በበረት) እንደ ወለደችው።

ወቅቱም ብርድ በመሆኑ በጎል (በበረቱ) የነበሩ እንስሳት ሕፃኑ ጌታን በእስትንፋሳቸው እንደ አሟሟቁት ቅዱስ መጽሐፋችን ያስረዳናል።

እናቱ ድንግል ማርያምም ለዚህ የታደሉ÷ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ በኋላ በሚቀብሩት ጊዜ በድርብ በፍታ ገንዘው እንደሚቀብሩት÷

ካህናትም ዕለት ዕለት (በየዕለቱ) በቅዳሴ ጊዜ ሥጋውን በማኅፈድ (በጨርቅ) እንደሚጠቀልሉት አስቀድሞ ተገልጸላት በማኅፈድ (በጨርቅ) ጠቀለለችው አውራ ጣቱንም እሠረችው ይላል።

www.zeyeneta.com

በዚያች ሀገር መንጋቸውን ተግተው የሚጠብቁ ዕረኞችም ስለ ነበሩ የእግዚአብሔር መልአክ መጥቶ በአጠባባቸው ቆመ።

ከቤተ ልሔም ጀምሮ እነርሱ እስከ አሉበት ድረስም ብርሃን ፈሰሰላቸው። (ልዩ የሆነ ብርሃን እንደ ውሃ ፍስስ ብሎ በራ ማለት ነው)

<u>እነርሱም</u> እጅግ እንደ ደነገጡ፥ እንደ ፈሩና መልአኩ ግን ሁል ጊዜ ዳንኤል አትፍራ፣ ዘካርያስ አትፍራ፣ ማርያም አትፍሪ እያለ ፍርሃትን እያስወገደ፣ እያረጋጋ መናገር፣ ማብሠርም ልማዱ ስለሆነ <u>እነዚህ ዕረኞችንም</u> አይዟችሁ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታን፣ የምሥራችን እነግራችኋለሁና አትፍሩ።

ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት፥ እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና እንዳላቸው ቅዱስ መጽሐፋችን እየነገረን ይገኛል።

<u>ይኸውም በመሠረታዊ ምሥጢሩ ሲብራራ የእግዚአብሔር መልአክ</u> መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለበት በረከተ ሥጋን በረከተ ነፍስን የሚያድል፣ የዓለም መድኃኒት የሚሆን የባሕርይ አምላክ ክርስቶስ፥ በዳዊት ባሕርይ፣ በዳዊት ከተማ ተወልዷልና እናንተንም ሌላውንም ሰውን ሁሉ ደስ የሚያሰኝ ዜናን፣ ትልቅ ደስታን አነግራችኋለሁ።

ምልክቱ ሕፃኑን አውራ ጣቱን ታሥሮ በጎል፥ ማለትም በበረት ተጥሎ (ተኝቶ) በጨርቅ ተጠቅልሎ ታገኙታላችሁ አላቸው ማለት ነው። <u>ሉቃስ 2፥10</u>

ይህን ሲናገርም ብዙ የሰማይ ሠራዊት ወይም የሰማይ መላእክት፥

<<ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ>> እያሉ ከመልአኩ ጋራ ድንግት ነጐደው ሲመጡ ተሰሙ።

<u>አዎ ጌታችን በተወለደ ጊዜ፥</u> መላእክት ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰው በጎ ፈቃዱ በማለት እግዚአብሔርን አመሰግነዋል።

<u>መሠረታዊ ትርጒሙ፥</u> አምላክ ፍጹም ሰው ቢሆን ሥጋ አምላክ ሆኖአልና፥ ፍጹም ሰው ለሆነ አምላክ ምስጋና ይገባዋል፣

እግዚአብሔር ለሰው ግእዛኑን (ነፃነቱን) ይሰጠው ዘንድ ከድንግል ማርያም ሰለ ተወለደ።

በምድር ዕርቅ ተወጠነ፣ (ተጀመረ) በዓለም ሰላም ሠፈነ፣ በአዳም ትውልድ ሁሉ እንድነት ሆነ ማለት ነው።

<u>ዋናው ምሥጢሩም፥</u> አምላክ ሥጋን በመዋሐዱ (ሥጋን በመልበሱ) ፍጹም ሰው ሆኖ ከቅድስት ድንግል ማርያም በመወለዱ፥ ፍጹም ተየሐደውን ለመግለጽ ነው።

<u><<ዮም አሐደ መርዔተ ኮኑ መላእክት ወሰብእ ከመ ይሰብሕዎ ለክርስቶስ በቃለ አሚን>> ይላል በግእዙ፥</u>

<u><<ይህ ከአበው ትርጓሜ የተጠቀሰ ሲሆን ቅዱስ ያሬድም በድጓው በጣዕመ ዜማው አመሥጥሮታል>></u>

ይኸውም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ፥ ሰውና መላእክት በአንድ ማኅበር ሆነው፥ ማለትም መላእክት ከኖሎት ጋራ፣ ኖሎትም ከመላእክት ጋራ በኅብረት በመሆን እግዚአብሔርን አመሰግነዋል ማለት ነው። <u>ሉቃስ 2፥14</u>

እኛም ያነን መሠረት በማድረግ ዛሬ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በአንድነት ሆነን እናመሰግነዋለን።

በጌታችን ልደት ጊዜ፥ ከዚህ ከፍ ብለው የተጠቀሱት ሰብአ ሰገል እየተባሉ የሚጠሩትም ለጌታችን ወርቅን፣ ዕጣንንና ከርቤን አቅርበውለታል።

<u>የሰብአ ሰገል ስጦታዎች በዝርዝር ሲብራሩ፥</u>

ከቅዳሳት መጻሕፍትና ከሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አባቶቻችን እንደምንረዳው፥ ሰብአ ሰገል በማለት የምንጠራቸው የሰገል ሰዎች አምላክ እንደ ሆነ ለማጠየቅ ዕጣንን አመጡለት፣ ንጉሥ እንደሆነ ለማጠየቅም ወርቅን አመጡለት፣ እንደዚሁም ማኅየዊ የሚሆን የሞቱ ምሳሌ ከርቤን አመጡለት ይላል።
እነዚህ በሰብአ ሰገል የቀረቡ ስጦታዎች እምላካዊ ሥራዎችን የሚያመለክቱ ዐበይት ምሥጢራት አሉዋቸው።

www.zeyeneta.com

ይኸውም ለምሳሌ ያህል ከመሠረታዊ ምሥጢሩ በዐጭሩ ብንጠቅስ÷

ወርቅ አመጡለት ይላል÷

የወርቅ ጥራት በእሳት ተረጋግጦ ይህ ንጹሕ ወርቅ ነው እንደሚባል፣ ጌታም ንጹሐ ባሕርይ በመሆኑ በዚህ ለማመሳሰል ሲሆን÷

በጌታችን አምነው እንደ ወርቅ በእሳት መከራ ተፈትነው ፈተናውን አልፈው ሰይጣንና የሰይጣንን ሥራዎች ሁሉ አሸንፈው የሚገኙ ምእመናንም (ሰዎችም) ሃይማኖታቸውና ምግባራቸው እንደወርቅ የነጠረ፣ የጠራ (ንጹሕ) እንደሆነ ለማመልከት ነው።

ዕጣንን አመጡለት ይላል÷

ዕጣን መልካም መዓዛ አለው ጌታችንንም ምዑዝ ባሕርይ ነህ ለማለት ሲሆን÷ እንዲሁም ዕጣን በተሰፋ ይመሰላል÷ ዕጣን ከሩቅ እንደሚሸት ተስፋም ያላዩትን እንዳዩት፣ ያልያዙትን እንደያዙት፣ (እንደጨበጡት) ታደርጋለች ወይም ታስመስላለች÷

ወደ ፊት ተስፋው መልካም የሆነ ሰው በፊቱ ይታወቃል÷ ፊቱ ደስተኛ ነው፣ አእምሮውም ሁሉ ብሩህ ነው።

ጌታችንም ተስፋ ላጡት ሁሉ ተስፋ፣ ፍጹም ደስታ፣ ፍጹም ሕይወት ስለ ሆነ በዚህ ለመግለጽ ነው።

ከርቤን አመጡለት ይላል÷

ከርቤም በአንድነት÷ በሰላምና በፍቅር ይመሰላል።

ከርቤ የተሰበረውን ይጠግናል፣ የተለያየውንም አንድ ያደርጋል።

ጌታችንም ከማኅበረ መላእክት የተለየውን አዳምን ወደ ቀደመ ክብሩ መልሶ ከማኅበረ መላእክት እንደሚጨምረው÷ የተለያየውንም ሁሉ በማዋሐድ÷ ለፍጥረቱ እውነተኛውን ፍቅር ሰጥቶ፣ መላውን ዓለም ሰላም እንደሚያደርግ ለማመልከት ነው። መዝ 71÷10።እንመልከት።

<<ምሥጢሩ በአበው ትርጓሜ መሠረት ሲብራራ ነው>

አም አስቀድመው የተገለጹ ምሳሌዎችና ምልክቶች በጌታችን አምላካዊ ሥራዎች በተለያየ ጊዜ በተግባር ላይ ታይተዋል፣ በየክፍሉና በየደረጃውም ተፈጽመዋል።

እነዚህ የፍጹም ሕይወት÷ የአንድነት÷ የሰላም÷ የዕርቅና የፍቅር ምሳሌዎችና ምልክቶች ሲሆኑ÷ በውስጣቸው እኛም በኅብረት፣ በእውነተኛው ፍቅር አንድ ሆነን ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባን የሚያስገነዝበን መልካም አርአያና ትምህርት ያለበት መልእክት አለ።

በተጨማሪም ከዚህ በታች ያሉትን የአማርኛ ጥቅሶች እንመልከታቸው÷

1ኛ እግዚአብሔር ጽዮንን (አመቤታችንን) ይህች ለዘለዓለ <<ማደሪያዬ>> (ማረፊያዬ) ናት ብሎ መርጧታል።
መዝ 131÷13 (132÷13)

2ኛ ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፣ ሰውም አይገባበትም፣ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር <<ገብቶበታልና>> ተዘግቶ ይኖራል። ሕዝ 44÷2

ይህ ቃል አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና የወለደች አመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም÷ አምላክን ከመፅነሰዋ በፊት፣ አምላክን በፀነሰች ጊዜ፣ በምትወልድበትም ሆነ ከወለደችው በኋላ ድንግል፣ ፍጽምት፣ ንጽሕት መሆኗን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ነቢዩ ሕዝቅኤል አስቀድሞ በዓይነ ኅሊና የተመለከተ፣ በምሥጢረ ትንቢትም የተናገረ እንደሆነ ነው የሚያስረዳን።

3ኛ በስድተኛውም ወር መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ወደ አንዲት <<ድንግል>> (ማርያም) ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ። ሉቃ 1÷26።

ቃሉ መልአክ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ቅድስት ድንግል ማርያም በተላከ ጊዜም እመቤታችን ክውርና ኃጢአት የሌለባት÷ ድንግል፣ ፍጽምት፣ ንጽሕት መሆኗን ነው የሚያረጋግጥልን።

ሰላምታ፣ የጸጋና የክብር ስግደት እንደሚገባትም ከዚሁ መረዳት እንችላለን። ሉቃ 1÷28

www.zeyeneta.com

ክፍል <<5>>

እኛ ልናደርገው የሚገባን÷

<<ሠ>> 5ኛ የልደቱ መሠረታዊ ምሥጢር

ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ሲሆን÷

ቀጥሎ ደግሞ የልደቱን ምሥጢር መሠረት እያደረ ከልዩ ልዩ ቅዱሳት መጻሕፍት እየጠቀሰና እያብራራ እኛ ልናደርገው የሚገባንን የሚያስገነዝብ መልእክት ይሆናል።

ይኸውም÷

<<በ1ኛው የዮሐንስ መልእክት ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅምና እርስ በእርሳችን እንዋደድ በእርሱም በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ>> ተብሎ እንደተነገረን ጌታችን የተወለደው ለእኛ ፍጹም ሕይወት መሆኑን በመረዳት ቃሉን ሰምተን በተግባር ላይ ልናውል፣ በእውነተኛው ፍቅር አንድ በመሆን ፈጣሪአችን እግዚአብሔርን ልናመሰግን ይገባናል። 1ኛ ዮሐ 4÷7። እንመልከት።

አዎ አሁንም በዚሁ መልእክት በምዕ 5÷1 ጀምሮ <<ክርስቶስ ነው ብሎ በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዷል፣ ወላጁንም የሚወድ ሁሉ ከርሱ የተወለደውን ይወዳል፣

እግዚአብሔርን ስንወድ ትእዛዛቱንም ስናደርግ የእግዚአብሔርን ልጆች እንድንወድ በዚሁ እናውቃለን፣ ትእዛዝቱንም ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና፣ ትእዛዛቱም ከባዶች አይደሉምና ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው>> ተብሎ እንደተነገረን÷

በእምነታችን ጸንተን፣ ሃይማኖታችንን በመልካም ምግባር፣ በሠናይ ሥራ እያነጽን÷ በሰላም፣ በፍቅርና በርኅራኄ እየተረዳዳን፣ በቅዱ ቃሉ መሠረት መንፈሳዊውን ባህላችን በመጠበቅ በሕገ እግዚአብሔር፣ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያናችን እየተመራን መኖር አለብን ማለት ነው።

እንደዚህ ሆነን የተገኘን እንደሆን አሁንም ከዚሁ መልእክት ሳንወጣ ማለትም በ1ኛ የዮሐንስ መልእክት ምዕራፍ 3÷1 ጀምሮ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን እዩ ተብሎ እንደተገለጸልን የእግዚአብሔር ልጆች ልንባል እንችላለን። መንገዳችን ከዚህ ውጭ ከሆነ ግን በጨለማ ጎዳና እየተጓዝን ነን ማለት ነው የጨለማ መንገድ ደግሞ ወደ ገደል ነው የሚወስድ።

በመሆኑም በዮሐንስ ወንጌል <<ብርሃን በጨለማ ይበራል ጨለማውም አላሸነፈውም>> ተብሎ እንደተመሠረረው ብርሃነ ሕይወት እግዚአብሔር አምላካችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፣ በእውነተኛው መንገድ ሆኖ እየበራልን ነውና የጨለማውን ጎዳና ትተን በትክክለኛው የብርሃን መሥመር ወደ እግዚአብሔር÷ ወደ ዘለዓለማዊ ሰፍራችን፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት ልንጓዝ ይገባናል። የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 1÷4።

አዎ ራሱ ጌታችን በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ስምንት ቁጥር አሥራ ሁለትም÷ <<እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም>> ብሏልና በእውነተኛው ብርሃን በኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ የሚጓዝ ሁሉ ወደ ጨለማ አይሔድም። ዮሐ 8÷12።
አሁንም በዚሁ ወንጌል÷ <<ብርሃነ ከእናንተ ጋር ነው የብርሃን ልጆች እንድትሆኑ በብርሃኑ እመኑ፣ ጨለማም እንዳይደርስባችሁ ብርሃን ሳለላችሁ በብርሃን ተመላለሱ>> በማለት በቅን ልቡና ከጠራነው እግዚአብሔር አምላካችን ምን ጊዜም ከእኛ ጋር ስለሆነ በእርሱ ብርሃንነት እንድንመላለስ አስረድቶናል። ዮሐ 12÷35።

ስለዚህ በጽድቅ፣ በእውነተኛ መንገድ ወደ እውነተኛው ብርሃናችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወታችን፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት መመላለስ ይገባናል ማለት ነው።

ቅዱስ ጳውሎስም በሮሜ ምዕራፍ 13÷11 መልእክቱ <<ከዕንቅልፍ የምትነሡበት ሰዓት አሁን እንደደረሰ ዘመኑን ዕወቁ>> በማለት እንደነገረን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሊያድነን ስለ መጣ፣ ምሕረትንና ሰላምን ለማስፈን ከቅድስት ድንግል ማርያም ስለ ተወለደ፣ ከልደቱ በፊት የነበረው መርገምና ፍዳ ተደምስሶ፣ ኀዘኑ ችግሩ ጭንቀቱ ሁሉ አልፎ፣ ጨለማው ተገፎ፣ እውነተኛው የሕይወት ብርሃን መጥቷልና÷

www.zeyeneta.com

ሊቁ ኢትዮጵያዊ ቅዱስ ያሬድም በድጓው÷
<<ብርሃነ ሕይወት ዘኢይጸልም>> ያለው

(ከቍስቋም ጎዳር 6 ቀን እስመ ለዓለም የተጠቀሰ ነው)

ጊዜያት የማይፈራረቁት፣ ጨለማ የማያሸንፈው፣ የማይጠፋ የሕይወት ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ በርቶልናልና
<<ንው ናንሶሱ በብርሃኑ>>

ኑ ሁላችንም በክርስቶስ በብርሃን እንመላለስ ይለናል ቅዱስ ቃሉ።

ቅዱስ ጳውሎስም በኤፌ 5÷14 መልእክቱ <<አንተ የምትተኛ ንቃ ከሙታንም ተነሣ (ተነሥ) ክርስቶስም ያበራልሃል>> ብሎ እንደገለጸው ነቃ ብለን እውነተኛው የማይጠፋ ብርሃን ወደሚበራበት፣ ፍጹም መድኃኒት ወደሚገኝበት ወደ ዘለዓለማዊ መኖሪያችን ወደ እግዚአብሔር ቤት ብንገሠግስ መልካም ነው።

አም ከላይ ከፍ ብሎ እንደተነገረን ከእንቅልፋችን የምንነቃበት ዘመን አሁን ነውና በእንቅልፍ ከሚመሰለው ካለማወቅ ወደማወቅ ከኃጢኣት ተግባር ወደ ጽድቅ ሥራ መሻገር ያስፈልገናል። ከእንቅልፋችን ነቃ ብለን ቅዱስ ቃሉን ልንመልከተው፣ ልብ ብለንም ልናስተውለው÷ የሚነገረን ያለው ለሁላችንም ለእያንዳንዳችን መሆኑን በሚገባ ልንረዳው ይገባናል።

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ÷ <<ከእርሱ ጋር ኅብረት አለን ብንል በጨለማም ብንመላለስ እንዋሻለን እውነትንም አናደርግም። ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን፣ የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደምም ከኃጢኣታችን ያነጻናል። ኃጢኣት የለብንም ብንልም ራሳችንን እናስታለን፣ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም>> በማለት እንደነገረን እያንዳንዳችን ቃሉን በተግባር ላይ ማዋል ይጠበቅብናል።

በደለኞች መሆናችንን አምነን ፈጣሪያችን ይቅር እንዲለን በንስሓ ወደ እርሱ መቅረብ ይገባናል ማለት ነው።

በ1ኛ የዮሐንስ መልእክት እንደተገለጸልን እግዚአብሔር ፍጹም ብርሃን ስለሆነ ጨለማ በእርሱ ዘንድ ከቶ የለምና ከእርሱ ጋር ኅብረት አለን የምንል ከሆን የጨለማውን ተግባር ሁሉ መጣል÷

ክፋትን፣ ተንኮልን፣ ቅንዓትን፣ ምቀኝነትን፣ ቂምንና በቀልን መተው ቀዳሚ ተግባራችን ሊሆን ይገባል። 1ኛ ዮሐ 1÷5 ጀምሮ።

በተጨማሪም ቅዱስ ጳውሎስ<<ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁና አሁን ግን በጌታ ብርሃን ናችሁ። የብርሃኑ ፍሬ በበጎነትና በጽድቅ በእውነትም ሁሉ ነውና ለጌታ ደስ የሚያሰኘውን እየመረመራችሁ (እያደረጋችሁ) እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ፣ ፍሬ ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ>> ብሎ እንደመከረን የብርሃንን ሥራ መሥራት እንጂ ከጨለማ ተግባር ጋር መተባበር ለእኛ ተገቢያችን አይደለም። ኤፌ 5÷8 ጀምሮ÷

አም ጌታችን በገዛ ራሳችን ያመጣነውን ፍዳንና መርገምን ደምስሶ ከዲያብሎስ ከቊ አገዛዝ ነፃ ሊያወጣን ከሰማይ ወረደ÷ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ።

ሕጉንና መመሪያውን አፍርሰን፣ ትእዛዛቱንም ጥሰን በመሸታችን በኃጢኣት ብንወድቅም እርሱ ግን በፍጥረቱ የማይጨክን ርኅሩኅ፣ ይቅር ባይ አምላክ ስለሆነ በደላችንን ሁሉ ይቅር ብሎ ከወደቅንበት ሊያነሣን መጣ።

ታዲያ አሁንስ ሕጉን መጠበቅ የለብንም እንደ?

አም አሁንም ቢሆን ሕጉንና መመሪያውን እንድንጠብቅ ትእዛዛቱንም እንድንፈጽም ታዘናል።

በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 14÷21 እና ምዕራፍ 15÷6 ጀምሮ ብንመለከት÷ ራሱ ጌታችን ትእዛዜን የሚፈጽም ቃሌንም የሚጠብቅ እውነተኛ ወዳጄ ነው ብሏልና እውነተኞች የእግዚአብሔር ወዳጆች ከሆን ትእዛዙን መፈጸም፣ ቃሉንም መጠበቅ ይገባናል።

ምክንያቱም እውነተኞች የእግዚአብሔር ወዳጆች መሆናችን የሚታወቀው በዚህ ነው።

አም ጌታችን የምትወዱኝስ ከሆነ ሕጌንና መመሪያዬን ጠብቁ ትእዛዜንም ፈጽሙ÷ ሕጌንና መመሪያዬን የሚጠብቅ፣ ትእዛዜንም የሚፈጽም ሁሉ አባቴም፣ እናቴም፣ ወንድሜም፣ እኅቴም ነው ብሎናልና፣ የእግዚአብሔርን ወዳጆች መሆን ከፈለግን፣ የእግዚአብሔር ወገኖችን ልንባል የምንወድ ከሆን ሕጉንና መመሪያውን መጠበቅ አለብን ትእዛዛቱንም መፈጸም አለብን ማለት ነው። ሚቴ 12÷50 እንመልከት።

www.zeyenota.com

<<ያለ ሕግ ኃጢኣትን ያደረጉ ሁሉ ያለ ሕግ ደግሞ ይጠፋሉና ሕግም ሳላቸው ኃጢኣትን ያደረጉ ሁሉ በሕግ ይፈረድባቸዋል።

በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉ ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉምና>> ተብሎ በጳውሎስ መልእክት ስለተነገረ። ሮሜ 2÷12

በሐዋርያው ያዕቆብ መልእክትም <<ቃሉን እየሰማ የማያደርገው የተፈጥሮ ፊቱን በመስተዋት አይቶ እንደሚሔድ ሰው ነውና ቃሉን በሰማችሁት መሠረት የምትፈጽሙት ሁኑ እንጂ እየሰማችሁ ራሳችሁን የምታስቱ አትሁኑ>> ተብሎ ስለ ተገለጸ። ያዕ 1÷22።

ይህ ሁሉ ችግር የመጣውም አዳምና ሔዋን ሕጉን ካለማክበራቸው፣ መመሪያውንም ካለመጠበቃቸው የተነሣ መሆኑን ተገንዝበን ሕጉን የምንሰማ ብቻ ሳንሆን በሰማነው መሠረት ልንጠብቀው፣ በተማርነውም መሠረት ልንፈጽመው ይገባናል ማለት ነው ሮሜ 5÷12

አሥ የጌታችን ልደት ዋና ምክንያትንና ምሥጢሩን ከዚህ በላይ በሚገባ የተረዳን ይመስለኛል።

ስለዚህም ዘወትር በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ጉባኤ፣ በእውነተኞች መምህራን እንደሚነገረን፣ አሁንም የቅዱሳት መጻሕፍት ምሥጢራትን መሠረት አድርጎ ተደጋግሞ እንደተገለጸልን ጥልን፣ ጠብንና ሞቅሞቅን ከራሳችንም፣ከወገኖቻችንም በማስወገድ፣ ከክፋት፣ ከተንኮል፣ ከምቀኝነት፣ ከቂም፣ ከበቀል÷

በአጠቃላይ እግዚአብሔርንና ሰውን ከሚያሳዝን ተግባር ሁሉ እየታቀብን ኃጢኣታችንን እየተናዘዝን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እየተቀበልን ለመንግሥተ ሰማያት ልንዘጋጅ፣ በተግባራዊ ፍቅር አንድ ሆነን፣ በሰላም ልንኖር፣ የልደቱ ምክንያትና መሠረታዊ ምሥጢሩ ምን እንደሆነ ተገንዝበን ትምህርቱንና ምክሩን ልብ ብለን ሰምተን በተግባር ልንተረጉመው ይገባናል።

ምንም ምክንያት ሳንሰጥም በእውነተኛው ጎዳና ዛሬ÷ ከአሁን ጀምሮ በፍጥነት ወደ ጽድቅ ሥፍራ መጓዝ አለብን።

የቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ÷ የትጉሃን መላእክት÷ የቅዱሳን ነቢያት÷ የሐዋርያት÷ የጻድቃንና የሰማዕታት በረከት ረድኤት ሁል ጊዜ አይለየን።

ክፍል <<6>>

<<ረ>> የጌታችን ዘመነ ልደት በቅደም ተከተል ሲተነተን÷

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ዘመን ጠቅለል ባለ መልኩ ሲነገርና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የአቆጣጠር ሥርዓት መሠረት ሲገለጽ በ5500 ዓመተ ዓለም ፍጻሜ ነው ይባላል።

ይህ ከልደቱ በፊት የነበረው 5500 ዘመን ምሕረት፣ ሕይወት ስለአልነበረበት የመርገምና የጨለማ ዘመን በመሆኑ ዓመተ ፍዳ ዓመተ ኩነኔ በመባል ሲታወቅ÷ ከልደቱ ወዲህ ያለው ዘመን 1998 ግን ጌታችን ሰው ሆኖ፣ ከድንግል ማርያም ተወልዶ፣ ለሰው ሁሉ ፍጹም ሕይወትን፣ ፍጹም ምሕረትን፣ ድኅነትንና አንድነትን÷ ፍጹም ነጻነትንና ፍጹም ሰላምን ሰጠ ዓመተ ሥጋዌ÷ ዓመተ ምሕረት÷ ዓመተ ድኅነት እንለዋለን።
ሁለቱ 5500 እና 1998 ሲደመር ደግሞ 7498 ይሆናል።
ይህ 7498 ዘመን ዓመተ ዓለም በመባል ይታወቃል።

ይኸውም እንደ ቤተ ክርስቲያናችን አቆጣጠር ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ 7498 ዘመን ሆነ ማለት ነው።
ዓመተ ምሕረት ስንልም ጌታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ስለ እኛነን÷ ፍጹም የሆነውን ምሕረት በመስጠት ከራሱ ጋር አስታረቀ፣ ወደ ጥንታዊ መኖሪያችን ስለመለሰን፣ ኑ ወደእኔ ቅረቡ ወደ ቤታችሁም ግቡ ብሎ ወደ ራሱ፣ ወደርስቱ ስለ አቀረበን÷ የምሕረት፣ የድኅነትና የይቅርታ ዘመን ማለታችን ነው

ስለ ጌታችን ከሥጋዌው ወይም ከፅንሰቱ ጀምሮ እስከ ዕርገቱ ያለው ዘመን እያንዳንዱ ሲተነተንም÷5500 ዓመተ ዓለም፣ ዘመነ ዮሐንስ መጋቢት 29 ቀን ትስብእቱ÷ (ፅንሰቱ)

5501 >> >> >>>> ወይም በ1ኛው ዓ ም መጨረሻ በ2ኛው ዓ ም መጀመሪያ ዘመነ ማቴዎስ ታኅሣሥ 29 ቀን ልደቱ÷5530 >> >> >>>> ወይም በ30 ዓ ም ዘመነ ሉቃስ ጥር 11 ቀን ጥምቀቱ (በ30 ክረምቱ ተጠመቀ ይላል ማቴ 3÷13 ትርጓሜው) 5533>> >>>>>> ወይም 33 ዓ ም ከ3ወር ዘመነ ማርቆስ መጋቢት 27 ቀን ስቅለቱ÷ በ3ኛ ቀኑም በዚሁ ዘመን መጋቢት

www.zeyeneta.com

29 ቀን ትንሣኤው፥ አሁንም በዚሁ ዘመን በተነሣ በአርብዓኛው ቀኑ ግንቦት 8 ቀን ዕርገቱ እንደሆነ ከቤተ ክርስቲያናችን የአቋጣጠር ሥርዓትና ከመንፈሳውያን የአገልግሎት መጻሕፍት እንረዳለን።

ይህ ከፅንሰቱ ጀምሮ እስከ ዕርገቱ ድረስ ያለው የጌታችን ጠቅላላው ዘመን፥ ማለትም ጌታችን ፍጹም ሰው ሆኖ፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በዚህ ዓለም የቆየበት ዘመን 33 ዓመት ከ3 ወር ብቻ ሆኖአል ማለት ነው። የእኛ አቋጣጠር ከሌሎች የሚለየውም እኛ ቀደም ሲልም በወርኀ (በጨረቃ) ስንቀጥር ስለ ነበርን እንደሆነ አንድ አንድ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አባቶቻችን ይናገራሉ። ይኸውም በጨረቃ አቋጣጠር አንድ ጊዜ 29 አንድ ጊዜ ደግሞ 30 ስለሚሆን ነው።

በመሆኑም፥ ነው ዓመቱን በወር የምንቆጥረው 1 ወር 2 ወር እያልን 12 ወር እያልን 4ቱን ሳምንት 30ውን ወይም 29ኙን ቀን 1 ወር እንለዋለን እንጂ 1 ፀሐይ አንለውም። ማለትም በዓውደ ፀሓይ (በፀሓይ) አንቀጥርም። በሌላ ቋንቋም ቢሆን በወር ስም ነው የሚጠራ አጠቃቀሙ ያው አንድ ነው ለማለት ነው።

ስለዚህም መሠረታችን፥ እውነተኛ ለመሆኑ ይህ ራሱ ማስረጃ ሊሆን ይችላል።

አዎ ደቂቃዎች በሰከንዶች፣ ሰዓታት በደቂቃዎች፣ ዕለታት በሰዓታት፣ ሳምንታት በዕለታት፣ አዋርኀ (ወሮች) በሳምንታት፣ ዓመታት በአዋርኀ፣ (በወሮች) እየተቆጠሩ ነው አዝማናት የሚኸ። ቋንቋው ቢለያይም እንኳ ይህ በሁሉም ዓለም የአቆጣጠር ዘዴ የሚገኝ ነው። ለምሳሌ ከሰከንድ ጀምሮ ያለው ደቂቃ ተቀጥሮ ሰዓት፥12 ወይም ሌሊቱንም ጨምሮ 24 ሰዓት 1 ቀን ይሆናል 7 ቀንም 1 ሳምንት፣ 4 ሳምንት (29 ቀን) ወይም 30 ቀንም 1 ወር፣ 12 ወይም ጳጉሜንን ጨምረን 13 ወር ደግሞ 1 ዓመት ይሆናል ማለት ነው።

በሌላም በኩል፥ ይልዮስ ቄሣር፥ የተባለ የሮም ንጉሥ የነበረው፥ አሁን እኛ ኢትዮጵያውን እየተጠቀምንበት ያለነውን የዘመን አቋጣጠር ከግብፅ ወስዶ ለሁሉም እንዳሰራጨውና በኋላ አባ ጎርጎሬዎስ የተባለው የሮም ፓፓ ሆኖ የነበረው የዚህ አቋጣጠር መሠረቱ ከአፍሪካ ሀገር ግብጽ (አስክንድርያ) ስለተገኘ ምናልባትም አፍሪካን የናቀ መስሎት ይሁን፥ ወይም ደግሞ መሬት በፀሐይ ዙሪያ ለመዞር 365 ቀን፣

ከ5 ሰዓት፣ ከ45 ደቂቃዎች፣ ከ46 ሰከንድ ይፈጅባታል የሚለውን የካልቪዮስንና የአልዮስይስን ጥናት መነሻ አድርጎ ሊሆን ይችላል የዘመን አቋጣጠራችን ትክክል አይደለም ብሎ እንደእነእርሱ አቋጣጠር ጥቅምት ወር በ1582 ዓ ም የተወሰኑትን ግለ ሰዎች ይዞ ከኋላ ዘመን ጀምሮ ደቂቃዎችንና ሰዓቶችን አስልቶ አሰባስቦ በማምጣት በነበረው ላይ ስምንትም ሰባትም እንደጨመረበትና ይህ ነው ትክክኛ ብሎ በሥራ ላይ እንዳዋለው አንድ አንድ የታሪክ ጽሑፎች ይገልጻሉ።

የዘመኑን አቆጣጠር በተለያየ መንገድ የሚገልጹትና አሥር ነው የተጨመረበት፣ 4 ሳምንትም 28 ቀን ነው የሚሉ ተመራማሪዎችም አሉ

ያም ሆነ ይህ የታሪክ መዛግብት የየራሳቸው ምክንያት ያላቸው ሲሆኑ ጽሑፎቹ ለመወያየትና ለመመራመር የሚያስችሉ የሐሳብ መነሻ ሆነው ወደፊት ግን ሁሉም በአንድ መሥመር ለመሔድ እንደሚስማሙ ተስፋ እደርጋለሁ።

የፈረንጆች የቀንና የዘመን አቋጣጠር በኋላ ዘመን የቫቲካን ፓፓ አባ ጎርጎሬውስ የፈለሰፈው እንደሆነም ይታወቅ ዘንድ የቀንና የዘመን መቁጠሪያቸው፥ የጎርጎሬስ ካላንደር (የጎርጎሬሳውያን አቋጣጠር) እየተባለ ይጠራል።

ማስረጃ ፥

ለምሳሌ ያህልም፥
ጁልዮስ ወይም የጁልዮስ ካላንደር የሚለው
(Julius Calendar Rushedy Wassef—p.20 Rushedy
እንዲሁም **CLANDAR OF DAVID**
Wassef —pp.32—34 Archer peter—p.36 World Book
Escalloped p.28. 2.Gorg Archer peter pp.10—11

በአሁኑ ጊዜ አብዛኛው የዓለም ክፍል የጎርጎሬዎስን የአቆጣጠር ልምድንና ዘይን ይዞ እየተጓዘ እንደሆነ ይታወቃል።

የሆነ ሆኖ የዘመን አቋጣጠር በየሀገሩ ብዙ ልዩነት ቢኖረውም በተለይም በጣም ረቂቅና ልዩ የሆነ ምሥጢር ካለበት ከቅዱስ ድሜጥሮስ ባሕረ ሐሳብ ጀምሮ ያለው የእኛ የዘመን አቋጣጠር ግን ባሕረ ሐሳቡን መሠረት በማድረግ ወቅቶችንና ምሥጢረ መጻሕፍትን ተከትሎ የሚሔድ ሥርዓት ያለው አቋጣጠር ነው።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ 3

<<ጥምቀት>>

በዚህ ጥምቀት በሚል ርእስ መነሻ፥ ከዚህ ቀጥለው ያሉትን፥ ማለትም፤

<<ሀ>> ስለ ጥምቀት ቀጥተኛ ትርጉምና መሠረታዊ ምሥጢሩ፥

<<ለ>> ስለ ጥምቀት አስቀድሞ የተነገረው ትንቢትና ፍጻሜው፥

<<ሐ>> ስለ ጥምቀትና መሠረታዊ ጥቅሙ በሐዲስ ኪዳን፥

<<መ>> ወንድ ልጅ በተወለደ በ40 ቀኑ፥ ሴት ልጅ በተወለደች በ80 ቀኗ እንዲጠመቁ የመደንገጉ ምክንያትና ዋና መሠረታዊ ምሥጢሩ፥

<<ሠ>> ስለ ግዝረት መሠረታዊ አመጣጥና ጥቅሙ፣ በሐዲስ ኪዳን ያለውም፥

<<ረ>> ስለ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት፥

<<ሰ>> ታቦታት በልዩ ልዩ ዝማሬ እየታጀቡ ወደ ባሕረ ጥምቀት መውረዳቸው፥

<<ሸ>> ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ሔዶ በፈጠረው፣ በባሪያው (በአገልጋዩ) በዮሐንስ እጅ የመጠመቁ ምሥጢር፥

እነዚህንና ከእነዚህ ጋር የተያያዙትንም ምሥጢራት ዐጠር ባለ መልኩ ደረጃ በደረጃ እንመለከታለን።

ክፍል 7

<<ሀ>> የጥምቀት ቀጥተኛ ትርጉምና መሠረታዊ ምሥጢሩ፥

ጥምቀት <<አጥመቀ አጠመቀ>> ከሚል የግእዝ ግስ የሚገኝ ዘር ነው።

ጥምቀት በነጠላ ትርጉም ሲተረጉም (ቀጥተኛ ትርጉሙ) ሰውነትን በውሃ መጠመቅ፥ ውሃ ውስጥ መጥለቅ፣ ውሃ ውስጥ ገብቶ መታጠብ፥ በውሃ መረጨት ማለት ሲሆን፥

ምሥጢራዊ ትርጉሙም፥ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በውሃ ተጠምቆ ስመ ክርስትናን መቀበል፥

ክርስቲያናዊ የክርስቶስ ወገን መባል፣ የመንፈስ ቅዱስ ልጅ መሆን ማለት ነው።

ክፍል <<8>>

<<ለ>> ስለ ጥምቀት በብሉይ ኪዳን አስቀድመው ከተነገሩት ትንቢታት መካከል፥

<<1>> በትንቢተ ኢሳይያስ እንደምንመለከተው እግዚአብሔር ያዕቆብን፥ <<በተጠማ ላይ ውሃን፥ በደረቅም መሬት ላይ ፈሳሾችን አፈስሳለሁና መንፈሴን በዘርህ ላይ በረከቴንም በልጆችህ ላይ አፈስሳለሁ>> ብሎታል። ኢሳ 44፥3።

<<2>> በትንቢተ ሕዝቅኤልም፥<<ጥሩ ውሃንም እረጭባችኋለሁ፥ እናንተም ትጠራላችሁ ከርኩሰታችሁም ሁሉ፣ ከጣዖታችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁ።

አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ>> ብሏል።

በጥምቀት የአዲስ ልደት እንደምንወለድ አስቀድሞ ትንቢቱ ተነግሯል ማለት ነው። ሕዝ 36፥25።

www.zeyeneta.com

<<3>> ነቢዩ ሚክያስም ስለ መድኃኒታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢኣትን የማስተስረይ አምላካዊ ሥራ ሲገልፅ፥

<<ተመልሶ ይምረናል ክፋታችንን ይጠቀጥቃል ኃጢኣታችንንም በባሕሩ ጥልቅ ይጥለዋል>> በማለት አስቀድሞ ተናግሯል። ሚክ 7፥19

ይኸውም ዲያብሎስ አዳምንና ሔዋንን የእርሱ ተገዥዎች፣ አገልጋዮቹ እንደሆኑ አስመስሎ፣ አታሎ በማጸፍ በሲኦልና በባሕር አስቀምጦት የነበረውን የዕዳና የጥፋት ውል ደምስሶ ከኃጢኣት ነፃ እንደሚያደርገን ጌታችን ስለገለፀለት ነው ትንቢቱን አስቀድሞ የተናገረ።

<<4>> መጥምቁ ዮሐንስ ደግሞ ቀደም ብሎ በነቢዩ ኢሳይያስ በተነገረው መሠረት፥ <<እኔ ለንስሓ በውሃ አጠምቃችኋለሁ እርሱ ግን በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል>> ብሎ ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጥምቀት አማካይነት ልጅነትን የመስጠት አምላካዊ ሥራ ገልጾአል። ማቴ 3፥11 ማር 1፥1 እና ዮሐ 1፥26 እንመልከት።

መጥምቁ መለኮቱ ቅዱስ ዮሐንስ አስቀድሞ እንደገለፀልን የዮሐንስ ጥምቀት በውሃ ሆኖ ለንስሓ ለዝግጅት ነበር እንጂ ልጅነትን አላሰጠም።

የጌታችን ጥምቀት ግን በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ስለ ሆነ የመንፈስ ቅዱስ ልጅነትን ያሰጣል።

አም ከጌታችን የምናገኘው ጥምቀት ፍጹም ልጅነትን የሚያሰጥ ለስርየተ ኃጢኣት፣ ለፍጹም ነፃነት፣ ለዲያብሎስ ድል መንሻ፣ ለመንግሥተ ሰማያት መውረሻ የሚያበቃ ነው። ከዚህ በስተቀር ለመንግሥተ ሰማያት መብቃት አይቻልም።

ምክንያቱም በቅዱስ ወንጌሉ ጌታችን አምኖ የተጠመቀ ይድናል፥ አምኖ ያልተጠመቀ ግን አይድንም ብሎ ስለተናገረ በእግዚአብሔር የባሕርይ አምላክነት፣ በእዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት፣ በእግዚአብሔር ፍጹም አዳኝነት አምኖ ያልተጠመቀ ፍጹም ድኅነት፣ ፍጹም ሕይወት የለውም። ማር 16፥16

አም ሰው ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ

ካልተወለደ፥ ማለትም ይህችን ልጅነትን የምታሰጠው ጥምቀት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በውሃ ያልተጠመቀ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ልጅ እንደማይባልና ወደ መንግሥተ እግዚአብሔርም (ወደ መንግሥተ ሰማያትም) ፈጽሞ መግባት እንደማይችል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌልም ነግሮናል። ዮሐ 3፥5።

አስቀድሞ በልዩ ልዩ ቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፎ፣ በነቢያት ልሳን (አንደበት) በትንቢት መልክ ተነግሮ በየክፍሉ ተዘግቦ የምናገኘው ቅዱስ ቃልም ለጊዜው በወቅቱ ለነበሩት ይሁን እንጂ የትንቢቱ ፍጻሜ ግን ጌታችን በዘመነ ሥጋዌው ስለሚሠራው አምላካዊ ሥራ፣ ስለ መድኃኒታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጢር የሚመለከት እንደመሆኑ መጠን በሐዲስ ኪዳን በእየደረጃው ተፈጽሞ እናገኘዋለን።

ክፍል <<9>>

<<ሐ>> ስለ ጥምቀትና መሠረታዊ ጥቅሙ በሐዲስ ኪዳን፥

ስለ ጥምቀት በሐዲስ ኪዳን ከተጠቀሱት መካከል ከዚህ ከፍ ብሎ በመ ተራ ፊደል የተገለጸው እንዳለ ሆኖ ጥቂቶችን ደግሞ ለምሳሌ ያህል ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

ጌታችን ደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያትን <<እንግዲህ ሒዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው>> ብሏቸዋል።

ማቴ 28፥18

ይህ ትእዛዝ ለጊዜው ለሐዋርያት ቢሆንም፥ በሐዋርያት እግር ተተክተው የሐዋርያትን ሥራ የሚሠሩ እስከ ምጽአቱ ድረስ የሚነሡትንም ካህናትን ሁሉ ይመለከታል።

ቃሉ ሲብራራም ያልተማሩትን እያስተማራችሁ፣ ያላመኑትንም እያሳመናችሁ፣ ያልተጠመቁትን ሁሉ እያጠመቃችሁ የክርስቶስ ተከታዮች የክርስቶስ ወገኖች ክርስቲያኖችን አድርጓቸው ማለት ነው።

አም በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አምኖ የተጠመቀ ሁሉ

www.zeyeneta.com

የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ልጅ ስለ ሆነ በእግዚአብሔር ማኅበር ገብቶ በክርስቶስ አንድነት ይኖራል።

በመሆኑም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፥ በገላትያ ምዕ 3፥26 መልእክቱ፥ <<በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ስለ ሆናችሁ ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ክርስቶስን ለብሳችኋልና በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁ>> ብሎአል።

በቲቶ 3፥4 መልእክቱ እንደምንረዳውም፥ በካህኑ አማካይነት በመንፈስ ቅዱስ ስም በውሃ ወንድ ልጅ በተወለደ በ40 ቀኑ፣ ሴት ልጅ በተወለደች በ80 ቀኗ አንድ ጊዜ ብቻ የምንጠመቀው ጥምቀት ከማኅፀነ ዮርዳኖስ ከአብራክ መንፈስ ቅዱስ በአዲስ ልደት ተወልደን የእግዚአብሔር ልጆች የምንባልበት፣ ስመ ክርስትና'ን የምናገኝበት፣ የክርስቶስ ወገኖች፣ ክርስቶሳውያን ክርስቲያኖች መሆናችንን የምንታወቅበት ልዩ ስጦታችን ነው።

ጥምቀት ለንስሓ፣ ለስርየተ ኃጢኣት የተሰጠ ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ነው።

ስለዚህም ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፋዊ ሥርዓቱንና ሃይማኖታዊ ትውፊቱን ከሊቃውንት አባቶቻችን ተቀብላ ስትፈጽመው ስታስፈጽመው ትገኛለች።

በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ ትውፊት (ቀ[illegible] መሠረት በየዓመቱ የምናከናውነው የጥምቀት ሥርዓት የጌታችንን ጥምቀት ለማስታወስ፣ በዐሉን ለማክበር፣ ትምህርቱን በተግባር ለማስተማር፣ መንፈሳዊ ሥርዓቱና ባህሉ ለሁሉም ሕዝበ ክርስቲያ ግልፅ ሆኖ እንዲሰራጭ፣ ጥንታዊ የሆነ መንፈሳዊ ታሪኩም ለመላው ዓለም በተግባራዊ ትምህርት መልክ እንዲዳረስ ለማድረግ ሲሆን፣

እንዲሁም በውስጡ እያዳንዳችን ከበቀል፣ ከቂም፣ ከሐሜት፣ ከቅንዓት፣ ከምቀኝነት፣ ከጥላቻ፣ ከተንኮልና ከመሳሰለው የኃጢኣት ተግባር ሁሉ ንጹሓን መሆን ተገቢያችን እንደሆነ የሚነግረን፥ እግዚአብሔርንና ሰውን ከሚያሳዝን ሥራ እንድንርቅም የሚመክረን፣ ኃጢኣታችንን እየተናዘዝን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እየተቀበልን ለመንግሥተ ሰማያት መዘጋጀት እንደሚገባን የሚያስገነዝበን ዐቢይ መልእክት ያለበት ነው።

ስለዚህም እያንዳንዳችን ትምህርቱንና ምክሩን ከልብ ተቀብለን በተግባር ልንተረጉመው ይገባናል ማለት ነው።

ክፍል <<10>>

<<መ>> ወንድ ልጅ በተወለደ በ40 ቀኑ፥ ሴት ልጅ በተወለደች በ80 ቀኗ እንዲጠመቁ የመደንገጉ ምክንያት፥

ወንድ ልጅ በተወለደ በዐርብዓ ቀኑ፥ ሴት ልጅ ከሆነች ግን በተወለደች በሰሚኒያ ቀኗ እንዲጠመቁ መወሰኑ ደግሞ መዋዕለ ንጽሕ፣ ወይም የንጽሕና ጊዜ፥ ወንድ ልጅ በተወለደ በ40 ቀኑ፥ ሴት ልጅ በተወለደች በ80 ቀኗ ስለሚፈጸም ሲሆን፥

ምሳሌውም አዳም በተፈጠረ በ40 ቀኑ፥ ሔዋንም በተፈጠረች በ80 ቀኗ በመላእክት ታጅበው ገነት ስለ ገቡ እንደሆነ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ይናገራሉ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትም ያመሠጥራሉ። ዘፍ 2፥8

በኦሪት ዘሌዋውያን ተዘግቦ እንደምናገኘው በሙሴ ዘመንም ወንድ በተወለደ በ40 ቀኑ፣ ሴት በተወለድች በ80 ቀኗ ወደ ቤተ መቅደስ እየሔዱ የእግዚአብሔርን በረከት እንዲቀበሉ በእግዚአብሔር ታዟል። ዘሌ 12፥1

ክፍል <<11>>

<<ሠ>> ስለ ግዝረት መሠረታዊ አመጣጥና ጥቅሙ፥

የስምንት ቀን ወንድ ልጅ ሁሉ እንዲገረዝ በእግዚአብሔር ታዟል ዘፍ 17፥10 በዘፍጥረት ምዕ 17፥9 ጀምሮ እንደምንመለከተው በኦሪት ሥርዓት በጥምቀት ፈንታ ግዝረት የአሕዛብ፥

ግለትም የአረማውያንና የእግዚአብሔር አማኞች መለያ፣ የእምነት ምልክት፣ የቃል ኪዳን መሠረት እንደ ነበር ይታወቃል።

በኦሪት ዘመን በ8ኛው ቀኑ ያልተገረዘ ሁሉ ከአብርሃም ቤተ ሰብ እንዲቆጠር፣ ምድረ ርስት እንዲወርስ፣ ከተስፋውም እጎዲካፈልና የእግዚአብሔር ወገንም እንዲባል ሥርዓቱ ፈጽሞ አይፈቅድለትም ነበር።

www.zeyeneta.com

ይኸውም አብርሃም ፈጣሪው እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት በ9
ዕድሜው የተገረዘ ሲሆን፥ ልጆቹ ደግሞ በ8ኛው ቀናቸው
እንዲገረዙ በእግዚአብሔር ተነግሯል። ዘፍ 17፥9።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በተወለደ በ8ኛ ቀኑ ሥርዓተ
ግዘረትን ፈጽሞ <<ኢየሱስ>> በሚል ስም ሊጠራ ችሏል።
ሉቃ 2፥21።

አሁን ባለንበት ዘመን በሐዲስ ኪዳን ጊዜ ግን መሠረታዊ ሕይወት
ያለው ጥምቀት ነው እንጂ ግዝረት እንዳልሆነ ተደጋግሞ ተነግሮናል

በተለይም ቅዱስ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ ነው
እንጂ መገረዝም ሆነ አለመገረዝ ከንቱ ነው በማለት
በመልእክቶቹ ደጋግሞ እንደገለፀልን ከክርስቶስ ጥምቀት ጀምሮ
ባለው የሐዲስ ኪዳን ዘመን ጥምቀት ነው እንጂ ግዝረት
ጉዳትም ጥቅምም የለውም። 1ኛ ቆሮ 7፥19,
ሮሜ 3፥29, 4፥9

ምዕራፍ <<4>>

ክፍል <<12>>

<<ረ>> የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት፥

የጌታችን ጥምቀት ከፍጡራን ጥምቀት የሚለይበት ሰፊ ምሥጢር
እንዳለው በቅዱሳት መጻሕፍት ተደጋግሞ ተገልጿል።

ጌታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከተወለደ በኋላ አምላክ ነኝ
በአንድ ጊዜ ልደግ ሳይል ከኃጢአት በስተቀር ሰው የሚሠራውን
ሥራ ሁሉ እየሠራ በትንሽ በትንሽ አደገ፤ ከዚያም በሰላሣ
ከረምቱ (በ30 ዓመቱ)ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ሔዶ በዮሐንስ
እጅ ተጠመቀ። ማቴ 3፥13, ማር 1፥9, ሉቃ 3፥21,ዮሐ 1፥29
እጎመልከት ጌታ ወደ ባሪያው ወደ ዮሐንስ ሔዶ የተጠመቀው
ለምንድ ነው? ቢባል ዋና ምሥጢራዊ መልእክቱ ጌታችን ወደዚህ
ዓለም የመጣው ለፍጹም ትሕትና መሆኑን የሚያስረዳ ሲሆን፥

ነገሥታትም ሆኑ መኳንንት ሌሎችም ሁሉ አጥማቂው ካህን
ወዳለበት ወደ ቤተ እግዚአብሔር እየሔዱ መጠመቅ
እንደሚገባቸው ለማስገንዘብ ለአብነትም ጭምር እንደሆነ
በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አባቶቻችን ተገልጸአል።

ክፍል <<13>>

<<ሰ>> ታቦታት በልዩ ልዩ መንፈሳዊ ዝማሬ ታጅበው ወደ ባሕረ ጥምቀት የሚወርዱ ለምንድ ነው?

ታቦታት ታጅበው ወደ ባሕረ ጥምቀት መውረዳቸው ጌታችን
ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ሔዶ በዮሐንስ እጅ ስለተጠመቀ፥ ጌታችን
ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ መውረዱንና፣ በዮሐንስ እጅ የመጠመቁን
መሠረታዊ ምሥጢር ለማስታወስ ነው።

ክፍል <<14>>

<<ሸ>> ጥምቀቱን በዮርዳኖስ ወንዝ ያደረገበት ምሥጢርስ ምንድ ነው? ቢባል ደግሞ፥

ትንቢቱና ምሳሌው መፈጸም ስለ አለበት ነው።

ይኸውም ዋናው ምሥጢሩ ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከሊቃውንተ
ቤተ ክርስቲያን መደበኛ ጉባኤ እንደምንረዳው፥ ትንቢቱ፥ ልበ
አምላክ የተባለው ነቢዩ ዳዊት ዮርዳኖስ ጌታዋን አይታ ሸሸች፣
የዮርዳኖስ ፈሳሽም ወደ ኋላው ተመለሰ ብሉ በመዝ 113፥3፥
አቤቱ የዮርዳኖስ ወንዞች አዩህ፤ አይተውህም ፈሩ ብሎም
በመዝ 76፥16 አስቀድሞ በትንቢት መልክ የዘመረው ሲሆን፥
ምሳሌውም፥ ዮርዳኖስ ከላይ ነቁ ወይም ምንጩ አንድ ሆኖ
ዝቅ ብሎ ከታች በደሴት ተከፍሎ መልሶ ደግሞ እንደሚገናኝ፥
አንድ እንደሚሆን፣ የሰውም ሁሉ የመጀመሪያ ምንጩ ወይም
የትውልድ ሐረጉ ከላይ አንድ አዳም ሆኖ ከታች ዝቅ ብሎ
እስራኤል በግዝረት፣ አሕዛብ በቁልፈት ተለያይተው ሲኖሩ፥
በክርስቶስ ጥምቀት ግን ሁሉም አንድ ስለ ሆኑ የአንድነታቸው
ምሳሌ ነው።

www.zeyeneta.com

ሌላው ዐቢይ ምሥጢሩ ደግሞ÷ ዲያብሎስ በአዳምና በሔዋን ላይ የጨለማ መጋረጃውን አጽንቶ አሰቃይቶ ይዞ በተዘዋዋሪ መንገድ ወዳጅ መስሎ በመቅረብ ስመ ገብርነታችሁን (ባርነታችሁ, የእኔ ተገዥዎች መሆናችሁን) ጽፋችሁ፣ ፈርማችሁ ብትሰጡኝ÷ ይህን ችግራችሁን አቀልልላችሁ ነበር ባላቸው ጊዜ ከባድ ጭንቀት ላይ ነበሩና ችግራቸውን የሚያስወግድላቸው÷ ጭንቀታቸውንም የሚያቀልላቸው እውነተኛው ረዳታቸውን መስሎዋቸው ይሁንብን ብለው አዳም የዲያብሎስ ባሪያ አገልጋይ÷ ሔዋንም የዲያብሎስ ባሪያ አገልጋይ በሚል ውል ከዲያብሎስ ጋር ስለ ተስማሙ ዲያብሎስም ይህንን በሁለት እብነ ርኪም (እብነ በረድ) ጽፎ አንዱን በቦርዳኖስ ባሕር÷ አንዱንም ደግሞ በሲኦል ጥሎት ነበርና በቦርዳኖስ ባሕር የጣለውን ጌታችን ሲጠመቅ እንደ ሰውነቱ ተረግጦ እንደ አምላክነቱ አቅልጦ አጥፍቶላቸዋል።

በሲኦል የጣለውንም በዕለተ ዓርብ መለኮት በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ በሲኦል የነበሩትን ነፍሳት በሚያወጣበት ጊዜ አጥፍቶላቸው ወጥቷል።

(ርኪም ብሂል እብነ በረድ)
(ርኪም ማለት እብነ በረድ ማለት ነው)

<<ከመ ይሥዓር መርገማ ለሔዋን ዲበ ዕፅ ተሰቅለ ይላል>>

(ሊቁ ኢትዮጵያዊ ቅዱስ ያሬድ በድጓው ከጥር ፲፩ ቀን ዓራራይ)

በጳውሎስ መልእክት ገላትያ 4÷1 በሰፊው እንደተገለለፀውና÷ ሊቁ ኢትዮጵያዊ ቅዱስ ያሬድም በድጓው÷ ጌታችን የሔዋንን መርገም ወይም ኃጢኣት ይሽር ዘንድ በዕንጨት ላይ ተሰቀለ በማለት እንዳመሠጠረው የርኅራኄና የጽድቅ ባለቤት የሆነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማይመረመር አምላካዊ ጥበቡ የአዳምንና የሔዋንን ዕዳ ሠረዘ፣ የሁላችን ኃጢኣትንም ደመሰሰ።

ከሞተ ኃጢኣት (ከውርስ የኃጢኣት ሞት) ከፍዳና ከመርገም፣ ሁሉ አዳነን፣ ከዲያብሎስ ክፉ አገዛዝም ነፃ አወጣን ማለት ነው።

በቅዳሳት መጻሕፍትና በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አባቶቻችን ምሥጢሩ በሚገባ ተብራርቶ እንደሚነገረን ፈለገ ዮርዳኖስ ልዩ ልዩ ሕይወታዊ ምሳሌን የያዘ ብዙ ድውያንንና ብዙ ደዌያትን የፈወሰ ወንዝ ነው።

ለምሳሌ ያህልም በዐጭሩ ብንጠቅስ÷

ኢዮብ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቆ ከቀሩስሉ፣ (ከደዌው) እንደተፈወሰና÷ ንእማንም በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቆ ከበሽታው እንደዳነ ከቅዱስ መጽሐፍትን የትርጓሜ ታሪክ እናገኘዋለን።

ይኸውም ፈለገ ዮርዳኖስ የሕይወት ወንዝ የድኀነት ምንጭ ነው ማለት ነው። ማቴዎስ 3÷13 ትርጓሜውን እንመልከት።

በትንቢተ ኢያሱ 3÷1 ጀምሮ, እና 1ኛ ቆሮ 10÷1 እንደምንመለከተውም÷ ሕዝበ እስራኤል የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግረው ምድረ ርስት ስለ ገቡ÷ ምእመናን ደግሞ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቀው ገነት መንግሥተ ሰማያት ለመግባታቸው ምሳሌ ሆኗል። ኢያሱ 3÷1 ጀምሮ, 1ኛ ቆሮ 10÷1።
<<በለበው ትርጓሜ መሠረት ሲብራራ ነው>>

ምስጋና ይድረሰውና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ ለፍጹም ሕይወት የመጣ እንደመሆኑ መጠን÷ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፣ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቆ፣ በመስቀል ተሰቅሎ፣ የኃጢኣት ቊስላችንን አጥፍቶልናል።

የመርገምና የፍዳ ዕዳችንን ሁሉ ደምስሶ ከደዌ ሥጋ ከደዌ ነፍስ አድኖናል፣ ዘለዓለማዊ የሆነውን ፍጹም ሕይወትን ሰጥቶናል፣ ከኃጢኣት ሞት ፍጹም ወደ ሆነው ድኀነት፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት አሻግሮናል።

<<አጥምቀኒ በማይ ከመ ይትቀደስ ማይ ወይኩን መድኃኒተ ለውሉደ ሰብእ>> በማለት ቅዱስ ያሬድ በጣዕመ ዜማው እንዳመሠጠረውና በማቴ 3÷13 እንደምንረዳው ጌታችን መጥምቁ ዮሐንስን ውሃው እንዲቀደስ በውሃ አጥምቀኝ ባለው ጊዜ ዮሐንስ ግን ባሪያ በጌታው እጅ ይጠመቃል እንጂ ጌታ በባሪያው እጅ ሊጠመቅ አይገባውምና እኔ ባሪያህ አንተን ጌታዬን ማጥመቅ አይገባኝም ብሎት ነበር።

የዮሐንስ ትሕትናም በዚህ ተገልጿል ማለት ነው።

በተለይም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለፍጹም ትሕትና፣ ለመልካም አብነት የመጣ÷ ትሕትናንና መልካሙን ሥራ በተግባር የሚያስተምር እንደ መሆኑ መጠን÷ ቀደም ብሎ በቅዱሳን ነቢያት የተነገረው ትንቢትና ምሳሌም መፈጸም ስላለበት በሰላሣ ክረምቱ

www.zeyeneta.com

(በ30 ዓመቱ) ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ሔዶ የእርሱ ፍጡር በሆነው በባሪያው በዮሐንስ እጅ ሊጠመቅ ችሏል።

ዮሐንስ ሌላውን ሳጠምቅ በአንተ ስም አጠምቃለሁ እንተንስ በማጠምቅበት ጊዜ አቤቱ ምን እላለሁ? (በማን ስም ላጥምቅህ) ብሎ ጌታን ቢጠይቀውም **<<ነዋ በግው ለእግዚአብሔር ዘያአትት ወያሴስል ኃጢኣተ ዓለም (ኃጢኣተ እምዓለም) ወልዱ ለቡሩክ ከሣቴ ብርሃን በል>>** ዮሐ.1÷29።

አለውና እነሆ የሰውን ኃጢኣት የሚያስተሰርይ (የዓለምን ኃጢኣት የሚያስወግድ) የእግዚአብሔር በግ, መሥዋዕት (የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ) በማለት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አጠመቀው።

በጥምቀቱ ጊዜም እግዚአብሔር አብ አንድ አካል አንድ ባሕርይ አድርጎ ለተዋሕዶ የመረጥኩት በእርሱ ህልው ሆኜ ልመለክበት የወደድኩት የባሕርይ ልጄ ይህ ነውና እርሱን ስሙት በማለት በደመና ላይ ሆኖ ሲመሰክርለት ተሰምቷል፤ መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ሲቀመጥ ታይቷል።

ማር 1÷9, ሉቃ 3÷21, 9÷35, 2ኛ ጴጥ 1÷16።

<<በአበው ትርጓሜ መሠረት ሲብራራ ነው>>

ይኸውም ከቅዳሳት መጻሕፍት ታሪክ እንደምንረዳው÷ ርግብ ቂምንና በቀልን ስለማትይዝ መንፈስ ቅዱስም ጎዳጌ አበሳ ጎዳጌ በቀል÷ (ይቅር ባይ) እንደሆነ ይታወቃልና መንፈስ ቅዱስን በርግብ ይመስለዋል።

ርግብ በኖኅ በማዕ አይኅ ጊዜ÷ ማለትም በኖኅ የጥፋት ውሃ ጊዜ ሐጸ ማዕ አይኅ ነትገ ማዕ አይኅ÷ የጥፋት ውሃ ጉደለ ስትል የዕፀ ዘይትን ቅጠል በአፏ ይዛ በብሥራት ምልክት የምሥራች እያለች የተገኘች ስትሆን መንፈስ ቅዱስም ተስፋ መስቀልን÷ ማለትም ጌታችን በመስቀል ተሰቅሎ የሚሰጠውን ድኅነት ያበሥራል።

ርግብ ክንፏን ቢመቷት ዕንቊላሏንም ቢሰብሩባት ቤቷን ካላፈረሱባት መኖሪያዋን ለቃ እንደማትሔድ ሲታወቅ መንፈስ ቅዱስም ፈጽመን ካልካድነው በስተቀር ኃጢኣትን ብንሠራም እንኳ ጨርሶ አይለይንም ንስሓ እንድንገባ ጊዜ ይሰጠናል በአጠገባችን ሆኖ ይጠብቀናል÷ ብንበድልም በንስሓ ከተመለስን ይቀርባል፤ መጥቶም በእኛ ላይ ያድራል ማለት ነው።

ለዚህ በትርጓሜ ወንጌል ማቴ 3÷17 የሚገኝ ታሪካዊ ምሳሌ አለው÷

ይኸውም አንድ መነኩሴ የግልፎ ልጅ ቆንጅታ (ተውባ) ስለአያት ልቡ በሐጸ ዝሙት ተነድፎ ፈተና ላይ ወደቀና ልጂቱን ሳግባሽ አላት።

እርሷም አባቱ ሳይፈቅድ አይሆንም ነገር ግን ብትጠይቀው እንቢ አይልህምና አባቴን ጠይቀው እርሱ ከፈቀደ ይሆናል አለችው።

መነኩሴውም ግልፎ የሚባለውን አባቷን ስጠኝ ፍቀድልኝ ብሎ ጠየቀው እርሱም አምላኬን ልጠይቅ ብሎ የሚያመልከውን ጣዖቱን ቢጠይቅ መጀመሪያ ፈጣሪውን ይክድ ቆቡንም ይቅደድ አለው።

ግልፎም ተመልሶ መጥቶ መነኩሴውን ፈጣሪህን ካድ ቆብህን ቅደድና ልፍቀድልህ አለው።

መነኩሴው ልጂቱን ለማግኘት ቸኩሉ ነበርና ያለውን ሁሉ አደረገ ፈጣሪውን ክዶ ቆቡንም ቀድዶ ያልከኝን ሁሉ አድርጌአለሁና ስጠኝ አለው።

አሁንም ሒጂ ልጠይቅ ብሎ ሔዶ ጣዖቱን ቢጠይቅ መንፈስ ቅዱስ ፈጽሞ አልተለየውም በአጠገቡ ሆኖ ይጠብቀዋልና ፈጽሞ እስኪለየው ድረስ እትሰጠው አለው።

መነኩሴው እሺ አሁንስ ቢለው ግልፎም ተነግሮታልና አይሆንም ቆይ ጠብቅ አለው።

በዚህ ጊዜ መነኩሴው የፈለኩትን ሳላገኝ÷ ያውም ለኃላፊ ለጠፊ ምኞት ስል ፈጣሪዬን ካድኩ፣ ቆቤንም ቀደድኩ ብሎ ከልቡ አዝኖ አልቅሶ ንስሓ ቢገባ ፈጽሞ አልተለየውም ነበርና መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል መጥቶ ሲያድርበት ታይቷል።

ይኸውም በተግባሩ ተፀፅቶ በንስሓ ወደ እግዚአብሔር በመመለሱ ነው።

ይህ ሁሉ ሲሆን ለመነኩሴው አልተገለጸለትም÷ ነገር ግን ለአንድ የበቃ ንጹሕ ባሕታዊ ምሥጢሩ ተገልጾለት ይመለከት እንደ ነበር በታሪኩ ተጠቅሷል።

<<ከአበው ትርጓሜ ማቴ 3÷1 የተጠቀሰ ነው>>

www.zeyeneta.com

እኛም ተሳስተን ብናጠፋ፣ ኃጢኣትን ብንሥራም እንኳ ተስፋ በመቊረጥ እኔ ኃጢኣተኛ ስለ ሆንኩ እግዚአብሔር አይምረኝም ማለት የለብንም። እንደዚህ የምንል ከሆን በእግዚአብሔር ፍጹም አምላክነትና ፍጹም መሓሪነት አንተማመንም ማለት ነው።

ምክንያቱም እግዚአብሔር የምሕረትና የይቅርታ አምላክ እንጂ ጨካኝ አይደለምና ከሁሉ በፊት ኃጢኣትን ከመሥራት፣ ከመበደል መቆጠብ፣ መጠንቀቅ ተገቢ ሲሆን፥ መቸም ሰው በተፈጥሮውም ደካማ ነውና ተሳስተን ከበደልን ደግሞ ምሕረትን በሚያስገኝ መልካም ሥራ፣ በዓውደ ምሕረት (በቅዳስ መካን) በእግዚአብሔር ቤት ተገኝተን፥ በበደላችን ተፀፅተን፣ ከልባችን አልቅሰን፣ ንስሓ ገብተን አምላካችንን ብንለምን እግዚአብሔር ፈጣሪአችን የርኅራኄና የጽድቅ ባለቤት፣ ይቅር ባይ፣ መሐሪ አምላክ ስለሆነ ይምረናል፣ በደላችንን ይቅር ይለናል መንፈስ ቅዱስም አይለየንም ማለት ነው።

ስለዚህ በፍጥረቱ የማይጨክን ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ፍጹም አምላክ ሲሆን ሊያድነን ስለ ፈቀደ ወደዚህ ዓለም መጥቶ፣ ፍጹም ሰው ሆኖ፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፣ በዮርዳኖስ ባሕርና በሲኦል የነበረውን የጥፋት ውላችንን ሁሉ ደምስሶ፥ ፍጹም የሆነውን ዘለዓለማዊውን ሕይወት ሰጥቶናልና እኛም በተከታተቹ በመምህራን አማካይነት በየጊዜው፥ በየክፍሉ የሚቀርብልንን ንጹሕ የሆነውን የእርሱን ቃል እየሰማን በተግባር ላይ ማዋል ይገባናል።

አዎ ሁል ጊዜ በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፥ በአባቶቻችንና በካህናት የሚሰጠንን ጠቃሚ ምክር እየተቀበልን ሕጉንና መመሪያውን መጠበቅ፥ ትእዛዛቱንም መፈጸም አለብን። የሃይማኖት መታወቂያው መልካም ምግባር ነውና ሃይማኖታውያን መሆናችንን በመልካም ሥራ መግለጽ ያስፈልገናል ማለት ነው። ሃይማኖታችንን ከመልካም ምግባር ጋር ይዘን፥ በማየ ንስሓ (በንስሓ ውሃ) ታጥበን፣ ከኃጢኣት ሁሉ ንጹሓን በመሆን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እየተቀበልን ወደ ባሕት፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት እንድንገባ የእርሱ መልካም ፈቃድ ይሁንልን።

የቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፥ የትጉሃን መላእክት፣ የቅዳሳን፣ የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃንና የሰማዕታት በረከት ረድኤት ሁል ጊዜ አይለየን።

ስብሐት ለእግዚአብሔር ለዘአብጽሐነ እስከ ዛቲ ሰዓት፤
ከዚህ ዕለት ከዚህ ሰዓት ላደረሰን ለእግዚአብሔር አምላካችን ምስጋና ይድረሰው።

<<ቃና ዘገሊላ፥>>

ምዕራፍ <<5>>

ቃና ዘገሊላ፥

በዚህ ቃና ዘገሊላ በሚለው ርእስ ስለ ቃና ዘገሊላና የቃና ዘገሊላ መሠረታዊ ምሥጢርን እንመለከታለን።

ክፍል <<15>>

የዕለቱ ምስባክ በልሳነ ግእዝ (በግእዝ ቋንቋ) ሲነገር፥

<<አስመ መምህረ ሕግ ይሁብ በረከተ
ወየሐውር እምኃይል ውስተ ኃይል
ወያስተርኢ አምላክ አማልክት በጽዮን>>
ይላል።

በአማርኛ ሲተረጐምም፥ የሕግ መምህር በረከትን ይሰጣልና ከኃይል ወደ ኃይል ይሔዳል፥ የአማልክት አምላክ በጽዮን ይታያል ማለት ነው። መዝ 83፥6።

ይህ መዝሙር ከመጀመሪያው ልበ አምላክ የተባለው ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት አቤቱ የኃያላኑ ባለቤት በማለት ፈጣሪው እግዚአብሔርን ያመሰገነበት ሲሆን፥ አለፍ ብሉ ከቊጥር 6 ደግሞ ሕግን የሠራ የወሰነ ያስተማረ መምህረ ሕግ ኢየሱስ ክርስቶስ በረከተ ሥጋን በረከተ ነፍስን ይሰጣልና ከኃይል ወደ ኃይል፥ ማለትም ድልን ከማድረግ ወደ ድል ማድረግ፣ ተአምራትን ከማድረግ ተአምራትን ወደ ማድረግ ይሔዳል፤

ጣዖታትን ቀጥቅጠ አጥፍቶ የእርሱ አገልጋዮች የሚሆኑ ካህናትን ያዘጋጀ (የመደበ) ልውል እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም በረድኤት ተገለጠ።

ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ በማለት የእግዚአብሔርን አምላካዊ ሥራ የሚገልጽ ምሥጢርን ያመሠጠረበት ነው።

www.zeyeneta.com

በመዝሙር 45፥7ም ከዚህ ጋር በተመሳሳይ የኃያላኑ ባለቤት አምላ መጠጊያችን የሚሆን የያዕቆብ ፈጣሪ በረድኤት፣ (በባሕርይ አምላክነት) ከእኛ ጋር አለ። መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅንም ትወልጅያለሽ ብሎ ደስ ካሰኛት ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደ አምላካችን በረድኤት ከእኛ ጋር ነው የሚል ምሥጢር ይገኛል።

ነቢይ ዳዊት በመዝሙር 86፥3 ደግሞ፥ <<ነኪር ነገሩ በእንቲአኪ ሀገረ እግዚአብሔር>> እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን የእግዚአብሔር ከተማ (ማደሪያ) ሆይ ስለ አንቺ (በአንቺ) የተደረገው ሁሉ ዕፁብ ድንቅ ነው በማለት አስቀድሞ በትንቢታዊ ምሥጢር አመስግኗታል ዘምሮላታልም።

ይኸውም አምላክን ያለ ዘርና ያለ ሩካቤ በድንግልና ፀንሳ፣ በድንግልና መውለድዋ ፈጽሞ የማይመረመር አምላካዊ ጥበብ፣ አምላካዊ ሥራ ነውና ስለ አንቺ የተነገረ፣ ባንቺ ምክንያት የተሻሻ ሕይወት፣ የተፈጸመው ተስፋና ለአንቺ የተደረገ ሁሉ በፍጡር ሊለካ የማይቻል ዕፁብ ድንቅ የሆነ አምላካዊ ሥራ ያለበት ምሥጢር ነው ማለት ነው።

<<በአበው ትርጓሜ መሠረት ሲብራራ ነው>>

አም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማኅፀኗን ዓለም አድርጎ 9 ወር ከ5 ቀን ሲመሰገንባት ኑሯልና እመቤታችን ሀገረ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር ሀገር, የእግዚአብሔር ከተማ, የእግዚአብሔር ማደሪያ) ትባላለች።

(በትርጓሜው ሲብራራ) እግዚአብሔር እመቤታችንን በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ አፀናት።

ከቅዳሳት መጻሕፍት ትርጓሜና ከሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አባቶቻችን እንደምንረዳው 3 አካላት አድረውባታል ይላል።

(አብ, ወልድ, መንፈስ ቅዱስ ማለታችን ነው)።

ይኸውም አብ ለአጽንኦ፥ መንፈስ ቅዱስ ለአንጽሖ፥ ወልድ በተለየ አካሉ ለመዋሐድ፣ ለመከፈል (ለመወለድ ነው)። ለአንጽሖ ሲልም ነውርና ኃጢአት ኑሮባት ሳይሆን ጠበቃት (ከለከላት) ማለት ነው ብሎ በማቴዎስ ወንጌል 1፥18 በትርጓሜው አመሥጥሮታል።

ምክንያቱም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከኃጢአትና ከነውር ሁሉ ንጽሕት የሆነች፣ በዘመናችን አንድ አንድ ሰዎች ጥንተ አብሶ እያሉ የሚጠሩትም ፈጽሞ የሌለባት ናት።

አም እግዚአብሔር አብ በነቢያት አድሮ በእርሱ ሀልው ሁኜ የምመሰገንበት የምወደው ልጄ ይወርዳል ይወለዳል ብሎ ትንቢትን ተናግረ፣ አካላዊ ቃሉን ለኩነተ ሥጋ ሰጠ።

ማለትም <<ቃል አብ ሕያው ዘወረደ እምሰማያት, ቃሉ ለአብ>> የአብ ቃል የሚባል የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ እግዚአብሔር ወልድ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን፣ ከነፍሷም ነፍስን ነሥቶ ተዋሐደ።

ይኸውም ትስብእት ከእመቤታችን ተከፈለ የያዕቆብ ፈጣሪ፣ የኃያላኑ ባለቤት እግዚአብሔር ፍጹም የባሕርይ አምላክ ሲሆን፥ ከእኛ ጋር ተዋሐደ፥ ከሥጋችን ሥጋን ከነፍሳችንም ነፍስን ነሥቶ (ተዋሕዶ) ፍጹም ሰው ሆነ፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ ማለት ነው።

በመሆኑም ከላይ በተገለጸው መዝሙር 45 በዚህ ዓለም ወይም በቃና ዘገሊላ ያደረገውን የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ፣ ተአምራቱን ሁሉ ታቦ ዘንድ በዕግረ ጎሊና ኑ ይለናል።

ስለዚህም ከአምልኮ ባዕድ ወደ አምልኮ እግዚአብሔር፥ ከትዕቢት ወደ ትሕትና፥ ከክፋትና ከተንኰል፣ ከምቀኝነትም ወደ የዋህነት፥ ከቂምና ከበቀልም ወደ ይቅር ባይነት ተመልሰን በንጹሕ ልብ ወደ እግዚአብሔር አምላካችን ልንቀርብ ይገባናል።

ክፍል <<16>>

ሰመሆኑ ቃና ዘገሊላና የቃና ዘገሊላ መሠረታዊ ምሥጢር ምንድ ነው?

ቃና ኢየሩሳሌም አካባቢ በገሊላ አውራጃ (አጠገብ) የምትገኝ መንደር እንደሆነች ይታወቃል።

<<ወአመ ሣልስት ዕለት ከብካብ ኮነ በቃና ዘገሊላ ዮሐ 2፥1

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማረያም ከተወለደ በኋላ በትንሽ በትንሽ አድጎ፣ በ30

www.zeyeneta.com

ክረምቱ ወይም በ30 ዓመቱ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ሔዶ፣ በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ ሳይውል ሳያድር ወድያውኑ ገዳመ ቆሮንቶስ ገብቶ 40 ቀንና 40 ሌሊት ጸመ።

መዋዕለ ጾሙን ፈጽሞ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰና በ3ኛ ቀኑ በቃና ዘገሊላ ሠርግ ተገኝቶ ቀዳሚ ወይም መጀመሪያ ተብሎ የሚታወቀውን ተአምራቱን ገለፀ፤ ውሃውን ግሩም የሆነ የወይን ጠጅ አደረገው ማለት ነው።

(ጥንተ ቃና ዘገሊላ ((ውሃውን የወይን ጠጅ ያደረገበት ጊዜ)) እንደ እኛ ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር የካቲት 23 ቀን መሆኑ ነው)።

ይህ እርሱ ራሱ፣ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምና ደቀ መዛሙርቱ የተኹበት ሠርግ÷ የሠርጉ ባለቤቶች ወይን (ጠጅ) ስለ አለቀባቸው ርኅርኅተ ኅሊና እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ጠጅ እኮ አልቆባቸዋል አለችው።

(አማላጅነቷንም ያመለክታል)

ጌታችንም አንቺ ሴት ከአንቺ ጋራ ምን አለኝ ጊዜዬ እኮ ገና ነው አልደረሰም አላት።

<u>በመሠረታዊ ምሥጢሩ ሲብራራም</u>÷ ጌታችን ውሃውን ጠጅ አድርግላቸው ብትዪኝ አይሆንም እልሽ ዘንድ ከአንቺ ጋር ምን ጠብ አለኝ÷ ነገር ግን ውሃውን ጠጅ አድርጌ የማጠጣቸው በእኔ ፈቃድ ነው እንጂ በአንቺ ትእዛዝ አይደለም።

ደግሞም እኮ ጊዜዬ ገና ነው አልደረሰም አላት ማለት ነው።

<u>እዚህ ላይ</u>÷ መናፍቃንና አፅራረ ማርያም (የቅድስት ድንግል ማርያም ጠላቶች) ይህን ትክክለኛውን ምሥጢር ለራሳቸው እንደሚመቻቸው አጣመው እየተረጉሙ የዋሃኑን ሲያታልሉበት ይገኛሉ። <u>ሐቁ ግን በዐጭሩ ከዚህ እንደሚከተለው ነው።</u>

<<ሀ>> ከአንቺ ጋር ምን ፀብ አለኝ ማለቱ÷ ማኅፀንሽን (አንቺን) ዓለም አድርጌ 9 ወር ከ5 ቀን በአንቺ ማኅፀን የተቀመጥኩ÷ በእኔ ምክንያት ብዙ ኀዘን የደረሰብሽ እናቴ አይደለሽም ወይ ለምን አልታዘዝሽም? ከአንቺ ጋራ እንቢ የምልበት ፀብ ወይም ምክንያት ምን አለኝ? ሲላት ነው።

<<ለ>> ጊዜዬ ገና ነው ማለቱ÷ አምላካዊ ሥራውን በስፋት የሚሠራበት፣ ሥጋውን ቍርሰ፣ ደሙን አፍስሶ የሚሰጥበት፣ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ዓለምን የሚያድንበት ጊዜ ገና ወደ ፊት የሚመጣ ስለሆነ ይህን ሲያመለክት ነው።

<<ሐ>> በእኔ ፈቃድ ነው እንጂ ማለቱ ደግሞ÷ የባሕርይ አምላክ ስለ ሆነ እርሱ ራሱ በማይመረመር አምላካዊ ጥበቡ የፈቀደውን እንደሚያደርግ ለማመልከት ነው እንጂ አማላጅነቷስ አልቀረም ርኅርኅት ናትና ሁል ጊዜ ታሳስባለች ጠጅ እኮ አልቆባቸዋል በማለት ስለ ጠየቀችው በዚህም ሊታወቅ ይችላል።

እመቤታችን አገልጋዮችን የሚላችሁን አድርጉ ማለቷም ከሃሊነቱን ስትገልጽ ነው። ምሥጢሩ እግዚአብሔር ራሱ በፈቃዱ አምላካዊ ሥራውን ይሠራል እንጂ እንደዚህ አድርግ የሚለው በአምላክነቱ ላይ ተአዝዞ (አዛዥ) እንደሌለበት ግን ያረጋግጣል።

<u><< ወአልቦ ዘይብሉ ምንተ ገበርከ</u> ዘንተ አኀሰምካ ወዘንተ አሰነይከ÷ ኢይጽሕቅ ዘይመክሮ ወኢየሐሥሥ ዘይረድኦ አልቦቱ ጥንት ወኢተፍጻሜት>> እንደሚባል ሁሉ÷ <u><<ከቅዱስ ያሬድ ዜማ የሰኑ ሚካኤል ዚቅ የተጠቀሰ ነው>></u> እግዚአብሔርን በአምላክነቱ ገብቶ ምን አደረክህ፣ ምን ሠራህ፣ ይህን መልካም አድርገሃል፣ ያ ግን ጥሩ አይደለም የሚለው ማንም የለም።

እግዚአብሔር የሚያማክረውንም ሆነ የሚረዳውን አይሻም ሁሉ በእጁ የሆነ፣ ሁሉንም ማድረግ የሚችል ምንም የሚሳነው ነገር የሌሰ የባሕርይ አምላክ ነው ማለት ነው።

እግዚአብሔር በዚያን ጊዜ ነበረ በዚያን ጊዜ ግን አልነበረም፣ ከዚህ እስከ ዚህ አለ፣ ከዚህ እስከ ዚያ ግን የለም ተብሎ አይወሰንም በሁሉ ይገኛል። የነበረ፣ ያለ፣ የሚኖር ነው።

እግዚአብሔር ዓለምንና የዓለምን ፍጥረት ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ የፈጠረ፣ በኋላም የፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ ከመኖር ወደ አለመኖር የሚያሳልፍ፣ ለእርሱ ግን ኅልፈት፣ ሽረት፣ የሌለበት ፈጣሪ፣ የፍቡራን ባለቤት፣ የአማልክት አምላክ፣ የገዦዎች ገዥ፣ ዘለዓለማዊ አምላክ፣ ዘለዓለማዊ ንጉሥ እንደሆነ ለማረጋገጥም ነው። <u>ዳን 7÷13፣ መጽ. ጥበብ 11÷18፣ 13÷1፣ መቃ ቀዳማዊ 27÷1፣ ሉቃ 1÷32 ዮሐ 1÷1።</u>

<u>ወደ ዋናው መነሻችን እንመለስና</u>÷ እመቤታችን አገልጋዮችን፣

www.zeyeneta.com

(የወይኑ አሳላፊዎችን) ማለትም ወይኑን የሚያቀርቡትን ጌታ የሚላቸሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው። ጌታችንም አገልጋዮችን ጋኖችን ውሃ ቀድተው እስከ አፋቸው ድረስ እንዲመሉዋቸው አዘዛቸው።

እነዚያ የድንጋይ ጋኖች 6 ሲሆኑ እያንዳንዳቸው ሁለት፣ ሁለት÷ ወይም ሦስት፣ ሦስት እንስራ የሚይዙ እንደ ነበሩ ቅዱስ መጽሐፉ ይገልጻል።

አገልጋዮችም ጌታ እንዳዘዛቸው ጋኖቹን እስከ አፋቸው ድረስ ውሃ መሉዋቸው።
ጌታችን አሁን ቀድታችሁ ለአሳዳሪው (ለሊቀ ምርፋቁ) ስጡት አላቸውና ቀድተው ለሊቀ ምርፋቁ ቢሰጡት ውሃው ወደ ወይን ተለውጦ ልዩና መልካም የሆነ ጣዕምን ስለ አመጣ ሊቀ ምርፋቁ የወይን ጠጅ የሆነውን ውሃ በቀመሰ ጊዜ እጅግ ተደነቀ።
እንደዚህ የሆነበትን ምሥጢር ግን አላወቀም ነበርና ሙሽራውን ጾኪማስ ብሎ ጠርቶ ሰው ጥሩውን በመጀመሪያ ያቀርባል እንጂ እንዴት ሰው ጥሩውን አቆይቶ አሁን ሰው ከጠገበ በኋላ ይሰጣል አለው ይላል ቅዱስ ታሪኩ።

አዎ ይህ ድንቅ የሆነ አምላካዊ ሥራ የጌታችን የመጀመሪያ ተአምራት ነው ተብሎ ይነገራል።

ከዚህ ቀጥሎም ደቀ መዛሙርቱን እያስከተለ፣ እያስተማረ፣ ጥቂቱን ኢያበረከተ እየመገበ፣ ድውያንን እየፈወሰ÷ በአጠቃላይ ልዩ ልዩ ተአምራትንና አምላካዊ ሥራዎቹንም እየሠራ ቆይቶ ጊዜው ሲደርስ በመስቀል ተሰቅሎ ፍጥረቱንና ዓለምን ሁሉ አዳነ።

አልደረሰም የተባለው ጊዜም ስለ ደረሰ እንኩ ብሎ፣ ጠጡም ብሎ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ሰጠን። መምህረ ሕግ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በረከተ ሥጋንና በረከተ ነፍስን ያሳድርብን።

የቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፣ የቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት፣ የሁሉም ትጉሃን መላእክት፣ የቅዱሳን ነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃንና የሰማዕታት በረከት፣ ረድኤት ሁል ጊዜ አይለየን።

ከዚህ ዕለት ከዚህ ሰዓት ስለ አደረሰንም ምስጋና
ለእርሱ ይሁን
አሜን።

ምዕራፍ <<6>>

<<ጾምና ጸሎት>>

በዚህ ጾምና ጸሎት በሚል ርእስ መነሻ÷

<<ሀ>> ጾም ማለት ምን ማለት ነው?

<<ለ>> አፈጻጸሙስ እንዴት ነው?

<<ሐ>> ጸሎትስ?

<<መ>> ጾምና ጸሎት ለምን ይጠቅማል? ከምንስ ያድናል?

<<ሠ>> ጾም በብሉይ ኪዳን÷

<<ረ>> ጾም በሐዲስ ኪዳን÷

<<ሰ>> በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ ቀኖና ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 15 እንዲጾሙ የተመደቡት አጽዋማት ቍጥርና የስማቸው ዝርዝር፣

<<ሸ>> ዐቢይ ጾም ማለት ምን ማለት ነው?

<<ቀ>> ዘወረደ ማለት ምን ማለት ነው?

<<በ>> የዘወረደ ጾምስ ምንድ ነው?

<<ተ>> ዐቢይ ጾም÷ ጾም እስከ ስንት ሰዓት ነው የሚጾመው?

<<ቸ>> ንስሓ ምንድ ነው?

<<ኀ>> ሰንበትና የሰንበት መሠረታዊ ምሥጢር ምንድ ነው?
የሚሉትን በየክፍላቸው እንመለከታለን።

www.zeyeneta.com

ዐቢይ መግለጫ ጸምና ጸሎት ምንም እንኳ የየራሳቸው ርእ
እንደሚያስፈልጋቸው ቢታመንበትም በመንፈሳዊ ጉዞኣቸው
ስለሚገናኙ፥ ማለትም የጸም መንፈሳዊ ተግባር በጸሎትና በስግደት
የሚከናወን እንደመሆኑ መጠን በዚሁ ዝግጅት የሁለቱም ምሥጢ
በሚገባ እየተብራራ በአንድነት እንዲገለጹ ተደርጓል።

ክፍል <<17>>

<<ሀ>> ጸም ማለት ምን ማለት ነው?

ጸም <<ጸመ ጦመ ወይም ጸመ>> ከሚል የግእዝ ግስ የሚገኝ
ጥሬ ዘር ሲሆን፥ ተግባራዊ ትርጉሙም መጸም ማለት በጸም ጊዜ
እንዳይበሉ በሃይማኖታዊ ቀኖና የጸም አንቀጽ በተገለጸው
መሠረት የተከለከሉትን ምግቦች አለመብላት፣ በተለይም ሥጋን
ከሚገነባ፣ ሥጋን ከሚያስደስት ነገር ሁሉ መቆጠብ፣ ለመብላት፥
ለመጠጣት፥ ለመደሰት፣ የሚያስጐመጀውን ጊዜያዊውን፣ ኃላፊውን
ተድላ ደስታ ስለ ጽድቅ፣ ስለማያልፈው፣ ስለ መንግሥተ ሰማያ
ብሎ መተው ነው።

ጸም የሥጋን ኃይል በማድከም ሥጋዊ ጉልበትንና ሥጋዊ
ፍላጎትን በመንፈሳዊ ልጓም ይዞ መላውን ሰውነት (አካል)
ለፈጣሪው ለእግዚአብሔር ማስገዛት ማለት ሲሆን፥

እንዲሁም ደግሞ ክፉውን ከመሥራት፣ ክፉውን ከመናገር፣
ክፉውን ከማየት፣ ክፉውንም ከመስማት፥ ከቅንዓት፣ ከተንኰል፣
ከክፋት፣ ከምቀኝነት፣ ከበቀል፣ ከሐሜትና ከዝሙት፥ በአጠቃላይ
እግዚአብሔርንና ሰውን ከሚያሳዝን ተግባር ሁሉ መታቀብ
መወገድ ነው።

አም ጸም ማለት፥ በአንቀጸ ብፁዓን የማቴዎስ ወንጌል 5፥6
እንደተገለጸው፥

መከራን መቻል፣ ልዩ ልዩ ፈተናን ማለፍ፣ ችግሩን ሁሉ ስለ
ጽድቅ ብሎ መታገሥ፥ የታመሙትንና የታሠሩትን መጠየቅ፣
ሕያዋንንና ሙታንን፣ በጸም፣ በጸሎት ማሰብ፥ ያዘኑትንና
የተጨነቁትን በመንፈሳዊ ምክር ማረጋጋት፥ የተቸገሩትንም
ሁሉ እንደራስ ቆጥሮ በተገኘ ዐቅም መርዳት ነው።

አም እነዚህ ከላይ ጀምሮ ደረጃ በደረጃ የተጠቀሱት ናቸው
በተግባር ላይ ከዋሉ የጸምን ትክክለኛ ትርጉም የሚገልጹ።

ክፍል <<18>>

<<ለ>> አፈጻጸሙስ እንዴት ነው?

<<ሐ>> ጸሎትስ?

ጸሎት ከፈጣሪያችን ጋር የምንነጋገርበት ልዩ የሆነ መንፈሳዊ
መገናኛ ነው። የጸም መሠረትና አፈጻጸሙ ሁሉ ደግሞ
በሃይማኖታዊ ሕግ የተደነገገ ሲሆን፥ የጸሎት ሒደትም ከዚሁ ጋር
የተያያዘ በመሆኑ አንድ ላይ እናብራራዋለን።

ጸም አስቀድሞ በእግዚአብሔር ሕግ የታዘዘ ነው፥
ጸሎትም እንደዚሁ።

ይኸውም፥ እግዚአብሔር አምላካችን፥ በፍጹም ፍቅርና ትሕትና
ሆነን ፈጣሪያችንን በጸም፣ በጸሎት መማፀን እንዳለብን
ሲያስገነዝበን በትንቢተ ኢዩኤል ከምዕራፍ 2፥12 ጀምሮ
<<አሁንስ በፍጹም ልባችሁ በጾምም በልቅሶና በዋይታ
ወደ እኔ ተመለሱ፥ ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ>>
ብሎናል።

ዋና መልእክቱ ጹሙ፣ ጸልዩ፣ በልባችሁ ፍጹም ፍቅርና ትሕትና
ይኑር፥ አትታበዩ፣ ተንኰልን፣ ክፋትን፣ ቅንዓትን፣ ምቀኝነትን፥
ቂምንና በቀልን ከልባችሁ አርቁ ማለት ነው።

ሕጉንና መመሪያውን ጠብቀን በትእዛዙ መሠረት እየጸምን
እየጸለይን በፍጹም ልባችን በንስሓ ወደ እርሱ ቀርበን ከለመነው
ደግሞ ፈጣሪያችን ርኅሩኅ፣ ይቅር ባይ፣ መሐሪ አምላክ ስለ ሆነ
በደላችንን ሁሉ ይቅር እንደሚለን፣ ከኃጢአታችንም
እንደሚያነጻን ደግሞ በዚሁ ምዕራፍ ከቊጥር 13 ነግሮናል።

እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን <<ዕፀ በለስን አትብሉ>> ማለቱ
ምንም እንኳ ዋናው ምሥጢሩ የፈጣሪና የፍጡር መለያ የሆነ

አምላካዊ ትእዛዝን እንዲጠብቁ የሚጠቀሙም፥ ማለትም ፍጡራን
እንደመሆናቸው መጠን የፈጣሪያቸውን ሕግንና መመሪያን ማክበር
አንዳለባቸው የሚያመለክት ቢሆንም በአንድ በኩልም ጹሙ
የሚል ምሥጢር አለው።

www.zeyeneta.com

ምክንያቱም አዳምና ሔዋን የፈጣሪያቸውን ሕግ ጥሰው፣ ትእዛዙንም ተላልፈው ያችን ዕፀ በለስ ባይበሉ ኖሮው ከገነት አይወጡም ነበር፣ ከክብራቸው ዝቅ ብለውም አይባረሩም ነበር። ያችን ዕፀ የበሉዋት የሚበላ አጥተው ርቧቸው ሳይሆን

ያልተፈቀደላቸው ዐቅማቸው የማይወሰነውን የባሕርይ አምላክነት በመብል መሻሪያነት ለማሸነት ሲሉ ስለ ነበር የኃጢኣትን ምግብ በልተዋል ማለት ነውና መብል ለውድቀታቸው ምክንያት ሆኖአል

ይኸውና አለመጾም፣ ሕግን መተላለፍ፣ (በሕግ የተከለከለውን መብላት) መመሪያን አለማክበር፣ ሥርዓትን መጣስ የውድቀት ምክንያት ይሆናል ማለት ነው። <u>ዘፍ 2÷16 3÷22</u>

ስለሆነም ሕግን አለማክበር ትእዛዝንም አለመፈጸም፣ ከተፈቀደው ውጭ፣ ከዐቅም በላይ የሆነ መብል፣ መጠጥ መጠቀም ወይም አለመጾም ችግርን እንደሚያስከትል፣ ጉዳትንም እንደሚያመጣ ከዚህ መገንዘብ እንችላለን።

አንድ አንድ ከርሣቸው (ሆዳቸው) አምላካቸው የሆነ ሰዎች፥ ፈሪሳውያን ጌታችንን ደቀ መዛሙርትህ እጃቸውን ሳይታጠቡ በሉ ባሉት ጊዜ፥ ሰውን የሚያረክሰው ከአፍ የሚወጣ እንጂ ወደ አፍ የሚገባ አይደለም ብሉ ስለ መለሰላቸው ይህን ቅዱስ ቃል ለእነርሱ እንደ ፈለጉ ለመሆን፥ ለመብላት፣ ለመጠጣት በሚመቻቸው መንገድ አጣመው እየተረጐሙ (ምሥጢሩን ሳይረዱ ነጠላ ትርጉሙን ብቻ በመያዝ) እህል ደግሞ ምን አበሳ አለበት ከአፉ የሚወጣ እንጂ በአፉ የሚገባ ሰውን አያረክሰውም እኮ ተብሏል እያሉ እየተደናገሩ የሚያደናግሩ አሉ።

በመሠረቱ ይህ ቅዱስ ቃል ሰፋ ያለ ምሥጢር ያለበት ሲሆን በዐጭሩ ሲገለጽም፥ እህል በአፍ ወደ ኾድ ይወርዳል፣ ከተወሰነ ሰዓት በኋላም ይሚሚል፣ ወደ አፈርነትም ይቀየራልና በመጠን ከተመገቡት ክፋት የለውም።

መርዛም ነገር ግን በልብ ታስቦ (ከልብ መንጭቶ) በምላስ ይነገርና ከአፍ ወጥቶ እግዚአብሔርንና ሰውን ስለሚያሳዝን ይህ የከፋ ነው ለማለት ነው።

ስለሆነም ክፉውን ከማሰብ፣ ክፉውን ከመናገር መጾም እንዳለብን ነው የሚያስገነዝበን እንጂ አንድ አንድ ሰዎች በጥሬ ንባቡ ብቻ እንደሚተርኩት አይደለም። <u>ማቴ 15÷1,ማር 7÷14።</u>

<u><< ይህ በአበው ትርጓሜ መሠረት ሲብራራ ነው>></u>

<u>ለመሆኑስ</u>፥ በአፋችን ገዳያችንን መርዝ ብንበላ ተቆራርጠን እንሞትም እንደ? ታዲያ የእግዚአብሔርን ሕግንና መመሪያን የሚያስጥስ፣ ለበቀል፣ ለክፋት፣ ለኃጢኣት ሥራ የሚገፋፋውን፣ ከዐቅም በላይ የሆነውን ምግብንና መጠጥ በአፋችን ወስደን እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያሳዝን ተግባር የፈጸምን እንደሆን ነፍሳችን በኃጢኣት መርዝ አትቆራረጥም ማለት ነውን በሥጋችንም እንጂ ካልሆነ ስፍራ ወድቀን እንጉዳለን።

ተመልከቱ ወገኖች እንኳን በአፍ የሚገባ በጆሮ የሚሰማ፣ በዓይን የሚታይ ክፉና አስቀያሚ ነገርም ወደ ውስጣችን ገብቶ፣ በልባችን ተቀምጦ ሲያሳዝነን፣ ክፉውን ነገር ሲያሰበን፥ ለቂምና ለጥላቻ ሲዳርገን፣ ለበቀል ሲያዘጋጀን፣ ለእጥቂነት ሲጋብዘን፥ ለመጥፎ ተግባርም ሲገፋፋን ይታያል።

<u>ይኸውም</u> በአፋችን የምንወስደው ከልክ በላይ የሆነ የኃጢኣት ምግብና መጠጥ ጥጋብንና ስካርን ያስከትላል፥ ጥጋብና ስካር ደግሞ ለችግር ይዳርጋል፥ እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያሳዝን ተግባር ለመፈጸም ይገፋፋል የኃጢኣትን ሥራ ለመሥራት አጋዥ ሆኖ በል በል ይላል ማለት ነው።

<u>እስቲ በተግባር ከምናየው መካከል አንድን ምሳሌ እንጥቀስ፥</u>

<u>ለምሳሌ</u>፥ አንድ ሰው ሥጋን የሚገነባ ጥሩ የሆነውን ምግብ በራሱም ይሁን በወዳጅ ዘመድ ተጋብዞ ከተመገበ በኋላ ለማወራረጃ ወይም ምግቡን ለመበተን ተብሎ ራሱ ወዶም ሆነ በእንብላ ባዮች ወገኖቹ ተገልግሎ አለ ከሚባለው መጠጥ አንድ ይልና፥ በልቡ እየፈለገም ቢሆን ለመግደርደር፥ ወይም ራሱን ለመጠበቅ ሲል በአፉ ይበቃኛል ይላል።

እነ እንጠጣ ወገኖቹ እባክህ አንድ እማ ጥፊ ነው ተብሏል በማለት አግባብተው ሁለት ሦስቱን ጠና ባለ (በደኅና) መጠጫ እንዲወስድ ያደርጉታል(በእጅ አዙር ሁለት ሦስት ጊዜ አእምሮውን በጥፊ ተመታ ማለት ነው

(በእውነት ከሆነ ምግቡን ለመበተን ሳይሆን ዓላማውንና ሐሳቡን፣ ኑሮውንም ሁሉ ለመበተን ነው)ከዚህ በኋላ እማ ጋባኝ አያስፈልግም ራሱ በእጁ እየጐተተ ይጨምረዋል አዛዡ ከራሱ ሳይ ተቀምጧል ከዚህ በኋላ እማ ምን ይነገራል? ምንስ ጥያቄ አለ? መታዘዝ ብቻ ነው፤ ሒድ ሲባል ወዴት አይልም ተከልክሏል፤ ዝም ብሎ መቀጠል ብቻ ነው።

www.zeyeneta.com

ምክንያቱም አንደበቱ ተቆላልፏል፣ እጁና እግሩም ተሰነካክለዋል፣ (ተሳሥረዋል) የሚያነጋግረው ባዕድ (ሌላ) ነው፣ መሪውን የያዘውም ሌላ ነው።

አሥ ነጂው ሌላ ስለ ሆነ ነጂው ወደ ወሰደው ዝም ብሎ ይነዳል ማለት ነው።

ታዲያ በዚህ ሁኔታ ውስጥ የገባ ሰው አለሊባል ይቻላል?

በዚህ ሁኔታ ውስጥ የገባ ሰውኮ የሚናገረውንምሆነ የሚያደርገውን ነገር ሁሉ አያውቅምና በቁሙ ሙቷል ማለት ነው÷ ወደ ኃጢአት ሞትም እየተጓዘ ነው።

ስለዚህ ይቅር በጸም ወቅት በሌላውም ጊዜ ቢሆን ከዚህ መጠንቀቅ አይገባምን?

አሥ መጸም ማለትም ሥጋችንን ከሥጋዊ ፍላጎት መከልከል፣ በማቴ 5÷6 ጀምሮ በሰፊው እንደተገለጸው የሚያምረውንና የሚያስኮመኵረውን ጊዜያዊ ደስታን ስለ ዘለዓለማዊ ደስታ ስለ ጽድቅ ብሎ መተው፣ መታገሥ ነው።

ክፍል 19÷

መ ጸም, ጸሎት ለምን ይጠቅማል?

ከምንስ ያድናል?

በልዩ ልዩ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደምንመለከተው÷ ጸም ከቀደምት አበው (አባቶች) ነቢያት ጀምሮ በየደረጃው፣ በየክፍሉ እየተጸመ መልካም ውጤት የታየበት ነው።

አሥ ጸም ጸሎት ብዙ ረድኤት የተገኘበት፣ ቅዱሳን፣ ጻድቃንና ሰማዕታት፤ እውነተኞች የእግዚአብሔር ወዳጆች ሁሉ የተጠቀሙበት ሀብተ መንፈስ ቅዱስም ነው።

ለምሳሌም÷ <<አይ 1÷13, 2÷12 መዝ 68÷10>> እንመልከት።

አሥ ጸም, ጸሎት ከሞተ ሥጋ፣ ከሞተ ነፍስ÷ ከፍዳ ከመርገም ከኃጢአትና ከመቅሰፍት ያድናል።

ጸም, ጸሎት÷ ከሐሰት ወደ እውነት፣ ከኃጢአት ወደ ጽድቅ ይመልሳል።

ጸም, ጸሎት÷ የመንግሥተ ሰማያትን መንገድ ያሳያል፣

ጸም, ጸሎት÷ የመንግሥተ ሰማያትን በር ያንኳኳል፣

ጸም,ጸሎት÷ በትክክለኛው መንገድ ወደ መንግሥተ ሰማያት ያስገባል።

ስለሆነም÷ ጸምን እንድንጸም፣ ጸሎትንም እንድናዘወትር (እንድንጸልይ) በብሉይ ኪዳንና በሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ታዘናል።

ክፍል 20÷

ሠ <<ጸም በብሉይ ኪዳን>>

1ኛ በትንቢተ ዮናስ ምዕራፍ 3÷5 እንደምንመለከተው የነነዌ ሰዎች አመድ ነስንሰው፣ ድንጋይ ተንተርሰው፣ ማቅ ለብሰው እግዚአብሔርን በጸም፣ በጸሎትና በልቅሶ ስለ ለመኑ፣ ንጉሡም መሣፍንቱም፣ ትልቁም፣ ትንሹም÷ እንሳሳትም ጭምር ለሦስት ቀን ያህል ምግባቸውን ተከልክለው በልዩ ሱባኤ ንስሓ ስለገቡ÷ በበደላቸውና በጥፋታቸው ተፀፅተው÷ ወደ እውነተኛው አምላካቸው ወደ ፈጣሪአቸው ወደ እግዚአሔር ስለ ጮኹ፣ እግዚአሔርም ጭኽታቸውን ሰማ÷ ልመናቸውንም ተቀበለ።

ሳይመክርና ሳያስጠነቅቅ የማይቀጣ የርኅራኄ አምላክ እግዚአሔር የፍጥረቱ ጥፋት ያሳዝነዋልና፣ የነነዌ ሰዎች በነቢዩ በዮናስ አማካይነት የተነገራቸውን ማስጠንቀቂያ ሰምተው ከጥፋት ጉዞአቸው ወደ እርሱ ወደ መሓሪው ፈጣሪአቸው ወደ እግዚአሔር ስለ ተመለሱ÷ እግዚአሔር ማራቸው።

አሥ እግዚአሔር ፍጥረቱ ሲጠፋ ቸል ስለማይል በተለይም በእንስሳትና ምንም በማያውቁ ሕፃናት መደምሰስ ስለአልጨከነ ይቅር ባይ እግዚአብሔር እንደበደላቸው ሳይሆን የነነዌን ሰዎች እንደቸርነቱና እንደ ምሕረቱ ይቅር አላቸው÷ ምሕረቱን ስለላከላቸውም በበደላቸው ምክንያት በላያቸው ላይ ታዞ ከነበረው መቅሰፍት ተረፉ፤ የእግዚአብሔር ቸርነት፣ ምሕረቱ፣ ይቅርታውና ርኅራኄውም በተግባር ላይ ታየማለት ነው። ዮና 3÷5

2ኛ ነቢያት 40,40 ቀን እየጸሙ ብዙ ተአምራት አድርገዋል። ይልቁንም የእግዚአብሔር ልዩ ወዳጅ የሆነው ሙሴ÷

www.zeyeneta.com

<<40 ቀንና 40 ሌሊት ጾሞ፣ ጸልዮ>> በእግዚአብሔር እጅ የተጻፉት የኪዳን ቃላት (ቃል ኪዳን) ያለባቸውን ሁለት የድንጋይ ጽላቶች ከእግዚአብሔር ተቀብሏል ዘዳ 9÷9÷

ሲቁ ቅዱስ ያሬድም በድጓው <<ሃሌ ሃሌ ሉያ በጸም ወበጸሎት፣ ተመጠወ ሙሴ ኦሪተ>> ኦሥሮነ ቃላተ በማለት አመሥጥሮታል። (ሙሴ ኦሪትንና ኦሥር ቃላት ከእግዚአብሔር ተቀበለ ማለት ነው)

<<አሠርቱ ቃላት እሰ ተጽሕፉ በአጻብዒሁ ለእግዚአብሔር>> (አሠርቱ,ኦሥር ቃላት በእግዚአብሔር እጅ የተጻፉት ናቸው ይላል የአሑድ ሰንበተ ክርስቲያን ውዳሴ ማርያምም)

እንደገናም <<40 ቀንና 40 ሌሊት ጾሞ፣ ጸልዮ>> በእግዚአብሔር ፊት ወድቆ ፈጣሪውን በመለመን ይቅርታንና ምሕረትን ከእግዚአብሔር አማልዶ ሕዝበ እስራኤል በበደላቸው ምክንያት ተፈርዶባቸው ከነበረው የመቅሰፍት ቅጣት እንዲድኑ አድርጓል።

(ስለ ምልጃና አማላጅነትም ከዚሁ መገንዘብ እንችላለን) ዘዳ 9÷25

<<ሙሴ አሁንም (በቃለ ኪዳንና) በትእዛዝ (በርእሰ ሕግ) የታወቁትን አሥሩን ቃላት በሚቀበልበት ጊዜ <<40 ቀንና 40 ሌሊት እየጾመ እየጸለየ>> ከእግዚአብሔር ጋር ይገናኝ እንደ ነበር። በዘፀ ምዕራፍ 34÷27>> ተዘግቦ ይገኛል።

ሕዝበ እስራኤልም በግብጽ የግፍ አገዛዝ ሥር በነበሩበት ዘመን እግዚአብሔርን በጸሎትና በልቅሶ ስለ ለመኑ የጽድቅና የርኅራኄ ባለቤት ልዑል እግዚአብሔር ልቅሶአቸውን ሰማቸው፣ ልመናቸው ንምተቀበለ፣ በመልአኩ ምክሩ ቅዱስ ሚካኤል ሲቁ መላእክትና የእርሱ ባለሟል፣ ታማኙና ወዳጁ በሆነ በሙሴ አማካይነት ከክፉ የባርነት ግዛት ነጻ አውጥቷቸዋል ዘፀ 2÷23።

ይኸውና ጸም, ጸሎት ከግፈኞች ያድናል÷ ከክፉው አገዛዝና ከጭቆናም ነጻ ያወጣል ማለት ነው።
ታዲያ ግን ጾም ሲባል ከዚህ ከፍ ብሎ እንደተገለጸው ከሥጋ ፍላጎት በመቆጠብ፣ ሥጋን ለፈጣሪው በማስገዛት፣ መንፈሳዊውን ሥራ በመሥራት ነው።

በመሆኑም ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት አስቀድሞ ሥጋን በጾምና በጸሎ ተቆጣጥሮ ለእግዚአብሔር ማስገዛት እንደሚገባ፣ ጠቃሚም እንደሆነ ለማስገንዘብ ነፍሴን በጾም አደከምኋት ብሎ በመዝ 34÷13፣

ጉልበቶቼ በጾም ደከሙ፣ ሥጋዬም ቅቤን በማጣት ከሳ ደረቀ ብሎም በመዝ 108÷24 ዘምሯል።

ነቢየ ዳንኤልም በጾም ጊዜ ምርጥ ምርጥ ምግቦችንና የሚያሰክር መጠጥን መውሰድ (መጠቀም) እንደማይገባ፥ በቅቤና በመሳሰለው መለምለምም ተገቢ እንዳልሆነ ሲያስረዳ÷<<እኔ ዳንኤል ሦስት ሳምንት ሙሉ ሳዝን ነበር፣ ማለፊያውን እንጀራ አልበላሁም፣

ሥጋና ጠጅም በአፌ አልገባም፣ ሦስት ሳምንት እስኪፈጸም ድረስ ዘይትንም አልተቀባሁም>> ብሏል። ዳን 10÷2

አዎ እነዚህ የእግዚአብሔር ወዳጆች ሲሆኑ መላ ሕይወታቸውን ለፈጣሪያቸው ያስገዙ÷ በጾማቸውና በጸሎታቸው ብዙ ችግርን ያስወገዱ ብዙ ችግረኞችንም የረዱ ናቸው።

ክፍል 21÷

ረ <<ጾም በሐዲስ ኪዳን>>

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ጾም ለነፍስ ፍጹም መድኃኒት መሆኑን ለማረጋገጥ ገዳመ ቆሮንቶስ (ወደ ቆሮንቶስ በረሃ) ገብቶ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ጹሟል።

ይኸውም በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 4÷1 ጀምሮ በሰፈው ተዘግቦአል።

ሙሉውን ዝርዝር ወደ ፊት ከቦታው በገጽ 94 እንመለከተዋለን።

እንዲሁም ከዚህ ቀጥለው ያሉትን እንደ ምሳሌ ብንመለከት እኛም እንድንጾም ታዘናል።

ጽድቅን የሚራቡ (ስለ ጽድቅ ብለው የሚራቡና የሚጠሙ) ብፁዓን ናቸው ይጠግባሉና። ማቴ 5÷6።

የዚህንም ዝርዝር ወደ ፊት ከቦታው ገጽ 93። እናገኘዋለን።

በዚያን ጊዜም ከጾሙ÷ ከጸለዩም፣ እጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቱአቸው ይላል። የሐ ሥራ 13÷3።

www.zeyeneta.com

ቅዱስ ጳውሎስም በዕብራውያን መልእክቱ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናትና፣ ዛሬ፣ እስከ ዘለዓለምም ያው ነው። <<ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ>> ልባችሁ በጸጋ ቢጸና መልካም ነው እንጂ <<በመብል>> አይደለም፥ በዚህ የሚሠሩባት አልተጠቀሙምና በማለት በጾም ጊዜ ከመብል መቆጠብ እንደሚገባ ገልጾአል። ዕብራ 13÷9።

ስለሆነም ጾም በሕግ የተደነገገ ነው፣ ጾም በመመሪያ የተሰጠን ነው፥ ጾም ከእግዚአብሔር የታዘዘ ነው፣ ጾም የሥጋና የነፍስ መድኃኒት ነው።

ለምን ጾም ጠና ነው፤

ጾም የነፍስ ደስታ ነው፣
ጾም ኃይል ነው፥

ጾም እውነተኛውን ሕይወት ያሰጣል፣
ጾም ድኅነትን (ሕይወትን) ያመጣል፣
ጾም ትዕግሥትን ያስይዛል፤

ጾም ርኅራኄን፣ ትሕትናንና ፍቅርን ያስተምራል፣
ጾም የጽድቅን መንገድ ይመራል፤

ጾም ወደ እግዚአብሔር ያቀርባል፣
ጾም ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት ይወስዳል።

በመሆኑም ይህን ለማግኘት ሁላችንም መጾም፣ መጸለይ ይገባናል ማለት ነው።

ክፍል 22÷

ሰ ከዚህ ቀጥለን በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ሃይማኖታዊ ቀኖና ታውቀው እንዲጾሙ የተመደቡትን የአጽዋማት ቍጥጥሮንና ስማቸውን በዐጭሩ በመዘርዘር እነማን በጾም በጸሎት ድነዋል?
እነማንስ በጾም በጸሎት ተጠቅመዋል? እያልን በጥያቄ መልክ እያነሣን መልሶቻቸውን ከነማስረጃቸው እንመለከታለን።

በሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ባህልና ሃይማኖታዊ ትውፊት (ቅብብሎሽ) ውስጥ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት የሐዋርያትን የጾም ሕግ መነሻ በማድረግ የሚጾሙት የጾም ሥርዓት እንዳላቸው ይታወቃል።

በተለይም ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ከጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት መካከል የመጀመሪያይቱ፣ እንጂና ዋናዋ እንደመሆኗ መጠን፥ በቍጥር የታወቁና ስማቸው የተገለጸ፥ በሃይማኖታዊ የጾም ሥርዓት (በሥርዓተ ቀኖና) ተመሰነው እንዲጾሙ የተመደቡ ሰባት አጽዋማት እንዳሏት ግልጽ ነው።

እንደዚሁም የሐዋርያትን የጾም ሕግ መሠረት በማድረግ የምታከናውነው በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 15 የተደነገገ ሥርዓተ ጾም (የጾም አፈጻጸም) አላት።

እነዚህ ሁሉ በየደረጃው የሚገለጹ ሲሆኑ፥ መጀመሪያ ግን የሰባቱ አጽዋማት ዝርዝርንና ምሥጢራቸውን እንመለከታለን።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ሃይማኖታዊ ቀኖና ፍ.መ.አ. 15 እንዲጾሙ የተመደቡት አጽዋማት ቍጥጥርና የስማቸው ዝርዝር÷

1ኛ የነነዌ ጾም÷

ጾመ ነነዌ (የነነዌ ጾም) በጥር (በየካቲት) ወር በዓመት ሦስት ቀን ብቻ ሰኞ፣ ማክሠኞና ሮብ የሚጾም ነው።

ቀኑ በባሕረ ሐሳብ ስለሚወጣ በየዓመቱ ሊቀያየር ይችላል።
(ትንቢተ ዮናስ 1÷1 ጀምሮ)

ሙሉ ዝርዝሩ ከቦታው ገጽ 66 ስለ አለ ከዚያው እንመልከት÷

2ኛ ጾመ ነቢያት (የነቢያት ጾም)

ይህ ጾም÷ በየዓመቱ ከኅዳር 15 ቀን እስከ ታኅሣሥ 28 ቀን የሚጾም ነው። ነገር ግን በዘመነ ዮሐንስ የጳጕሜን ወር 6 ቀን ስለሚሆን ልደት ታኅሣሥ 28 ቀን ይከበራልና፥ ከኅዳር 14 ቀን እስከ ታኅሣሥ 27 ቀን ድረስ ይጾማል ማለት ነው።

www.zeyeneta.com

ጸሙ ነቢያት የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መምጣትንና መወለድን በጉጉት እየተጠባበቁ ስለ ሥጋዌው (ስለ ልደቱ) የጸሙት ነው።

3ኛ ዐቢይ ጾም (የጌታችን ጾም ነው)

የዐቢይ ጾም (የጌታችን ጾም) ጠቅላላ ዝርዝርና መሠረታዊ ምሥጢሩ ሁሉ በሰፊው በቦታው በጾሙ ክፍል ገጽ 94 ስለ ተጻፈ ከዚያው እንመልከት (ማቴ 4፥1 ጀምሮ)

4ኛ ጾመ ሐዋርያት (የሰኔ ጾም)

የሰኔ ጾም፥ ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ወንጌልን ለማስተማር አስቀድመው የጾሙት፣ የተልዕኮአቸው መሠረት ያደረጉበት፥ የማስተማርና ድውያንን የመፈወስ ሥራቸው ሁሉ የተቃና እንዲሆንላቸው ፈጣሪአቸውን በጸምና በጸሎት የለመኑበት ጾም ነው።

5ኛ የፍልሰታ ጾም (የእመቤታችን ጾም)

ይህ የፍልሰታ ጾም በመባል የሚታወቀው የእመቤታችን ጾም ሁል ጊዜ ከነሐሴ 1 ቀን እስከ ነሐሴ 15 ቀን ድረስ ሲ15 ቀናት ብቻ የሚጾም ሐዋርያት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ለማየትና ለማግኘት የጾሙት ነው።

6ኛ ጾመ ገሃድ፥

ገሃድ ማለት መገለጥ፣ ግልጽነት ማለት ሲሆን፥ የጌታችን መወለድንና በግልጽ መታየትን ያመለክታል።

የገሃድ ጾም ልደትና ጥምቀት ዓርብ ወይም ሮብ ሲውሉ ስለ ማንጸማቸው ተውላጣቸው (የእነአርሱ ለውጥ ነው)

ይህ ጾም ሁል ጊዜ በልደትና በጥምቀት ዋዜማ ሲ1 ቀን ብቻ እስከ ምሽቱ ድረስ ይጾማል። ዋዜማው ቅዳሜና እሑድ በሚሆንበት ጊዜም እስከ ማታ አንጾምም እንጂ በፍስክ ቀን የሚበሉትን እንደ ሥጋ፣ ቅቤ፣ ወተትና እንቍላል የመሳሰሉትን አንበላም ማለት ነው።

7ኛ ዓርብና ሮብ ናቸው።

ሮብ፥ አይሁድ ጌታችንን ለመያዝ የመከሩበትና ምክራቸው የተሳከበት፣ ምክረ መስቀል (ምክረ ሞት) የተፈጸመበት ሲሆን፥ ዓርብም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት በመሆኑ የሮብና የዓርብ ጾም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ሲል የተቀበለውን ልዩ ልዩ መከራ በማሰታመስ ነው የምንጾመው።

የእነዚህ ምሥጢር ሁሉ በእየቦታው በሰፊው ተገልጿል። በሚገባም ተብራርቷልና ከዚያው እንመልከት። በተለይም ምዕራፍ 11 ገጽ 127 እና ከሰሙነ ሕማማት ውስጥ ይገኛል።

ክፍል 23፥

ዐቢይ ጾም፥

ሸ ዐቢይ ጾም ማለት ምን ማለት ነው?

የጾም ጥሬ ንባብና ትርጉሙ ከላይ እንደተገለጸው ሲሆን፥ ዐቢይ ደግሞ፥ <<ዐብየ ከፍ ከፍ አለ ትልቅ ሆነ>> ይልና ዐቢይ ትልቅ ብሉ ይገኛል።

ስለሆነም ዐቢይ ጾም ስንል ትልቅ ጾም ማለታችን ነው።

ትልቅ ጾም ወይም ዐቢይ ጾም መባሉም፥

1ኛ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ጾመው፥

2ኛ በቁጥር ወይም በዕለታት ብዛት ከሌሎች አጽዋማት የሚበልጥ በመሆኑና በፍጥረቱ ሁል ጊዜ <<ዐቢይ እግዚአብሔር ወብዙኅ አኰቴቱ>> እግዚአብሔር ትልቅ ነው፣ ገናናም ነው።

ምስጋነውም ብዙ ነው፣ ፍጹምም ነው እየታሰበ የሚመሰገን የአምላካችን፣ የፈጣሪአችን ጾም ስለ ሆነ ነው። መዝ 47፥1።

www.zeyeneta.com

<<ጾመ ሁዳዴ>>

ጾመ ሁዳዴ ስንልስ ምን ማለታችን ነው?

ሁዳዴ ማለት ደግሞ የመንግሥት፣ የሀብታም (የብዙ ሕዝብ) ሰፊ እርሻ ማለት ሲሆን፥ ዐቢይ ጾምም ጌታችን የጾመው፣ ሁሉም ሕዝበ ክርስቲያን የሚጾመው ትልቅ ጾም ስለ ሆነ በሁዳዴ ይመሰላል፣ በሁዳዴ ስም ይጠራል ማለት ነው።

ክፍል 24፥

<<ዘወረደ>>

ቂ ዘወረደ ማለት ምን ማለት ነው?

የመጀመሪያ ጾም መግቢያ ሰንበት ወይም እሑድ ዘወረደ ይባላል።

ከጌታችን ጾም አስቀድሞ የሚገኘው ዘወረደ የሚባለው እሑድና ሳምንቱ የዐቢይ ጾም መጀመሪያ (ዋዜማ) ሲሆን፥ ለዋናው የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጾም መቅድሙ (መግቢያው) ነው።

ዘወረደ መባሉም በቅዱሳት መጻሕፍት በየክፍሉ ተዘግቦ እንደምናገኘው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ዓለምን በማዳኑ፥ ወረደ መጣ ስለተባለ በጌታችን ከሰማይ መውረድ ምክንያት፣ ወደዚህ ዓለም በመምጣቱ ምሥጢር ነው።

ሊቁ ኢትዮጵያዊ ቅዱስ ያሬድም በግእዙ <<ዘወረደ እምላዕሉ አይሁድ ሰቀሉ>>

ትርጉሙ፥ ከላይ (ከሰማይ) የወረደውን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አይሁድ ሰቀሉት በማለት በጣዕመ ዜማው አመሥጥሮታል። (ከጾመ ድጓው መጀመሪያው ላይ ይገኛል)።

ስለዚህም ዘወረደ የጌታችን ሥጋዌ (ሰው መሆን) መታሰቢያ ነው ማለት ነው።

በተጨማሪም፥<<ማቴ 1፥23, 2፥1, ሉቃ 1፥26, ዮሐ 1፥1, 3፥12>> እንመልከት።

ክፍል 25፥

<<የዘወረደ ጾም>>

በ የዘወረደ ጾምስ ምንድ ነው?

ዘወረደ የዐቢይ ጾም መጀመሪያ ሳምንት ሲሆን፥ ጾሙም ጾመ ሕርቃል ይባላል።

<<ጾመ ሕርቃል መባሉ>>

በአንዳንድ የአባቶች ጉባኤ እንደሚተረከው ፎቃ የተባለ አይሁዳዊ ንጉሥ በኢየሩሳሌም በሚኖሩት ክርስቲያኖች ላይ የማፍ አገዛዙን አጽንቶ ስለ አስቸገራቸው ክርስቲያኖቹ በወቅቱ ኃይለኛ ገዥ ለነበረው ሕርቃል ለተባለው የሮም ንጉሥ፥ የቪዛንታይን ንጉሥ ነውም ይባላል።

ያም ሆነ ይህ እባክህ ፎቃን አስወግደህ ከዚህ ክፉ አገዛዝ ገላግለን ብለው ቢልኩበት ሕርቃል ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው ሰውን የገደለ ዕድሜ ልኩን ይጹም ብለው ሥርዓት ሠርተዋልና አይሆንም ስለአላቸው ክርስቲያኖቹ ይህን ክፉ ገዥ አጥፋልን እንጂ ጾሙንስ ተካፍለን እንጾምልሃለን እንዳሉትና ሕርቃልም እንግዲያስ እሺ ብሉ ተስማምቶ ፎቃን በማጥፋት ክርስቲያኖችን ከችግርና ከክፉ አገዛዝ ስለገላገላቸው አንድ ላይ እንደጾሙትና በዚህ ምክንያት ጾመ ሕርቃል እየተባለ እንደሚጠራ ይታወቃል።

ይህ ጾም ቀደምት አባቶቻችንና የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት ሁሉ ስለጾሙት ከጌታችን ጾም ተጨምሮ በዐቢይ ጾሙ መግቢያ ሳምንት እንዲጾም በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 15 ተደንግጎአል።

ስለሆነም ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ እየጾመው ይገኛል።

www.zeyeneta.com

የዘወረደ ቃለ እግዚአብሔር በሙሉ፥ ከአሁን ቀደም ለሥጋችሁ የተገዛችሁበት፥ በሥጋችሁ የተደሰታችሁበት ጊዜ ይበቃል።

ከእንግዲህስ በኋላ ጹሙ፣ ጸልዩ፣ ለነፍሳችሁ አስቡ፥ ለእግዚአብሔር ተገዙ ይለናል። ማር 14÷38።

ቅዱስ ጳውሎስም በገላትያ ምዕራፍ 5÷16 መልእክቱ፥ <<ነገር ግን እላለሁ በመንፈስ ተመላለሱ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ፥ ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቃወማሉ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም>> በማለት አስተምሮናል።

መልእክቱ የሥጋን ፍላጎት ብቻ ተከትለን የምንጓዝ ከሆን ከቅዱስ መንፈስ ውጭ ስለምንወጣ ፍጹም የሆነውን ሕይወት ማጣት እንደማንችል ነው የሚያስገነዝበን።

በተጨማሪም ከዚህ በታች ያሉትን ጥቅሶች እንመልከታቸው።

1ኛ ለእግዚአብሔር <<በፍርሃት ተገዙ>> ዋጋ ያለበት ነውና በረዓድም ደስ ይበላችሁ። መዝ 2÷11።
(ሕጉንና መመሪያውን እየጠበቃችሁ ትእዛዛቱንም እየፈጸማችሁ ኑሩ ማለት ነው)።

2ኛ በሌሊት በቤተ መቅደስ እጆቻችሁን አንሡ እግዚአብሔርንም ባርኩ። መዝ 133÷2

3ኛ ስትጸልዩ ወገባችሁ የታጠቀ፣ መብራታችሁም የበራ ይሁን። ሉቃ 12÷35

4ኛ ወንድሞች ሆይ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው፥ ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ። ሮሜ 12÷1

5ኛ ይልቁን አሁን በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ። ፊል 2÷12

6ኛ ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን፣ ክፋውን ነገር ተጸየፉት፣ ከበጎ ነገር ጋር ተባበሩ። ሮሜ 12÷9

7ኛ በተቀደሰ አሳሳም (ሰላምታ) እርስ በእርሳችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ (ሰላም ተባባሉ) ሮሜ 16÷16

8ኛ በፍቅር አሳሳም እርስ በእርሳችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ፥

በክርስቶስ ላላችሁ ለሁላችሁ ሰላም ይሁን። 1ኛ ጴጥ 5÷14።

(በእውነተኛው ፍቅር ተሰማሙ ከልብ ሰላም ተባባሉ ማለቱ ነው)

9ኛ በትሕትና፣ በየዋህነትና በትዕግሥት እርስ በእርሳችሁ በፍቅር ታገሡ (ተፋቀሩ) ኤፌ 4÷2

10ኛ እውነትን ተነጋገሩ፣ ኃጢአትንም አታድርጉ፣ በቍጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ፣ ለዲያብሎስ ፈንታን አትስጡት።

(ተሉ ታረቁ ማለቱ ነው)

እርስ በእርሳችሁ ቸሮችና ርኅሩኖች ሁኑ፣ እግዚአብሔር ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ።

ኤፌ 4÷ ቍጥር 26 እና ቍጥር 32 እንመልከት።

11 እንግዲህ እንደ ባለ አእምሮ አስቡ፣ ትጸልዩም ዘንድ በመጠን ኑሩ፥ ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናልና ከሁሉ በፊት እርስ በእርሳችሁ አጥብቃችሁ ተፋቀሩ። 1ኛ ጴጥ 4÷8

12 እንግዲህስ ለእግዚአብሔር ተገዙ፣ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙት፣ ከእናንተም ይሸሻል፥ ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል። ያዕቆብ 4÷7

አዎ ይህ ቅዱስ ቃል በትሕትና፣ በንጽሕና እና በእውነተኛው ፍቅር አንድ በመሆን እየተረዳዳን እንድንኖር፥

እየጸምን፣ እየጸለይን፣ በፍጹም ልባችን ወደ ፈጣሪያችን ወደ እግዚአብሔር እንድንቀርብ ነው እየመከረን ያለ።

እነዚህ ጥቅሶች ለአስፈላጊው ማብራሪያ እየተደረገበት ከልዩ ልዩ ክፍል የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው።

www.zeyeneta.com

ክፍል 26÷

ተ ዐቢይ ጾም÷ ለመሆኑ ጾም እስከ ሰንት ሰዓት ነው የሚጾመው?

በአጠቃላይ ሁሉም ጾም እስከ ቀኑ 9 ሰዓት (3 p.m) ነው የሚጾም።

ነገር ግን አንድ አንድ አጽዋማት ከ9 ሰዓት በላይ እንዲጾሙ የሚያደርግ የየራሳቸው የሆነ ምሥጢር አላቸው።
በዚሁም መሠረት ዐቢይ ጾም ከትንሣኤ በኋላ ኀምሳ ቀን ሮብና ዓርብ የማንጾምበት ምክንያት÷ ሰፋ ያለ ምሥጢር ስለ አለበት ከ9 ሰዓት (3 p.m) በላይ እንዲጾም ተወስኖአል።
ይኸውም ትርፍ ሰዓቱ በበዐለ ኀምሳ ለማይጾሙ ሮብና ዓርብ የሚካፈል እንደሆነ ይነገራል። ትርፍ ሰዓቱ በበዓለ ኀምሳ ለማንጾማቸው ሮብና ዓርብ ሲካፈል 9, 9 ሰዓት ይደርሳቸዋል ማለት ነው።

(ይህ ከአበው የጉባኤ መምህራን፣ በተለይም ከቃል ትምህርት የተገኘ ምሥጢር ነው)።

ነገር ግን በበዐለ ኀምሳ የሚገኙ ሮብና ዓርብ አለመጾማቸው በመንግሥተ ሰማያት ጾም፣ ረኀብ እንደሌለ የሚያመለክት መሆኑ ደግሞ በሊቃውተ ቤተ ክርስቲያን በሌላ መልኩ ይገለጻል።

ስለዚህም ከቅዳሜና ከእሑድ በስተቀር የሚጀመሪያ ጾም የዘወረደ ሳምንት÷ እስከ ቀኑ 12 ሰዓት (6 p.m)

ከቅድስት እስከ ሆሳዕና ያሉት ሳምንታት እስከ ቀኑ 11 ሰዓት (5 p.m) ድረስ

ሰሙነ ሕማማትም እስከ ምሽቱ 1 ሰዓት (7 p.m) ድረስ እንዲጾም በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 15 ተወስኖአል።

ይህን ያህል ሰዓት ማን ይጾማል የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል።

አም እንደሚከብድ ይገመታል ቢሆንም በሥርዓተ ቀኖናው ታዟል።

ይህን ጾም በተለይም በገዳም ያሉት አባቶችና ባሕታውያን÷ እንዲሁም ለዚህ የታደሉ ወገኖች ይጾሙታል ይላሉ አባቶቻችን በጉባኤ ትርጓሜያቸው።

ሌሎቻችን ለዚህ ያልታደልን በሥራና በተለያየ ምክንያት እስከ ተባለው ሰዓት መቆየት ባንችልም እንኳ እስከ ቀኑ 9 ሰዓት (3 p.m) ግን መጾም ይገባናል።

ምክንያቱም ሃይማኖታዊ ግደታ ነው መጽሐፋዊ ትእዛዝም ነው።

ጾምን እንዲጾሙ የማይገደዱ÷

>>> ዕድሜያቸው ከ7 ዓመት በታች የሆኑት ልጆች÷
>>> ለመጻን ተሰፋ ያላቸው በከባድ ችግር ላይ ያሉት ሕመምን÷ እና ጉዳት የደረሰባት (በወሊድ የተጻከመች) አራስ ብቻ ናቸው። ከዚህ በተረፈ ግን ሁሉም ሕዝበ ክርስቲያን እንዲጾም በቤተ ክርስቲያናችን የጾም ሥርዓት ታዟል።

በመሆኑም÷ እኛ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትንና ሥርዓትን የምንከተል ሁላችንም ጌታችንን÷ ሐዋርያትን ቀዳማውያን ቅዱሳን አባቶቻችንንና የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንትን አብነት በማድረግ በየዓመቱ በዐዋጅ የምንጾመው÷

ዐቢይ ጾም በመባል የሚታወቀው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጾም÷ ሁል ጊዜ በባሕረ ሐሳብ ስለሚወጣ በየጊዜው ወሩ ሊቀያየር ቢችልም የመጀመሪያው ቀኑ ግን ዘወትር ሰኞ ስለሚሆን ዐቢይ ጾሙን እንደተለመደው በሥርዓተ ቀኖናችን መሠረት እንድንጾመው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን መልእክቷን በዐዋጅ ታስተላልፋለች ማለት ነው።

ዐቢይ ጾም ያለፈው ለሥጋችሁ የተገዛችሁበት ጊዜ ይበቃችኋል ከእንግዲህ ወዲህስ ጹሙ፣ ጸልዩ በተባልነው መሠረት÷

እየጾምን፣ እየጸለይን÷ ነፍሳችንን በመንፈስ ቅዱስ የምናስደስትበት፣ ሰውነታችንን ለእግዚአብሔር የምናስገዛበት፣ የጽድቅ ሥራን የምንሠራበት÷ ልዩ የሆነ የሕይወት ወቅት ነው።

(በተጨማሪም መዝ 2÷11, ፊል 2÷12, ዕብራ 12÷28, እና 1ኛ ጴጥ 1÷17 እንመልከት)

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ 7÷

ቸ ንስሓ÷

ንስሓ÷ **<<ነስሐ ተፀፀተ>>** ብሎ ከግእዝ ግስ የሚገኝ ጥሬ ዘር ሲሆን÷ ንስሓን መግባት ማለትም÷ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ባጠፉት ጥፋት፣ በበደሉት በደል በተሳሳቱት ስሕተት ተፀፅተው÷ ከጥፋት፣ ከበደልና ከስሕተት ወደ እውነተኛ መንገድ መመለስ÷ ክፉ ዐመልንና መጥፎ ባሕርይን (ፀባይን) መተው፣ ወደክፉ ተግባር ላለመመለስም በቀሩጥ ሐሳብ መወሰን ማለት ነው።

ንስሓ÷ በጸም፣ በጸሎትና በስግደት የሚከናወን ሱባኤ እንደመሆኑ መጠን÷ መንፈሳዊ ምሥጢሩና አፈጻጸሙ ሁሉ ከጸምና ከጸሎት ጋር የተያያዘ ነው።

ከዚህ ከፍ ብሎ በጸምና በጸሎት ክፍል የተገለጸውም በሙሉ ይመለከተዋል።

ንስሓ÷ በደሉን አምኖ ለሚናዘዝ ሰው እንደጥፋቱ፣ እንደበደሉና እንደስሕተቱ ክብደት እየታየ ሥልጣነ ክህነት ባላቸው የቤተ ክርስቲያናችን አባቶች ካህናት አማካይነት ምንም ልዩነት ሳይደረግ ለሁሉ የሚሰጥ÷ በምግባረ እከይ የተጣመመውን ሰው የሚያቀና÷

ከገቢረ ሠናይ (ከመልካም ምግባር) የጉደለውንም የሚሞላ፣ (ስርዋጸ) ተብሎ ሊጠራ የሚችል መንፈሳዊ ቅዋት ነው።

አዎ ንስሓ÷ ጥፋቱንና ስሕተቱን በትክክል አምኖ የሚናዘዝ÷ ከበደሉና ከስሕተቱ ሁሉ ተመልሶ ፈጣሪውን በንጹሕ ልብ የሚለምነውን ሰው ከአበሳው የሚያነጻ፣ ጻድቅንም የሚያደርግ÷

በማጠቢያ ሳሙና እና በንጹሕ ውሃ የሚመሰል የኃጢኣት ዕድፍ ማስወገጃ መንፈሳዊ መሣሪያ ነው።

ንስሓ÷ በደሉን በሚናዘዝ ሰውና በካህኑ መካከል ብቻ የሚከናወን፣ ከእግዚአብሔር ይቅርታን የሚለመንበት፣ ከካህኑና ከተናዛዚው ሰው በስተቀር ማንም ሊያውቀው የማይገባው መንፈሳዊ ምሥጢር ነው።

ንስሓ÷ ምንም እንኳ በሐዲስ ኪዳን አፈጻጸሙ ሁሉ በሃይማኖታዊ ሥርዓት (በቀኖና ቤተ ክርስቲያን) ተለይቶ የተቀመጠና እየተሠራበት ያለ ቢሆንም÷ ቀደም ሲልም÷ ብዙ ሕዝብ በልዩ ልዩ ጥፋታቸው እየተፀፀቱ፣ በበደሉት በደል እያዘኑ፣ እያለቀሱ፣ ከስሕተታቸው ወደ እግዚአብሔር እየተመለሱ÷ ከፈጣሪአቸው ምሕረትንና ይቅርታን ሲለምኑበት የነበረ÷ የበደለኞችና የይቅር ባይ፣ የመሐሪው አምላክ እግዚአብሔር መገናኛ፣ ድልድይ፣ አስታራቂ÷ (ልዩ የሆነ መንፈሳዊ ሽማግሌ) መሆኑን ከቅዱሳት መጻሕፍት መረዳት እንችላለን።

ክፍል 27÷

ንስሓ÷ በብሉይ ኪዳን÷

ለምሳሌ ያህልም÷ ከላይ በጸም አንቀጽ በሰፊው እንደተገለጸው የነነዌ ሰዎች አመድ ነስንሰው፣ ድንጋይ ተንተርሰው፣ ማቅ ለብሰው እግዚአብሔርን በጸም፣ በጸሎትና በልቅሶ÷ በልዩ ሱባኤ ንስሓ ገብተው በለመኑት ጊዜ እግዚአብሔር ሰምቷቸዋል።

በበደላቸውና በጥፋታቸው ተፀፅተው ንስሓ ስለ ገቡ÷ ወደ እውነተኛው አምላካቸው ስለ ተመለሱ ከታዘዘባቸው መቅሠፍት ተርፈዋል።

ትንቢተ ዮናስን ከመጀመሪያው አንሥተን ብንመለከት ምሥጢሩን በሰፊው ያስረዳናል። ትንቢተ ዮናስ 1÷1, 3÷1።

አዎ ንስሓ የይቅርታ መጠየቅያ ልዩ ሞይል በመሆኑ የምሕረትና የርኅራኄ ባለቤት ፈጣሪአችን እግዚአብሔር በፍጹም ልባችን ንስሓ ገብተን፣ ባጠፋነው ጥፋት ተፀፅተን፣ ከስሕተት ወደ እውነት፣ ወደ እርሱ መመለስ እንደሚገባን÷ ይቅር እንዲለን፣ ከኃጢኣታችን ሁሉ እንዲያነጻንም አምላካችንን በፍጹም ልባችን መለመን እንዳለብን÷ ደጋግሞ ነግሮናል።

ለምሳሌም÷ ኢዩኤል 2÷ ከቊጥር 1 ጀምሮ÷ በተለይም ቊጥር 12 ብንመለከት ይህን በሰፊው መረዳት እንችላለን።

ንስሓ ለምሳሌ ያህል ከዚህ በዐጭሩ የተገለጸ ሲሆን÷ በተጨማሪም ቅዱሳት መጻሕፍትን ቀስ ብለን በሰፊው

www.zeyeneta.com

ብንመረምር መሠረታዊ አመጣጡና ጥቅሙ በብዙ ክፍል ተዘግቦ እናገኘዋለን። በተለይም ሕዝበ እስራኤል በዘመናቸው ሁሉ እግዚአብሔርን በሚያሳዝኑበት ጊዜ ልዩ ልዩ ቅጣት ይታዘዝባቸው ስለ ነበር፥ በንስሓ፣ በጎዘንና በልቅሶ ወደ እርሱ ተመልሰው ፈጣሪያቸውን ሲለምኑ ደግሞ ምሕረትንና ይቅርታን ያገኙ ነበር።

መዝ 77፥1 ጀምሮ በተለይም ቁጥር 44ትን እንመልከት።

<<የንስሓ>> መሠረታዊ አመጣጥና ጥቅሙ በብሉይ ኪዳን በዐጭሩ ሲገለጽ እንደዚህ አሁን እንደሰማነው ሲሆን በሐዲስ ኪዳን ደግሞ በልዩ ልዩ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል ተዘግቦ እናገኘዋለን።

ክፍል 28፥

ንስሓ በሐዲስ ኪዳን፥

በሐዋርያት ሥራ 3፥14 ጀምሮ፥ በተለይም ከቁጥር 17 ብንመለከት፥

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ የአይሁድ ሕዝብን ፈጣሪ፣ የዓለም መድኃኒት የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ያለጥፋት አሳልፋችሁ ለሞት ሰጥታችኋልና፣ የንጹሕ ሰው ደምን በከንቱ አፍሳችኋልና፤ ይቅር እንዲላችሁ፣ ኃጢአታችሁም ይደመሰስ ዘንድ ንስሓ ግቡ በማለት አስተምሯቸዋል። (ግብ ሐዋ) የሐዋ• ሥራ 3፥19።

በሐዋ ሥራ ምዕራፍ 2፥37 ብንመለከትም፥ ሐዋያው ቅዱስ ጴጥሮስ ኃጢአታችሁ ይሰረይ ዘንድ ንስሓ ግቡ ብሎ ካስተማራቸውና ከመከራቸው ሕዝብ መካከል ከሦስት ሺሕ የሚበልጡ ሰዎች ትምህርቱን ተቀብለው በሥራ ላይ እንዳሞሉና ተፀፅተው ከበደላቸው ተመልሰው፣ ንስሓ ገብተው ተጠምቀው እንደዳኑ እንገነዘባለን። (ግብ ሐዋ) የሐዋ ሥራ 2፥37

ቅዱስ ጴጥሮስ ጸጋ እግዚአብሔርን በገንዘብ ለመለወጥ (ለመግዛት) የሞከረውንም ሰው የልብህን ሓሳብ ይቅር ይልህ ዘንድ ስለዚህ ክፋትህ ንስሓ ግባ በማለት መክሮታል። የሐዋ ሥራ 8፥22።

ቅዱስ ጴጥሮስ ካህን ስለ ሆነ የንስሓ ኑዛዜ ሥልጣነ ክህነት ላላቸው አባቶች ካህናት ብቻ የሚነገር ልዩ ምሥጢር እንደሆነ፥ መልሱና አፈጻጸሙም በአባቶች በካህናት ብቻ የሚሰጥ የጥፋት መመለሻ፣ የበደል ሩጫ መግቻ፣ መንፈሳዊ ልጓም፥ የስሕተት ማረሚያ፣ የሕይወት ማስተካከያ መሣሪያ መሆኑንም ከዚሁ መረዳት እንችላለን።

ይህ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው እኛ ሰዎች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ባጠፋነው ጥፋት በበደልነውም በደል ተፀፅተን፣ ነገ ከነገ ወዲያ ሳንል ዛሬ፥ ከአሁኑ ጀምሮ በፍጹም ልባችን ወደ ፈጣሪአችን ወደ እግዚአብሔር ብንመለስ፥ አምላካችን የምሕረትና የይቅርታ አምላክ በመሆኑ ይቅር እንደሚለን ከኃጢአታችን ሁሉ ነጻ አድርጎ መንግሥቱንና ጽድቁን እንደሚያወርሰን የሚያረጋግጥልን ነው።

አዎ ቅዱስ ቃሉ እውነተኛውን ፍቅር መሠረት በማድረግ፥ እየጸለየን፣ እየጸለይን በፍጹም ትሕትና ሆነን፣ በንጹሕ ልብ ወደ እርሱ ቀርበን ልንለምነው እንደሚገባንና ሁለተኛም እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያሳዝን የኃጢአት ተግባር መፈጸም ተገቢ እንዳልሆነ ነው እየመከረን ያለው።

በተጨማሪም ከዚህ ቀጥለው ያሉትን ቀስ ብለን እንመልከታቸው

1ኛ ነገር ግን <<ንስሓ>> የሚገቡትን ምክንያት ሰጣቸው፣ ተስፋቸውን ያጡ ሰዎችንም ደስ ያሰኛቸዋልና <<በንስሓ>> ወደ እግዚአብሔር ተመለስ፥ ኃጢአትንም ተዋት ከኃጢአትህ ተመልሰህ በፊቱ ተለማመጥ፥ ፈጽመህ ከኃጢአትህ <<በንስሓ>> ወደ እግዚአብሔር ተመለስ፣ ኃጢአትን ሁሉ ጥላ የእግዚአብሔርንም ፈቃድ ፈጽም። ሲራክ 17፥24 ጀምሮ

2ኛ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ወደ እኔ <ተመለሱ> ይላል። ዘካ 1፥3 (ንስሓ ግቡ ማለት) ነው።

3ኛ ንስሓ ግቡ ኃጢአትም ዕንቅፋት እንዳይሆንባችሁ ከኃጢአታችሁ ሁሉ ተመለሱ፣ የበደላችሁትን በደል ሁሉ ከእናንተ ጣሉ፣ አዲስ ልብና አዲስ መንፈስም ለእናንተ አድርጉ ሕዝ 18፥30

4ኛ ሰው በችኮላ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ነው ብሎ ቢሳል፥ ከተሳለም በኋላ <ቢፀፀት> ወጥመድ ነው። መጽሐፈ ምሳሌ 20፥25 (ፀፀት ማለት በግእዝ ቋንቋ ንስሓ ነው)

www.zeyeneta.com

5ኛ በንስሓ ወደ እኔ የተመለሰውን እጠብቀዋለሁ።
መጽሐፈ መቃብያን ሣልስ 7÷4

6ኛ አንተ <በንስሓ> መለማመጥ ተሳነህ፣ ከመሬት የተፈጠረ አዳም ግን ስለ ኃጢአቱ በእግዚአብሔር ፊት ፈጽሞ አያለቀሰ <በንስሓ> ተመለሰ።

ያ አዳም ግን በልቅሶና በጎዘን ወደ ንስሓ ተመለሰ።
መጽሐፈ መቃብ ሣልስ 4÷23,4÷ 26 7÷4 10÷16, 10÷27 እንመልከት።

7ኛ በዚያም ወራት መጥምቁ ዮሐንስ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና <ንስሓ> ግቡ ብሉ በይሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ ማቴ 3÷1

8ኛ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኢየሱስ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና <ንስሓ> ግቡ እያለ ይሰብክ ጀመር። ማቴ 4÷17

9ኛ ለማንም እንዳትናገር ተጠንቀቅ ነገር ግን ሔደህ ራስህን ለካህን አሳይ። ማቴ 8÷4።

አሳይ ማለት ራስህን በካህን አማካይነት <በንስሓ> አስመርምር፣ ንስሓ ግባ ማለት ሲሆን ቃሉ በደላችንን ለንስሓ አባታችን ብቻ መናገር እንደሚገባን ነው የሚያስረዳን።

10ኛ <ንስሓ> በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል። ሉቃ 15÷10።

11ኛ ሰው ሆይ አንተ ከእግዚአብሔር ፍርድ የምታመልጥ ይመስልሃልን?

ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ <ንስሓ> እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግስቱንም ባለጠግነት ትንቃለህን?

ነገር ግን እንደ ጥንካሬህና <ንስሓ> እንደማይገባ (በማይገባ) ልብህ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ በሚገለጥበት በቊጣ ቀን ቊጣን በራስህ ላይ ታከማቻለህ። ሮሜ 2÷3

12 አስቀድመውም ኃጢኣትን ከሠሩትና ስለአደረጉት ርኩሰትና ዝሙት መዳራትም <ንስሓ> ካልገቡት ወገን ስለ ብዙዎች ምናልባትም አዝናለሁ ብዬ እፈራለሁ።
2ኛ ቆሮ 12÷21።

13 አሁን <ለንስሓ> ስላዘናችሁ ደስ ብሎኛል እንጂ ስላዘናችሁ አይደለም።

(አሁን ደስ ብሎኛል ደስታቱም ስላዘናችሁ ሳይሆን ኀዘናችሁ ለንስሓ ስላበቃችሁ ነው) 2ኛ ቆሮ 7÷9, እንዲሁም 2ኛ ጴጥ 2÷18 ጀምሮ እስከ ፍጻሜው።

14 እንግዲህ ከወዴት እንደወደቅህ አስብ <ንስሓም> ግባ፥ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ፥ አለዚያ እመጣብሃለሁ <ንስሓም> ባትገባ መቅረዝህን ከሥፍራው እወስዳለሁ። ራዕ ዮሐ 2÷5

መቅረዝ ማለት አንድ እግር ሆኖ ብዙ ቅርንጫፍ ያለው የሻማ ማብሪያ ቀንዲል ነው ራዕ ዮሐ 1÷12, 11÷4 እንመልከት።

15 <<እርስ በርሳችሁ በኃጢኣት ተናዘዙ፥ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይልን ታደርጋለችና ይላል>> ያዕ 5÷16 ጀምሮ÷

16 ሊቀ ካህናት ሁሉ ስለ ኃጢኣት መባንና መሥዋዕትን ሊያቀርብ ከሰው ተመርጦ ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ ስለ ሰው ይሾማልና ላልተማሩትና ለሚስቱት ሊራራላቸው ይችላል።
ዕብ 5÷1።

(ቃሉ የንስሓ አባት የሚያስፈልግ መሆኑን የሚያመለክት ነው)።

<<ጥቅሶቹ አስፈላጊው ማብራሪያ እየተደረገባቸው ከልዩ ልዩ የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንዳሉ የተወሰዱ ናቸው>>

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ 8÷

ጎ ሰንበትና የሰንበት መሠረታዊ ምሥጢር÷

ሰንበት ማለት ምን ማለት ነው?

በወቢይ ጾም ውስጥ የሚገኙ የሰንበታት÷ (የእሑዶች) መሠረታዊ ምሥጢርስ ምንድ ነው?

ሰንበት ማለትስ ምን ማለት ነው?
ለሚለው ጥያቄ መልሱ ከዚህ ቀጥሎ ይገኛል።

ሰንበት ማለት 7ኛ ማለት ነው።

ሰንበት÷ <<ሰንበተ አከበረ>> ከሚል የግእዝ ግስ ስለሚገኝ የክብር ቀን ማለትም ነው።

ዕለተ ሰንበት ስንልም÷ የክብርና የዕረፍት ቀን ማለታችን ነው።

ይኸውም በኦሪት ዘፍጥረት ከምዕራፍ 1÷1,÷

በዘፀአትም ከምዕራፍ 20÷8 ጀምሮ እንደምንመለከተው÷

እግዚአብሔር በስድስቱ ቀናት ፍጥረቱን ሁሉ ሲፈጥር ሰንብቶ በሰባተኛው ቀን (ቅዳሜ) ዕረፍቱን አደረገ።

በዘፀ ምዕራፍ 20÷1 ጀምሮ ከሚገኙት የጌታችን የሕግና የትእዛዝ ቃላትም አንዱ ሰንበትን አክብሩ የሚል ስለሆነ ሰንበት በእግዚአብሔር የተባረከች፣ የተቀደሰች÷ የዕረፍት፣ የክብርና የምስጋና ቀን ናት ማለት ነው።

በተጨማሪም ዘፍጥ 1÷1, ዘፀ 20÷11።

ክፍል 29÷

ቅዳሜ

ቅዳሜ÷ ቀዳሚት ሰንበት እየተባለች ትጠራለች።
ትርጉሙ÷ አንደኛይቱ፣ የመጀመሪያይቱ፣ ጥንታዊቷ ሰንበት (ቅዳሜ) ማለት ሲሆን÷ ከቀዳሚት በፊት ሌላ የተመረጠች የከበረ፣ የዕረፍትና የምስጋና የሆነች ዕለተ ሰንበት እንደሌለችና ይህች ቀዳሚት ሰንበት (ቅዳሜ) የመጀመሪያ መሆኗን ነው የሚያስገነዝበን።

ስለዚህ በብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት በተለያየ ክፍል የሚገኘው ስለ ሰንበት የሚገልፅ ሁሉ ቅዳሜ እየተባለች የምትጠራውን ይህችን ቀዳሚት ሰንበትን የሚመለከት ሆኖ÷ ሰንበተ ክርስቲያንንም በትንቢታዊ ምሥጢር ይጠቀሙባታል ማለት ነው።

ቀዳሚት ሰንበት÷ ቀዳሚት፣ ቀዳም÷ ቅዳሜ፣ ሰንበተ አይሁድ የሚል መጠሪያ ያላት ስትሆን÷ እኛ ሰንበተ ክርስቲያንን በልዩ ደረጃ እንደምናከብራት ቀዳሚት ሰንበት በአይሁድ ዘንድ ከጥንቱ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ከሌሎች ዕለታት ይልቅ ለየት ባለ መልኩ እንደምትከበር ይታወቃል።

ሊቁ ኢትዮጵያዊ ቅዱስ ያሬድም ሰንበትን በጣዕመ ዜማው አመሥጥሯታል።

በግእዙ ሲጠቀስ÷ <<ሰንበት ተወቢ እምኩሉ ዕለት ወሰብእ ይክብር እምኩሉ ፍጥረት÷ አዕበያ ኖኅ በውስተ ታቦት÷ አብርሃም አክበራ በውስተ ምሥዋዕ÷ እዝማቹም ይቀጥላል።
አዘዞሙ ሙሴ በትእይንት ያክብሩ ሰንበተ በጽድቅ>> ይላል።

የአማርኛ ትርጉሙም÷ ሰንበት ከሁሉ ዕለት ትበልጣለች፣ ሰውም ከሁሉ ፍጥረት ይበልጣል÷ ኖኅ በታቦት (በመርከቡ) ውስጥ ከፍ ከፍ አደረጋት÷ አብርሃምም በመሠዊያው አከበራት÷ ሙሴ ደግሞ ሕዝበ እስራኤል ሰንበትን በአንድነት ሆነው በእውነት እንዲያከብሩዋት አዘዛቸው ማለት ነው።
(ይህ ድጓ ከክረምት መዝሙር የተጠቀሰ ነው)።

www.zeyeneta.com

እንደዚሁም <<ሰንበትሰ በእንተ ሰብእ ተፈጥረት ወአኮ ሰብእ በእንተ ሰንበት>> ይላል።

ትርጉሙ÷ ሰንበት ስለ ሰው ተፈጥራለች እንጂ ሰው ስለ ሰንበት አልተፈጠረም ማለት ነው። ማር 2÷27።

ይህ ቅዱስ ቃል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው ሲሆን÷ ቅዱስ ያሬድም በጣዕመ ዜማው ጠቅሶታል።

ይኸውም ሰንበት ከሁሉም ዕለታት እንደምትበልጥና በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረው ሰውም ከሁሉም ፍጥረት የበለጠ፣ የከበረ እንደሆነ ነው የሚያስረዳን።

እኛ ሕዝበ ክርስትያን ቀዳሚት ሰንበትን (ቅዳሜን) መጽሐፋዊ ሥርዓቷንና ታሪካዊ መሠረቷን በመጠበቅ በሐዲስ ኪዳን ተጠንቶ በተቀመጠልን የሥርዓተ ሃይማኖት አፈጻጸምና የበዐላት አከባበር መሠረት እናከብራታለን።

ክፍል 30÷

ሰንበተ ክርስቲያን (እሑድ)

እሑድ ማለት አንድ ማለት ሲሆን÷ እሑድ ማለቱ ሰንበት የፍጥረት መጀመሪያ ስለሆነች እንደኛ፣ ጥንተ ዕለት፣ (የፍጥረት መጀመሪያ) መሆኗን ሲያመለክተን ነው።

ከላይ በሰፊው እደተገለጸው ዘፍጥረትን 1÷1 መጽ. ኩፋሌንም 2÷1 ጀምሮ እንመልከት።

ይህች ሁላችንም ፈጣሪያችንን በማመስገን በልዩ ክብር የምናርፍባት አስቀድማ በምሥጢራዊ ትንቢት የተጠቀሰች ሰንበተ ክርስቲያን (የክርስቲያን ሰንበት)

በሐዲስ ኪዳን የተከበረች ሰንበት ስትሆን÷ በጌታችን የተመረጠች መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ድውያንን የፈወሰባት፣ የተነሣባትና ልዩ ልዩ ተአምራቱንም ያደረገባት÷ በክርስቶስ ክርስቲያን ለተባልነው የክብር፣ የዕረፍትና የምስጋና ዕለት እንድትሆነን የመደባት በዓለም ፍጻሜም በእርሷ ቀን መጥቶ ፍጥረቱን ሁሉ የሚያሰናብትባት ዕለት ናት።

ሰንበተ ክርስቲያን (የክርስቲያን ሰንበት)

ስሟ እንደሚያመለክተን ለእኛ ለሕዝበ ክርስቲያን በፈጣሪአችን በልዩ ክብር የተሰጠችበት ዋናው ዓላማ÷ ዝም ብለን ተቀምጠን እንድንውልባት ሳይሆን÷ መንፈሳውያን ሥራዎችን እንድናከናውንባት

ማለትም እግዚአብሔር አምላካችንን ከሌሎች ዕለታት ይልቅ ለየት ባለ መልኩ እንድናመሰግንባት÷ ስለ ነፍሳችን ዘለዓለማዊ ሕይወት እንድንጸልይባት÷ በሰላምና በእውነተኛ ፍቅር አንድ በመሆን ፈጣሪአችንን በልዩ ልዩ ዝማሬ እያመሰገን የነፍስ ዕረፍት፣ የመንፈስ ደስታ እንድናደርግባት÷

የታመሙትንና የታሠሩትን እንድንጠይቅባት፣ የተጣሉትን እንድናስታርቅባት÷ የተራቡትን እንድንመግብባት÷ (እንድንመጸውት) የተቸገሩትንም ሁሉ በሚቻለን ዐቅም እንድንረዳባት ነው።

ጥቅስ <<እግዚአብሔር አምላክህ እንዳዘዘህ በሰንበት ቀን ትቀድሰው ዘንድ ጠብቅ>> ዘዳ 5÷11

በዕለተ ሰንበት ወደቤተ ክርስቲያን ሔዶ እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባ ሲያስገነዝበን ነው።

በዕለተ ሰንበት እግዚአብሔርንና ሰውን ከሚያሳዝን ነገር ሁሉ ተጠብቀን የጽድቅን ሥራ ብቻ እንድንሠራ መታዘዛችንን ሲነግረንም እንደዚህ ይላል።

<<ሰንበትን የሚያከብር እጁንም ክፉትን ከማድረግ የሚጠብቅ ሰው ብፁዕ ነው>>። ኢሳ 56÷2።

በሰንበት ወደ ጸሎት ቦታ መሔድ እንደሚያስፈልግ ሲያስረዳን ደግሞ <<በሰንበት ቀንም ከከተማው በር ውጭ የጸሎት ሥፍራ በዚያ መሆኑን ስለአሰብን ወደወንዝ አጠገብ ወጣን>> ይላል። ግሐ (የሐዋ ሥራ) 16÷13።

አም ሰው ከሁሉ ፍጥረት እንደሚከብር ሰንበትም እግዚአብሔር ስለመረጣት ከሁሉም ዕለታት ትበልጣለችና ከዚህ በላይ በየደረጃው እንደተገለጸው ሥጋዊውን ተግባር ሳይሆን መንፈሳዊውን የጽድቅ ሥራ ብቻ ልንሠራባት ይገባናል ማለት ነው።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ 9፥

በዐቢይ ጾም ውስጥ የሚኙት ሰንበታት፥

በዐቢይ ጾም ውስጥ የሚኙት ሰንበታት፥ ደግሞ የተለያየ የመጠሪያ ስም አላቸው።

ይኸውም በየዓመቱ የዐቢይ ጾም መጀመሪያው (መግቢያ) የሚኘው ሰንበት (እሑድ) <<ዘወረደ>> ለዐቢይ ጾም መቅድሙ፥

ወይም መግቢያውና ዋዜማው ነው ማለት ነው።

ስለሆነም የዐቢይ ጾም (የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጾም) መጀመሪያ እሑድና ሳምንቱ <<ዘወረደ>> ይባላል።

ከዘወረደ ቀጥሉ ያለው <<ቅድስት>>

ከቅድስት ቀጥሉ ያለው <<ምኩራብ>>

ከምኩራብ ቀጥሉ ያለው <<መፃጉዕ>>

ከመፃጉዕ ቀጥሉ ያለውም <<ደብረ ዘይት>>

ከደብረ ዘይት በኋላም <<ገብር ኄር>>

በመጨረሻው የሚኘውም <<ኒቆዲሞስ>> በመባል ይታወቃሉ።

ከዚሁ ከኒቆዲሞስ በኋላ፥ <<ሆሳዕና>> በበነገታው ሕማማት ሲሆን፥

በሳምንቱም <<ትንሣኤ ክርስቶስ>> {{ፋሲካ}} ይሆናል ማለት ነው።

እነዚህ <<ሰንበታት>> በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጾም ውስጥ የሚውሉ ሲሆኑ፥ ጌታችን ልዩ ልዩ አምላካዊ ሥራውን የሠራባቸው፥ የድኅነት፣ የተአምራት፣ የምስጋና እና የታሪክ ዕለታት ናቸው።

<<ሰንበታት>> ስማቸው እንደሚጠቁመን ምሥጢራቸውም በስያሜያቸው መሠረት ሰፋ ያለ ይዘት ያለው ነው።

በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የምስጋና እና የአገልግሎት ሥርዓት መሠረት በአንድ እሑድ የጀመረ የዕለት ስያሜም (ስምም) እስከሚቀጥለው እሑድ ድረስ ይሰነብታል።

ለምሳሌ፥
የዐቢይ ጾም መግቢያ ዋዜማ እሑድ <<ዘወረደ>> ሲሆን፥

ሰኞም፣

ማክሰኞም፣

ሮብም፣

ሐሙስም፥

ዓርብና ቅዳሜም ከእሑድ እስከሚቀጥለው እሑድ ድረስ ያሉት ቀናት በሙሉ <<ዘወረደ>> ይባላሉ።

ከዚህ ቀጥሉ ደግሞ <<ቅድስት>> የሚባል እሑድ ሳምንቱን <<ከዘወረደ>> ተቀብሉ እስከ ቀጣዩ እስከ <<ምኩራብ>> ድረስ ይይዘዋል።

ሌሎችም በዚሁ መሠረት ከዓመት እስከ ዓመት ይቀጥላሉ ማለት ነው።

www.zeyeneta.com

ክፍል 31÷

<<ዘወረደ>>

የመጀመሪያ ጾም መግቢያ ሰንበት ዘወረደ እየተባለ መጠራቱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ከርስቶስ ከሰማይ ወርዶ ከድንግል ማርያም በመወለዱ ወረደ፣ መጣ፣ በመባሉ÷ ምክንያት እንደሆነና

ጾሙም ጾመ ሕርቃል መባሉ ሕርቃል ለተባለ የሮም (የሺዛንታይን) ገዥ ስለ ተጾመ እንደሆነ ከቦታው በሰፈው ተገልጿል። ገጽ 72ና 73 እንመልከት።

ክፍል 32÷

ቅድስት÷

<<ቅድስት የዐቢይ ጾም 2ኛ እሑድና ሳምንት>>

ይህች እሑድና ሳምንት <<ቅድስት>> በመባል የምትታወቅ ስትሆን የዐቢይ ጾሙን ሁለተኛ ሳምንት የምንጀምርባት ወቅት ናት።

<<ቅድስት ማለት>> እመቤታችን ከሁሉም ፍጥረት የተለየች ንጽሕትና ቅድስት እንደሆነች ሁል ጊዜ በእመቤታችን ክብርና ቅድስና ክፍል እንደሚገለጸው÷ የቅድስት ዕለትም ከሌሎች ዕለታት ተለይታ በጌታችን ለጾም፣ ለነፍስ መድኃኒት ተመርጣ የተከበረች ቅድስት ዕለትና ሳምንት ናት ማለት ነው።

ቅድስት የምትባለው እለትና ሳምንቷ ጌታችን በመባል ምክንያት የጠፋውን ሕይወታችንን ያለ መብል በጾም ለመመለስ÷

ለሁላችንም አብነቱን ለመስጠት እኛንም በተግባር ለማስተማር ሲል መዋዕለ ጾሙን የጀመረባት÷

በጌታችን፣ በፈጣሪአችን ለፍጹም ሕይወት የተመረጠች፣ የተቀደሰች ናት።

ስለሆነም ከዚህ ቀጥለን የቅድስት እሑድ ቃለ እግዚአብሔርን መሠረት በማድረግ ሁሉንም በየክፍላቸውና፣ በየደረጃቸው እንመለከታቸዋለን።

የቅድስት እሑድ የቅዳሴው ምስባክ በግእዙ ሲጠቀስ÷

እግዚአብሔርሰ ሰማያተ ገብረ÷
አሚን ወሠናይት ቅድሜሁ÷
ቅድሳት ወዕበየ ስብሐት ውስተ መቅደሱ÷ ይላል።
መዝ 95÷5።

ይህ መዝሙር÷ ልበ አምላክ የተባለው ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት እግዚአብሔር አምላክ ነውና ሰባቱን ሰማያት ፈጠረ÷ ምስጋና፣ ቅድስነትና ግርማ በመቅደሱ ውስጥ ናቸው፣ ሃይማኖትና ምግባርን የያዘ ሰውንም ይወዳል።

<<ቅዳስ ቅዳስ ቅዳስ>> ተብሎ መመስገን ዐቢየ ስብሐት መባል ገንዘቡ ነው።

(ምስጋና የባሕርዩ ነው) በማለት ፈጣሪውን አመስግኖበታል።
<<በአበው ትርጓሜ መሠረት ሲብራራ>>

የፍጥረታት ባለቤት የሆነው ፈጣሪያችን ልዑል እግዚአብሔር ሰባቱን ሰማያትንና በሰማያት ያሉትን ፍጥረታት ሁሉ ፈጠረ÷ ዓለምንና በውስጧ ያሉትንም ሁሉ ፈጠረ ሃይማኖትና ቅድስና የእርሱ ነው÷ ምስጋና የባሕርዩ ቢሆንም በኦሪት ዘፍጥረት 1÷26 ጀምሮ እንደምንመለከተው ሰውና መላእክት በእርሱ አርአያና አምሳል የተፈጠሩበት ዋና ዓላማም እርሱን ለማመስገን እንደመሆኑ መጠን ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ተብሎ መመስገን የሚገባው ነውና ፍጥረትን ሁሉ ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ለፈጠረ ለእግዚአብሔር አምላካችን በሰማያትም በምድርም ምስጋና ይድረሰው።

ከዚህ በላይ እንደተገለጸልን እግዚአብሔር ሃይማኖትን ከምግባር ጋር አጣምሮ የያዘውን፣ ሃይማኖቱን በመልካም ምግባር፣ በሠናይ ሥራ የሚገልጸውን ሰው ይወዳል÷ ይረደዋል የሃይማኖት ትርጉም መልካም ምግባር ነውና÷ መገለጫውም በጎው ሥራ ስለሆነ አንድ ሰው ሃይማኖት አለው ሲባል የሚቻለው የሃይማኖት ሥራ ሲሠራ የታየ እንደሆነ ነው።

www.zeyeneta.com

ይኸውም፥ እውነተኛ ፍቅር፥ ንጽሕና፥ ትሕትና፥ ጾም፥ ጸሎት፥ ርኅራኄና ምጽዋት፤ በአጠቃላይ እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያስደስት መልካም ምግባር፥ ሠናይ ሥራ ነው።

በተለይም የዚህ ሁሉ የጽድቅ ሥራ ማሠሪያው እውነተኛው ፍቅር በመሆኑ እውነተኛው ፍቅርን መሠረት አድርገን ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን መልካሙን ሥራ ሁሉ መሥራት ይገባናል ማለት ነው።

ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ የዘመረው የቅድስት ምስባክ ውስጠ ምሥጢሩ በአበው ትርጓሜ መሠረት ሲተነተን እንደዚህ አሁን እንደሰማነው ነው።

ቅዱስ ወንጌሉ ደግሞ፥ <<ወሶበ ትጸውሙ ኢትኩኑ ከመ መደልዋን>> ይላል፥ ማቴ 6፥16 ነው።

ስትጾሙም እንደ ግብዞች አትጠውልጉ፥ ሰነፎች ጾመኞች እንደሆኑ ሰው ያውቅላቸው ዘንድ ፊታቸውን አጠውልገው፥ ግንባራቸውን ቋጥረው፥ ሰውነታቸውንም ለውጠው ይታያሉና እንደነዚህ አትሁኑ። እናንተስ በምትጾሙበት ጊዜ ራሳችሁን ተቀቡ፥ ፊታችሁንም ታጠቡ፤ ጾመኞች መሆናችሁን ሁሉን የሚያውቅ አባታችሁ ጌታ እንጂ ሌላሰው አይወቅባችሁ። በማለት ጌታችን አስተምሮናል።

የዚህ ምሥጢራዊ ትንታኔ ስትጾሙ በስውር ይሁን ያለው፥

በጾመ ፈቃድ ማለትም በግል ለትሩፋት በምትጾሙበት ጊዜ ማለቱ ነው እንጂ በቤተ ክርስቲያናችን በሥርዓተ ቀኖና የተመደበውን፥ በግልጽ በጎብረት የምንጾመውን የዓዋጁን ጾም ማለቱ አይደለም።

ምክንያቱም በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ ቀኖና የተወሰነ ጾም እማ በመንፈሳዊ ሕግ የተደነገገ፥ በመጽሐፋዊ መመሪያ የታዘዘ፤ በግልጽ፣ በይፋ የሚታወጅ ስለሆነ የዓዋጅ ጾም ነው የሚባለው።

በሰባቱ አጽዋማት ውስጥ ያለ ጾም፥
የማኅሌቱ፥ የሰዓታቱ፥ የስብሐተ ነግሁ፥ የቅዳሴውና የጸሎተ ሠርኩ፥ በአጠቃላይ የጾሙና የጸሎቱ ጊዜያት በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ ቀኖና ስለ ተወሰነ በውሳኔው መሠረት ነው በጎብረት ሆነን በግልጽ የምንጾመው።

<<ቅድስት>> የዐቢይ ጾም 2ኛ እሑድና ሳምንት >>

ራሳችሁን ተቀቡ ማለቱ ደግሞ እውነተኛውን ፍቅር ያዙ እርስበእርሳችሁ ተፋቀሩ ሲለን ነው።

ፊታችሁን ታጠቡ ማለቱም፥ ንጽሕናንና ትሕትናን ገንዘብ አድርጉ፤ በትሕትና፤ በንጽሕና ሆናችሁ ጹሙ፤ ጸልዩ፤ እያለቀሳችሁ ንስሓ ግቡ ሲለን ነው።
<<በአበው ትርጓሜ መሠረት ሲብራራ ነው>>

በመሆኑም የዚህ ምሥጢር ተራራ ተብሎ በሚጠራው እንቁጸ <<ብፁዓን የጌታችን ትምህርት፥ ብፁዓን እለ ይርህቡ ወይፀምዑ በእንተ ጽድቅ ብሎ >> ተብራርቶ እናገኘዋለን።

ይኸውም፥ አብዝተን ከተመገብን፥ አብዝተን ከጠጣን እማ ሰውነታችንን ወስነን ገተን ማኖር እንዴት ይቻለናል ብለው የሚበሉትንና የሚጠጡትን ቆጥበው የሚራቡ ንዑዳን ክቡራን ናቸው።

ጨርሰን ከተመገብን፥ ጨርሰን ከጠጣን እማ መንግሥተ ሰማያትንስ በምን እንዋኃታለን ብለው ከሚበሉት ከሚጠጡት ከፍለው ለነዳያን ሰጥተው (መጽውተው) የሚራቡ የሚጠሙ (የሚጸሙም) ንዑዳን ክቡራን ናቸው።

እንዲሁም ከመብልዓ ኃጢኣት፥ ከስቴ ኃጢአት የሚራቡ፥ ማለትም ኃጢኣትን ከማድረግ፥ የኃጢኣትን ተግባር ከመፈጸም፥ እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያሳዝንን ሥራ ከመሥራት የሚቆጠቡ ንዑዳን ክቡራን ናቸው።

በመማር፥ በማስተማር፥ በምናኔ በንስሓ የሚራቡ ንዑዳን ክቡራን ናቸው። በመንግሥተ ሰማያት ይጠግባሉና፥ ማለትም መንግሥተ ሰማያት የተዘጋጀችው ይህን ለሚፈጽሙ ሰዎች ስለሆነች መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናት። ብሎአል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ።

አዎ ይህን መልካሙን ሥራ ሠርተው የተሻሉ ሰዎች መንግሥተ ሰማያት እንደሚወርሱ የመንግሥተ ሰማያት ባለቤት የሆነው ፈጣሪአችን በማይለወጥ ቃሉ አረጋግጧል።
ማቴ 5፥6

እንግዲህ የጾም ትክክለኛ ተግባር ይህ ነውና ቃሉን በሥራ መተርጉም የእኛ ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው ማለት ነው።

www.zeyeneta.com

ከዚህ በላይ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ቅድስት፥
የዐቢይ ጾሙን ሁለተኛ ሳምንት የምንጀምርባት ስትሆን፥

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ለመጾም መዋዕለ ጾሙን የጀመረባት ዕለትና ሳምንት በመሆኗ የጌታችን ጾም መጀመሪያና መታሰቢያ ናት ማለት ነው።

ጌታችን በተለያዩ ሦስት የስሕተትና የኃጢኣት ኅዳናዎች፥ ማለትም በስስት፣ በትዕቢትና በአፍቅሮ ርእስ (ራስ ወዳድነት) ይኸውም ሥጋዊውን ሹመት በመሻም፣ ግላዊ ዝናን፣ ግላዊ ክብርንና ገንዘብን መውደድ ማለት ነው።

በነዚህ የኃጢኣት ርእሶች በሚባሉት የመጣውን ሰይጣን፥ በአንዓራቸው ተሰልፎ፥ በጾም፣ በትዕግሥትና በትሕትና ድል አድርጎ ጾም የሥጋና የነፍስ ፍጹም መድኃኒት መሆኑን በተግባር አሳይቶ ለራሱ ጹሞ እኛንም ጹሙ ብሎናል።

በጾም፥ በጸሎት የተለያየዩትን ፈተናዎች ማለፍ፥ ሰይጣንንና ሰይጣናዊ ጠላትን ማሸነፍ እንደሚቻልም በተግባር አስተምሮናል። ማቴ ፥ 4፥1።

ሐዋርያት፥ አርድእትና ሊቃውንትም እርሱን አብነት በማድረግ ጹመዋል በጾም በጸሎት ድውያንን ፈውሰዋል፣ ሙታንንም አስነሥተዋል፣ ብዙ ተአምራትን አድርገዋል።

እኛ ደግሞ ጌታችንን፥ ሐዋርያትን፣ ቅዱሳንና ሊቃውንት አባቶቻችንን አብነት አድርገን ልንጾም፣ ልንጸልይ፣ በእነርሱ እግር ልንተካ ይገባናል።

ከቅዱስ መጽሐፉ እንደምንረዳው ጌታችን ጾሙን ገዳመ ቆሮንቶስ (ወደ ቆሮንቶስ በረኻ) ገብቶ እንደቆመ ሳይቀመጥ፣

ሰውነቱን ሁሉ እንደዘረጋ ሳያጥፍ፣ አንዳችንም ዕረፍት ሳያደርግ፥ አርብዓ መዓልትና አርብዓ ሌሊት (አርባ ቀንና አርባ ሌሊት) በሚጾምበት ጊዜ፥ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት የስሕተትና የጥፋት ኅዳናዎች ለማሰናከል የመጣውን ሰይጣን ድል ካደረገ በኋላ መላእክት ሊያገለግሉት ቀርበው እንደ ነበር። ቅዱስ ወንጌሉ ያስረዳናል። ማቴ 4፥11

እኛም ትምህርቱንና ተግባራዊ አብነቱን በመቀበል ጾሙን በአግባቡ ከጸምነው መላእክት ይረዱናል፣ መንፈሰ ኃይል፣ መንፈሰ ረድኤት ይሰጠናል፣ ስርየተ ኃጢኣትን እናገኛለን።

ሰማያዊ ክብርንም ከጌታችን መድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ እንቀዳጃለን ማለት ነው።

በተጨማሪም ከዚህ በታች ያሉትን ጥቅሶች እንመልከታቸው፥

1ኛ በጾማችሁ ቀን ፈቃዳችሁን ታደርጋላችሁ፣ ሠራተኞቻችሁን ሁሉ ታስጨንቃላችሁ፣ ለጥልና ለክርክር ትጾማላችሁ፣ በግፍ ጡጫም ትማታላችሁ፣...እኔ የመረጥኩት ጾም ይህ ነውን?....

በውኑ ይህን ጾም በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ቀን ትለዋለህን? ኢሳ 58።3።

(ይህ ቅዱስ ቃል ጾማችን እውነተኛ እንዲሆን ነው በመገሠጽ እየመከረን ያለው)።

2ኛ እግዚአብሔርን አመስግኑ ስሙንም ጥሩ ተቀኙለት ዘምሩለት ሥራውን ሁሉ ለአሕዛብ ንገሩ። መዝ 104፥1

3ኛ ክብርንና ምስጋናን ለእግዚአብሔር አምጡ በቅድስናውም ሥፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ። መዝ 28፥2

4ኛ የልቡናችሁን ወገብ ታጥቃችሁና በመጠን ኑራችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ የምታገኙትን ጸጋ ፈጽማችሁ ተስፋ አድርጉ። 1ኛ ጴጥ 1፥13።

ይህ ቅዱስ ቃል ሁል ጊዜ በሚመሰገንበት፣ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙም በሚፈተትበት በቤተ ክርስቲያኑ፣ (በቤተ መቅደሱ) እየተገኘን እግዚአብሔር አምላካችንን ማመስገን እንደሚገባን ነው እየነገረን ያለው።

<<ጥቅሶቹ ለአስፈላጊው ማብራሪያ እየተደረገበት እንዳሉ ከአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የተወሰዱ ናቸው>>።

www.zeyeneta.com

ክፍል 33

ምኩራብ የወቢይ ጸም 3ኛ እሑድ÷

ምኩራብ ማለት÷ በቀጥታ ሲተረጉም አዳራሽ ማለት ሲሆን÷ ጌታችን ወደ አይሁድ ቤተ ጸሎት፣ ምኩራብ (አዳራሽ) ገብቶ ቤቴ የጸሎት ቤት እንጂ የንግድ ቤት አይደለም በማለት ያስተማረበት በቤተ ጸሎቱ ውስጥ ሲነግዱ፣ ሲሸጡ፣ ሲለውጡ የነበሩትን ሰዎች ያስወገደበት መታሰቢያ ነው።

ጌታችን ወደ አይሁድ ምኩራብ (የአይሁድ አዳራሽ) ወይም ቤተ ጸሎት በገባ ጊዜ የመማማሪያ÷ የጸሎት ቤትና የሥርዓተ አምልኮ ማስፈጸሚያ የሆነውን ምኩራብ አይሁድ መገበያያ፣ መሸጫና መለወጫ አድርገውት ስለ አገኛቸው ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል።

እናንተ ግን መገበያያ መሸጫና መለወጫ አደረጋችሁት በማለት ሸቃጮች ሰዎቹንና እንስሳቱን በጅራፍ እየገረፈ ሰዱቃዊውንም (መደረደሪያቸውንም,ገበታዎቻቸውንም) እየገለባበጠ አባርሮአቸዋል።

የሃይማኖት ትምህርቱንም እዚሁ ምኩራብ ውስጥ ገብቶ አስተምሮአል።

አዎ ጌታችን ቤተ ክርስቲያን (ቤተ መቅደስ) የእግዚአብሔር መመስገኛ፣ የምሕረትና የይቅርታ መለመኛ፣ የነፍስ ገበያ÷ የሕይወት ማግኛ እንጂ÷ የሥጋ ገበያ፣ የግለ ሰቦች መጠቃቀሚያ ልትሆን እንደማይገባት በምኩራብ አይሁድ ተገኝቶ አረጋግጧል።

ትምህርቱን፣ ምክሩንና መመሪያውንም ሰጥቷል።

አዎ ምሥጢራዊ መልእክቱ ሁላችንንም ስለሚመለከት ልብ ብለን ልንገነዘበው÷ ልናስተውለውም ይገባናል።

ስለዚህም ይህ የወቢይ ጸም ሦስተኛ እሑድና ሳምንቱ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ምሥጢር ምክንያት ምኩራብ እየተባለ ይጠራል ማለት ነው። ዮሐ 2÷13።

በተጨማሪም ከዚህ በታች ያሉትን ጥቅሶች እንመልከት።

1ኛ የቤትህ ቅንዓት በልታኛለችና፣ የሚሰድቡህም ስድብ

በላዬ ወድቆአልና፣ ነፍሴን በጾም አስመረርኋት። መዝ 68÷9

(ጥቅሱ ከምኩራብ ምስባክ የተወሰደ ነው)።

2ኛ እንጀራህን ለተራበ ትቆርስ ዘንድ ስደተኞችን (ድኾችን) ወደ ቤትህ ታገባ ዘንድ የተራቆተውንስ ታለብሰው ዘንድ፣ ከሥጋ ዘመድህ እንዳትሸሸግ አይደለምን?

የዚያን ጊዜ ብርሃንህ እንደ ንጋት ይበራልሃል፣ ፈውስህም ፈጥኖ ይበቅላል፣ ጽድቅህም በፊትህ ይሔዳል÷ የእግዚአብሔርም ክብር በኋላህ ሆኖ ይጠብቅሃል። ኢሳ 58÷7

3ኛ ፍጹም ልትሆን ብትወድ ሒድና ያለህን ሁሉ ሽጠህ ለድኾች ስጥ፣ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ÷

መጥተህም ተከተለኝ። ማቴ 19÷21

ቅዱስ ቃሉ ምጽዋት በእግዚአብሔር ዘንድ ትልቅ ዋጋን እንደሚያሰጥ ነው የሚያስረዳን።

በተጨማሪም ማቴ 12÷7 ሆሴዕ 6÷6 2ኛ ቆር 9÷7 ገላ 13÷16 ዳን 4÷27 ማር 4÷24 ሉቃ 7÷47 እንመልከት።

4ኛ ምጽዋትን የሚመጸውት ሰው ለእግዚአብሔር በማደሩ ነው። መጽሐፈ ሲራክ 29÷1

5ኛ ወንድሞቼ ሆይ እምነት አለኝ የሚል ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል?

እምነቱስ ሊያድነው ይችላል? ያዕቆብ 2÷14።

ይህ ቅዱስ ቃል መልካም ሥራ (ምጽዋት) የሌለው እምነት ብቻ እንደማይጠቅም ነው እያስገነዘበን ያለው

<<ጥቅሶቹ ለአስፈላጊው ማብራሪያ እየተደረገበት እንዳሉ ከአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው>>።

www.zeyeneta.com

ክፍል 34፥

መግኑዕ የዐቢይ ጾም 4ኛ እሑድ፥

መግኑዕ ማለት በሽተኛ ማለት ሲሆን፥ በዮሐንስ ወንጌል 5፥5 ጀምሮ እንደምናገኘው ጌታችን ለ38 ዓመታት ያህል በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ ተይዞ፥ (በጽኑዕ በሽታ ታሞ) ሲማቅቅ የነበረውን መግኑዕ በመባል የሚታወቀውን በሽተኛ ሰው የፈወሰበት መታሰቢያ ነው።

ይህ መግኑዕ በመባል የሚታወቀው በሽተኛ ለ38 ዓመታት ያህል በጽኑዕ ደዌ ተይዞ ታሞ እያለ ተስፋን ባለመቁረጥ ለመዳን ደጅ ሲጠናበት በነበረው ሥፍራ ሕሙማን ፈጥነው ገብተው እየተጠመቁ ከደዌያቸው የሚፈወሱበት ውሃ ነበር።

ይኸውም የእግዚአብሔር መልአክ በሳምንት አንድ ጊዜ መጥቶ ውሃውን ሲባርከው ውሃው ስለሚንቀሳቀስ የውሃውን አንቅስቃሴ ሰምቶ ቀድሞ የገባ አንድ በሽተኛ ተጠምቆ ሲወጣ ከደዌው ሁሉ ይፈወስ እንደነበርና መግኑዕም በውሃው ተጠምቆ ከደዌው መዳን ይፈልግ ነበር።

ነገር ግን መግኑዕ ቀድሞ ለመግባት ዐቅም ስለአልነበረው፣ ተሸክሞ ከመጠመቂያው የሚያኖረውም ሆነ የሚያጠምቀው ወገን ስለሌለው ይህን ዕድል ሞሽት እንዳልቻለ ቅዱስ መጽሐፍትን ይናገራል።

ስለሆነም የርኅራኄና የፍጹም ሕይወት አምላክ እግዚአብሔር የበሽተኛውን ልመና፣ ጸሎቱን፣ ገዓሩንና ጭኾቱን ሰምቶ በአንድ ጊዜ ከደዌው ፈውሶ በል ተነሥና አልጋህን ተሸክመህ ወደ ቤትህ ሒድ አለው።

ለ38 ዓመታት ያህል በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ ተይዞ (በጽኑዕ በሽታ ታሞ) ሲማቅቅ የነበረው መግኑዕም ጌታችን ስለፈወሰው ፍጹም ጤነኛ ሆኖ ታሞ ተኝቶበት የነበረውን አልጋ በመሸከም እየተደነቀ ወደ ቤቱ እንደ ሒደ ይታወቃል።

(መግኑዕ ለ38 ዓመታት ያህል ተሸክሞት የነበረውን አልጋ እርሱ ደግሞ ድኖ በተራው ተሸከመው)

ይህ እኛም በትክክለኛ እምነታችን ጸንተን ፈጣሪአችን እግዚአብሔርን በንጹሕ ልብ ከለመነው ከደዌ ሥጋ፣ ከደዌ ነፍስ ልያድነን እንደሚችል ነው የሚያስገነዝበን። ዮሐ ወንግጌል 5፥5።

በተጨማሪም ከዚህ በታች ያለውን እንመልከተው፥

እግዚአብሔር በሽተኛውን በደዌው አልጋ ላይ ሳለ ይረዳዋል፣ ከደዌው ፈውሶም መኝታውን ይለውጥለታል።

አቤቱ እኔ ግን ለዚህ የሚያበቃ ሥራ የለኝምና ማረኝ ይቅርም በለኝ፣ አንተን በድያለሁና ነፍሴን ፈውሳት ይላል ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት በመዝሙሩ። (መዝ 40፥3)

እዎ ይህ ቅዳሰ ቃል ከዕለቱ ምስባክ የተጠቀሰ ሲሆን፥ በፍጹም ልባችን ወደ እግዚአብሔር አምላካችን ከቀረብን፣ ፈጣሪያችንን በንጹሕ ልብ ከለመን፥ ከእርሱ ፍጹም ምሕረትና ፍጹም ሕይወት እንደሚገኝ ነው እያመለከተን ያለው።

ክፍል 35፥

ደብረ ዘይት የዐቢይ ጾም 5ኛ እሑድ

<<ደብረ ዘይት>> የዐቢይ ጾም 5ኛ እሑድ ነው።

ዘይት የወይራ ሰም ሲሆን፥ ደብርም ተራራ ማለት ነው።

ስለዚህም <<ደብረ ዘይት>> ማለት የወይራ ዛፍ ያለበት ተራራ ማለት ነው።

<<ደብረ ዘይት>> በምሥራቃዊ ኢየሩሳሌም በቀድሞ የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ትይዩ የሚገኝ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያትን ሰብስቦ የዳግማይ ምጽአቱንና የዓለም ፍጻሜ ሁኔታን በምሳሌ አድርጎ ያስተማረበት ተራራ ነው።

www.zeyeneta.com

<<ደብረ ዘይት>> ከኢየሩሳሌም በስተምሥራቅ 75 ኪ.ሜ ርቀት ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል።

(1 ኪ.ሜ ያህል የሰንበት መንገድ ያህልም ይላል የሐ. ሥራ 1÷12)

በዐቢይ ጾም ውስጥ ያለው የጾሙ 5ኛ እሑድና ሳምንቱም <<ደብረ ዘይት>> ይባላል።

<<ደብረ ዘይት>> በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24÷1 ጀምሮ እንደምንመለከተው የጌታችን ዳግማይ ምጽአትንና የዓለም ፍጻሜ ሁኔታን የምናስታውስበት ዕለት ነው።

ጌታችን የሚመጣበት ዓመተ ምሕረትና ሰዓቱ ተለይቶ ባይታወቅም÷ ዘመኑ ዘመነ ዮሐንስ፣ ወሩ ወርኀ መጋቢት፣ ዕለቱ ዕለተ እሑድ፣ ጊዜውም መንፈቀ ሌሊት እንደሚሆን በአባቶቻችን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ተገልጸአል።

ነገር ግን ብዙ ዘመነ ዮሐንስ፣ ብዙ ወርኀ መጋቢት፣ ብዙ ዕለተ እሑድና ብዙ መንፈቀ ሌሊት ስለ አለ÷ በዚህ ጊዜ ነው ተብሎ ሰዓቱ ተለይቶ እንደማይታወቅ የተነገረ ሲሆን÷ የመቃረቡ ምልክቶችና ምሳሌዎቹ ደግሞ ከላይ በተጠቀሰው የማቴዎስ ወንጌል 24÷1 አማካይነት በጌታችን አንድ ባንድ ስለ ተገለጹ ልብ ብለን ልናስተውላቸው ይገባናል።

ጌታችን ምንም እንኳን የሚመጣበት ጊዜ ባይታወቅም መምጣቱ ግን አንዳችም ጥርጥር ስለሌለው ሰው ሁሉ በሃማኖትና በሃይማኖታዊ መልካም ምግባር ዝግጁ ሆኖ እንዲኖር አስቀድሞ መክሮአል፣ አንዳትሳሳቱ ብሎም አስጠንቅቆአል።

ጌታችን ደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያትን ደብረ ዘይት በተባለው ቦታ ሰብስቦ ከእኔ በኋላ በስሜ የሚነግዱ ብዙ አታላዮች ይመጣሉና እንዳትታለሉ ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ ሁል ጊዜም ዝግጁዎች ሆናችሁ ኑሩ በማለት አስተምሮአቸዋል። ትምህርቱና መልእክቱ ሁላችንንም ይመለከታል።

አዎ በመዝሙር 49÷2 ጀምሮ÷ <<እግዚአብሔርሰ ገሀደ ይመጽእ፣ ወአምላክነሂ ኢያረምም፣ እሳት ይነድድ ቅድሜሁ>> ተብሎ በግእዙ እንደተጠቀሰልን እግዚአብሔር አምላካችን በግልጽ ይመጣል፣ መጥቶም ዝም አይልም በጻድቃንና በኃጥኣን መካከል ሆኖ ይፈርዳል። ለሁሉም እንደየሥራው ይሰጠዋል። ለጻድቃን ይፈርድላቸዋል በኃጢኣተኞች ላይም ይፈርዳል ማለት ነው።

በሚመጣበት ጊዜ እሳት በፊቱ ይቃጠላል በዙሪያውም ብዙ ዐውሎ አለ ይላል ነቢዩ ዳዊት።

ይህ ማለት ጻድቃን የሚድኑበት ሕይወት፣ ኃጥኣን ግን የሚጠፉበት መቅሰፍት በባሕርዩ አለ ማለት ነው።
<<በአበው ትርጓሜ መሠረት ሲብራራ ነው>>

አዎ በቅዱሳት መጻሕፍት÷ በተለይም ደግሞ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24÷1 ጀምሮ ተዘርዝሮ እንደሚገኘው እግዚአብሔር አምላካችን በማይታወቅ ጊዜና ባልተጠረጠረ ሰዓት በግርማ መንግሥቱ በድንገት መጥቶ ጻድቃንን ኑ ወደ እኔ ብሎ ይጠራል፣ ለጻድቃን ጽድቅን መንግሥተ ሰማያትን ያወርሳል።

ኃጥኣንን ግን ወግዱ ከእኔ ራቁ ለሰይጣንና ለመልእክተኞቹ ወደ ተዘጋጀው፣ እሳቱ ለዘለዓለም ወደማይጠፋው ሒዱ ብሎ ያሰናብታል፣ ለኃጥኣን ገሃነመ እሳትን ፈርዶ ይሰጣል።

ሰማይንና ምድርን÷ ሌላውንም የፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ ከህልው፣ ከምንት÷ (ከመኖር) ወደ ኢህልው፣ ወደ ኢምንት÷ (ወደ አለመኖር) ያሳልፋል፣ ፍጥረቱን ሁሉ ያሰናብታል። እርሱ ግን ጎልፈት የሌለበት ዘለዓለማዊ የሆነ የባሕርይ አምላክ ነው።

ስለዚህ ጌታችን አስቀድሞ ያችን የማታዳግመውን የከባድ ፍርድ ቀን መጨረሻ አታውቋትምና ሁል ጊዜ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ ብሎ ነግሮናል።

አርቶድክሳዊት ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም ይህን የጌታችን ቃል መሠረት አድርጋ÷ በእምነታችን እንድንጸና፣ ሃይማኖታችንን በመልካም ምግባር እንድንገልጽ÷ ሕጉንና መመሪያውን እንድንጠብቅ፣ ትእዛዛቱን እንድንፈጽም፣

የተቸገሩትንም ባለን ዐቅም እንድንረዳ፣ በሰላምና በእውነተኛው ፍቅር እንድ ሆነን÷ እየጸምን፣ እየጸለይን፣ በወንጌሳ ንስሓ እየታጠብን፣ (ንስሓ እየገባን) ማለትም ኃጢኣታችንን እየተናዘዝን÷ እግዚአብሔርንና ሰውን ከሚያሳዝን ማንኛውም የኃጢኣት ተግባር ተቆጥበን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እየተቀበልን ድንገተኛ የሆነውን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ምጽአት ዝግጁዎች ሆነን እንድንጠባበቅ በመምህራንና በአባቶች ካህናት አማካይነት ዘወትር ታስተምረናለች፣ አሁንም እያስተማረችን፣ እየመከረችን ትገኛለች።

www.zeyeneta.com

አዎ ትምህርቱ ሁል ጊዜ ይሰጣል እንሰማዋለን ነገር ግን መስማት ብቻ እንደማያጸድቅ በቅዱስ መጽሐፋችን ተነግሮናልና በሰማነው መሠረት መልካሙን ሥራ መሥራት ይጠበቅብናል። ያዕ 1÷22 እንመልከት።

ምሥጢረ መጻሕፍትን ከሊቃውንት አባቶቻችን ተምረን፥ ስለ እምነታችን፣ ስለ ሃይማኖታችንና ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ ሥርዓት ከመሠረቱ በማወቅ እምነታችንን በሠናይ ሥራ መግለጽ፣ ሃይማኖታችንን በመልካም ምግባር ማሳመቅ አለብን።

ምክንያቱም እምነት የሥራ መሠረት እንደመሆኑ መጠን፥ መልካም ምግባርም የእምነት መታወቅያና ራስ ነው።

ስለዚህ ሃይማኖት ሊታወቅ የሚችለው በመልካም ምግባር ሲገለጽ ነው።

በመሆኑም ነው ሃይማኖት ያለ ምግባር ምግባርም ያለ ሃይማኖት ምንም እንደማይጠቅም በቅዱስ መጽሐፋችን የተነገረን። ያዕ 2÷14 እንመልከት።

አንድ ሰው ሃይማኖት አለው ሊባል የሚችለው የሃይማኖትን ሥራ ሲሠራ የታየ እንደሆነ ነው ብለናል።

መልካም ምግባር ሠናይ ሥራ ማለትም ጾም ጸሎት ምጽዋት፣ ርኅራኄ፣ ትሕትና እና እውነተኛው ፍቅር ሲሆን በተለይም እውነተኛው ፍቅር የእነዚህ መልካም ሥራዎች ሁሉ ዋና ማሠሪያ እንደሆነም ተደጋግሞ ተገልጿል።

ይኸውም እውነተኛው ፍቅር ካለ ሌሎችም የጽድቅ ሥራዎች ሁሉ በእውነተኛው ፍቅር ውስጥ ሊካተቱ ስለሚችሉ ነው።

አንድ ሰው ወንድሙን በእውነት የሚወደው ከሆነ ችግር ቢደርስበት ያዝንለታል ይራራለታል ይጠይቀዋል በሁሉም ዐቅሙ ይረዳዋል። ይህ ማለት ደግሞ መጸወተ፣ የታመመውንና የታሠረውን ጠየቀ፣ ለተቸገረው ራራ።
በአጠቃላይ በቅዱስ ወንጌል ማቴዎስ 25÷34 የሚገኘውን <<ተርቤ አብልታችሁኛልና ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፣ እንግዳ ሁኜ ተቀብላችሁኛልና፣ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፣ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፣ ታሥሬ ወደ እኔ መጥታችሁ ጠይቃችሁኛልና የተባረካችሁ ናችሁ ኑ ወደ እኔ>> የሚለውን የጌታችንን ቃል ፈጸመ ማለት ነው።

የምንጾመው ጾም ትርጉም ያለው ጾም ሊሆን ይገባዋል። የጾም ምሥጢርና ተግባራዊ ትርጉም ለሁላችን ግልጽ እንዲሆንልን ያስፈልጋል።

አዎ የጾም ትርጉም፥ ትሕትና፣ ይቅር ባይነት፣ የዋህነትና ደግነት ነው።

የጾም ተግባራዊ ትርጉም፥ ርኅራኄና ምጽዋት ነው።
የጾም ዋና ማሠሪያው እውነተኛ ፍቅር ነው።

የምንጾመው ጾም ትርጉም ሊኖረው የሚችለው ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያስደስቱ መልካሞች ሥራዎችን የሠራን፣ ሕገ እግዚአብሔርን ያከበርን፣ መመሪያውን የጠበቅን፣ ትእዛዙንም የፈጽምን እንደሆን ነው።
ከዚህ ውጭ የምንጾመው ጾም ግን ለታይታ፣ ለይምሰል የምናደርገው ትርጉም የሌለው ጾም ሊሆንብን ነው ማለት ነው።

በተለይም ደግሞ ምጽዋት ከመሥዋዕት እንደሚበልጥና በእውነተኛው ፍቅርም ሌሎች የኃጢኣት ተግባራት ሊሸፈኑ (ሊደመሰሱ) እንደሚችሉ በቅዱስ መጽሐፍ ተደጋግሞ ተነግሮናልና እነዚህን ገንዘብ ማድረግ ተገቢያችን ነው። 1ኛ ጴጥ 4÷8።

ይቅር ባይነት፥ ይልቁንም ወንድምን ልክ እንደራስ አድርጎ ማየት፣ በእውነተኛው ፍቅር መውደድ ከዋናው ትእዛዝ 2ኛው ነው። ዘሌዋ 19÷18 ማቴ 22÷39።

አዎ አባታችን ሆይ እያልን ሁል ጊዜ የምንጸልያት በማቴዎስ ወንጌል ምዕ 6÷9 የምትገኘ የዘወትር ጸሎታችንም በውስጧ በቅዳሳት መጻሕፍት የሚገኙ 5 ዐቢይ መንፈሳውያን ቁም ነገሮች እንዳሏት ይታወቃል።

እነርሱም፥ 1ኛ ሃይማኖት፥ 2ኛ ተስፋ፥ 3ኛ ፍቅር፥ 4ኛ ትሕትና እና 5ኛ ጸሎት ናቸው።

1ኛ ሃይማኖት፥ ያላየኑን እንዳየ አድርገው አቅርበው አባታችን ሆይ በሰማይ የምትኖር እያሉ መጸለይ፣

2ኛ ተስፋ፥ መንግሥትህ ትምጣ እያሉ መንግሥተ ሰማያትን የሕይወት ተስፋ አድርገው መጠባበቅ፣

www.zeyeneta.com

3ኛ ፍቅር÷ ለእኔ ብቻ ሳይሉ በደላችንን ይቅር በለን በማለት አንዱ ስለ ሌላው መጸለይ ስለ ወንድሙ መራራት መተዛዘን÷ ይኸውም÷ በደላችንን ይቅር በለን ማለት ስለሌላውም መጸለይ ነው በደሌን ይቅር በለኝ ቢል ኑሮ ግን ለራሱ ብቻ መጸለይ ማለት ስለ ሆነ ራስ ወዳድ ይሆን ነበር።

4ኛ ትሕትና÷ እያንዳንዱ ኃጢአታችንን (በደላችንን) ይቅር በለን እያለ መጸለዩ፣ ኃጥእም ቢሆን ጻድቅ÷ ኃጢአተኛ ነኝ በማለት በትሕትና ሆኖ በደላችንን ይቅር በለን እያለ ይጸልያል።

5ኛ እምስተኛውም ጸሎት ነው።

ይህች ታላቅ ጸሎት ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ልዩ የሆነ መንፈሳዊ ጥቅምና ብዙ ምሥጢርም ስለአላት ሁል ጊዜ ብንጸልያት መልካም ነው።

ታዲያ ግን እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል (እንድንል) የሚለው በውስጧ የሚገኘውን ጽኑዕ ውል በየጊዜው እያጸናነው መሆናችንን በመረዳት ከፈጣሪአችን ጋር የምንዋዋለውን ውል በተግባር መፈጸም አለብን።

ማንንም ማስቀየም የለብንም፣ የበደሉንንም ሁሉ ይቅር ልንል ይገባናል።

ይህ ካልሆነ ግን በፈጣሪአችን ላይ እየቀለድን÷ አሊያም ራሳችንን ባራሳችን እያታለልን ነን ማለት ነው።

ምክንያቱም በዚሁ ምዕራፍ ከቊጥር 14 ጀምሮ ማለትም ማቴ 6÷14። ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ ኃጢአታችሁ አይቀርላችሁም ተብለናል።

ይኸውም ምንም ሳንበድላቸው የበደሉንን በክፉ ተግባራቸው ያስቀየሙንን ነው እንጂ ወዳጆቻችንንማ ስለሚወዱን እንወዳቸዋለን ስለሚረዱንም እንረዳቸዋለን ይህ ብድር ነው።

በዓለማችን ሲታይ ከነፍሰ ገዳይ የከፋ ጠላት እንደሌለ ለሁላችንም ግልጽ ይመስለኛል።

ይኸውም ጌታችን የሰደቡት በክፉ ተግባራቸው ያሳዘኑት÷ የገረፉት፣ የቸነከሩትና የሰቀሉት፣ ሞትን የፈረዳበት እንዲማሩ÷ በዕኩይ ተግባራቸው ተፀፅተው፣ ከክፉ ሥራቸውም ተመልሰው፣

ንስሓ ገብተው እንዲጸድቁ፣ የእርሱ ወገኖች እንዲሆኑ ነው አባት ሆይ ይህን ማድረጋቸው ባያውቁ ነውና እኔ የባሕርይ አምላካቸውና ፍጹም መድኃኒታቸው መሆኔን ተረድተው ወደ እኔ እንዲመጡ አድርጋቸው÷ ማራቸው፣ ይቅርም በላቸው በማለት በመስቀል ላይ ሆኖ ወደ ባሕርይ አባቱ ወደ እግዚአብሔር አብ የጸለየው። እግዚአብሔር ጠላቶቹን እዚያው በአንድ ጊዜ ማጥፋት ይችል ነበር ነገር ግን አላጠፋቸውም።

ምክንያቱም እግዚአብሔር የርኅራኄና የይቅርታ አምላክ ስለ ሆነ የፈጠራቸው ሁሉ እንዲማሩ፣ በእኩይ ተግባራቸው ተፀፅተው÷ ከክፉ ሥራቸው ተመልሰው ንስሓ ገብተው እንዲጸድቁ የእርሱ ወገኖች እንዲሆኑ እንጂ እንዲጠፉ አይፈልግም።

<<እኛስ? እኮ እኛስ ምንድ ነው የምናደርገው?
ጥያቄው እያንዳንዳችንን የሚመለከት ሲሆን÷
ተግባራዊ መልሱም ከእያንዳንዳችን ይጠበቃል>>

አዎ እኛም በክፉ ተግባራቸው የሚያስቀይሙንንም ልባቸው በጎ ሐሳብ፣ እጃቸውም ወደ መልካም ሥራ እንዲመለስ እየጸለይን ከልባችን ይቅር ልንላቸው፣ በእውነትም ልንወዳቸው ይገባናል ማለት ነው።

ስመ ክርስትናን በመቀበል ክርስቲያን የተባልነው በክርስቶስ ስለ ሆነ የክርስቶስን መልካም ምግባር መሥራት፣ የእርሱን ሠናይ አርአያ እየተከተልን ወገኖቻችንን በእውነተኛው ፍቅር ልንወድ፣ ልንረዳቸውም ተገቢያችን ነው።

ጌታችን በዮሐንስ ወንጌል እኔ እንደወደድኋችሁ እርስበርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት÷ እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ ብሎአልና ቅዱስ ቃሉን ተቀብለን በተግባር ላይ ልናውለው ይገባናል። ዮሐ 15÷12።

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም ወንድሙን የማይወድ ነፍሰ ገዳይ እንደሆነና በሞት ውስጥም እንደሚኖር በ1ኛ መልእክቱ በምዕራፍ 3÷14 ጀምሮ ሲያስጠነቅቀን÷ ወንድሙን እንደ ራሱ አድርጎ የሚወድና በእውነተኛው ፍቅር የሚኖር ግን በእግዚአብሔር እንደሚኖርና እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር እንደሆነ በዚሁ መልእክት በምዕራፍ 4÷16 ገልጸልናል።

ይኸውም የጽድቅ ሥራዎች ዋና ማሠሪያ እውነተኛው ፍቅር እንደሆነ ነው የሚያስረዳን ሁሉም መልካም ሥራ ቢሠራ

www.zeyeneta.com

በእውነተኛው ፍቅር ካልታሠረ ይበተናል ያለ ፍቅር የሚሠራ ሥራ ሁሉ ዋጋ የለውም ማለት ነው።

ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ በሰውና በመላእክት አንደበት ብናገር፣ ትንቢት ቢኖረኝ፣ ሁሉንም ምሥጢር ባውቅ፣ ተራሮችን እስካፈርስ ድረስ እምነት ቢኖረኝ፣ ሥጋዬንም በእሳት እስክሚቃጠል አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም በማለት የተናገረ። 1ኛ ቆሮ ምዕ 13÷1።

እውነተኛውን ፍቅርና ርኅራኄን መሠረት በማድረግ በትሕትና ሆነው እየጸሙ እየጸለዩ እየመጸወቱ ፈጣሪአችው እግዚአብሔርን የሚማፀኑ ሰዎች ምንኛ የታደሉ ናቸው።

ምክንያቱም ከዚህ በላይ በሰፊው እንደተገለጸው ጌታችን ተራራ ተብሎ በሚታወቀው የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 5÷6 አንቀጸ ብፁዓን ትምህርቱ፥ በማይለወጥ ቅዱስ ቃሉ ተናግሮአል።

ለዚህ የታደልን ስንቶቻችን ነን?

እንጃ በዘመናችን ሌላ ገጽታ ነው እየተከሠተ ያለው፥ በዘመናችን እውነተኛው ፍቅር ርኅራኄ መተዛዘን መረዳዳት የሚባል ነገር ስለ ሌለ ዓለሙ ሁሉ እየተበላሸ፣ እየተጨነቀ ነው የሚገኘው።

ማን ያውቃል በማቴ ወንጌል ምዕራፍ 24÷1 ጀምሮ እንደተነገረን ምናልባትም የጌታችን መምጫ እየተጻረሰ፣ የዓለም መጨረሻ እየተቃረበ ሊሆን ይችላል።

ምክንያቱም ጌታችን ምልክት እንዲሆኑ በምሳሌ አድርጎ የተናገራቸው በዘመናችን እየተፈጸመ ያለውን ሁሉ አንድ በአንድ ያመለክታሉ።

ልብ ብለን ብናስተውላቸው ሁኔታዎቹን ይጠቁማሉ።

ለምሳሌ÷

ፍቅር ትቀዘቅዛለች ብሏል÷ ከጊዜያዊ ጥቅም÷ ከዓመፅ፣ ከውሸትና ከአልቧልታ የተነሣ እውነተኛይቱ ፍቅር ከእኛ እየጠፋች ናት÷ ተንኮል ቅንዓትና ምቀኝነት÷ በተለይም ሐሜት፣ ቂምና በቀል በመካከላችን ነግሦአል አብዛኛው ሰው ከአንጣቱ በላይ ነው በውሸት ፍቅር ሰላም ሰላም የሚባባለው ዞር ሲል ግን በሓሜት ይተናነካል።

ይህ ደግሞ ማታለያ ነው እንጂ እውነተኛው የእግዚአብሔር ፍቅር አይደለም።

በእኔ ስም ስለምታስተምሩ፣ እኔን ስለምትከተሉ ትናቃላችሁ፣ ትጠላላችሁ ብሏል።

የተነገረው ለጊዜው ለሐዋርያት ቢሆንም ፍጻሜው ግን በሐዋርያት እግር የሚተኩትን፣ የሐዋርያትን ሥራ የሚሠሩ ሁሉንም የክርስቶስ አገልጋዮች ሊቃውንትንና አባቶች ካህናትንም ይመለከታል።

በመሆኑም አባቶችን፣ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን እውነተኞች ሊቃውንትንና አገልጋዮች ካህናትን የሚንቁ÷ የተለያየ የማጥላላት ክፉ ስምንም እያወጡ፣ እያዋረዱ የሚያባርሩ፣ የሚያሳድዱ <<ገበርተ እከይ>> ማለትም ክፉ አድራጊዎች÷ ነቃን፣ ሰለጠን ባዮች የሰይጣን መልእክተኞች እየተበራከቱ ናቸው።

እርስ በርስ መጠላላት አሳልፎም ለሞት መሰጣጣት ይኖራል ብሏል÷

ይህውና በዘመናችን ወገን ወገኑን ለጊዜያዊ ጥቅም ሲል ለሞት አሳልፎ ይሰጣል። በመካከላችን ፍጹም የሆነ መተማመን የለም ወገን ወገኑን ይጠረጥራዋል። ደግ፣ ታጋሽና ትሑት ሆኖ መልካሙን ሥራ ቢሠራለትም እንኳ ለምን ይሆን? በማለት በሌላ መንገድ ይመለከተዋል÷ እንደ አላዋቂ በመቍጠርም ይንቀዋል እንጂ አያከብረውም፣ በበለጠ አያቀርበውም፣ አይወደውም፣ ከልቡ ሙሉ በሙሉ አያምነውም።

ዓለም ሁሉ የጎሪጥ ነው የሚተያየው፤ ኃይለኛ ነኝ የሚል ደካማውን ለማጥቃት፣ አንዱ ሌላውን ለመጫንና ጨርሶም ለማጥፋት ይጥራል፣ ከቻለ መላውን ዓለም የበላይ ሆኖ ለመቆጣጠር ይሯሯጣል።

ስለ ሥጋዊ ጥቅም ሲል ሥጋውንና ነፍሱን ለሞት አሳልፎ የሚሰጥ ብዙ ነው። ስለ ነፍሱ የሚጨነቅ ግን በጣም ጥቂት ነው።

የአብዛኛዎችን ጸሎት ሥጋዊ ሀብትንና ምድራዊ ብልጽግናን÷ እንዲሁም ለሥጋችን ሙሉ ጤናን ስጠን የሚል ነው እንጂ በነፍሳችን ማረን ኃጢአታችንንና በደላችንን ሁሉ ይቅር ብለህ ለመንግሥተ ሰማያት አብቃን የሚል አይደለም።

ይህ ደግሞ የአረማውያን እንጂ የሕዝበ ክርስቲያን ጸሎት እንዳልሆነ ራሱ ጌታችን ነግሮናል። ማቴ 6÷31

www.zeyeneta.com

ብዙች ሃይማኖታቸውን ይለውጣሉ ብሏል÷

ሳይማሩ የሚያስተምሩ፣ በክፋትና በተንኮል የሚመራመሩ፣ ተምረው ሳያውቁ ዕድሜ ልካቸው በመደበኛ ጕባኤ የኖሩትን መምህራን በአፈ ጮሌነት እያናናቁ የሚያሰቅቁ÷ መሠረታዊ ዕውቀትና ልባዊ ትሕትና የሌላቸው አወቅን ባዮች ብልጣ ብልጦች በተለያየ ዘዴ ቀስ በቀስ ሃይማኖታችንንና ጥንታዊ ሥርዓቱን ይሸራርፋሉ።

አያሌ ወገኖቻችን ትክክለኛው እምነታቸውን በጊዜያዊ ጥቅም እየለወጡ በተለያየ ሁኔታ እየተታለሉ፣ መልካም ምግባራቸውን እየተው÷ ማንነታቸውን በሚገባ የሚያስረዳቸው የራሳቸውን ቋንቋ እየተው፣ መንፈሳዊ ባህላቸውንና ሀገራዊ ታሪካቸውንም እየረሱ፣ በሌሎች ቋንቋና ባህል እየተማረኩ ወደ ጊዜያዊና ወቅታዊ እምነት እየጐረፉ ናቸው።

ስለዚህ÷ ጌታችን አስቀድሜ ተናግሬለሁና ምልክቶቹንና ምሳሌዎቹን ተመልከቱ፣ ሁኔታዎቹን አስተውሉ፣ ማንም እንዳይስታችሁ ተጠንቀቁ። መከራውን ታግሦ ፈተናውን ያለፈ ዘለዓለማዊውን ደስታ ያገኛልና መከራውን ቻሉ፣ ታገሡ በማለት እንዳስገነዘበን÷ በነፍሳችን ዘለዓለማዊውን ሕይወት ለማግኘት በሥጋችን ጊዜያዊን መከራ መቻል፣ ችግሩን መታገሥ፣ ፈተናውንም ሁሉ ማለፍ÷ በእምነታችን መጽናት፣ ሃይማኖታችንንና መንፈሳዊ ሥርዓቱን ሁሉ መጠበቅ፣ ማስጠበቅ ይገባናል ማለት ነው።

አንድ አንድ የጽድቅ ሥራዎችን የሠራን እንደሆን ትልቁን ቁም ነገር ሠርተን የበቃን መስሎን በቂ ነው በማለት እንኩራራ ይሆናል። መልካሙን ሥራ መሥራታችን ጥሩ ነው። ነገር ግን እንጨምርበት ምክንያቱም የእግዚአብሔር መንግሥት (መንግሥተ ሰማይ) በብዙ ድካም እንጂ በቀላሉ፣ በዋዛ ፈዛዛ እንደማትገኝ በቅዱስ መጽሐፍት ተደጋግሞ ተገልጸልናል። የሐዋ ሥራ 14÷22

ጌታችን ለእኛ ሲል የተቀበለው መከራም ብዙ ነው ምንም ተወዳዳሪ የለውም።

ለዚህ የቅዱስ መጽሐፍት አንድ ምሳሌን መጥቀስ ይቻላል÷

ይኼውም÷

አንድ አባ ጳኩሚስ የተባለ መናኝ ባሕታዊ አባት እየጸለየ ፈጣሪውን እየለመነ በብዙ ድካም ሲሰግድ ላቡቱ መሬትን አራሰውና እግዚአብሔር ድካሙን አይቶ ስለተግለጸለት፣ አባ ጳኩሚስ እፎይ አንተን ፈጣሪዬን አገኛለሁ ብዬ ይኸውና እንደዚህ እደክማለሁ እንዳለውና ጌታችን ደግሞ አኔም እንጂ ለአንተ ብዬ እንደዚህ ሆኜ ተሰቀያለሁ ብሎ በዕለተ ዓርብ እንደ ተሰቀለ ሆኖ እንደታየው የቅዱስ መጽሐፋችን የትርጓሜው ታሪክ ያስረዳናል።

<<ከአባቶች ትርጓሜ የተጠቀሰ ነው>>

አዎ ጌታችን ለእኛ ሲል የተቀበለው መከራ በማንም በምን ሊለካ አይችልም፣ ሲመጣም ለባሕታዊው አባት እንደታየው በዕለተ ዓርብ እንደተሰቀለ ሆኖ (መስሎ) ነው ለወቀሳ የሚመጣ ስለሚባል በዚህ ጊዜ ማን ከፊቱ ቆሞ ጥያቄውን እንደሚመልስ እንጃ?

ለጥያቄው ትክክለኛውን መልስ ለመስጠት ከአሁኑ በመልካም ምግባር መዘጋጀት ይገባል ማለት ነው።

ጌታችን በሚቴዎስ ወንጌል እንዳስጠነቀቀን የሚመጣበት ሰዓት አይታወቅምና፣ እኛ ራሳችን ከዚህ ካለንበት ጊዜያዊ ስፍራ በሞት የምንጠራበትን ጊዜ አናውቅምና ኃጢአታችንን እየተናዘዝን ከማንኛውም የነውርና የኃጢአት ተግባር በመታቀብ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙንም እየተቀበልን ለመንግሥተ ሰማይ ዝግጁዎች ሆነን መኖር ተገቢያችን ነው። ማቴ 24÷36

አዎ ሁል ጊዜ እንደሚነገረን÷ አሁንም በእየደረጃው እንደተገለጸልን እውነተኛውን ሃይማኖታችንን ከመልካም ምግባር ጋር ይዘን የጽድቅን ሥራ ሳንሠራ ሞት የቀደመን እንደሆነ በፈጣሪአችን ፊት ቆመን በምንጠየቅበት ጊዜ ፍጹም ሕይወትን የምናገኝበት አጥጋቢ መልስ ሊኖረን ስለ ማይችል የጽድቅ ሥራ፣ መልካም ምግባር የሚባለው ጸም፣ ጸሎት፣ ርኅራኄ፣ ምጽዋት፣ ትሕትና እና እውነተኛው ፍቅር ሁል ጊዜ በመካከላችን እንዲኖር ያስፈልጋል።

የጽድቅና የርኅራኄ ባለቤት የሆነው ፈጣሪያችን ልዑል እግዚአብሔር ኃጢአታችንንና በደላችንን ሁሉ ይቅር ብሎ በሚመጣበት ጊዜ በቀኙ አቁሞ÷

<<የተባረካችሁ ናችሁና ኑ ወደ እኔ>> በማለት

የማያልፈውን ጽድቁን መንግሥተ ሰማያትን እንዲያወርሰን÷ በእምነታችን ጸንተን፣ እውነተኛውን ፍቅር መሠረት አድርገን፣

www.zeyeneta.com

በመልካም ምግባር ታንጸን፣ ሕጉን ጠብቀን፣ መመሪያውንም አክብረን፣ ትእዛዛቱን እየፈጸምን፣ እየጸምን፣ እየጸለይን፣ የተቸገሩትን ወገኖቻችን ሁሉ ባለን ዐቅም እየረዳን መኖር ይገባናል።

ኃጢኣታችንን እየተናዘዝን፥ ከማንኛውም ነውርና አሳዛኝ ተግባር ንጹሓን በመሆንም፣ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እየተቀበልን፣ መንግሥተ ሰማያት ለመውረስ፥ የጽድቅና የመንግሥተ ሰማያት ባለቤት የሆነው ሁሉም የሚቻለውን ፈጣሪአችን እግዚአብሔርን ከልባችን እያለቀስን መለመን ያስፈልገናል ማለት ነው።

<u>በተጨማሪም ከዚህ በታች ያሉትን እናስተውላቸው፥</u>

<u>1ኛ</u> በቀልና ፍርድ የእኔ ነው። <u>ዘዳግ 32÷35</u>

ይሆን ስናስተውለው እንደየሥራችን ይፈረድልናል (ይፈረድብናል) ማለት ነው።

<u>2ኛ</u> የወደደኝን እወደዋለሁ፣ ያከበረኝንም አከብረዋለሁ።

በንስሓ ወደ እኔ የተመለሰውን እጠብቀዋለሁ። <u>መጽ.መቃ. ሚልስ 7÷4</u>

<u>3ኛ</u> ዕውቀት ሳለህ ንስሓ የምትገባበት ይህ ዓለምም ሳለህ አልተዘጋጀህምና የማይረባ ፀፀት ይሆንብሃል።

ገንዘብም ሳለህ የተራበውን አላጉረሰኽውምና።
<u>መጽ.መቃ. ሚልስ 10÷16</u>

<u>4ኛ</u> በዚህ ዓለም ንስሓን ካልገባን በገሃነም የማይረባ፣ የማይጠቅም ጭንቅትንና ልቅሶን እናዘጋጃለን። <u>መጽ.መቃ. ሚልስ 10÷27</u>

<u>5ኛ</u> እንዲህ አይደለም በዚህ ዓለም እንደሠራኸው ሥራ መጠን በጎም ቢሆን፣ ክፉም ቢሆን ተነሥተህ ፍዳህን ትቀበላለህ እንጂ የምትቀር አይምሰልህ።

<u>መጽ. መቃ. ሚልስ 10÷10 ጀምሮ በሰፊው እንመልከተው።</u>

<u>6ኛ</u> ለእግዚአብሔር ብሎ መከራውን ለሚታገሥ ሰው ጠላቱን ተበቅሎ ያጠፋለታል።

ኃጢኣቱንም ያስተሰርይለታል። <u>መጽሐፈ ሲራክ 28÷1</u>

<u>7ኛ</u> ነገረ ሠሪ አንደበት ብዙ ሰዎችን አወካቸው፣

ከአንዱ ወገንም ወደ አንዱ ወገን እንዲሰደዱ አደረጋቸው።
<u>መጽ. ሲራክ28÷14</u>

<u>8ኛ</u> የሰው ልጅ (ጌታችን) ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለው ያን ጊዜም ለሁሉ እንደሥራው ያስረክበዋል
<u>ማቴ 16÷27</u>

ሁሉም እንደ እየሥራው ዋጋውን ይቀበላል ማለት ነው።

<u>9ኛ</u> በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም። <u>ማቴ 7÷20</u>

<u>10ኛ</u> እንግዲህ ሊመጣ ካለው ከዚህ ሁሉ ለማምለጥ በሰው ልጅም ፊት ለመቆም እንድትችሉ ስትጸልዩ ሁሉ ጊዜ ትጉ።
<u>ሉቃ 21÷36።</u>

<u>11ኛ</u> እነሆ በተሉ እመጣለሁ ለእያንዳንዱም እንደሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።

አልፋና ኦሜጋ፣ ፊተኛውና ኋለኛው፣ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። <u>ራዕ ዮሐ 22÷12</u>

ይህ ቅዱስ ቃል አሁን በሁሉም መዘጋጀት እንደሚገባን ነው አስቀድሞ እያስገነዘበንና እያስጠነቀቀን ያለው።

<u>ኢሳ 51÷6, ማር 13÷33, ሉቃስ 12÷39,1ኛ ተሰ 4÷13, 2ኛ ጴጥ 3÷7÷ ቀስ ብለን እንመልከታቸው።</u>

<u>ጥቅሶቹ ለአስፈላጊው ማብራሪያ እየተደረገበት እንዳሉ ከአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው።</u>

www.zeyeneta.com

ክፍል 36፦

<<ገብር ኄር የዐቢይ ጾም 6ኛ እሑድ>>

ገብር ኄር የዐቢይ ጾም 6ኛ እሑድ ሲሆን፦ ገብር ኄር ማለት ደግኛ ባሪያ፣ ታማኝ፣ አገልጋይ፣ ቅን፣ ታዛዥ ማለት ነው።

ገብር ኄር ወጥተው ወርደው እንዲያተርፉብት በጌታቸው ገንዘብ በተሰጣቸው ሰዎች ምሳሌ ትምህርት የተሰጠበት መታሰቢያ ነው።

ስለሆነም የዐቢይ ጾም 6ኛ እሑድ ሳምንቱም በዚሁ ምክንያት ገብር ኄር በመባል ይታወቃል፣ ገብር ኄር እየተባለም ይጠራል ማለት ነው። ማቴ 25፦14።

ጌታችን በዘመነ ሥጋዌው በየቦታው እየተዘዋወረ በሚያስተምርበት ጊዜ በልዩ ልዩ ምሳሌ እየመሰለ ሲያስተምር እንደነበር ከቅዳሳት መጻሕፍትና ከሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አባቶቻችን እንረዳለን።

በመሆኑም በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24፦1 ጀምሮ እንደተገለጸው ጌታችን የእርሱ መምጣትንና የዓለም ፍጻሜን ለደቀ መዛሙርቱ ለሐዋርያት በኢየሩሳሌም አጠገብ በሚገኘው ደብረ ዘይት በተባለው ቦታ በምሳሌ አድርጎ ካስረዳቸው በኋላ አያይዞም በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 25፦1 ጀምሮ እንደምንመለከተው መንግሥተ ሰማያት ሙሽራን ለመቀበል መብራት ይዘው የወጡትን አሥሩን ቆነጃጅት ትመስላለች በማለት ትምህርቱን ቀጥሏል።

ይኸውም አምስቱ ጠባባት (ልባሞች) ጠንቃቆች ሲሆኑ፦ አምስቱ ግን አብዳት (ሰነፎች) ናቸው ተብለዋል።

ምክንያቱም ልባሞች የተባሉ አምስቱ ዘይቱንም መብራቱንም ሁሉ በጥንቃቄ አዘጋጅተው የሙሽራውን መምጣት ሲጠባበቁ፤ እነዚያ ሰነፎች የተባሉ አምስቱ ግን መብራቱን ቢይዙም ማብራት የሚችሉበትን ዘይት አልያዙም ነበር።

በመሆኑም በዚህ ጊዜ ሙሽራው በድንገት መጣ ሁሉንም አሟልተው ይዘው ተዘጋጅተው ሲጠባበቁት የነበሩት እነዚህ

አምስት ልባሞች በሰዓታቸው ተገኝተዋልና ሙሽራውን በደስታ ተቀበሉት አብረውትም ወደ ሰርግ ሥፍራ በክብር ገቡ ከእርሱ ጋርም ሆኑ።

አምስቱ ሰነፎች ግን በቂ ዘይት ስለአልነበረባቸው ማብራት አልቻሉም። ልባሞችን እባካችሁ ዘይትን አበድሩን ቢልዋቸውም ለእኛና ለእናንተ አይበቃም አይሆንም ከፈለጋችሁ ከሚሸጡት ገዝታችሁ ኑ ስለ አልዋቸው ዘይትን ለመግዛት እንደሔዱ በኋላቸው ሙሽራው ገብቷልና በሙሽራው አቀባበል አልተሸኙም።

ሙሽራው ሳያዩት ገባ በሩም ተዘጋባቸው ሰዓት ስለ አሰፉ መግባት አልቻሉም ማለት ነው።

ይህ ምሳሌ ነው፦

በትርጓሜው መሠረት ሲብራራ ደግሞ፦ አምስቱ አብዳት (ሰነፎች) የሚላቸው ሃይማኖትን፣ ጸምን፣ ጸሎትን፣ ትሕትናንና ርኅራኄን ይዘው የዚህ ሁሉ ማሠሪያ የሆነውን በቅብዕ ወይም በዘይት የሚመሰለውን ዋናውን እውነተኛውን ፍቅር ያልያዙ ናቸው።

አምስቱ ጠባባት ወይም ልባሞች የሚባሉ ግን፦ ሃይማኖትን፣ ጸምን፣ ጸሎትን፣ ትሕትናንና ርኅራኄን የያዙ ሲሆኑ፦ ከዚህም ጋር የመልካም ምግባር ዋና ማሠሪያ የሆነውን በቅብዕ ወይም በዘይት የሚመሰለውን እውነተኛውን ፍቅር የተጐናፀፉ (የያዙ) ናቸው።

አብዳት (ሰነፎች) ነገ ከነገ ወዲያ እናሚለለን ሲሉ ነበር።

ይኸውም ኃጢአታችንን በሚቀጥለው ጊዜ እንናዘዛለን ቀስ ብለን ንስሓ እንጋባለን በሚቀጥለው ዓመት እንቆርባለን እያሉ ሲኖሩ ባሳሰቡት ጊዜ ሞት በድንገት መጥቶ ይወስዳቸዋልና በኃጥኣን ሥፍራ ይቀመጣሉ ማለት ነው።

አምስቱ ጠባባት ወይም ልባሞች የተባሉት ግን ሁሉንም አሟልተዋል።

አዎ ጠባባት (ልባሞች) በሃይማኖት በጸም በጸሎት በትሕትና እና በርኅራኄ ተመሥርተው፦ የዚህ ሁሉ ዋና ማሠሪያ የሆነውን በቅብዕ ወይም በዘይት የሚመሰለውን እውነተኛውን ፍቅር የያዙ፦ ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ ቅዳሴ ሥጋውንና ክቡር ደሙን

www.zeyeneta.com

እየተቀበሉ በሁሉም እየተዘጋጁ ስለኖሩ በጸድቃን ሥፍራ ይቀመጣሉ ማለት ነው።

ሙሽራው በመንፈቀ ሌሊት መጣ ብሏል።
በሙሽራ የሚመሰል ጌታችን ነው ልደቱ ጥምቀቱ ትንሣኤውና ምጽአቱ በመንፈቀ ሌሊት እንደሆነ በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንና በቅዱስ መጽሐፍ ተነግሯል።

አምስቱ አብዳት ወይም ሰነፎች ልባሞችን ዘይት አበድሩን ቢሉዋቸው አይሆንም ለሁላችንም አይበቃም በማለት መለሱላቸው።

አዎ ሕገ እግዚአብሔር፣ ትእዛዘ መጻሕፍት ለሁሉም በዕኩል በአንድ ዓይነት ነው የታደለው። ትምህርቱና ምክሩ በቤተ ክርስቲያናችን ለመላው ሕዝበ ክርስቲያን ያለ አድልዎ በአንድነት ነው የሚሰጠውና ሁሉም በተማረው፣ በትእዛዘ ቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት በየራሱ መልካሙን ሥራ ሠርቶ እንዲጸድቅ ያስፈልጋል ማለት ነው።

ይኸውም በአንዱ ሥራ አንዱ እንደማይጠቀም፣ በአንዱ ኃጢኣትም አንዱ እንደማይጎዳ የሚያስገነዝብ ሲሆን፥ እያንዳንዳችን በእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት የማመናችንን፣ በክርስቶስ ክርስቲያን የመባላችንን፣ በቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ አምላጅነት፣ በእግዚአብሔር ወዳጆች ቅዱሳን ጻድቃንና ሰማዕታት በረከትና ረድኤት የመማፀናችንን ምሥጢር በሚገባ መረዳት፣ በእውነተኛው እምነታችን መፅናት፣ ትክክለኛውን ሃይማኖታችንን ከዚህ በላይ በተደጋጋሚ እንደተጠቀሰው በመልካም ምግባር በእውነተኛው ፍቅር መግለጽ እንዳለብን ነው የሚያስገነዝበን።

አዎ ጽድቅና ኩነኔ በእጃችን ስለሆነ የሚያስኩንን ተግባር ከፈጸምን እንኩነናለን የሚያጸድቅ የጽድቅን ሥራ ከሠራን ደግሞ እንጸድቃለን ማለት ነው።

ከዚሁ እንደምንረዳው ልባሞቹ ሰነፎችን ሒዱና ከሚሸጡ ገዝታችሁ ኑ ማለታቸውም ከሥላሴ ምሕረትንና ይቅርታን የሚያሰጡ ነዳያን ስለ ሆኑ ለእነርሱ መጽውቱ ሲሉዋቸው ነው። ምጽዋት ትልቅ ዋጋ እንዳለው ጌታችንም ነግሮናል።
ማቴ. 10÷40, ማር. 9÷37
<<በአበው ትርጓሜ መሠረት ሲብራራ ነው>>
ነገር ግን ሰነፎች ዕድሉን ሳይጠቀሙበት ነገ ከነገ ወዲያ ሲሉ፥ ጸሙን፣ ጸሎቱን፣ ለትምክሕት፣ ለታይታና ለውዳሴ ከንቱ ብቻ

ይዘውት በእውነተኛው ፍቅር ሳይዘጋጁ ሞት በድንገት መጥቶ ይወስዳቸዋል፤ ሥፍራቸው በሲኦል፥ በመጨረሻም በገሃነመ እሳት ይሆናል።

አምስቱ ጠባባት ወይም ልባሞች የተባሉ ግን ሁሉንም ከእውነተኛው ፍቅር ጋር ስለያዙ መኖሪያቸው ገነት፥ በኋላም መንግሥተ ሰማያት ይሆናል ማለት ነው።

<u>ዋናው መልእክቱ</u> ሁላችንም የጌታችን ምጽአትና የዓለም መጨረሻ ሳይደርስብን፣ እንግዳው ሞት ሳይቀድመን በሁሉም መዘጋጀት እንዳለብን ነው እየመከረን ያለው።

እንደዚሁም ደግሞ ሃይማኖትን ከመልካም ምግባር፣ ንጽሐ ሥጋን ከንጽሐ ነፍስ ጋር ይዘን ሳንመካ እየጸምን፣ እየጸለይን፣ እየመጸወትን፣ በትሕትና በርኅራሄና በትዕግሥት በእውነተኛውም ፍቅር አንድ ሆነን እየተረዳዳን፥ ኃጢኣታችንን እየተናዘዝን፥ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙንም እየተቀበልን ከኖርን ሙሉውን ዝግጅት ማድረግ ማለት ይህው ነውና፥ መንግሥተ ሰማያት የእኛ መሆኗን ነው የሚያረጋግጥልን።

ስለሆነም ቅዱስ ቃሉን ልብ ብለን ልናስተውለው ይገባናል ማለት ነው።

<u>ከዚህ ቀጥሎም</u> በመግቢያው እንደተገለጸው ጌታችን ወጥተው ወርደው እንዲያተርፉበት በጌታቸው ገንዘብ በተሰጣቸው ሰዎች ምሳሌ ያስተማረበትን ምሥጢር እናስታውሳለን።

አዎ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 25÷14÷ በተመሳሳይም በሉቃስ ወንጌል 19÷12 ጀምሮ እንደምንመለከተው÷

መንግሥተ ሰማያት ወጥተው ወርደው ያተርፉበት ዘንድ ብላቴኖቹን (ባሮቹን) ጠርቶ ገንዘቡን የሰጣቸው ነጋዴን ትመስላለች ይላል።

እነዚህ አግብርት (ባሮች) ወይም ደግሞ ብላቴኖች እየተባሉ የሚጠሩ ሰዎች ነግደው፣ ሠርተው እንዲያተርፉበት እንደየዐቅማቸው ታይቶ ለአንዱ አምስት፣ ለአንዱ ሁለት፣ ለአንዱም አንድ የተሰጣቸው ናቸው።

(<u>የሉቃስ ወንጌል 19÷12 አሥር ቢልም ምሥጢሩ አንድ ነው</u>)

www.zeyeneta.com

አምስት የተቀበለ ወጥቶ ወርዶ ነግዶ ሌላ አምስትን አትርፎ ተገኘ። ሁለት የተቀበለም እንደዚሁ ወጥቶ ወርዶ ነግዶ ሌላ ሁለትን አትርፎ ተገኘ።

ባለ አንድ ግን የጌታውን ገንዘብ በጨርቅ ጠቅልሎ መሬት ቆፍሮ አኖረው።

ከጊዜም በኋላ ባለ ገንዘቡ ንብረቱ ውጤት ማስገኘቱን ለማወቅ ሊቆጣጠራቸው መጣ። ገንዘቡ በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ጠየቀ።

አምስት የተቀበለው አምስት ሰጥተኸኝ ነበር ሌላውን አምስት አተረፍሁበት ብሎ ዋናውንና ትርፉን ይዞ ወደ ጌታው ቀረበ። ጌታውም አንተ መልካም ታማኝ ቸር አገልጋይ (ባሪያ) ነህ፥ በጥቂት ታምነሃልና በብዙ ላይ እሾምሃለሁ ወደ ጌታህ ደስታም ግባ አለው።

ባለ ሁለቱም ልክ እንደባለ አምስቱ በጌታው የታመነና ወደ ጌታው ደስታ የሚገባ ሆነ።

ባለ አንድ ግን ወደ ጌታው ቀርቦ ጌታ ሆይ አንተ ካልዘራህበት የምታጭድ፣ ካልበተንህበትም የምትሰበስብ፣ ኃይለኛ ጨካኝ መሆንህን ስለማውቅ፥ እንዳይጠፋብኝ፣ ሌባ እንዳይሠርቀኝ፣ ወንበደ እንዳይቀማኝ፣ ቀጣፊም እንዳያታልለኝ ብሎ ፈርቼ በጨርቅ ጠቅልዬ፣ መሬት ቆፍሬ ቀብሬ አኑሬው ነበር አሁን ግን ይህውልህ ገንዘብህ ተቀበለኝ ብሎ ዋናውን ብቻ ይዞ ቀረበ

ጌታውም አንተ ክፉና ሃኬተኛ ባሪያ እኔ ካልዘራህበት የማጭድ፥ ካልበተንህበትም የምሰበስብ ኃይለኛ ጨካኝ መሆኔን ታውቃለህን? ይህንማ ካወቅህ ገንዘቤን ወዲያውኑ ልትመልስልኝ (ልትሰጠኝ) በተገባህ ነበር እኔም ወጥቶ ወርዶ ነግዶ ለሚያተርፍበት በሰጠሁትና መጥቼም ያለኝን ከትርፉ ጋር በተቀጣጠርሁት ወይም ራሴ በሠራሁበት በማለት ያለውን ነጥቃችሁ ለባለ አምስቱ ስጡት ብሎ አዘዘ። እርሱን ክፉ ሃኬተኛውን ባሪያ ግን ወደ ጨለማ ውሰዱት አለ ይላል የወንጌሉ ቃል። ማቴ 25÷14።

አም እነዚህ ባለ አምስትና ባለ ሁለት አግብርት (ብላቴኖች) ታማኞች አገልጋዮች በተሰጣቸው ገንዘብ ጠንክረው ስለ ሠሩ አትርፈው በመገኘታቸው ሲጠቀሙ፣ በጌታቸው በእምላካቸው በእግዚአብሔር ተመስግነው ወደ ገነት፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት ሲገቡ፥ ክፉው ሃኬተኛው ባሪያ ግን የጌታውን ገንዘብ ቀብሮ ያለምንም ውጤት በማስቀረቱ በተሠጠው ገንዘብ ባለመሥራቱ፣

ባገኘው ዕድል ባለመጠቀሙ ተጐዳ። በጌታው በእግዚአብሔር ተወቅሶ ወደ ሲኦል፣ ወደ ገሃነመ እሳት ሒድ ተባለ ማለት ነው።

አዎ ይህ ወቢይ ምሥጢርና ዋና መልእክቱ ሁላችንንም ይመለከታል።

ይኸውም በትርጓሜው መሠረት ሲብራራ መምህራን ካህናት ተምረው ካላስተማሩ፣ በተሰጣቸው ዕውቀት ካልሠሩበት ካላቸው መንፈሳዊ ደርጃ ወርደው በተራ ሰዎች ቦታ እንደሚሆኑ፥ ማለትም፥ በሰማይና በምድር ትልቅ መብት ያለውን የክህነት መዓርጋቸውን (ሹመታቸውን) እንደሚገፈፉ፥ ክህነታዊ ክብራቸው ቀርቶ ከተራ ሰዎች ጋር እንደሚመደቡ፣ እንደ ባለ አንዱ በጌታችን እንደሚወቀሱና ሒዱ ተብለውም ወደ ጨለማ እንደሚባረሩ፥ አስተምረው መክረው ራሳቸውን አስመስለው የሚተኩ ደግሞ እንደባለ አምስትና እንደባለ ሁለት በክብር ላይ ክብር እንደሚጨመርላቸው ወደ ገነት፣ ወደ መንግሥተ ሰማያትም እንደሚገቡ ሲያስረዳን። ምእመናንም ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ሙሉ አካልና ሀብት የጽድቅን ሥራ ካልሠሩበት፣ ካልመጸወቱ ካልጸሙ፣ ካልጸለዩ፥ በሁሉም ችግራቸው እየተረዳዱ በእውነተኛው ፍቅር አንድ ሆነው ካልኖሩ እንደ ባለአንዱ ይወቀሳሉ ሥፍራቸው በጨለማ ውስጥ ይሆናል፣ ሒዱ ተብለውም ወደ ገሃነመ እሳት ይባረራሉ ማለት ነው።

በአጠቃላይ ይህ ቃል ሁላችንም ባገኘነው ዕውቀት ካላስተማርንበት በምንችለው ዐቅም ሁሉ መልካሙን ሥራ ካልሠራን፣ እንደ እኛ መሥራት የማይችሉት ደካሞች ወገኖችን ከእግዚአብሔር በተሰጠን ሙሉ አካል ወጥተን ወርደን ካልረዳን፣ ከምናገኘው ሁሉ አሥራትንና በኩራትን ካላወጣንበት በዓለም ፍጻሜ፥ ማለትም፥ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በግርማ መንግሥቱ መጥቶ ጻድቃንን በሚቀበልበት፣ ኃጥኣንን በሚያሰናብትበት ጊዜ እንደ ባለ አንዱ ተወቅሰን እንደምንባረር ወደ መንግሥተ ሰማያትም መግባት እንደማንችል ነው አስቀድሞ እያስጠነቀቀን ያለው።

ስለሆነም በበጎች የሚመሰሉ ጻድቃን በቀኙ፣ በፍየሎች የሚመሰሉ ኃጥኣንም በግራው ቆመው የመጨረሻው ፍርድ በሚፈረድበት ሰዓት ለመንግሥተ ሰማያት እንድንበቃ፥ በእምነታችን ጸንተን፥ እየጸምን፣ እየጸለይን፣ እየመጸወትን፣ በትሕትና፥ በርኅራኄና በትዕግሥት፣ በእውነተኛው ፍቅር አንድ ሆነን እየተረዳዳን፥ ኃጢኣታችንን እየተናዘዝን፥ ቅዳሴ ሥጋውንና ክቡር ደሙንም እየተቀበልን መኖር ይገባናል ማለት ነው። <<ጌታው በቤተ ሰዎቹ ላይ የሾመው ታማኝና ልባም ባሪያ ማን ነው? ማቴ 24÷45 >>

www.zeyeneta.com

ክፍል 37፦

<<ኒቆዲሞስ የዐቢይ ጾም 7ኛ እሑድ>>

የዐቢይ ጾም 7ኛ እሑድ፣ ሳምንቱም ኒቆዲሞስ ይባላል።

ከኒቆዲሞስ ቀጥሎ ያለው ሳምንት ሆሣዕና ሲሆን፥ ከሰኞው ጀምሮም ሕማማት ይሆናል፥ ከዛም በመጨረሻው ዓርብ ስቅለት፥ በ3ኛው ቀን እሑድ ደግሞ ትንሣኤ ክርስቶስ ነው ማለት ነው።

የዐቢይ ጾሙ 7ኛ እሑድ ኒቆዲሞስ የተባለ የአይሁድ አለቃ የነበረ ፈሪሳዊ በሌሊት ወደ ጌታችን እየሔደ እየሰገደ ምሥጢረ መጻሕፍትን ሲማር መኖሩን የምናስታውስበት ዕለት ነው።

በቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል እንደምንመለከተው፥ በሀብት በዕውቀትና በሹመት የላቀ ከፈሪሳውያን ወገን የሚሆን ኒቆዲሞስ የተባለ የአይሁድ አለቃ የነበረ መምህር በሌሊት ወደ ጌታችን ሔዶ ሊቀ መምህር ሆይ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ ከአንተ በስተቀር አንተ የምታደርጋቸውን ተአምራት የሚያደርግ ከቶ ማንም የለምና አንተ ልታስተምር ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣህ እናውቃለን አለው።

ጌታችንም እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት አያይም የሚል ድንገተኛ የሆነውን ምሥጢር ነገረው። ዮሐ 3፥1።

በትርጓሜው መሠረት እንደምንገነዘበው ኒቆዲሞስ ወደ ጌታችን ሔዶ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ ከአንተ በስተቀር አንተ የምታደርጋቸውን ተአምራት የሚያደርግ ከቶ ማንም የለምና ልታስተምር ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣህ እናውቃለን ማለቱ ጌታችን ምሥጢሩን ስለገለጸለት እግዚአብሔር አብ በህልውና ከእርሱ ጋር ካለ ከአንተ በቀር እንደዚህ ያለውን አምላካዊ የሆነ ድንቅ ሥራን ሊሠራ የሚችል ከቶ ማንም የለምና አንተ ከእግዚአብሔር አብ፣ አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ ተወልደህ ልታስተምር፣ ዓለምን ልታድን እንደመጣህ እናውቃለን ሲለው፥ ፈጣሪው እግዚአብሔር በገለጸለት መሠረት አንድነቱን ሲናገር ነው ማለት ነው።

ጌታችንም <<አማን አማን እብለከ ዘኢተወልደ ዳግመ እማይ ወእመንፈስ ቅዱስ ኢይክል በዊኦ ውስተ መንግሥተ እግዚአብሔር>>

እውነት እውነት እልሃለሁ ዳግመኛ ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ፥ (ከአብራሕ መንፈስ ቅዱስ ከሚነፀነ ዮርዳኖስ) ያልተወለደ፥ ማለትም ተምሮ ተረድቶ አምኖ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም፣ በውሃ ያልተጠመቀ ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር አይገባም አለው።

<<ዘኢተወልደ ዳግመ እማይ>>

ዳግመኛ ከውሃ ያልተወለደ ብሉ እግዚአብሔር ወልድን፣

<<ወእመንፈስ ቅዱስ>>

ከመንፈስ ቅዱስ ብሉ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን፣

<<መንግሥተ እግዚአብሔር>>

መንግሥተ እግዚአብሔር ብሉም፥ እግዚአብሔር አብን፥ አስተምሮታል።

በአጠቃላይ ምሥጢረ ሥላሴንና ምሥጢረ ጥምቀትን በምሳሌ አድርጎ በሚገባ ገልጾለታል ማለት ነው።
<<ምሥጢሩ በአበው ትርጓሜ መሠረት ሲብራራ ነው>>

ከዚህ በኋላ ኒቆዲሞስ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ ሆነ ጌታችን በመስቀል በተሰቀለ ጊዜም ከዮሴፍ ጋር በመሆን በክብር ገንዞ ቀበረው።

እም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጢረ ሥላሴንና ምሥጢረ ጥምቀትን፥ ማለትም የእግዚአብሔርን አንድነትንና ሦስትነትን ተምሮ አውቆ አጸኝነቱን ተረድቶ፥ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ያልተጠመቀ ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር (መንግሥተ ሰማያት) መግባት እንደማይችል ለሁላችንም በዚሁ ምሥጢር አረጋግጦልናል ማለት ነው።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ 10፦

ሆሳዕና በአርያም፦

ሆሳዕና ማለት በግእዝ ቋንቋ በቀጥታ ሲተረጉም መድኃኒት ማለት ሲሆን፥ በሮማይክ ቋንቋም የጌታችን ስም ሆኖ አሁን አድን አሁን ርዳ ማለት እንደሆነ ይነገራል።

<<ሆሳዕና በአርያም>> ስንል፥ በሰማይ ያለ፣ ከሰማይ የወረደ (የመጣ) መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ የተመሰገነ ነው ማለታችን ነው።

አዎ ሆሳዕና፥ ፍጹም መድኃኒታችን የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ከደብረ ዘይት (ከቢታንያ) ወደ ቅድስት ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ <<ሆሳዕና በአርያም ለወልደ ዳዊት>> በሰማይ ያለ መድኃኒት የዳዊት ልጅ የእስራኤል ንጉሥ እየተባለ በደማቅ መልክ አቀባበል የተደረገበትን፣ የተመሰገነበትንና ልዩ ልዩ ተአምራትንም ያደረገበትን ምሥጢር በማስታወስ የምናከብረው ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ በዐላችን ነው።

ይህን ዐቢይ ምሥጢር ነቢዩ ዘካርያስ አስቀድሞ፥
<<አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ እጅግ ደስ ይበልሽ፥ አንቺ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ ዕልል በዪ፥ እነሆ ንጉሥሽ ጻድቅና አዳኝ ነው፤ ትሑትም ሆኖ በአህያና በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል>> ብሎ በትንቢቱ ገልጾታል። ዘካ 9፥9።

ትንቢቱና ምሳሌው በሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍትም ተዘግቦ እናገኘዋለን።

በተለይም ደግሞ በኢሳይያስ ምዕራፍ 52፥1, 60፥1 እና በመዝሙር 8፥2፥ እንዲሁም በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 12፥12 ጀምሮ እንደምንመለከተው፥ ጌታችን ከደብረ ዘይት (ከቢታንያ) ወደ ቅድስት ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ፥ ሕዝቡ፥ ማለትም አረጋውያን፣ ወጣቶችና ሕፃናት የሰሌን ዛፍ ዝንጣፊን ይዘው ሆሳዕና በአርያም እያሉ ሲቀበሉት ጽዮን (ኢየሩሳሌምም) በእግዚአብሔር ምስጋና፣ በዕልልታና በጭብጨባ ደምቃ ነበር።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከፋሲካው 6 ቀን አስቀድሞ ከሙታን ያስነሣው አልዓዛር ወደ ነበረበት ወደ ቢታንያ ሔደና በዚያው ራት ተደረገለት።

ማርያም እንተ ዕፍረት አስቆረታዊው ይሁዳ ይህ ሽቱ ተሸጦ ለነዳያን ቢመጸወት ይሻል ነበር በማለት በሁኔታው ያኮረፈበት፥ ከዚያም አልፎ ከሸያጩ ሊያገኘው ይችል የነበረው ጥቅም ስለ አልተሳካለት ተናዶ ጌታውን ለመሸጥ ምክንያት አድርጎ የተነሣሳበት፣ ዋጋው ከፍ ያለ በጣም የተወደደና የከበረ፥ ልዩና መልካም የሆነ መዓዛ ያለውን ሽቱ ጌታችንን እግሩን የቀባችበት ጊዜ ማለት ነው።

ከዚህ ራት በኋላ ጌታችን ወደ ቅድስት ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም እንደመጣ ስለ ተሰማ ሕዝቡ፥ አረጋውያንና ወጣቶች፥ ሕፃናትም ፌምር የሰሌን ዛፍ ዝንጣፊን ይዘው፥

<<ሆሳዕና በአርያም ለወልደ ዳዊት ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር ወንጉሥሙ ለእስራኤል>>

በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ በሰማይ ያለ መድኃኒት የዳዊት ልጅ፣ የእስራኤል ንጉሥ የተባረከ ነው። በማለት በደማቅ ዕልልታና በልዩ ልዩ ምስጋና ተቀበሉት።

የቢታንያ ድንጋዮችም በልሳነ ሰብእ (እንደ ሰው አፍ አውጥተው) እንዳመሰገኑት ይነገራል።

ከዚህ በላይ ከፍ ብሎ እንደ ተጠቀሰው አስቀድሞ የተነገረው ትንቢት በዚሁ ጊዜ ተፈጸመ ማለት ነው።

ጌታችን ወደ ቅድስት ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም በገባበት ሰዓት፥ ፍጹም ሕይወትን ለማግኘት ሲሉ ፈጣሪያቸውን በጸሎት እየተማፀኑ በእርሷ ተጠግተው የሚኖሩትን ሕሙማን ፈውሶ በቤተ ክርስቲያን (በቤተ መቅደሱ) ሲፈጸም የማይገባውን በማስወገድ፣ እውነተኛውን ትምህርቱን አስተምሮ፣ መመሪያውንም ሰጥቶ፣ በዘመኑ ምኩራብ በመባል የምትታወቀው ምሕረትንና ይቅርታን ከእግዚአብሔር የሚለመንባት ቤተ ክርስቲያን (ቤተ መቅደስ) ለፍጹም ሕይወት፣ ለጸሎት የመረጣት ልዩ የምስጋና ቤት መሆኗን አረጋግጧል።

በመሆኑም ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ይህን መሠረት በማድረግ ጥንታዊ ሥርዓቱን በመጽሐፋዊ ትውፊት ከአበው ተቀብላ ሃይማኖታዊ ታሪኩንና መንፈሳዊ ባህሉን ጠብቃ በአየዓመቱ በደማቅ መልክ እያከበረችው ትገኛለች።

www.zeyeneta.com

በተጨማሪም እነዚህን ጥቅሶች ቀስ ብለን እንመልከታቸው÷

1ኛ ከእግዚአብሔር እጅ የቀጣውን ጽዋ የጠጣሽ ኢየሩሳሌም ሆይ ንቂ ንቂ ቁሚ ኢሳ 51÷17

2ኛ ጽዮን ሆይ ተነሺ ተነሺ ኃይልሽን ልበሺ። ኢሳ 52÷1

3ኛ ብርሃንሽ መጥቶአልና የእግዚአብሔርም ክብር ወጥቶልሻልና ተነሺ አብሪ እነሆ ጨለማ ምድርን ድቅድቅ ጨለማም አሕዛብን ይሸፍናል። ነገር ግን በእንቺ ላይ እግዚአብሔር ይወጣል ክብሩም በእንቺ ላይ ይታያል አሕዛብም ወደ ብርሃንሽ፣ ነገሥታትም ወደ መውጫሽ ጸዳል ይመጣሉ ዓይኖችሽን እንሥተሽ በዙሪያሽ ተመልከቺ እነዚህ ሁሉ ተሰብስበው ወደ አንቺ ይመጣሉ። ኢሳ 60÷1 ጀምሮ

አም ከዚህ በላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ይህ አስቀድሞ የተነገረው ትንቢት ነው ኢየሩሳሌም ውስጥ በሆሳዕና ዕለት የተከናወነው።

4ኛ <<ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር>> በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው ይላል ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት። በመሠረታዊ ትርጓሜው ምሥጢሩ ሲተነተንም÷
ከላይ በሰፊው እንደተገለጸው የባሕርይ አባቱ እግዚአብሔር አብ አንድ አካል፣ አንድ ባሕርይ አድርጎ÷ ለተዋሕዶ የመረጥኩት በእርሱ ሀልው ሆነ ልመለክበት የወደድኩት የባሕርይ ልጄ ይህ ነው ብሎ መስክሮለት የሚመጣ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምልዓት ያለ በረድኤት የተገለጸ የባሕርይ አምላክ ነው ማለት ነው። መዝ 117÷26 <<በትርጓሜ መሠረት ሲብራራ ነው>

5ኛ በጽዮን ለሚኖር ለእግዚአብሔር ዘምሩ። መዝ 9÷11
ይህ ቅዱስ ቃል ትንቢቱ አስቀድሞ መነገሩን ነው የሚያመለክተን

6ኛ ከሕፃናትና ከሚጠቡ ልጆች ምስጋናን አዘጋጀህ።መዝ 8÷2
ይህም ጌታችን በሕፃናትና በሚጠቡ ልጆችም ጭምር እንደሚመሰገን አስቀድሞ በትንቢት መልክ መነገሩን ነው የሚጠቁመን ያለው። በዚያን ጊዜም የታሠረችውን አህያን ውርንጫም ከእርሷ ጋር ታገኛላችሁ ፈትታችሁ አምጡልኝ ማንም አንዳች ቢላችሁ ለጌታ ያስፈልጉታል በሉ ወዲያውም ይሰዳችኋል። ማቴ 21÷1,ማር 11÷1, ሉቃ 19÷28። <<ጥቅሶቹ ከአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው>>

ምዕራፍ 11÷

ሕማማት፤ ሰሙነ ሕማማት÷ (የሕማማት ሳምንት)

ክፍል 38÷

የዕለታት ምሥጢር÷

ከሰነ ፍጥረት ጀምሮ ሁሉም ዕለታት የየራሳቸው የሆነ ምሥጢር አላቸው።

እሑድ ማለት አንድ ማለት እንደሆነ ስለ ሰንበት በተዘረዘረው ክፍል በሰፊው እንደተገለጸውና እንደተብራራው÷ ሰኞ ማለት ሁለተኛ÷ ማለትም ፍጥረት በእሑድ ስለሚጀምር ሰኞ ማለት የፍጥረት ሁለተኛ ዕለት ማለት ስለሆነ÷

ማክሠኞ ማለት የፍጥረት ሦስተኛ ዕለት፣

ሮብ ማለት የፍጥረት አራተኛ ዕለት፣

ሐሙስ ማለትም የፍጥረት አምስተኛ ዕለት ማለት ሲሆን÷

ዓርብ ማለት ደግሞ የመና ወይም የፍጥረት መካተቻ (መጨረሻ) ማለት እንደሆነ የቅዳሴ መጽሐፍትን ታሪክ ያስረዳናል።

(በተራው በእሑድ የጀመረው ፍጥረት እስከ ዓርብ ድረስ በቲራው ቁጥር ቢቀጠር ግን ዓርብ ስድስተኛይቱ የፍጥረት ዕለት መሆኗነው)

ስለዚህም በአንድ ሳምንት ውስጥ የሚገኙ ዕለታት በዚሁ በመጠኑ ይገለጻሉ።

ለምሳሌም በዐጭሩ።

1ኛ በእሑድ ዕለት አስሪው ፍጥረታት (የፍጥረታት መሠረቶች) የሆኑ 4 ባሕርያት፤ ማለትም÷ ማይ፣ (ውሃ) መሬት፣ ነፋስና እሳት ተፈጥረዋል።

www.zeyenota.com

2ኛ በሰኑይ (ሰኞ) ዕለት ከምድር እስከ ሰማይ ድረስ ሞልቶ የነበረው ውሃ ከሦስት ክፍሉ በየሥራው መድቦታል።

3ኛ በሠሉስ (ማክሠኞ) ዕለት ሣርና ዕፀዋት ተፈጥረዋል።

4ኛ በረቡዕ (ሮብ) ዕለት ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ተፈጥረዋል።

5ኛ በሐሙስ ዕለት በልባቸው የሚሳቡ፣ በዕግራቸው የሚሽከረከሩ፣ በክንፋቸው የሚበሩ በደመ ነፍስ ሕያዋን ሆነው የሚኖሩ ፍጥረታት ተፈጥረዋል።

6ኛ በዓርብ ዕለት በኩረ ፍጥረታት (የፍጥረታት በኽር የሚባለው አዳም ተፈጥሯል) ዓርብ የፍጥረት መጨረሻ ናት። ከዚህ በኋላ አልፈጠረም።

ስለሆነም÷

7ኛ ቅዳሜ ጌታችን ፍጥረቱን ሁሉ ፈጥሮ ደምድሞ ዕረፍቱን ያደረገባት የዕረፍት ቀን ናት ማለት ነው።
(አሪት ዘፍጥረት ከምዕ 1÷1 ጀምሮና መጽ. ኩፋሌ 2÷1 ጀምሮ በሰፊው እንመልከት)

<<ከአበው የዓርብ ውዳሴ ማርያም ትርጓሜም የተጠቀሰ ነው>>

ሰሙነ ሕማማት በቤተ ክርስቲያናችን ልዩ ትኩረት የሚሰጥባት ሳምንት ናት።

ሰሙነ ሕማማት (የሕማማት ሳምንት) ከዚህ በስተመጨረሻ የተጠቀሱት የቅዳሳት መጻሕፍት መግለጫዎች እንደሚያስረዱን÷

ሰኞና ማክሠኞ አይሁድ ጌታችንን ለመያዝ የመከሩባቸው ቀናት ሲሆኑ÷

ሮብ ደግሞ እንዴት አድርገው እንደሚይዙት ምክራቸው ተሳክቶላቸዋልና። ሐሙስ እንዳይዙት ፋሲካቸው በመሆኑ ከሕዝብ ሁከት እንዳይነሣባቸው ፈርተው÷ በበዐላቸው ምክንያት ሐሙስን አሳልፈው÷ ዓርብ ዕለት በመክሩትና በወሰኑት መሠረት

በአስቆሮታዊው በይሁዳ አማካይነት ይዘውት የተለያየውን ግፍ ሲፈጽሙበት ከዋሉ በኋላ በመጨረሻው ጊዜ ሰቀሉት።
ዮሐ 11÷46, 19÷17, ሉቃ 23÷26

ሰሙነ ሕማማት በቤተ ክርስቲያን እየተሸን ምንም በደል ሳይኖረው ስለ እኛ ስለ በደለኞች ሲል የተቀበለውን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ፀዋትው መከራ እያሰብን ስለ ስርየተ ኃጢኣት የምንጸልይባትና የምንሰግድባት ሳምንት ስትሆን በተለይም ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ከጸሎተ ሐሙስ በፊት ያሉትን ሦስቱን ቀናት÷ ማለትም ሰኞን፣ ማክሠኞንና ሮብን የ5500 ዘመን÷ የፍዳን፣ የመርገምንና የጨለማን ምሳሌ አድርጋ እንደምትቆጥራቸው ይገለጻል።

አሥ ሰሙነ ሕማማት ሰሙኑን ሙሉ በቤተ ክርስቲያን እየተሸን ጌታችን ምንም በደል ሳይኖረው ስለ እኛ ሲል የተቀበለውን ልዩ ልዩ ፀዋትው መከራን እያሰብን በጸም፣ በጸሎት፣ በስግደት፣ በ·ነዘንና በልቅሶ ልናሳልፋት የሚገባን ልዩ የሆነች የሱባኤ ሳምንት ናት።

ክፍል 39÷

ሐሙስ፣ ጸሎተ ሐሙስ÷ (የሐሙስ ጸሎት)

ጸሎተ ሐሙስ ጌታችን የጸለየባት፣ የሰገደባት÷ የሐዋርያትን እግር በማጠብ ትሕትናን በተግባር ያስተማረባት ዕለት ስትሆን÷ በተለይም ደግሞ የሐዲሱን ምሥጢረ ቍርባን ለሐዋርያት ያሳየባት÷ ይህ ሥጋዬ ነው ይህም ደሜ ነው ብሎ ሥጋውን በስንዴ፣ ደሙንም በወይን አድርጎ ይህን ያልበላ፣ ይህንንም ያልጠጣ ሕይወት የለውም በማለት ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን የሰጠባት÷ ሐዲስ ምሥጢርም የተገለጸባት ዕለት ናት።

(ጸሎተ ሐሙስ ማለት የሐሙስ ጸሎት ማለት ሲሆን ምሥጢሩም ከላይ የተገለጸው ነው)

ጥቅስ <<ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን (ዳቦውን) አንሥቶ ባረከ፣ አከበረ፣ ለወጠ÷ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና÷ ነገ በመልዕልተ መስቀል የሚሰዋው ሥጋዬ ይህ ነው እንካችሁ ብሉ አለ። ጽዋውንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ ሁላችሁ ከርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ለኃጢኣት ይቅርታ የሚፈስ የሐዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው>> (ማቴ 26÷26)

www.zeyeneta.com

አዎ ጌታችን በጸሎተ ሐሙስ፥ ማለትም በስቅለቱ ዋዜማ ጎብስቱንና ወይኑን ባርኮ፣ ቀድሶ፣ ፈትቶ፥ እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው። ሁላችሁም ከእርሱ ጠጡ። ይህ ስለ ብዙዎች የኃጢኣት ስርየት የሚፈስ የሐዲስ ኪዳን ደሜ ነው ብሉ ለደቀ መዛሙርቱ ለሐዋርያት ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ሰጥቶአቸዋል። የሐዲስ ኪዳን ምሥጢረ ቍርባንንና ሥርዓቱንም ሁሉ አሳይቶአቸዋል።

በተጨማሪም እነዚህን ጥቅሶች እንመልከታቸው፥

1ኛ ኢየሱስ (ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ እግዚአብሔር ወልድ ማለት ነው)፥ አብ (የባሕርይ አባቱ እግዚአብሔር አብ ማለት ነው) ሁሉን በእጁ እንደ ሰጠው ከእግዚአብሔርም እንደ ወጣ ወደ እግዚአብሔርም እንዲሔድ አውቆ ከራት ተነሣ ልብሱንም አኖረ። ማበሻም ጨርቅ ወስዶ ታጠቀ በኋላም በመታጠቢያው ውሃ ጨመረ የደቀ መዛሙርትንም እግር ሊያጥብና በታጠቀበት ማበሻ ጨርቅ ሊያብስ ጀመረ። (አዎ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትሕትናን በተግባር አስተማረ) ዮሐ 13፥3።

2ኛ በሩ እኔ ነኝ፣ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፣ ይገባልም፣ ይወጣልም። ዮሐ 10፥9

(ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገባል <<ይጸድቃል>> ማለት ነው)።

3ኛ የሕይወት ምግብ (እንጀራ) እኔ ነኝ፥ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፣ በእኔ የሚያምንም ለዘለዓለም አይጠማም። ዮሐ 6፥35

(ጌታችን ስለ ብዙ ሰዎች የሚፈስ የሐዲስ ኪዳን ሥርዓት ደሜ ይህ ነው ንሡ አላቸው) ማር 14፥22, 1ኛ ቆሮ 11፥23 ጀምሮ

4ኛ ጌታችን በአይሁድ ከመያዙ በፊት እንደጸለየና ትጉ ጸልዩም እንዳለ በማቴ 26፥36, በተመሳሳይም በማር 14፥32, በሉቃ 22፥39 እና በዮሐ 17፥1 እናገኘዋለን።

በመሆኑም ትምህርቱ ሁላችንንም ስለሚመለከት ተግተን መጸለይ ይገባናል ማለት ነው።

ክፍል 40፥

በሰሙነ ሕማማት ውስጥ ዓርብ ስቅለት፥

ዓርብ ማለት ከላይ እንደተጠቀሰው የፍጥረት መካተቻ (መደምደሚያ) ማለት ነው።
ምክንያቱም ጌታችን እስከ ዓርብ ድረስ ፍጥረቱን ሲፈጥር ሰንብቶ ዓርብ ፍጥረቱን ሁሉ ፈጥሮ ስለ ደመደመ የፍጥረት መካተቻ ወይም መደምደሚያ ትባላለች።

እንዲሁም ሕዝበ እስራኤል እስከ ዓርብ ድረስ መና እየዘነመላቸው ሲለቅሙ ሰንብተው በዓርብ ስለሚጨርሱ፣ ዓርብ የቅዳሜንም ጭምር ደርበው ስለሚከቱ (ስለ ሚሰበስቡ) የመና መካተቻም እየተባለች ትጠራለች ማለት ነው።
<<ከአበው ትርጓሜ የዓርብ ውዳሴ ማርያም>>

ዓርብ፥ ዓርብ ስቅለት መባሏም ጌታችን የተሰቀለባት ቀን ስለ ሆነች ነው።

ሰሙነ ሕማማት፥ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው አይሁድ ጌታችንን ለመያዝ ሰኞና ማክሠኞ ተሰብስበው መክረው ባይሳካላቸውም ሮብ ምክራቸው ስለ ተሳካ ሐሙስ የፋሲካ በዐላቸውን አክብረው ዓርብ መጋቢት 27 ቀን በአስቆሪታዊው በይሁዳ አማካይነት ይዘውት አስረው ወስደው ከዘመኑ ገዥ ከጲላጦስ ፊት አቅርበው ካስገረፉት በኋላ በግፍ ስለ ሰቀሉት ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን በገዛ ሥልጣኑ ቅድስት ነፍሱን ከክቡር ሥጋው ለይቶ፣ መለኮት በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ፣ አስቀድሞ ለአዳም በሰጠው የድኅነት ተስፋ መሠረት ከአዳም ጀምሮ እስከ ዚያች ቀን ድረስ በሲኦል ውስጥ ተግዘው የነበሩትን ነፍሳት አውጥቶ ወደ ገነት አስገባቸው።

አዎ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ፥ ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጥኣት ምክንያት ሞቶአልና፥ በሥጋ ሞተ ባመንፈስ ግን ሕያው ሆነ። በእርሱም ደግሞ ሔዶ በወኅኒ ለነበሩት ነፍሳት ነጻነትን ሰበከላቸው እንዳለው። 1ኛ ጴጥ 3፥18
ጌታችን ወደ እርሱ ሊያቀርበን፣ ከራሱ ጋር ሊያስታርቀን ስለወደደ በለበሰው ሥጋ በፈቃዱ ሞቶ ለእኛ ግን ፍጹም ሕይወትን ሰጠን።

www.zeyeneta.com

በዕለተ ዓርብ ጌታችን በተሰቀለ ጊዜ ብዙ ተአምራትም ተደርጓል።

ለምሳሌ÷ ምድር ተናውጣለች፣ ፀሐይ ጨልሞአል፣ ጨረቃ ደም ሆኖአል፣ ከዋክብት እንደ ቅጠል ረግፈዋል፣ አዕባን (ድንጋዮች) ተፈትተዋል (ደቅቀዋል) የምኩራቡ (የቤተ ጸሎቱ) መጋረጃም ከላይ እንሥቶ እስከ ታች ድረስ ከሁለት ተሰንጥቋል (ተከፍሎአል) መቃብራት ተከፍተዋል፣ ሙታንም ተነሥተዋል። ማቴ 27÷51, ማር 15÷37።

ክፍል 41÷

የዓርብ ስቅለት ጥብጣቤ፣ የንስሓውና የስግደቱ ምሥጢር÷

የዕለተ ዓርብ ጥብጣቤ ከላይ በሰፊው እንደተገለጸው ጌታችን ለእኛ ሲል ስለ ተገረፈ ግርፋቱን በማስታወስ÷ በሥጋችን መከራን ችለን ታግሠን ፈተናውን ካለፍን ፍጹም ሕይወትን እንደምናገኝ የሚያመለክት ሲሆን÷ ንስሓውና ስግደቱም አሁን እንደተነገረው ከምሥጢሩ ጋር የተያያዘ ሆኖ÷ በውስጡ ሁሳችንም ንስሓን እየገባን፣ እየሰገድን ከኃጢኣት ከበደል ሁሉ ንጹሓን መሆን እንደሚገባን የሚያስገነዝበን ትምህርታዊ መልእክት ያለበት ነው።

ዓርብ ከጥንት÷ አዳም የተፈጠረባት፣ ከገነትም የወጣባት ስትሆን÷ በሐዲስ ዘመን በአሁኑ ደግሞ ጌታችን የተሰቀለባት÷ በመጨረሻም ፍጹም ሕይወትን የሰጠባት፣ ነፍሳትን ከሲኦል ወደ ገነት ያስገባባት፣ እኛን ያዳነባት፣ ሞትና ሕይወት የታየባት፣ ሌሊትና ቀን (ጨለማና ብርሃን) የተፈራረቀባት÷ በነቢያት የተነገረው፣ በልዩ ልዩ ቅዱሳት መጻሕፍት የተዘገበው ትንቢት የተፈጸመባት በመሆኗ በቤተ ክርስቲያናችን ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ታሪክ ለየት ያለ ሥፍራ አላት።

ሕዝበ እስራኤል በመልአኩ በቅዱስ ሚካኤል ተራዳኢነትና መሪነት፣ በነቢዩ ሙሴ አስተባባሪነት ከግብፅ ክፉ እገዛዝ ነጻ ወጥተው የኤርትራን ባሕር በተሻገሩ ጊዜ የጠላታቸውን ሰጥመትንና የእግዚአብሔርን ድንቅ የሆነ አምላካዊ ሥራ ተመልክተው የተመሰገነውን እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን

በማለት ከጠላታቸው ያዳናቸውን፣ የኤርትራን ባሕር ከሁለት ከፍሎ በሰላም ያሻገራቸውን ፈጣሪያቸው እግዚአብሔርን እንዳመሰገኑት። ዘፀ 15÷1, መዝ 135÷10

እኛ የክርስቶስ ወገኖች ሕዝበ ክርስቲያንም በቅዳሳት መጻሕፍት እና በሃይማኖታዊ ትውፊት (ቅብብሎሽ) በተረከብነው መንፈሳዊ ሥርዓት መሠረት÷ በየዓመቱ ዓርብ ስቅለት በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን እየተገኘን ጌታችን ምንም በደል ሳይኖረው ስለእኛ ስለበደለኞች ሲል የተቀበለውን ልዩ ልዩ ፀዋትወ መከራ እያሰብን÷ ስለ ኃጢኣታችን ስርየት እየሰገድን ውለን ሠርክ ሲሆን ደግሞ ድኅነታችንን በማስታወስ ባሕረ አሳት ያሻገረንን፣ ከዲያብሎስ የባርነት ግዛት ነጻ ያወጣንን፣ ከሞተ ኃጢኣት ያዳነን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን÷

<<ንሴብሐ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ>>

የተመሰገነውን እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን በማለት ይህን ያደረገልን አምላካችንን በከበሮና በጸናጽል ስናመሰግን እንኖራለን።

አም አስቀድሞ በትንቢት ተነግሮ፣ በቅዳሳት መጻሕፍት በየክፍሉ ተዘግቦ እንደምናገኘው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአዳም በሰጠው የማይሻር የሕይወት ተስፋ መሠረት ዘመኑ ሲደርስ እንደ እኛ አቆጣጠር በ5500 ዓመተ ዓለም ፍጻሜ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በ5533 ዓመተ ዓለም (በ33 ዓመተ ምሕረት) በዘመነ ቅዳስ ማርቆስ መጋቢት 27 ቀን በመስቀል ተሰቅሎ ዓለምን አዳነ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ከጽኑዕ ፍቅሩ የተነሣ ጌታችንን ሞትስ አይገባህም እንዳለው እኛም ጌታችን ባይሞት እንወድ ነበር።

ነገር ግን ምንም እንኳን ሞት የማይገባው የባሕርይ አምላክ ቢሆንም እርሱ ሞቶ ካላዳነን እኛ ሁላችን ፍጹም ሕይወት ሊኖረን ስለማይችል÷ ለፍጹም ሕይወታችን ሲል በፈቃዱ በለበሰው ሥጋ ሞቶ ፍጹም የሆነውን ሕይወት ሰጠን።
ማቴ 16÷21

አዎ ሰው ምንም እንኳን በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል የተፈጠረ ልዩ ክቡር ፍጥረት ቢሆንም÷ አስቸጋሪና ደካማ የሆነ ባሕርይ ያለበት እንደመሆኑ መጠን÷ የፈጣሪውን ሕግንና

www.zeyeneta.com

መመሪያን ባለማክበሩ ምክንያት በኃጢኣት ስለ ወደቀ በፍጥረቱ የማይጨክንን የምሕረትና የይቅርታ አምላክ፣ ልዑል እግዚአብሔር ሞቶ አዳነው።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ለሰው ልጆች ፍጹም ሕይወትን አደለ ለመላ ዓለምም ፍጹም ሰላምን ሰጠ።

እኛስ ሰላሙን በአግባቡ እንቀበለዋለንን? ያ ሁሉ ችግር የመጣው ሕግን ካለማክበር፣ መመሪያንም ካለመጠበቅ፣ የታዘዘውን ካለመፈጸም የተነሣ መሆኑን በሚገባ እንረዳለንን? የሥጋችን ተገዥዎች ብቻ ነው የምንሆነውን? ወይስ በቅዱስ መንፈስ እንመራለንን?

እም ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክት እንደምንረዳው፥ እንደ ቅዱስ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ ብቻ መኖር እንደማይገባን ታዘናል። ሮሜ ምዕ 8፥3።

በተለይም በገላትያ መልእክቱ <<በመንፈስ ተመላለሱ የሥጋንም ሥሮች ከቶ አትፈጽሙ ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና እነዚህ እርስ በእርሳቸው ይቀዋወማሉ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም፣ የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው።

እርሱም፥ ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣዖትን ማምለክ፣ ሟርት፣ ጥል፣ ክርክር፣ ቅንዓት፣ ቁጣ አድመኛነት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ ዘፋኝነት፣ ይህንም የሚመስል ነው አስቀድሜም እንዳልሁ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።

የመንፈስ ፍሬ ግን፥ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት ነው>>። ተብሉ ተነግሮናልና ልብ ብለን ልንሰማው፣ ልናስተውለውና የተማርነውን ቅዱስ ቃል በተግባር ላይ ልናውለው ይገባናል። ገላ 5፥ከ16

እም ሥጋ ደካማ ነው፥ ሥጋዊ መንፈስ ቀለዋዋጭ ነው፣ ሥጋዊ መንፈስ በቃኝን አያውቅም፣ ሥጋ የሥጋን ፍላጎት ብቻ ይመኛል ቅዱስ መንፈስ ግን ጠንካራ ስለሆነ የመንፈስን ፍላጎት ይመኛል።

አሁን እንዳየነው ሥጋ ኃላፊውን ጊዜያዊውን ጥቅም ሲመኝ፥ ቅዱስ የሆነ መንፈስ ግን የማያልፈውን የዘለዓለም ሕይወት ይመኛል ማለት ነው።

ስለሆነም የዘለዓለም ሕይወት እንደሚገኝበት እንደመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ እንጂ እንደ ኃላፊው፣ እንደ ጠፊው፣ ጊዜያዊውን ጥቅም እንደሚመኘው እንደ ሥጋዊ መንፈስ እንደ ሥጋ ፈቃድ መኖር አይገባንም።

ቅዱስ ቃሉ አሁን እንዳስጠነቀቀን፥ ራሳችንን በመግዛት ሰውነታችንን መቈጣጠር፣ ከስግብግብነትም መታገሥ ያስፈልገናል።

ምክንያቱም በገላትያ ምዕ 4፥ከቊጥር 1 ጀምሮም እንደተነገረን፥ የሥጋ ፈቃድ ብቻ ተገዥዎች ከሆን ነፃ አልወጣንም፣ አሁንም ገና ነን፣ እዚያው ከባርነት ቦታ ነው ያለነው።

የሥጋ ፍላጎት ብቻ ታዛዦች ከሆን የዓለም ባሮች የርኩሰት ተገዦች እየሆን ነን ማለት ነው።

በዚሁ መልእክት፥ ማለትም በገላ ምዕ 5፥ከ1 ጀምሮ <<በነፃነት ልንኖር ክርስቶስነፃ አወጣን እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ>> ተብሉ እንደ ተገለፀልን፥ ጌታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በመስቀል ተሰቅሎ ነጻ አውጥቶናልና ከእግዚህ በኋላ የኃላፊው፣ የሥጋዊው ፍላጎት ብቻ ታዛዦች፣ የሰይጣን ባሮች፣ የዲያብሎስ ተገዦች መሆን የለብንም።

አሁንም በቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ኤፌ 2፥11፥ እንደምንረዳው እኛ ራሳችን ባመጣነው ችግር ምክንያት ከፈጣሪያችን ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልተን፣ ተስፋ ቆርጠን፣ ከአምላካችን ተለይተን ስንኖር፣ ፈጣሪያችን ግን በመካከላችን የነበረውን የጥል ግድግዳ አፍርሶ ፍጹም የሆነውን ሰላም አሥፍኖልናልና በፍጹም ልባችን ወደ እርሱ መቅረብ ይገባናል።

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሰላምን፣ ፍጹም ሕይወትንና ፍጹም ነጻነትን ሰጠ እንጂ፥ በሰዎች ላይ ጥርጥርን፣ መለያየትን፣ ብጥብጥን፣ ጠብንና ጭንቀትን አላመጣም።
ዮሐ 12፥44 ጀምሮ

ስለሆነም የተሰጠንን ዕድልና መንፈሳዊ መብት በአግባቡ ልንጠቀምበት ተገቢያችን ነው ራሱ ጌታችን እንደነገረን በእውነት ወደ እርሱ ከቀረብን ችግራችንና ጭንቀታችን ሁሉ ይወገዳል፥ ከእርሱ ሩቆች፣ ከሕጉም ውጭ ከሆን ግን በከንቱ እንቀራለን፥ (በከንቱ እንጠፋለን) ማለት ነው።

www.zeyeneta.com

ከእንግዲህ በኋላ እኛ ራሳችን በክፉ ተግባራችን እንደገና ካልገነባነው በስተቀር ቀድሞ የነበረው መርገምና የውርስ ኃጢአት በክርስቶስ መስቀል ተደምሷል፣ ሽክማችን ቀልሏል፣ በክርስቶስ ቤት መልካም የሆነ ማረፊያ ተዘጋጅቶልናል። ማቴ 11÷29

በተጨማሪም ከዚህ ቀጥለው ያሉትን ጥቅሶች እንመልከታቸው÷

1ኛ <<እግዚአብሔርስ ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ ዓለም>> እግዚአብሔርስ ከዓለም (ከፍጥረት ሁሉ) አስቀድሞ ንጉሥ ነው፣ በምድርም መካከል መድኃኒትን አደረገ። መዝ 73÷12። ይህ ቅዱስ ቃል እግዚአብሔር ምንም እንኳን እኛን ለማዳን ሲል በለበሰው ሥጋ መራራውን ሞት ቢቀምስም በመለኮቱ ግን የማይሞት ሕያው የባሕርይ አምላክ÷ የነበረ፣ ያለ፣ ፍጥረታትን ሁሉ አሳልፎ የሚኖር ፈጣሪ መሆኑን ነው የሚገልጽልን።

2ኛ በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ፣ ሕማማችንንም ተሸከመ..... ስለ በደላችንም ደቀቀ፣.....የደኅንነታችንም ተግሣፅ በእርሱ ላይ ነበረ፣ በእርሱ ቍስል እኛ ተፈወስን፣ የሁላችንንም በደል በእርሱ ላይ አኖረ። ኢሳ 53÷4

3ኛ <<የተጠራችሁት ለዚህ ነውና ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌን ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሏልና እርሱ ኃጢአትን አላደረገም፣ ተንኮልም በአፉ አልተገኘበትም። ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም፣ መከራንም ሲቀበል አልዛተም። ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ። ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ በመገረፉ ቍስል ተፈወሳችሁ>> 1ኛ ጴጥ 2÷21 ጀምሮ ይህ ቅዱስ ቃል ጌታችን ስለ እኛ ሲል የተቀበለውን ፀዋትወ መከራን፣ ትዕግሥቱንና ትሕትናውን በመግለጽ እኛም የእርሱን መልካም ሥራ እንድንከተል ነው እያስተማረን ያለው።

4ኛ <<በክርስቶስ እንዳች ምክር ቢሆን፣ የፍቅር መጽናናት ቢሆን፣ የመንፈስ ኅብረት ቢሆን፣ ምሕረትና ርኅራኄም ቢሆኑ÷ ደስታዬን ፈጽሙልኝ በአንድ አሳብም ተስማሙ>> ፊልጵ 2÷1 ጀምሮ ይህም ጌታችን ያ ሁሉ ፀዋትወ መከራ የተቀበለውና የተሰቀለውምንም ልዩነትን ሳያደርግ ለመላ ዓለም እንደ

መሆኑ መጠን፣ እኛ ሁላችንም በክርስቶስ አንድ ክርስቲያን ሆነን በእውነተኛው ፍቅር ተስማምተን እየተረዳዳን እንድንኖር ነው እየመከረን ያለው ይኸውም ትሕትናን፣ ርኅራኄንና እውነተኛውን ፍቅር ገንዘብ አድርገን በጽድቁ መኖር እንደሚገባን÷ በክርስቶስ ነፃ ስለወጣን ተመልሰን ወደ ኃጢአት ባርነት፣ ወደ ዲያብሎስ ክፉ አገዛዝ እንዳንገባ ብርቱ ጥንቃቄን ማድረግ እንዳለብን ነው የሚያስገነዝበን።

<<ጥቅሶቹ ከልዩ ልዩ ክፍል የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው>>

እንዲሁም ማቴ 27÷1 ጀምሮ, በተመሳሳይም ማር 14÷1ጀምሮ,ሉቃ 22÷1 ጀምሮ እና ዮሐ 17÷1 ጀምሮም ቀስ ብለን እንመልከት÷

ይህን ላደረገልን ለእግዚአብሔር አምላካችን ምስጋና ይድረሰው።

ምዕራፍ 12÷

ቅዳሜ ሥውር÷

ቅዳሜ ሥውር ማለት÷ ቅዳሜና እሑድ የማይጸሙ ሲሆኑ÷ በጌታችን ስቅለት ማግሥት ቅዳሜ ግን ጌታችን በክርሠ መቃብር በማደሩ ምክንያት ቀዳሚት (ቅዳሜ) በአክፍሎት እንድትጾም በቤተ ክርስቲያናችን የጾም ሥርዓት ፍትሕ መንፈሳዊ ስለታዘዘ ትጾማለችና የቅዳሜ ሥውርነት ለመጾሚ ነው።

ዋናው ምሥጢሩ ደግሞ ቅዳሜ ሥውር ማለት በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተዘገበው÷ <<ሠዓሮ ለሞት>> ይላል በግእዙ ሲጠቀስ ጌታችን ሞተ ኃጢአትንና ዲያብሎስን ሽሮ ፍዳንና መርገምን ሁሉ ደምስሶ ፍጹም የሆነውን ሕይወት ስለሰጠን ይህን ያንፀባርቃል።

በቅዳሜ ሥውር ለሁሉም ለምለም ቄጤማ (ሣር) እየታደለ የምሥራች ይባላል።

www.zeyeneta.com

ይኸውም፡

<<ግብረ ሰላመ በመስቀሉ>> ይላል በግእዙ ሲጠቀስ

ጌታችን ከ5500 ዘመናት በላይ በዲያብሎስ ባርነት፣ በክፉ አገዛዝ ተይዘው በሲኦል በጨለማ ውስጥ ታሥረው የነበሩትን ሁሉ ወደ ግነት አስገባቸው። በመስቀሉ ዓለምን ሁሉ ሰላም አደረገ።

ለፍጥረቱ ሁሉ ፍጹም ድኅነትንና ፍጹም ነጻነትን ሰጠ።

<< የምሥራች ደስ ይበላችሁ>> ማለት ነው።

የምሥራቹም በለመለመ ቄጤማ (ሣር) አማካይነት ይካሔዳል። ምክንያቱም ልምላሜ ያለው ቄጤማ (ሣር) እንዲሁም ቅጠል የደስታ መግለጫ እንደሆነ በቅዱሳት መጻሕፍት በብዙ ክፍል ይገኛል።

ለምሳሌ፡ በዘሌዋውያን ብንመለከት፡ እግዚአብሔር ሙሴንና ሕዝበ እስራኤልን በየዓመቱ በለመለመው የዛፍ ቅርንጫፍ አማካይነት መንፈሳዊ የሆነውን የምስጋና እና የደስታ በዐል እንዲያደርጉ አዟቸዋል። ዘሌዋ 23፡39

በግእዙ ሲጠቀስ፡

<<ነሥአ አብርሃም አዕፁቀ በቀልት ሰብሐ ወዘመረ በዕለተ ሰንበት>>

የአማርኛ ትርጉሙም፡ አብሃም የሰሌን ዛፍ ዝንጣፊን ይዞ በሰንበት ቀን ፈጣሪው እግዚአብሔርን አመሰገነ ማለት ነው።

ቅዱስ ያሬድም በጣዕመ ዜማው አመሥጥሮታል።

<<ድጓው ከሆሳዕና እዝል የተጠቀሰ ነው>>

አም እነአብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብም የምስጋናንና የደስታን

በዐል በሚያደርጉበት ጊዜ ቁፅለ ልምላሜን መያዝ ያዘወትሩ እንደነበር ይታወቃል።

ከዚህ በላይ ከፍ ብሎ በቦታው (በሆሳዕና) እንደተገለጸው ጌታችን ወደ ቅድስት ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም እንደመጣ በተሰማ ጊዜም ሕዝቡ፡ አረጋውያንና ወጣቶች፡ ሕፃናትም ሞምር የሰሌን ዛፍ ዝንጣፊን ይዘው፡ <<ሆሳዕና በአርያም ለወልደ ዳዊት ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር ወንጉሥሙ ለእስራኤል>> በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ በሰማይ ያለ መድኃኒት የዳዊት ልጅ፣ የእስራኤል ንጉሥ የተባረከ ነው በማለት በደማቅ ዕልልታና በልዩ ልዩ ምስጋና ተቀብለውታል። ኢሳ 52፡1, 60፡1,መዝ 8፡2፡ እንዲሁም ዮሐ 12፡12 ጀምሮ እንመልከት

በተለይም ደግሞ በዘፍጥረት እንደምንመለከተው፡ በማየ አይኅ፡ ማለትም በኖኅ ዘመን የጥፋት ውሃ ዓለምን በሙሉ ሣጥለቀለቀው ጊዜ ውሃው በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ እንድታረጋግጥ ከመርከቡ ውስጥ በኖኅ የተላከችው በመንፈስ ቅዱስ የምትመሰለው ርግብ የጥፋት ውሃ መጉደሉን አረጋግጣ፡ ለምልክት ከለመለመ ሣር (ከቄጤማው) በጥርሷ ይዛ ወደላካት ወደ ኖኅ ተመልሳ የጥፋት ውሃ ጉደለ ደረቀ ብላ እንዳበሠረችው እንመለከታለን። ዘፍጥ 8፡6።

አም ከዚህ በላይ እንደተረዳነው በመንፈስ ቅዱስ የምትመሰለው ርግብ የጥፋት ውሃ መጉደሉን አረጋግጣ የጥፋት ውሃ ጉደለ፣ ደረቀ ብላ ለኖኅ እንዳበሠረችው። ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ደግሞ ይህንን ምሳሌ መሠረት በማድረግ፡ በግእዙ ሲጠቀስ <<ተሥዕረ ሞተ ኃጢኣት>> ይላል የኃጢኣት ሞት በክርስቶስ መስቀል ተሻረ፣ የጥፋትና የመርገም ማዕበል ጸጥ አለ፣ የፍዳና የኮነኔ ባሕር ደረቀ፡ ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ ከ5500 ዘመናት በላይ በዲያብሎስ ባርነት በክፉ አገዛዝ ተይዘው በሲኦል በጨለማ ውስጥ ታሥረው የነበሩትን ሁሉ ወደ ግነት አስገባቸው። በመስቀሉ ዓለምን ሁሉ ሰላም አደረገ፡ ለፍጥረቱ ሁሉ ፍጹም ድኅነትንና ፍጹም ነጻነትን ሰጠ፡ የምሥራች ደስ ይበላችሁ እያለች የለመለመውን ሣሩን፡ (ቄጤማውን) እያደለች ሕዝበ ክርስቲያኗን የሕይወት ምሥራችን እያበሠረች ትገኛለች።

ይህን ያደረገልን እግዚአብሔር አምላካችን ይመስገን።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ 13፦

ትንሣኤ (ፋሲካ) ትንሣኤ ክርስቶስ፦

ግእዝ፦ << ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን በዐቢይ ኃይል ወሥልጣን ዓሠሮ ለሰይጣን አግአዞ ለአዳም ሰላም እምይእዜሰ ይኩን (ኮነ) ፍሥሓ ወሰላም>>

አማርኛ ትርጉሙ፦ ክርስቶስ በታላቅ ኃይልና ሥልጣን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፣ ሰይጣንን ሻረው (በመስቀሉ ድል አደረገው)፣ አዳምን ነጻ አወጣው፣ ከእንግዲህ ወዲህማ ሰላም ይሁን፣ ከእንግዲህ ወዲህ ፍጹም ሰላም ሆነ ማለት ነው።

ትንሣኤ ክርስቶስ ወይም ፋሲካ ስንል፦ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ ዓለምን ያዳነበትንና በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ የተነሣበትን በማሰብ ከሌሎች ዐበይት በዐላት ለየት ባለ መልኩ የምናከብረው ዐቢይ በዐላችን ማለታችን ነው።

ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት የዘመረው ምስባክ በግእዝ ቋንቋ ሲጠቀስ፦

<<ወተንሥአ እግዚአብሔር ከመ ዘንቃሕ እምንዋም
ወከመ ኃያል ወጎዳግ ወይን
ወቀተለ ፀሮ በድኅሬሁ>> ይላል።

ትርጉሙም፦ እግዚአብሔር ከዕንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ፦ የወይን ስካር እንደተወው እንደ ኃያልም ሰው፦ ጠላቶቹንም በኋላቸው መታቸው። ይላልና፦ ጌታችን ሞትን ድል አድርጎ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቷል። መዝ 77፦65።

በመሠረታዊ ትርጓሜው ምሥጢሩ ሲተነተንም፦
ትንቢቱ፦ እግዚአብሔር ከሰባ ዘመን በኋላ በረድኤት ተነሣ፣ እስራኤልን ጠላቶቻቸውን አጥፍቶ ከክፉ የባርነት ግዛት ነጻ አወጣቸው ማለት ሲሆን፦

ፍጻሜው ደግሞ፦

እግዚአብሔር መግነዝ ፍቱልኝ፣ መቃብርንም ከፈቱልኝ ሳይል በመስቀል ተሰቅሎ በሞተ በሦስተኛው ቀን ልክ ከዕንቅልፉ እንደሚነሣ ሰው ከሙታን ተለይቶ ተነሣ።

የወይን ስካር እንደተወው እንደ ኃያል ሰውም ሆነ።

የአዳምንና የሔዋንን፤ የሁላችንንም ጠላት የሆነውን ዲያብሎስን በመስቀሉ ድል አደረገ። መርገማችንን ሻረ፣ ዕዳችንንም ደመሰሰ፤ ዓለምንና የዓለምን ፍጥረት ሁሉ ነጻ አወጣ ማለት ነው።

በተጨማሪም ማቴ 28፦1, ማር 16፦1, ሉቃ 24፦1, ዮሐ 20፦11, 1ኛ ቆሮ15፦20 እና 1ኛ ጴጥ 1፦1 እንመልከት።

አጋ ነቢይ ዳዊት በ117፦24 መዝሙሩም፦
በግእዙ፦ <<ዛቲ ዕለት እንተ ገብረ እግዚአብሔር>>
እግዚአብሔር የሠራት ቀን ይህች ናት፣ ሐሤትን እናድርግባት፣ በእርሷም ደስ ይበለን ብሏል። (ዕለተ ሰንበትን ነው)
ይኸውም ይህች ዕለተ ሰንበት እግዚአብሔር አምላካችን ከሙታን ተለይቶ የተነሣባት፣ ልዩ ልዩ ተአምራቱንም ያደረገባት ናትና በእርሷ ፈጽሞ ደስ ይበለን፦ የነፍስ ዕረፍት የመንፈስ ደስታ እናድርግባት ማለት ነው።

ፋሲካ ማለት ከግእዝ ወደ አማርኛ ቋንቋ በቀጥታ ሲተረጉም ደስታ ማለት ሲሆን፦ በአይሁድ ዘንድ ከጥንት ጀምሮ የተለመደ የነጻነት፣ የክብርና የደስታ በዐል እንደሆነ ይታወቃል። ሙሉ ምሥጢሩ በዓርብ ስቅለት ክፍል ገጽ 128 ስለተገለጸ ከዚያው እንመልከት።

በዐለ ፋሲካ (የፋሲካ በዐል) ስንልም፦ ጌታችን በመስቀል ተሰቅሎ መላውን ፍጥረቱ በማዳን ከሙታን ተለይቶ የተናሣባት ዕለት ስለሆነች መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በልዩ ልዩ ዝማሬ እያመሰገን የምናከብረው፦ ድኅነታችንና መንፈሳዊ ደስታችንን የምንገልጽበት በዐል፦ ሕዝበ እስራኤል የኤርትራን ባሕር በሰላም የተሻገሩባትን ዕለት በማስታወስ በዐላቸውን እንደሚያከብሩ ሁሉ፦

እኛም ከሞተ ኃጢአት ወደ ፍጹም ሕይወት የተሻገርንበትን በማሰብ፣ ይህን ያደረገልንን ፈጣሪአችንን በማመስገን የምናንጸባርቀው ልዩ የሆነ የምስጋና እና የመንፈሳዊ ደስታ በዐላችን ማለታችን ነው።

www.zeyeneta.com

ስለ ሕዝበ እስራኤል የኤርትራን ባሕር በሰላም መሻገርና ነጻ መውጣት፣ ዘፀ 15÷1,12÷11, መዝ 135÷10፣ ስለ ፋሲካ በዐልም ማቴ 26÷1,ማር 14÷1, ሉቃ 22÷1, ዮሐ 12÷1, 13÷1 እንመልከት።

ትንሣኤ ደግሞ ተንሥአ ተነሣ ከሚል የግእዝ ግስ የሚገኝ ጥሬ ዘር ሆኖ÷ ቀጥተኛ ትርጕሙ ከተቀመጡበት ይሁን ከዕንቅልፍ ነቃ ብሎ መነሣት÷ በተለይም ደግሞ ከሞት ሕያው ሆኖ መነሣት፣ ከመቃብርም መውጣት ማለት ነው።

ትንሣኤን÷ የሞት ሁኔታንና ስለ ጽድቅና ኃጢኣት፣ ጻድቅንና ኃጥእንም÷ በመጥቀስ በሦስት ክፍል መድበን እንመለከተዋለን÷

ይኸውም÷

ሀ የፈጣሪ (የጌታችን) ሞትና ትንሣኤ÷

ለ የፍጡራን ሞትና ትንሣኤ÷

ሐ የሕያዋን ሞትና ትንሣኤ በማለት ነው።

ክፍል 42÷

ሀ የጌታችን ሞትና ትንሣኤ÷

የፈጣሪአችን፣ የጌታችን፣ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ከፍጡራን ሞትና ትንሣኤ የተለየ ዐቢይ ምሥጢር ያለበት ነው።

የሰው (የፍጡር) ሞት ሳይወድ በተፈጥሮአዊ ግዴታ በፈጣሪው ትእዛዝ የሚመጣ ሲሆን ቢሞትም መለኮታዊ አምላክ ሆኖ በራሱ ኃይልና ሥልጣን ሌላውን ፍጥረት ሊያድን አይችልም።

የጌታችን ሞት ግን በፈቃዱ ነው።

<<ሐመ በፈቃዱ ወተቀብረ በሥምረቱ ከመ ኪያነ ይርዳእ ወይቤዝወነ ወልድ ተንሥአ>>

ሊቁ ቅዳስ ያሬድ ቅዳስ መጽሐፉን መሠረት አድርጎ እኛን ለማዳን ሲል በፈቃዱ ታሞ ሞተ፣ በፈቃዱም ተቀበረ÷ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ በማለት በጣዕመ ዜማው በልዩ ልዩ ክፍል እንዳመሠጠረው÷ ጌታችን ፍጥረቱን ለማዳን ሲል በፈቃዱ በለበሰው ሥጋ በፈቃዱ ተሰቅሎ ሞተ፣ ሞቱም ለፍጹም ሕይወት ነው። (ይህ ድጓ ሚያዝያ 24 ከጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እስመ ለዓለምም ይገኛል)

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም በመልእክቱ እንደነገረን በእርሱ መቀኖል የእኛ ቀኖል ተፈወሰ በእርሱም ሞት እኛ ዳን። እርሱ ተሰቅሎ ሞቶ ባያድነን ኑሮ ግን ሁላችንም ፍጥረቱ ለዘለዓለም ሕይወትን አናገኝም ነበርና ሞቱ ሕይወታችን ነው ማለት ነው። 1ኛ ጴጥ 2÷24

(አዎ የጌታችን ሞት ለሕይወት ነው)

በመስቀል ተሰቅሎ በሞተ በሦስተኛው ቀንም ሞትን አሸንፎ፣ መግነዙን ፍቱልኝ÷ መቃብሩንም ክፈቱልኝ ሳይል ከዕንቅልፍ እንደሚነቃ፣ የወይን ስካር እንደተወው እንደ ኃያል ሰው÷ ከሙታን በመለየት በገዛ ሥልጣኑ ብድግ ብሎ ተነሣ።

በትንሣኤውም ዓለምን አበራ÷ በትንሣኤው ሙታንን አነሣ÷ በትንሣኤው ልዩ ልዩ ተአምራትንም አደረገ፣ ፍጹም የሆነውንም ሕይወት ሰበከልን።

(አዎ የጌታችን፣ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ከፍጡራን ትንሣኤ የተለየ ዐቢይ ምሥጢር ያለበት ነው)

ፍጡር ቢበቃም (ጻድቅም ቢሆን) በፈጣሪው በእግዚአብሔር ፈቃድ በተሰጠው ቃለ ኪዳን (ቃል ኪዳን) መሠረት የተወሰነውን ተአምራት ያደርጋል እንጂ መለኮታዊ አምላክ ሆኖ በራሱ ፈቃድና ውሳኔ አምላካዊ ሥራን ሊሠራ አይችልም።

ፍጡር ሲሞት በፈጣሪው ውሳኔ ይሞታል፣ ሲነሣም በእግዚአብሔር ኃይል ይነሣል እንጂ እንደ ፈጣሪ በራሱ ፈቃድና ሥልጣን ሊነሣ ከቶ አይችልም።

ጌታችን ግን የባሕርይ አምላክ፣ የፍጥረታት ሁሉ ባለቤት ሁሉንም ማድረግ የሚችል እንደ መሆኑ መጠን በራሱ መልካም ፈቃድ ሞቶ በራሱ መልካም ፈቃድ ተነሣ፣ ዓለምን ሁሉ አዳነ÷ ልዩ ልዩ አምላካዊ ሥራውንም ሠራ።

www.zeyeneta.com

አም በማር 16÷12, በሉቃስ 24÷36 እና በዮሐ 20÷19 ጀምሮ በተመሳሳይ ተዘግቦ እንደምናገኘው ጌታችን ደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያት በእርሱ ላይ እየደረሰ የነበረውን መከራ አይተው እኛንም እርሱን ያገኘ መከራ ያገኘናል ብለው ፈርተው ተደብቀው ወደ ነበሩበት ቤት ገብቶ÷ ቤቱ እንደተዘጋ በሩ እንደተቆለፈ በመካከላቸው ተገኝቶ ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው በችንካር የተቸነከሩትን እጆቹንና በጦር የተወጋውንም ጐኑን አሳያቸው። ዓለምን ሁሉ ዙረው እንዲያስተምሩ አዘዛቸው።

ደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያትም ከጌታችን ኃይልንና ጽናትን አግኝተው እንደበፊቱ ምንም ሳይፈሩ በጌታቸው በታዘዙት መሠረት እምላካዊ ሥራውን÷ መከራውን÷ ልዩ ልዩ ተአምራቱንና ንጹሕ የሆነውን ትምህርቱን ሁሉ ለመላው ዓለም አስተማሩ።

በመጨረሻም የጌታቸውን መከራ መስቀል ተሸክመው÷ ዓሠሩን በመከተል፣ በእምነታቸው ጸንተው፣ ሃይማኖታቸውን አስፋፍተው÷ ችግሩን፣ ፈተናውንና ተጋድሎውን ታግሠው ችለው÷ ዓለምንና የዓለምን ጣጣ ሁሉ በማሸነፍ በልዩ ልዩ መከራ በመንፈሳዊ ክብር አለፉ፣ ዓረፉ።

አርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም ይህን ምንም ያልተቀላቀለበትን ንጹሑ የክርስቶስ ትምህርት ከሐዋርያት አንሥቶ በሃይማኖታዊ ትውፊት (ቅብብሎሽ) ከአበው ተቀብላ አንድን ነገር ሳትቀላቅል ሕዝበ ክርስቲያኗን እያስተማረች ትገኛለች።

ይህ ከዚህ በላይ የተገለጸው የፈጣሪ (የጌታችን) ትንሣኤን የሚመለክት ሲሆን÷ ከዚህ ቀጥሎም <u>የፍጡራን ሞትና ትንሣኤ ይገለጻል።</u>

ክፍል 43÷

ሀ የፍጡራን ሞትና ትንሣኤ÷

ፍጡር (ሰው) ፈጣሪው እግዚአብሔር እስከ ወሰነለት ዘመን ድረስ በዚሁ ጊዜያዊና ወቅታዊ በሆነ ዓለም ቢቆይም ባላወቀውና ባልጠበቀው ሰዓት ሳይወድ በግድ በፈጣሪው በእግዚአብሔር ፈቃድ በተለያየ ምክንያት በሞት ይጠራል።
<u>በጳውሎስ መልእክት 1ኛ ቆሮ ምዕራፍ 15÷22 እና ቊጥር 37፣</u> እንዲሁም በ1ኛ ተሰሎንቄ ምዕራፍ 4÷13 ጀምሮ በሰፊው

እንደተገለጸው÷ በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረ ሰው ከሞተ በኋላም በጌታችን ምጽአት (በዓለም ፍጻሜ) ጊዜ ከሌሎች ፍጥረታት ተለይቶ በመነሣት እንደየሥራው የመጨረሻውን ፍርድ ከፈጣሪው ይቀበላል። እስከዚያም ጻድቃን በገነት፣ ኃጥኣን ግን በሲኦል ይቆያሉ። ሁለቱ ገነት እና ሲኦል የማቆያ ሥፍራ ናቸው ማለት ነው።

አም ገነት ማለት ለጻድቃን የተዘጋጀ ልዩ የሆነ መልካም ቦታ ሲሆን÷ ሲኦል ማለት ደግሞ ለኃጥኣን የተወሰነ የድቅድቅ ጨለማ ሥፍራ ነው። <u>ዮሐ 5÷28, 2ኛ ቆሮ 5÷10</u>

በመሆኑም ሕያዊት÷ ነባቢትና ለባዊት የሆነችው ነፍስ ስለማትሞት የመጨረሻ ፍርድ እስኪሰጥ ድረስ የጻድቃን ነፍስ በገነት፣ የኃጥኣን ነፍስም በሲኦል መቆየት ግዴታ ነው።

መንግሥተ ሰማያት እና ገሃነመ እሳት ግን እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ዝግ ሲሆኑ÷ ከመጨረሻው ፍርድ በኋላ ደግሞ ሁለቱ መንግሥተ ሰማያት እና ገሃነመ እሳት ተከፍተው ጻድቃን ከፈጣሪኣቸው የመጨረሻውን ፍርድ ተቀብለው ኑ ወደ እኔ ተብለው ወደ ዘለዓለማዊ ደስታ ወደ መንግሥተ ሰማይ ይገባሉ።

ኃጥኣን ደግሞ የመጨረሻውን ፍርድ ተቀብለው ወደ ዘለዓለም ሥቃይ፣ ወደ ዘለዓለም ልቅሶ ወደ ገሃነመ እሳት ሒዱ ይባላሉ።

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው የቅዱስ መጽሐፍ መልእክት እንደምንረዳው ጻድቃንና ኃጥኣን በአንድ ጐድጓድ ውስጥ ቢቀበሩም እንኳ በሕይወተ ሥጋ እያሉ የሠሩትን የየራሳቸውን ሥራ (ግብር) ይዘው በመነሣት የመጨረሻውን ፍርድ ለመቀበል ወደ ፈጣሪኣቸው ይቀርባሉ እንጂ ጻድቅ የኃጥኡን፣ ኃጥእም የጻድቁን ሥራ ከቶ አይወስድም።

ይኸውም በአንድ እርሻ በሚዘራ ሁሉት ዓይነት እህል እንደሚመሰል ተነግሮኣል።

<u>ምሳሌውም÷</u> ሥንደና ኑግ ተቀላቅሉ በአንድ እርሻ ቢዘራ÷ ሥንደ ሥንደውን፣ ኑግም ኑጉን ያፈራል እንጂ÷ ሥንደ ኑጉን፣ ኑጉም ሥንደውን አያፈራም ተብሏል።

ስለዚህ ሁሉም በሕይወተ ሥጋ እያለ በሠራው መሠረት እንደየሥራው ይቀበላል ማለት ነውና አሁን በሕይወተ ሥጋ እያሉ መልካሙን ሥራ መሥራት ያስፈልጋል።

www.zeyeneta.com

እንግዲህ የፋሲካና የትንሣኤ ቀጥተኛ ትርጉምና ምሥጢሩ እንደት እንደሆነ፥ እንደዚሁም የፍጡራንና የፈጣሪ ትንሣኤ ምንን እንደሚመስል ለመግለጽ ተሞክሯል።

በተጨማሪም 1ኛ ቆሮ 15፥22 እና ከቊጥር 37፣ እንዲሁም 1ኛ ተሰሎ 4፥13 ጀምሮ ሌሎችንም ቅዱሳት መጻሕፍትን በሰፊው እንመልከት፥

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የእኛ የሕያዋን ትንሣኤ ምንን እንደሚመስል እንመለከተዋለን፥

ሳንሞት እንነሣለን እንዴ ብንልም መልሱን በዚሁ እናገኘዋለን።

ከዚያ በፊት ግን የሚጠቀሱ ያሉት ተግባራት ሁሉ ጻድቅና ኃጥእ፥ (ጻድቃንና ኃጥኣን) በሚባሉ ሰዎች የሚከናወኑ በመሆናቸው ስለ ጽድቅና ኃጢኣት፣ ስለ ጻድቅና ኃጥእ፥ እንዲሁም በብዛት ስለ ጻድቃንና ኃጥኣን በዐጭሩ እናብራራለን።

ክፍል 44፥

ጽድቅና ኃጢኣት፣ ጻድቅና ኃጥእ፥

ለመሆኑ ጽድቅና ኃጢኣት ማለት ምን ማለት ነው?

ጽድቅ በቀጥታ ሲተረጉም እውነት ማለት ሲሆን፥ ጻድቃን ስንልም ለብዙ ሰዎች እውነተኞች ማለታችን ነው።

ጻድቅ ማለት እውነተኛ፣ የማይዋሽ፣ የእውነት ባለቤት የሆነው የእግዚአብሔር ወገን ማለት ነው።

ምክንያቱም በእግዚአብሔር ዘንድ ውሸት ስለሌለ እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰውም እግዚአብሔርን ስለ ሚፈራ፣ በፍጹም ልቡ እግዚአብሔርን ስለሚያመልክ፣ እግዚአብሔርን ስለሚወድ ፈጽሞ አይዋሽም።

እንዲሁም ጻድቅ ማለት በዚሁ ምሥጢር ሲብራራ የጸደቀ ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር (ወደ መንግሥተ ሰማይ) የሚገባ ማለት ነው።

ኃጢኣት ማለት ደግሞ በቀጥታ ሲተረጉም ሚጣት፣ ያጣ ማለት ሲሆን፥ ኃጥኣን ስንልም ለብዙ ሰዎች ያጡ፣ ኃጢኣተኞች ማለታችን ነው።

ምሥጢራዊ ትርጉሙም መንግሥተ እግዚአብሔርን (መንግሥተ ሰማያትን) ማጣት፣ ያጣ፣ ያጡ ማለት ነው።

ስለዚህም ትንሣኤ በሌላ መልኩ ሲተነተን ከዚህ በላይ በተገለጹት በጻድቃንና በኃጥኣን የሚከናወን ድርጊት ያለበት፥ የልብ፣ የሐሳብና የሥራ ትንሣኤ በሚል መንገድ ይገለጻል።

ክፍል 45፥

ሐ የእኛ የሕያዋን ሞትና ትንሣኤ፥

አም በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠረ ሰው በልቡ አስቦ ተነሥቶ በዕግሩ ተንቀሳቅሶ ሔዶ የተለያየ ዓላማ ያላቸውን ሁለት ዓይነት ሥራዎች ሊሠራ ይችላል።

ይኸውም፥

1ኛ የኃጢኣት ተገዥ የዲያብሎስ ወገን የሆነ ክፉ ሰው በልቡ አስቦ ተነሣስቶ በእግሩ ተንቀሳቅሶ ሔዶ ይዋሻል፣ ክፉውን ነገር በመሥራት ሰዎችን ያጣላል፣ አባትንና ልጅን፣ እናትንና ልጅን ወንድምንና ወንድምን፣ እኅትንና እኅትን፣ ወንድምንና እኅትን ያጋጫል። በባለትዳሮችና በሚዋደዱት ሰዎች መካከል እየገባ ያለያያል፥ ከሃይማኖታዊ መልካም ምግባር ውጭ የሆነውን ሰይጣናዊ ሥራ ይሠራል። ክፉ ሰው በልቡ አስቦ ተነሥቶ በእግሩ ተንቀሳቅሶ ገሥግሦ ሔዶ በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠረውን ክቡሩን ሰው ገድሉ ንብረቱን ይዘርፋል።

በአጠቃላይ እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያሳዝን ሰይጣናዊውን ተግባር ይፈጽማል።

ይህ ተግባር የኃጢኣት ተግባር ነው።

www.zeyeneta.com

ይህ ሥራ የኃጢኣት ባለቤት የሆነው የሠይጣን ሥራ ነው።
ይህንን ተግባር የሚፈጽም ሰው ኃጥእ (ኃጢኣተኛ) ይባላል።
ኃጥእ (ኃጢኣተኛ) ማለትም ማጣት፣ ያጣ ማለት ነው።
ምንን ያጣ ማለት ነው ብንልም?
መንግሥተ እግዚአብሔርን (መንግሥተ ሰማያትን) ያጣ ማለት ነው።

ይህንን ተግባር የሚፈጽም ሰው የሰይጣን ወገን ነው።
የሰይጣን ወገን የሆነ ሰው በመጨረሻው የፍርድ ቀን
ወደ ወገኑ ወደ ሰይጣን (ወደ ዲያብሎስ) ነው የሚሔደው።
የሰይጣን ሥፍራ ደግሞ ገሃነመ እሳት ነው።

2ኛ የታደለው የክርስቶስ ተከታይ፣ የእግዚአብሔር ወገን
የሆነው ሰው ግን በልቡ አስቦ፣ ከተቀመጠበት፣ ወይም ከተኛበት
ሥፍራ÷

**<<በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ
አምላክ>> በማለት በእግዚአብሔር ስም ተነሥቶ÷**

በእግሩ ተንቀሳቅሶ በመገሥገስ የእግዚአብሔር መመስገኛ ወደ
ሆነችው ለስርየተ ኃጢኣት ለመላው ዓለም ሰላም ሲል በቀራንዮ
የተሰቀለው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ
ሥጋና ክቡር ደም ወደሚፈተትባት ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን
ሔዶ፣ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሆኖ እግዚአብሔር ያደረገለትን
በጎ ነገር ሁሉ እያሰበ ፈጣሪውን ያመሰግናል።

እውነተኛ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሰው÷ ጌታችን
ስለ እኛ ፍጹም ሕይወት ሲል የተቀበለውን ልዩ ልዩ ፀዋትወ
መከራ በልቡ እየተመለከተ እያለቀሰ ስለ ኃጢኣቱ ስርየት
ይጸልያል÷ ለበደሉ፣ ለጥፋቱ ይቅርታን ከፈጣሪው ይለምናል።

እውነተኛ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሰው÷ ገነትን
መንግሥተ ሰማያትን ያወርሰው ዘንድ ፈጣሪውን በጸሎትና
በምስጋና ይማፀናል።

እውነተኛ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሰው÷ የጽድቅ
ዋና ማሰሪያ እውነተኛው ፍቅር ስለ ሆነ ራሱ ከሁሉም ጋር
እየተፋቀረ ሌላውም ሰው ሁሉ እርስበርሱ እንዲፋቀር ከፍተኛውን
ጥረት ያደርጋል።

እውነተኛ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሰው÷ በተለያየ
ምክንያት የተጣሉትን ያስታርቃል፣ የተራራቁትን ያቀራርባል
በሰዎች መካከል የሚታየውን መለያየት በማስወገድ በሁሉም ዘንድ
እውነተኛ አንድነት እንዲኖር ያደርጋል።

እውነተኛ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሰው÷
የታሠረውንና የታመመውን ይጠይቃል የተቸገረውንም ባለው
ዐቅም ሁሉ ይረዳል። በተለያየ ምክንያት ከእውነተኛው ሃይማኖቱ
ወጥቶ በሌሎች አዳዲስ እምነቶች አካባቢ የሚደናገረውን ሰው
እያስተማረ፣ እየመከረ ወደ ጥንታዊት ሃይማኖቱ ይመልሳል።

እውነተኛ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሰው÷ በፍቅረ
ንዋይ (ገንዘብን በመውደድ)፣ በጊዜያዊና በኃላፊ ጥቅም
የሚሳሳተውን ይመክራል÷ ለጊዜያዊና ለኃላፊ ጥቅም ሲል ወገኑን
የሚጎዳውን÷ በሐሜት፣ በተንኮል፣ በቅንዓት፣ በምቀኝነትና
በመሳሰለው የጥፋት ጉዳና የሚሔደውን ሁሉ እያስተማረ፣
እየመከረ ወደ ጽድቅ ጉዳና ይመራል።

በአጠቃላይ እውነተኛ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሰው÷
ሁሉም የሚጠቀምበትን መልካሙን ሥራ ይሠራል።
እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያስደስተውን በልቡ እያሰበ
ያከናውናል።

ይህስ የምን ሥራ ነው? ብንል
መልሱ የጽድቅ ሥራ ነው።

ይህ ሥራ የጽድቅ ባለቤት የሆነው የእግዚአብሔር (የክርስቶስ)
ሥራ ነው።

በክርስቶስ ክርስቲያን ተብሎ በተሰየመበት መሠረት ክርስቶስን
እየተከተለ፣ የእግዚአብሔር ሕግንና መመሪያን እየጠበቀ፣
ትእዛዛቱንም እየፈጸመ የሚኖር÷ መልካሙን የጽድቅ ሥራ
የሚሠራ ሰው ደግሞ ጻድቅ ይባላል። ጻድቅ ሰው ከራሱ አልፎ
ሌሎችንም ይጠቅማል በጸሎቱም ብዙ ሥራን ሊሠራ ይችላል።

ለዚህም ከቅዱስ መጽሐፍችን ውስጥ ማስረጃ አለን÷
ሰምሳሌ ከያዕቆብ መልእክት ብንመለከት።

<<እርስበርሳችሁ በኃጢኣት ተናዘዙ÷ ትፈወሱም ዘንድ
እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ
እጅግ ኃይልን ታደርጋለችና ይላል>> ያዕ 5÷16።

www.zeyeneta.com

አም ጻድቅ ሰው ከራሱ አልፎ ለሌላውም ሊያማልድ ይችላል ማለት ነው። ታዲያ እንደዚህ ያለ ጻድቅ ሰው በመጨረሻው የፍርድ ቀንስ ወይት ይሔዳል? ያልን እንደሆን፥ መልሱ ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር (ወደ እግዚአብሔር መንግሥት) ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት ማለት ማን ናት? ብንልም መልሱ መንግሥተ ሰማይ ነው።

ስለዚህ ጻድቃን ተብለን ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመግባት እንድንችል የጽድቅን ሥራ መሥራት አለብን ማለት ነው።

አም ቅዱስ ጳውሎስ ከዕንቅልፍ የምትነሡበት ሰዓት አሁን እንደደረሰ ዘመኑን እወቁ፣ ካመንበት ጊዜ ይልቅ መዳናችን ዛሬ ወደ እኛ ቀርቦአልና፥ ሌሊቱ አልፎአል ቀኑም ቀርቦአል፥ እንግዲህ የጨለማውን ሥራ አውጥተን የብርሃንን ጋሻ ጦር እንልበስ በማለት እንዳስተማረን። ሮሜ 13÷11

ጌታችን በመስቀል ተሰቅሎ አድኖናልና፥ በትንሣኤውም ፍጹም የሆነውን ብርሃኑን ሰጥቶናልና፥ መርገሙ፣ ፍዳው፣ ጨለማው ሁሉ አልፎአል።

በመሆኑም ይህን ያደረገልን አምላካችንን በልዩ ልዩ ዝማሬ እያመሰገን፣ በሰጠን የትንሣኤ ብርሃን ልንመላለስ ይገባናል። ትንሣኤ ክርስቶስ (ፋሲካ) የፈጣሪአችንን ፀዋትዉ መከራ፣ ሞቱንና ትንሣኤውን፣ ቸርነቱንም ሁሉ እያስታወስን የምናከብረው ከሌሎች ዐበይት በዐላት የተለየ ክብርና መንፈሳዊ ታሪክ ያለበት፥ የጉዞዎች ሁሉ ዋና መዳረሻ፣ የሕይወት ተስፋዎች ሁሉ ማጠቃለያ የሆነ ልዩ በዐላችን ነው።

በተጨማሪም ከዚህ ቀጥለው ያሉትን ጥቅሶች እንመልከታቸው፥

1ኛ እውነት እውነት እላችኋለሁ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል.....በመቃብር ያሉትም ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፣ መልካም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ፣ ክፉውም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ። ዮሐ 5÷25 ጀምሮ።

2ኛ መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናል። 2ኛ ቆሮ 5÷10

3ኛ ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል። (ይድናል) ዮሐ 11÷25

<<ጥቅሶቹ ከአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው>>

የጽድቅና የርኅራኄ ባለቤት እግዚአብሔር አምላካችን ይህን በፍጡር ሊለካና ሊገለጽ የማይቻል ቸርነቱን ሁሉ ስለ አደረገልን ለዘለዓለም የተመሰገነ ይሁን፥

በዐሉን የሰላም፣ የአንድነት፣ የፍቅርና የፍጹም ደስታ በዐል ያድርግልን

አሜን።

ምዕራፍ 14።

ዕርገተ ክርስቶስ፥

የዕለቱ ምስባክ በግእዙ፥

<<ዐርገ እግዚአብሔር በይባቤ÷
ወእግዚእነ በቃለ ቀርን÷
ዘምሩ ለአምላክነ ዘምሩ>>

በአማርኛው ኒጠላ ትርጉሙ ሲገለጽ÷

እግዚአብሔር በመለከት ድምፅ ዐረገ፣ ዘምሩ ለአምላካችን ዘምሩ፥ እግዚአብሔር ለምድር ሁሉ ንጉሥ ነውና በማስተዋል ዘምሩ ይላል።

በትርጓሜው መሠረት ተብራርቶ ሲነገር ደግሞ÷

ጌታችን ከትንሣኤው በኋላ 40 ቀን ለደቀ መዛሙርቱ ለሐዋርያት መጽሐፈ ኪዳንን፣ ሥርዓተ ሃይማኖትንና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ሁሉ ሲያስተምራቸው ሰንብቶ በተነሣ በዓርባኛው ቀኑ በይባቤ መላእክት በቅዳሴ መላእክት÷ (በመላእክት ምስጋና)

www.zeyeneta.com

ወደሰ ማይ ዐረገ፤ (ወጣ) በአብ ቀኝ ተቀመጠ፥ ለእርሱ ምስጋና አቅርቡ ማለት ነው። (መዝ 46፥5)

አም በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 24፥44 ጀምሮ እንደምንመለከተው፥

ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ ለሐዋርያት ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት፥ እንዲሁም በመዝሙራት ስለ እኔ የተነገረው፤ የተጻፈውም ሊፈጸም ይገበዋል ብዬ እንደነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው በማለት፥ ስለ እርሱ መከራ መቀበልና ከሙታን ተለይቶ መነሣት፤ በእርሱ ስም ወንጌልን መሰበክ፤ ስለ ንስሓና ስለ ኃጢአት ስርየት አስረዳቸው ባረገ በአሥረኛው ቀንም መንፈስ ቅዱስ ስለሚወርድላቸው እስከዚያ ድረስ በኢየሩሳሌም (በቤተ መቅደሱ) መቆየት እንዳለባቸው ካዘዛቸው በኋላ እያዩት፤ እየባረካቸው ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ አለ፤ ዐረገ። (ወጣ) በባሕርይ አባቱ በእግዚአብሔር አብ ቀኝም ተቀመጠ።

በተጨማሪም እነዚህን ቁስ ብለን እንመልከታቸው፥

1ኛ እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል። (ዮሐ 16፥13)

2ኛ ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር አመኑ፤ በእኔ ደግሞ አመኑ፤ በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ። ዮሐ 14፥1 ጀምሮ

3ኛ ደግሞም አርባ ቀን እየታያቸው ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እየነገራቸው በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ ሕያው ሆኖ ለእነእርሱ ራሱን አያሳያቸው።

ከእነእርሱም ጋር አብሮ ሳለ ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ አዘዛቸው። የሐዋ ሥራ 1፥3

4ኛ መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ። ግብረ ሐዋ (የሐዋ ሥራ) 1፥8 እንደዚሁም ሮሜ 10፥1 እና 1ኛ ጴጥ 3፥18 እንመልከት።

<<ጥቅሶቹ ከአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው>>

ምዕራፍ 15።

በዐለ ጰራቅሊጦስ (ርደተ መንፈስ ቅዱስ) {{መንፈስ ቅዱስ የወረደበት ዕለት}}

ከጌታችን ትንሣኤ ጀምሮ እስከ በዐለ ጰራቅሊጦስ ባለው ጊዜ ውስጥ የሚኖሩ ቀናት በቁጥር ኀምሳ እንደመሆናቸው መጠን ወቅቱና ጊዜው በዐለ ኀምሳ በመባል ይታወቃል።

በዐለ ኀምሳ ማለት በቁጥር ሲተረጉም የኀምሳ ቀናት በዐል ማለት ነው።

ይህ በዐለ ኀምሳ ጌታችን እኛን ለማዳን ሲል የተቀበለውን ልዩ ልዩ ፀዋትው መከራንና በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያገኘነውን ፍጹም ሕይወት እያሰብን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እያመሰገን መንፈሳዊ ደስታን የምናደርግበት ወቅት ነው።

በቤተ ክርስቲያናችን ፍትሕ መንፈሳዊ ሕግ መሠረት በበዐለ ኀምሳ ጊዜ በንስሓ ቅጣት የሚሰጥ (የሚታዘዝ) ጾም፤ ቀኖና እና የንስሓ ስግደት የለም።

ይኸውም በዚህ ወቅት ቅጣት፤ ጾም፤ ስግደት፤ ንስሓና የመሳሰለው አለመሰጠቱ፥ እንደዚሁም በበዐለ ኀምሳ የሚኖሩ ሮብና ዓርብ፥ አለመጾማቸውና በገዳምም ሆነ በገጠር የምትገኝ የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴ ሁሉ በነግህ (በሧት) መሆኑ በመንግሥተ ሰማያት ጾም፤ ረኀብ፤ ኀዘን፤ መከራና ችግር እንደሌለ ለማመልከት እንደሆነ በሊቃውተ ቤተ ክርስቲያን አባቶቻችን ጉባኤ ይነገራል።

በበዐለ ኀምሳ መጨረሻ በኀምሳኛው ቀኑ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ጰራቅሊጦስ በሐዋርያት ላይ የወረደበትን መንፈሳዊ ታሪክንና ምሥጢሩን የምናስታውስበት ዕለት ነው።

በበነግታው ሰኞም የሐዋርያት ጾም ይገባል ማለት ነው።

የበዐለ መንፈስ ቅዱስ (የጰራቅሊጦስ) የዕለቱ ምስባክ፥

በግእዙ << ልበ ንጹሐ ፍጥር ሊተ እግዚኦ፥
መንፈሰ ርቱዓ ሐድስ ውስተ ከርሥየ፥
ኢትግድፈኒ እምቅድመ ገጽከ>> ይላል።

www.zeyenet.com

አማርኛው በትርጓሜው መሠረት ተብራርቶ ሲገለጽም÷
አቤቱ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ÷ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ፤ ከፊትህ አትጣለኝ ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ፤ የማዳንህን ደስታ ስጠኝ ይላል። (መዝ 50÷10
ከዚህ በላይ በተከታታይ እንደተገለጸው ጌታችን ወደ ሰማይ በሚያርግበት (በሚወጣበት) ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ ለሐዋርያት መንፈስ ቅዱስ እንደሚወርድላቸው በነገራቸው መሠረት÷ በተነሣ በ፶ኛው ቀኑ፤ ባረገም በአሥረኛው ቀኑ በጽርሐ ጽዮን (በጽዮን አዳራሽ) ተሰብስበው ሳሉ የዓለምን ቋንቋዎች ሁሉ የሚያውቁበት÷ አጽናኝ፤ ኃይልንና ብርታትን የሚሰጥ፤ ምሥጢራትን ሁሉ የሚገልጽ÷ ጰራቅሊጦስ መንፈስ ጽድቅ፤ የእውነት መንፈስ÷ (መንፈስ ቅዱስ) ወረደላቸው።

የሐዋ ሥራ 2÷1 ርኩስ መንፈስ ስለ አለ ከዚያ ሲለየው መንፈሰ ጽድቅ፤ የእውነት መንፈስ÷ (መንፈስ ቅዱስ) ይለዋል ይላሉ ሊቃውንት አባቶቻችን በጉባኤያቸው። ዘሩም <<ነፍሰ ነፈሰ>> ከሚል የግእዝ ግስ ነፋስ፤ መንፈስ ብሉ ይገኛል። ስለ ሆነም ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው የማስተማር፤ (ቅዱስ ወንጌልን የመስበክ) ድውያንን የመፈወስና ሙታንንም የማንሣት ሥራቸውን በጸምና በጸሎት ጀመሩ።

አሁ በቅዳሳት መጻሕፍት በየክፍሉ ተዘግቦ እንደምናገኘው ቅዱሳን ሐዋርያት ጌታችን በዋለበት እየዋሉ፤ ባደረበትም እያደሩ÷ በሚሔድበት ሁሉ እርሱን ተከትለው እየሔዱ በቀጥታ ከእርሱ የተማሩትን ንጹሑን የቅዱስ ወንጌል ቃል ለመላ ዓለም አስተማሩ አርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም ይህን ምንም ያልተቀላቀለበትን የክርስቶስን ንጹሕ ቅምህርት ነው ከሐዋርያት እንሥቶ በሃይማኖታዊ ትውፊት (ቅብብሎሽ) ከእውነተኞች አበው ሊቃውንተ ቤተክርስቲያንና ከቅዱሳት መጻሕፍት በተላለፈላት መሠረት እንድን ነገር ሳትቀላቅል ሕዝበ ክርስቲያኗን እያስተማረች የምትገኘው።

በመሆኑም ቅዱስ ጳውሎስ በ2ኛው የጢሞ መልእክቱ በምዕ 3÷14 ጀምሮ አንተ ግን በተማርኸበትና በተረዳኸበት ጸንተህ ኑር በማለት እንደመከረን÷ እኛ የአርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልጆች ትክክለኛውን እምነታችን ከማን እንደተማርነው እናውቃለንና፤ የቱ የአርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት እውነተኛ ትምህርት እንደሆነ በማስተዋል በሚገባ ስለምንረዳ በየጊዜው በሚነፍሰው የኑፋቄ (የጥርጥር) ነፋስ የምንደናገር አይደለንም።

ቅዱስ ጳውሎስ በ2ኛ ተሰሎንቄ መልእክቱ በምዕራፍ 2÷15ም <<ወንድሞች ሆይ ጸንታችሁ ቁሙ በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ>> በማለት እንደመከረን መሠረታዊ እምነታችንንና መንፈሳዊ ታሪካችንን ጠንቅቀን በማወቅ አሁንም በተማርነው መሠረት መጽናት ይገባናል። በጊዜያዊ የፍልስፍና ዕድገት እየተመሠረተ ሁል ጊዜ የሚነዋወጠው የኑፋቄ (የጥርጥር) ማዕበል እንዳይገለባብጠን፤ የክህደት ባሕሩም እንዳያሰጥመን÷ በእየሸንተረሩ የሚወርደው አዳዲስ የማደናገሪያና የማታሊያ ጉርፍም አደባልቆ እንዳይወስደን። ስለ እምነታችንና ስለሃይማኖታዊ ሥርዓታችን አፈጻጸም ከቤተ ክርስቲያናችን እውነተኞች ምሁራን እየጠየቅን፤ በሚገባም እየተረዳን፤ ምንጊዜም ተገቢውን መንፈሳዊ ዝግጅት በማድረግ በቅዱስ መንፈሳዊ ሰይፍ የሚመሰለውን ቃለ እግዚአብሔር ታጥቀን ነቃ ብለን መኖር ያስፈልገናል። ኤፌ 6÷11

በተጨማሪም እነዚህን ጥቅሶች እንመልከታቸው÷

1ኛ አሥራ እንዱ ደቀ መዛሙርቱ ግን ወደ ገሊላ ሔዱ፤ ባዩትም ጊዜ ሰገዱለት የተጠራጠሩም ነበሩ። ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው÷ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ እንግዲህ ሒዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፤ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው። <<እነሆ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ>> ማቴ 28÷16 ይህ የአምላካችን ቅዱስ ቃል ለጊዜው የተነገረው ለሐዋርያት ቢሆንም የፍጻሜው ዋና መልእክት ግን ለሐዋርያት ብቻ ሳይሆን እንደ ሐዋርያት መልካሙን ሥራ የሚሠሩ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የሚነሡትን ሁሉንም የእግዚአብሔር አገልጋዮችን ይመለከታል።

2ኛ <<የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል>> ዮሐ 14÷23።

3ኛ በዐለ ኀምሳም የተባለው ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ ድንገት እንደሚነጥቅ ዐውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ። ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩዋቸው በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው። በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞሳባቸው በሌላም ልሳኖች ይናገሩ ጀመር። የሐዋ ሥራ) 2÷1።

<<በዐለ ኀምሳ>> ማለት ከትንሣኤው ጀምሮ እስከ በዐለ

www.zeyeneta.com

ጰራቅሊጦስ (ርደተ መንፈስ ቅዱስ) {(መንፈስ ቅዱስ እስከ ወረደበት ዕለት)} ድረስ ያሉት <<ኀምሳ(50) ዕለታት>> ናቸው።

4ኛ <<ወንድሞች ሆይ ስለ መንፈሳዊ ነገር ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ>> (1ኛ ቆሮ 12÷1)

5ኛ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ። ዘሌዋ 19÷2

6ኛ <<ቅዱሳነ ኩኑ እስመ አነሂ ቅዱስ አነ>> በግእዙ ሲጠቀስ ነው÷ አማርኛውም÷ እኔ ቅዱስ እንደሆንሁ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ (የጠራችሁ (ክርስቶስ) እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሉ ስለ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑም ይላል) 1ኛ ጴጥ 1÷16። ቅድስና ለእግዚአብሔር የባሕርዩ ሲሆን÷ ሰው ደግሞ የቅድስናን ሥራ ሲሠራ ቅዱስ ነው ይባላል። ስለሆነም ቅድስና የእግዚአብሔር የባሕርዩ (ገንዘቡ) ሆኖ ለሰው ግን የመልካም ተግባሩ መገለጫው ነው ማለት ነው።

7ኛ እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብታችኋል፣ ሁሉንም ታውቃላችሁ። (1ኛ ዮሐ 2÷20 ጀምሮ)
<<ጥቅሶቹ ከመጽሐፍ ቅዱስ ልዩ ልዩ ክፍል የተወሰዱ ናቸው>>

እንግዲህ ስለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከትስብእቱ (ከጽንሰቱ) ጀምሮ እስከ ዕርገቱ ድረስ ያለው ምሥጢር÷ የእጥሞትና የጸሎት÷ የቀዳሚት፣ የሰንበታት÷ የንስሓ ተግባራዊ ትርጉም÷ እንዲሁም በዐቢይ ጾም ውስጥ የሚገኙት የሰንበታት መሠረታዊ ምሥጢርና የመሳሰለው ሁሉ ከዚህ በዐጭሩ ለመግለጽ እንደተሞከረው ሲሆን÷ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ቅዱሳት መጻሕፍትን በስፋት ልንመረምር፣ በየቀኑ፣ በየበዐላቱና በየእሑዱ በመንፈሳዊው ሥፍራ እየተገኘን ትምህርቱን ልንከታተል÷ አባቶችን፣ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንና አገልጋዮች ካህናትንም እየጠየቅን ልረዳ፣ ልናስረዳም ይገባናል።

ምክንያቱም ሃይማኖታዊ ኃላፊነቱና ክርስቲያናዊ ግዴታው ሁላችንንም የሚመለከት በመሆኑ እያንዳንዳችን የየራሳችንን ድርሻ በተግባር መወጣት አለብን ማለት ነው።

ምዕራፍ 16።

እምነት÷ (ሃይማኖት)

እምነት÷ (ሃይማኖት) የእምነት ቃል ኪዳንና ተፈጥሮ፣ እንዲሁም እምነታዊ ተስፋ÷

በዚህ እምነት በሚል ሒደት ውስጥ ቃለ ኪዳንና (ቃል ኪዳንና) መሠረቱ÷ ተፈጥሮና የተፈጥሮ ሁኔታዎች÷ እንዲሁም እምነታዊ ተስፋ እየተጠቀሱ፣ በምሥጢርም እየተገናኙ ይብራራሉ።

እምነት (ሃይማኖት) ለሚለው ግስ መታመን (ማመን) ወይም ደግሞ እንዳለ እምነት የሚል አንድ ዓይነት ትርጉም ነው ሊኖረው የሚችለው።

ምእመን፣ መሃይምን (መሃይም)ማለትም ሃይማኖታዊ ማለት ነው እንጂ በተለምዶ እንደሚነገረው አላዋቂ ማለት አይደለም።

ዋና ግንዱም <<ሃይመነ አሰመነ>> ከሚል የግእዝ ግስ ይገኛል።

እምነት (ሃይማኖት) ማለት÷ አስቀድመው በሐሳብ አውጥተው አውርደው አንድን ነገር ለመተግበር ጥናት ካደረጉ በኋላ ይሆን ካደረግሁ አጥጋቢ ውጤት አገኛለሁና እንደዚህ ማድረግ አለብኝ ብለው በሚሠራው ሥራ ላይና በውጤቱ እርግጠኛ መሆን÷ እንደዚሁም ደግሞ ያዩትንም ሆነ የሰሙትን ጉዳይ አስፈላጊ በሆነው ማስረጃ አረጋግጠው ትክክል ነው ብለው ያለ ጥርጥር ማመን፣ ያመኑትንም እምነት በተግባር ላይ ማዋል፣ በጉዳዩ እምነት ያለዎት መሆንዎን በሥራ መግለፅ ማለት ነው።

እምነት ወይም ማመን ሲባል ይህን ያገዘኛል (ያደርግልኛል) ብለው ለሚያምኑትና ተስፋ ለሚያደርጉት፣ ለሚወዱት ወገንም ልባዊ ሓሳብዎንና ምሥጢርዎን ማካፈል፣ ማወያየትም ሊሆን ይችላል።

(ነገር ግን ይህ በሰው ባሕርይ (በሰው ፀባይ) የሚከናወን እንደመሆኑ መጠን ድጋፍም፣ አደጋም ሊኖረው እንደሚችል ይገመታል)።

www.zeyeneta.com

እምነት (ሃይማኖት) በልብ የሚታሰብ ከተስፋ ጋር የተያያዘ የማይታይ ረቂቅ ሲሆን÷ በተግባር ሲገለጽ ግን ውጤትን በማሳየት ጉልቶ የሚታይ÷ ባለቤትና ተሳቢ (አድራጊና ተደራጊ) ያለበት ነው።

የሁሉም ሥራ መሠረቱ እምነት (ሃይማኖት) እንደመሆኑ መጠን የሆነ ይሁን ሥራ በእምነት ላይ ካልተመሠረተ ዋጋ የለውም።

በመሆኑም አንድን ተግባር ለመፈጸም ከታሰበ ከሁሉ በፊት ምንም ጥርጥር የሌለበት ልባዊ እምነት ሊኖር ይገባል፤ ከዚያም እምነቱን በሥራ መግለጽ ያስፈልጋል።

ምክንያቱም ጥርጥር ባለበት እምነት ላይ ተመሥርቶ የሚሠራ ሥራ አጥጋቢውን ውጤት የማያስገኝ ከመሆኑም በተጨማሪ እምነትና ሥራ ከተለያዩ ዋጋ እንደሌላቸው በቅዱሳት መጻሕፍትም ተነግሮናል። <u>ለምሳሌ ያዕቆ ምዕራፍ 2÷14 ጀምሮ እንመልከት</u>

አያሌ ምሁራን ስለ እምነት፤ ስለ ተስፋና ስለ ተፈጥሮ በተለያየ ቋንቋ ብዙ ይላሉ፤ ብዙውን ያነሣሉ፤ ብዙውንም ይጽፋሉ። ነገር ግን አብዛኛዎቹ ከኋላው ዋናውን ቁም ነገር እየረሱ ናቸው። <u>ያውም</u> ፈጽሞ ሊረሳ የማይገባው የእምነት፤ የተስፋና የተፈጥሮ ባለቤት የሆነውን ፈጣሪን ነው።

አዎ መሪ (አስተዳዳሪ) የሌለበት ሀገር፤ ባለቤት የሌለበት ቤት÷ እንዲሁም ሠሪው (ሠራተኛው) የማይታወቅ ሥራ እንደማይኖር ሁሉ÷ ባለቤት (ፈጣሪ) የሌለበት ፍጥረትና እምነትም ሊኖር ስለማይችል እምነትን፤ ተስፋንና ተፈጥሮን ስናነሣ የእነዚህ ሁሉ ባለቤት የሆነውን እግዚአብሔርን ማንሣት÷ ፍጡር በእውቀት ቢጉለብትና ብዙውንም ቢፈላሰፍ ምንም ሊደርስበት የማይችል አምላካዊ ጥበቡንና ድንቅ ሥራውንም ሁሉ ማስተዋል፤ በተግባርም (በሥራም) ማወቅ ተገቢ ነው። <u>ኢሳ 11÷1, 43÷1</u>።

መጽሐፈ መቃብያን ሣልስንም ምዕራፍ ዘጠኝ ከቁጥር አንድ ጀምሮ ብንመለከት ሁሉም በእግዚአብሔር ቍጥጥር መሆኑን ያስረዳናል። <u>መቃ. ሣልስ 9÷1</u>

ብዙ የዓለም ጠበብት አፈርን ቢቆነጥሩ፤ መሬትንም ቢቆፍሩ፤ ከአድማስ እስከ አድማስ ቢዞሩ፤ በምድር ቢሽከረከሩ፤ ወደ ጠፈር (ወደ ሰማይም) ወጥተው ቢመራመሩ መለኮታዊ የሆነውን የእግዚአብሔር ጥበብ ፈጽመው ማሾት አልቻሉም፤ ወደፊትም አይችሉም።

አዎ ብዙዎች አዋቂዎች ነን ባዮች ከዓቅማቸው በላይ የሆነውን አምላካዊ ሥራ ሲመራመሩ ከፊሎቹ ከክሕደት ባሕር ገብተው በማዕበሉ ድራሻቸው ሲጠፋ፤ ከፊሎች ደግሞ ግራ ተጋብተው መንገድ ላይ እንደቆሙ ደርቀው ይቀራሉ።

የታደሉ የእግዚአብሔር ወገኖች ግን የፈጣሪአቸውን ድንቅ ሥራ እያደነቁ ሁሉን ማድረግ የሚቻለው እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ይኖራሉ።

እምነት (ሃይማኖት) ማለት÷ ማድረጊያ፤ የሥራ ማስፈጸሚያ፤ የዕቅዶች ማከናወኛ ልባዊ መሣሪያ ሲሆን÷ እምነት (ሃይማኖት) ሲባል ምን እንደሆነ፤ የሚታመነውም ማን እንደ ሆነ አስቀድሞ ማወቅ ተገቢ ነው።

<u>እምነት (ሃይማኖት) በመንፈሳዊ ሕይወት ሲታይ የማመሰገኛና የመጸለያ (የመለመኛ) ዋና መሠረት ማለት ነው።</u>

ምክንያቱም በትክክለኛ እምነት ላይ ቆመን ነው መጸለይና ማመስገን የምንችለው።

የሚታመነውና የሚመሰገነውም÷ የእምነትና የስጦታ ባለቤት የሆነው÷ ሰጥቶ የማያልቅበት፤ ከሰጠ በኋላም እንደሰው የማይፀፀት የባሕርይ አምላክ፤ የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ፤ ሁሉን የሚያስገኝ፤ ከፍጥረት አስቀድሞ የነበረ፤ አሁንም ያለ፤ ዘለዓለም ሀልው የሆነ (ለዘለዓለም የሚኖር) ጎልፈት ወይም ሽረት የሌለበት ዘለዓለማዊ ንጉሥ÷ መጀመሪያውና መጨረሻው በፍጡር ሊታወቅ የማይችል፤ ሙሉ ተስፋ የሚጣልበት የባሕርይ አምላክ እግዚአብሔር ነው።

<u>ዘፍ. 1÷1, መጽ. ኩፋ. 2÷1, ኢሳ. 42÷5,ኢዮ. 12÷7, ዮሐ 1÷1, ራዕ. ዮሐ. 22÷12 እንመልከት።</u>

በመንፈሳውያንና በታሪካውያን ጽሑፎች የተመለከትን እንደሆነ ምንም እንኳን አፈጻጸሙና ሁኔታው ሊለያይ ቢችልም ከጥንት ጀምሮ ያለ እምነት የኖረ ሰው ግን እንዳልነበረ ለሁላችንም ግልጽ ነው።

እምነት በተለይም የእግዚአብሔር ልዩ ወዳጅ ተብሎ በሚታወቀው በአብርሃም ዘንድ በመልካም ሥራ ላይ ጎልቶ ታይቷል፤ ለሌላው እውነተኛ አማኝም ትክክለኛ የእምነት ትምህርት ሆኖለል።

www.zeyeneta.com

እምነት ማለት ምን እንደሆነ፣ የእምነት ባለቤት ማን እንደሆነም በአብርሃም ተግባራዊ የእምነት እንቅስቃሴ ተገልጿል።

አም አብርሃም እምነቱን በመልካም ሥራ በመግለጹ ነው የእግዚአብሔር ልዩ ወዳጅ የተባለው።
ዘፍጥ 12÷7, 18÷1, 22÷1 እንመልከት።

እምነት ምንም እንኳን ሥርዓቱና አፈጻጸሙ ሁሉ በሐዲስ ኪዳን ተለይቶ የተቀመጠ ቢሆንም÷ ዋና መሠረታዊ መነሻው ግን ከብሉይ ኪዳን ስለሆነ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍትንም በሚገባ ልንመለከታቸው ይገባናል።

ምክንያቱም የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ለሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት መሠረታቸውና ጥሬ ንባባቸው እንደመሆናቸው መጠን÷ የሐዲስ ኪዳን ምንጭ ከብሉይ ኪዳን ነው የሚገኘው።

የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍትም ለብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜያቸውና የተግባር ፍጻሜያቸው ናቸው።

ይህም ማለት በዘመነ አሪት÷ በሐዲስ ዘመን ምን እንደሚፈጸም በእግዚአብሔር መልእክተኞች ቅዱሳን ነቢያት በትንቢት መልክ ተነግሮ በብሉያት ቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፏል።

በዘመነ አሪት በቅዱሳን ነቢያት ተነግሮ በብሉያት ቅዱሳት መጻሕፍት የተዘገበው ደግሞ በሐዲስ ዘመን ተግባራዊ ሆኖአል።

ለምሳሌ÷ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ሲሆን÷ ፍጹም ሰው ሆኖ፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፣ በመስቀል ተሰቅሎ ፍጥረቱን ሁሉ እንደሚያድን አስቀድሞ በቅዱሳን ነቢያት ተነግሮ በብሉያት መጻሕፍት ተዘግቧል። ኢሳ 7÷14, ዳን. 7÷13

በብሉይ ኪዳን የተነገረው ትንቢት ደግሞ በሐዲስ ኪዳን ተከናውኗል። ሁሉም በየደረጃው ተፈጽሟል።

ስለ ልደቱ ማቴ 2÷1, ሉቃ 2÷7÷

ስለ ስቅለቱም ማቴ27÷27, ማር 15÷15,ሉቃ 23÷40, ዮሐ 19÷1 ጀምሮ እንመልከት።

ክፍል 46÷

የእምነትና የቃል ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት÷

በርእሱ የተጠቀሰው የእምነት ቃል ኪዳን፣ ተፈጥሮና እምነታዊ ተሰፋ በዚሁ በእምነትና በቃለ ኪዳን (በቃል ኪዳን) ቅዱሳት መጻሕፍት÷ ውስጥ ይገኛል።

የአምላክን ሥራ ስለሚናገሩ÷ አምላካውያን፣ የአምላክ ልሳናት (ሆእግዚአብሔር አምላክ ቃላት) በመባል የሚጠሩ ቅዱሳት መጻሕፍት በመሠረታዊ ምሥጢር ሰምና ወርቅ ናቸው።

(81 የሚባሉ ቅዱሳት መጻሕፍት 36 ብሉያትና 35 ሐዲሳት ጠቅላላ 81 ናቸው)

አም ጥንታዊውን መንፈሳዊ ሥርዓታችንንና ባህላችንን የሚያስረዳን መጽሐፍ ቅዱስ <<ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን>> እያለ የራሱ ስም እንደሚጠቁመን በዘመነ አሪትና በሐዲስ ኪዳን ዘመን ከእግዚአብሔር የተሰጠን ልዩ ልዩ ቃለ ኪዳን (ቃል ኪዳን) ማለትም ምን ጊዜም የማይለወጥ የውልና የመሐላ ቃልን የያዘ ቅዱስ መጽሐፍም ነው

ለምሳሌም ብሉይ ኪዳን÷

1ኛ እግዚአብሔር ሰውንም ሆነ ሌላውን ፍጥረቱን ሁሉ ዳግመኛ በጥፋት ውሃ እንደማያጠፋው ከኖኅና ከልጆቹ፣ ከዘራቸውም ጋር ቃለ ኪዳንን (ቃል ኪዳንን) እንዳቆመ (እንደመሠረተ) በብሉይ ኪዳን ቅዱስ መጽሐፍ እናገኛለን።
ዘፍ 9÷8 ጀምሮ እንመለከት

2ኛ እግዚአብሔር ከአብርሃምና ከአብርሃም በኋላ ከሚተኩ ከትውልዱ፣ ከዘሩም ሁሉ ጋር የሕይወትና የምሕረት ቃል ኪዳኑን እንዳደረገም በዚሁ በዘፍ 17÷1 ጀምሮ ብንመለከት መረዳት እንችላለን።

3ኛ እግዚአብሔር ከእነሙሴና ከእነአሮን ከሴሎችም ወዳጆቹ ኣባው ጋር ቃለ ኪዳኑን ያደረገበትን የሚገልጽልንም ይህው የብሉይ ኪዳን ቅዱስ መጽሐፍ ነው።

www.zeyeneta.com

4ኛ ከወዳጆቹ ጋር የተካሔደው ቃለ ኪዳንም ለዘለዓለም የጸና እንደሆነና ምድርንም በቃል ኪዳኑ እንደሚያስባት የተናገረበት በዚሁ በብሉይ ኪዳን ቅዱስ መጽሐፍ ይገኛል።

ይኸውም እግዚአብሔር አምላካችን ምድሪቱንም አስባታለሁ ማለቱ÷ የቅዱሳን፣ የጻድቃንና የሰማዕታት ዓፅም ያረፈበት ቦታ፣ (የተቀበሩበት መካን) ፍጥረቱንና ዓለሙን በሙሉ በቃል ኪዳኑ መሠረት እንደሚጠብቅና በቸርነቱም እንደሚጎበኝን ነው የሚያስረዳን።

(እዝራ ሱቱ 1÷15,ዘሌዋ 26÷42,መዝ 88÷2,88÷28, ዳን 9÷4 እንመልከት)

አዎ ሃይማኖታዊውንና መንፈሳዊውን ታሪካችን ከመነሻውና ከመሠረቱ ጀምረን ስንገልጽ፣ ብሉይ ኪዳንንም ስንል ይህን ቁም ነገር የያዘውን ጥንታዊውን ቅዱስ መጽሐፍ ማለታችን ነው።

ሐዲስ ኪዳንስ?

ሐዲስ ኪዳንም የብሉይ ኪዳንን ቃል መሠረት አድርጎ ይቀጥላል።

ይኸውም÷

ሀ የሉቃስን ወንጌል ብንመለከት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወሳዲተ አምላክ ከዘመዷ ከኤልሳቤጥ ጋር ተገናኝታ የእግዚአብሔርን ቸርነት ባደነቀች ጊዜ÷ <<ወተዘከረ ሣህሉ ዘይቤሎሙ ለአበዊነ ለአብርሃም ወለዘርዑ እስከለዓለም>>

እግዚአብሔር ለአባቶቻችን ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ የተናገረውን ምሕረቱንና ይቅርታውን እስከ ዘለዓለም አሰበ።

(አፀና) በማለት ከእግዚአብሔር የተሰጠው የማይሻር የቅዱሳን፣ የጻድቃንና የሰማዕታት ቃል ኪዳን (ቃለ ኪዳን) ለዘለዓለም ፀንቶ ሲያማልድ እንደሚኖር ያስረዳችበት ቃለ ምስጋና (የምስጋና ቃል) በዚሁ መንፈሳዊ ሰንሰለቱን ጠብቆ በመጣው በሐዲስ ኪዳን ቅዱስ መጽሐፍ ነው የሚገኘው። ሉቃ 1÷55 1÷71።

ሐ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እናንተ የነቢያት ልጆችና እግዚአብሔር ለአብርሃም የምድር ወገኖች ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ ብሎ ከአባቶቻችን ጋር ያደረገው የኪዳን ልጆች ናችሁ ያለው ቃልም በዚሁ ተዘግቦአል። ግብሐዋ (የሐዋ ሥራ) 3÷25።

አዎ ሐዲስ ኪዳን ስንልም እነዚህ ለምሳሌ የተጠቀሱትና እነዚህን የመሰሉት ቁም ነገሮች የሚገኙበት፣ መሠረቱ የብሉይ ኪዳን ቅዱስ መጽሐፍ የሆነ ቅዱስ መጽሐፋችን ማለታችን ነው።

ብሉይ ማለት የቆየ (ጥንታዊ) ወይም ደግሞ በቀጥተኛ ትርጉሙ ያረጀ ማለት ሲሆን ኪዳን ማለት ደግሞ መሐላ ማለት ነው።

ይኸውም የቆየ (ጥንታዊ) ማለት ነው እንጂ አርጂቶ የተጣለ ማለት አይደለም።

ቃለ ኪዳን (ቃል ኪዳን) ጠቅለል ባለ መልኩ ሲነገርም የመሐላ ቃል (ቃለ መሐላ) ማለት ሲሆን፣ ቅድሳት መጻሕፍትም የቃል ኪዳን መጻሕፍት ናቸው ማለት ነው።

ሐዲስ ኪዳን ስንል ደግሞ በዘመነ ብሉይ የነበረውን መሠረት አድርጎ የሚሔድ፣ ቀደም ብሎ በቅዱሳን ነቢያት የተነገረውንና በብሉይ ኪዳን የተዘገበውን÷ ይሆናል፣ ይደረጋል የሚለውን ሆነ ተደረገ እያለ በጽሑፉ ተርጉሞ የሚገኝ፣ በዘመነ ሐዲስ የተሠራውንም በብዛት የያዘ፣ ከክርስቶስ ልደት ወዲህ የተጻፈ የሐዲስ ኪዳን ቅዱስ መጽሐፍ ማለታችን ነው።

አሪታዊው (ጥንታዊው) የብሉይ ኪዳን ቅዱስ መጽሐፍ በሐዲስ ኪዳን ጊዜም እንዳልተሻረ ራሱ ጌታችን በማቴዎስ ወንጌል ነግሮናል። ማቴ 5÷17

ሆኖም በሐዲስ ኪዳን ዘመን አንዳንድ የተሻሻሉ እንዳሉ ግልጽ ነው።

ለምሳሌ ያህልም÷ የብሉይ ኪዳን ቅዱስ መጽሐፍ ነፍስን የገደለ ሞት እንደሚገባው ሲፈርድ÷ ሐዲስ ኪዳን (አዲስ ኪዳን) ግን ነፍስ የገደለን ጨምሮ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የኃጢአትን ተግባር የፈጸመ ሁሉ በንስሓ እንዲመለስ፣ መሥዋዕተ አሪት በመሥዋዕተ ሐዲስ እንዲሻሻል፣ ጾም፣ ጸሎት÷ የበዐላት አከባበርና

www.zeyeneta.com

ሃማኖታዊ ሥርዓቱ÷ አገልግሎቱም ሁሉ በሃማኖታዊና በመንፈሳዊ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት እንዲመራ በሐዲስ ኪዳን ዘመን በጽሑፍ ተጽፎ፣ በክፍልም ተለይቶ ስለታወቀ በመመሪያው መሠረት እየተከናወነ ይገኛል።

ብሉይ ኪዳን ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረው ዘመነ አሪት ሲሆን÷ ሐዲስ ኪዳን ግን ከክርስቶስ ልደት ወዲህ ያለው ዘመነ ሐዲስ (አዲስ ዘመን) ማለት ነው።

የአባቶቻችን ትርጓሜ ደግሞ ብሉይ ኪዳን አሪት (ምድረ ርስት) ሐዲስ ኪዳን ወንጌል (መንግሥተ ሰማያት) ይላል።
<<የእሑድ ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ>>

ይህ እንዲጠቀስ ያስፈለገበት ምክንያት የሚነገር ያለው ምሥጢር እነዚህን ቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት ያደረገ ስለሆነ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው የሁለቱ÷ ማለትም የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት እንዴት ብለው ተስማምተው እንደሚሔዱ ለማስገንዘብ ያህል ነው።

በመሆኑም ነው ከላይ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ለሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት መሠረታቸውና ጥሬ ንባባቸው እንደመሆናቸው መጠን÷ የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍትም ለብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜያቸውና የተግባር ፍጻሜያቸው ናቸው ያልን።

ስለዚህ የብሉዩን (የአሪቱን) መንፈሳዊ ምንጭ መነሻ በማድረግ÷ መንፈሳዊ ታሪኩንና ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን ,ጠብቆ የተላለፈልን አሁን የተተነተነው ቅዱስ መጽሐፋችን እንደሚያስረዳን ከሌሎች ፍጥረታት ሁሉ ለየት ባለ መልኩ በአርአያ እግዚአብሔር ተፈጥሮ በፈጣሪው በእግዚአብሔር ዘንድ ከሌላው ፍጥረት የላቀ ክብርና መብት የተሰጠው ሰው÷ ከሁሉም በፊት ከፈጣሪው፣ ከአምላኩ ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኝበት፣ ፈጣሪው እግዚአብሔርን የሚያገለግልበት፣ የሚያመሰግንበትና የሚያስደስትበት በተስፋ መንግሥተ ሰማያት የተሞላ ምንም ጥርጥር የሌለበት ትክክለኛ እምነት ሊኖረው ይገባል ማለት ነው።

ምክንያቱም ያለ እምነት እግዚአብሔርን ማገልገልም ሆነ ማስደሰት እንደማይቻል በብዙ ከፍል የተገለጸ ሲሆን÷ በጽኑዕ እምነት በመጓዝ ግን ሕይወታዊውን ጥቅም መጨበጥ እንደሚቻል ተረጋግጧል።

ለምሳሌም ዕብራውያን 10÷38 እና 11÷1 ጀምሮ ብንመለከት ስለ እምነትና መሠረታዊ ጥቅሙ በሰፊው መረዳት እንችላለን።

በዐሬሩ ብንጠቅስም÷

1ኛ አብርሃም እግዚአብሔርን እንዳመነና ጽድቅም ሆኖ እንደተቆጠረለት÷ ሮሜ 4÷3

2ኛ ጻድቅ ሰው በእግዚአብሔር <<እምነት>> እንደሚኖር÷ ዕብ 10÷38፤

3ኛ <<እምነት>> ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያረጋግጥልንና የማናየውን የሚያስረዳን እንደሆነ÷ ዕብ 11÷1፤

4ኛ አቤል መሥዋዕቱን <<በእምነት>> ለእግዚአብሔር ባቀረበ ጊዜ እግዚአብሔር እንደ ተቀበለለትና ጻድቅ መሆኑም እንደተመሠከረለት÷ ዘፍ 4÷3 ዕብ 11÷4፤

5ኛ ሄኖክ እንዳይሞት <<በእምነት>> ፈጣሪውን እንደሰመነና እግዚአብሔርም ጸሎቱን ተቀብሎ ከሞት እንደሰወረው÷ ዕብ 11÷5፤

6ኛ ያለ እግዚአብሔር <<እምነት>> እግዚአብሔርን ማገልገልም ሆነ ማስደሰት እንደማይቻል÷ ዕብ 11÷6፤

7ኛ የሚጸልይም ሆነ የሚያገለግል ሁሉ አስቀድሞ የእግዚአብሔር ህልውናንና ሰጭነቱንም ከልቡ ማመን እንዳለበት÷ ዕብ 11÷7፤

8ኛ ኖኅ ከፈጣሪው በተነገረው መሠረት መርከቡን በእግዚአብሔር <<እምነት>> እንዳዘጋጀና ከጥፋት ውሃ በመዳንም ጻድቅና የዓለም ወራሽ እንደሆነ÷ ዕብ 11÷7

9ኛ አብርሃም በእግዚአብሔር <<እምነት>> ፈጣሪው ወዳዘዘው ወደ ከነዓን እንደሔደና በከነዓንም ሀገር <<በእምነት>> እንደተጠቀመ ዘፍ 12÷1,17÷8, ዕብራ 11÷8

www.zeyeneta.com

10ኛ የአብርሃም ሚስት ሣራ ዕድሜዋ ካለፈ በኋላ በእግዚአብሔር <<እምነት>> ደጉን ልጅ ይስሐቅን እንደወለደች÷ ዘፍ 21÷1, ዕብራ 11÷11፤

11 አብርሃም በጽኑዕ <<እምነት>> ልጁ ይስሐቅን ለመሥዋዕት እንዳቀረበና እግዚአብሔርም እንደተቀበለለት÷ ዘፍ 22÷9, ዕብራ 11÷17፤

12 ሕዝበ እስራኤል ልክ በደረቅ ምድር እንደሚያልፉ የኤርትራን ባሕር በእግዚአብሔር <<እምነት>> እንደተሻገሩና ጠላቶቻቸው ግን ለመሻገር ሲሞክሩ ባሕሩ ውስጥ እንደሰጠሙ (እንደተዋጡ) ዘፀ 14÷26, ዕብ 11÷29÷

13 ኢያሱና ተከታዮቹ ሁሉ እግዚአብሔርን በማመን በውሃ የተመላውን የዮርዳኖስን ወንዝ እንደተሻገሩና የኢያርኮ ግንብም ሰባት ቀን ከዞሩባት በኋላ በእግዚአብሔር <<እምነት>> እንደወደቀች÷ እንዲሁም ዘማ የምትባለው ረዓብ የኢያሪኮን ሁኔታ እንዲያጠኑ በነዌ ልጅ ኢያሱ ተልከው በእግዚአብሔር <<እምነት>> የመጡትን መልእክተኞች (ሰላዮች) በሰላምና በእግዚአብሔር <<እምነት>> ተቀብላ ከሞት በማትረፏ ከትዕቢተኞች ጋር እንዳልጠፋች÷ ኢያሱ 2÷1, 3÷5, 6÷20, 6÷25, ዕብ 11÷30

14 እንደዚሁም እነጌዴዎን፣ እነባርቅ፣ እነሶምሶን፣ እነዮፍታሔ፣ እነዳዊት፣ ሕዝበ እስራኤልና ሌሎችም ነቢያት በእግዚአብሔር <<እምነት>> መንግሥታትን ድል እንደነሡ፣ ጽድቅን እንዳደረጉ፣ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን የሕይወትና የተስፋ ቃል እንዳገኙ፣ የአንበሶችን አፍ እንደዘጉ፣ የእሳትን ኃይል እንዳጠፉ፣ ከሰይፍ ስለት እንዳመለጡ፣ ከድካማቸው እንደበረቱ፣ በጦርነት ኃይለኞችን እንደሆኑ፣ የባዕዳንን ጭፍሮች እንዳባረሩ። ዕብ. 11÷32

በአጠቃላይ ይህ የተጠቀሰውን ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ ፍጻሜው ድረስ ብንመለከተው የእምነትን መሠረታዊ ጥቅም በሚገባ ያስረዳናል። ዕብ. 10 እና 11÷ ከቁጥር 1 ጀምሮ እንመልከት። ስለ <<እምነት>> ብዙ መጥቀስ የሚቻል ቢሆንም ለምሳሌ ያህል ግን ይህ በቂ ይመስለኛል።

ክፍል 47÷

እምነትና መልካም ምግባር÷

የእምነት ትርጉምና አጥጋቢ ውጤት መልካም ሥራ ነው።

ለዚህም ከዚህ ቀጥለው ያሉትን ምሳሌዎች እንመልከት÷

1ኛ ሰው <<በእምነት>> ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ እንደዚሁም ጋለሞታይቱ ረዓብ ደግሞ መልእክተኞቹን ተቀብላ በሌላ መንገድ በሰደደቻቸው ጊዜ በሥራ አልጸደቀችምን? ይላል። ያዕ 2÷24, 2÷14, ኢያሱ 2÷1, 6÷25, እንመልከት።

2ኛ መልካም ፍሬ የማያደርግ (የማያፈራ) ዛፍ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል። ማቴ 7÷19 ይህ ቃል ጌታችን የተናገረው ሲሆን ሃይማኖቱን በመልካም ፍሬ በሚመሰለው በመልካም ምግባር የማይገልጽ ሰው ዋጋ እንደሌለው ነው የሚያስረዳን።

3ኛ ነፍስ የተለየው ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ <<እምነት>> የሞተ ነው። ያዕ. 2÷25÷

4ኛ እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ አንተ ታምናለህ፣ አጋንንትም ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል÷ አንተ ከንቱ ሰው <<እምነት>> ከሥራ ተለይቶ የሞተ መሆኑን ልታውቅ ትወዳለህን? ይላል። ያዕ. 2÷19÷

5ኛ አብርሃም ልጁ ይስሐቅን ለመሥዋዕት ማቅረቡ <<እምነቱን>> በሥራ ገልጿል። ያዕ. 2÷21

6ኛ ሰው <<በእምነት>> ብቻ ሳይሆን በሥራ እንደሚጸድቅ ታያላችሁ ይላል። ያዕ. 2÷24÷

በመሆኑም እምነት በሥራ፣ ሥራም በእምነት ይገለጻል ማለት ነው

ስለዚህ በመንፈሳዊ ሕይወት በኩል እምነት ስንል÷

www.zeyeneta.com

እግዚአብሔር የባሕርይ አምላክ፣ ፈጣሪ፣ ሁሉን ማድረግ የሚችል መሆኑን፣ ያለእርሱ ምንም ምን ማድረግ የማይቻል÷ በእርሱ ግን የሚሳን ነገር እንደሌለ በሚገባ ማመን÷ በእምነቱ መጽናት፣ በሕጉ መመራት፣ ትእዛዛቱንም መፈጸም፣ እምነትን (ሃይማኖትን) በመልካም ሥራ መግለጽ ማለታችን ነው።

ምክንያቱም እግዚአብሔርን የማይወዱ ሰዎች ሕጉን እንደማይጠብቁና ልቡናቸውም የቀና እንዳይደለ በመጽሐፈ መቃብያን ሣልስ 6÷14 የተገለጸ ሲሆን÷ በሕይወት (በጽድቅ) ሊኖርና የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርስ የሚፈልግ ሁሉ ትእዛዘ እግዚአብሔርን በመጠበቅ <<በእምነቱ>> ጸንቶ በእግዚአብሔር መንገድ መሔድ እንዳለበትም ከዚህ ቀጥለው ባሉት የቅዳሳት መጻሕፍት ክፍሎች ተነግሮናል። ዘፀ 20÷1, ዘዳግ 30÷15, እንደዚሁም 2ኛ ጢሞ. 3÷14 እንመልከት

አዎ <<እምነት>> (ሃይማኖት) ስንል÷ የእግዚአብሔርን የአካል፣ የግብርና የስም ሦስትነት፣ የባሕርይ፣ የህልውና እና የመለኮት (የአምላክነት) አንድነት ጠንቅቆ በመረዳት፣ ለሌላውም ማስረዳት እግዚአብሔር የባሕርይ አምላክ፣ መሐሪና ይቅር ባይ መሆኑን ከልብ በማመን በተግባር ወደ እርሱ መቅረብ÷ ምሕረትን በሚያስገኝ መልክ በመዘጋጀት፣ በምሕረት ሥፍራ በመኖር ከእርሱ ምሕረትንና ይቅርታን መጠየቅ ማለታችን ነው።

ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ሁሉ እንደሚገኝ ያለ ምንም ጥርጥር በልብ አምኖ በተግባር ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ ምሕረትንና ይቅርታን ከእግዚአብሔር መጠየቅ፣ ዘለዓለማዊ ሕይወትን መንግሥተ ሰማያትን ከእርሱ መለመን ማለት የእግዚአብሔርን የባሕርይ አምላክነት በተግባር ማረጋገጥ ማለት ነው። እግዚአብሔር አምላካችንም እንደዚህ ሆነን ከቀረብነው በትንቢተ ኤርምያስ÷ <<በዚያን ቀን አድንሃለሁ÷ በምትፈራቸው ሰዎች እጅ አልሰጥህም (አማርኛው ሲቃና በምትፈራቸው ሰዎች እጅ ላይ አልጥልህም) ፈጽሜ አድንሃለሁ>> በማለት በማይሻር ቃሉ በተናገረው መሠረት ሁላችንንም ይምረናል፣ ይቅርንም ይለናልና በመልካም ምግባር የሚገለጽ ትክክለኛ እምነት ሊኖረን ያስፈልጋል፣ በእምነታችን ጸንተንም በንጹሕ ልብ ወደ እርሱ ልንቀርብ ይገባናል። ኤር. 39÷17

እምነት (ሃይማኖት) በምን ይታወቃልን? ያልን እንደሆነም መልሱ በመልካም ምግባር (በሥራ) ነው።

አዎ ከዚህ በላይ በሰፊው እንደተገለጸው የእምነት መታወቂያው መልካም ምግባር ሠናይ ሥራ ሲሆን÷ መልካም ምግባር ሠናይ ሥራ የሚባለውም ጾም፣ ጸሎት፣ ምጽዋት፣ ትሕትና፣ ርኅራኄ እና የመሳሰለው እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያስደስት መልካም ግብር ሁሉ እንደሆነ ተደጋግሞ ተገልጸአል።

የእነዚህ ሁሉ ዋና ማሠሪያም እውነተኛ ፍቅር እንደሆነ ብዙ ጊዜ ተነግሮናል። በቅዳሴ መጽሐፍ በብዙ ክፍል ተጽፎአል። አሁንም በዚሁ ዝግጅት በየክፍሉ ተጠቅሶአል።

ምክንያቱም የጽድቅ ሥራ የሚባሉት ሁሉ በእውነተኛው ፍቅር ሊከናወኑ ስለሚችሉ ነው በብዙ ክፍል የተጠቀሰው እውነተኛ ፍቅር ከሌለ ግን መልካሙን ሥራ መሥራት እንደማይቻል የታወቀ ነው

እምነት (ሃይማኖት) እና መልካም ምግባርም ከተለያዩ

ዋጋ ስለሌላቸው እምነት (ሃይማኖት) እና መልካም ምግባር ፈጽመው ሊለያዩ እንደማይችሉ በብዙ ክፍል ተደጋግሞ ተጠቅሶአል።

ስለሆነም እውነተኛውን ፍቅር መሠረት በማድረግ ትክክለኛውን እምነታችን (ሃይማኖታችንን) በመልካም ምግባር መግለጽ ይገባናል ማለት ነው።

በተጨማሪም እነዚህ ጥቅሶችንና ማብራሪያቸውንም እንመልከት÷

1ኛ እግዚአብሔር አስቀድሞ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ። ዘፍ. 1÷1

2ኛ ሁሉንም የፈጠረ እግዚአብሔር ነው። ዕብ. 3÷4

3ኛ ሰማያትን የፈጠረ፣ የዘርጋቸውም÷ ምድርንና በውስጧ ያለውንም ያጸና በእርሷ ላይ ለሚኖሩ ሕዝብ እስትንፋስን፣ ለሚሔዱባትም መንፈስን የሚሰጥ አምላክ እግዚአብሔር በጽድቅ ጠርቼሃለሁ ይላል። ኢሳ. 42÷5

4ኛ ሁሉን ለሚችል ለሥልጣንህ አይሳነውምና ቍጡ የሆኑ አንበሶችንና ብዙ ጅቦችን ታመጣባቸው ዘንድ እምነበ አልቦ ዓለምን ለፈጠረች ለሥልጣንህ አይሳናትምና መጽ.ጥበብ. 11÷18።

www.zeyeneta.com

5ኛ ዓለሙን ሁሉ ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ፈጠረ። ኮረብቶችንና ተራሮችንም ፈጽሞ አዘጋጀ ምድርንም በውሃ ላይ አጸናት፣ ባሕርም እንዳትናወጥ በአሸዋ ወሰናት።

እግዚአብሔር በመጀመሪያ ቃሉ ብርሃን ይሁን አለ። መጽ.መቃ. ቀዳማዊ 27÷1

6ኛ ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ የፈጠረህ እግዚአብሔር አይደለምን? መጽ.መቃ. ቀዳማዊ 7÷2

7ኛ የፈጠራችሁ እግዚአብሔርን የማታውቁ...ወዮላችሁ... መጽ.መቃ. ካልዕ 7÷1

እነዚህ ቃላት የሁሉም ፍጥረታት ባለቤት እግዚአብሔር መሆኑን ነው የሚያስረዱን።

8ኛ እግዚአብሔርን የማወቅ ጉድለት በልቡናቸው ያለባቸው ሰዎች ሁሉ በእውነት ከንቱ ናቸውና በእነዚህ በሚታዩ ፍጥረቶች በዚህ ዓለም የሚኖር እርሱን ያውቁ ዘንድ ተሳናቸው።

ሥራውንም እያዩ ፈጣሪአቸውን አላወቁም....ፀሓይንና ጨረቃን አይተው የፈጠራቸውን ይወቁ። መጽ ጥበብ 13÷1።

9ኛ እንሰሶችን ጠይቅ ያስተምሩሃል፣ የሰማይንም ወፎች ጠይቅ ይነግሩሃል....የእግዚአብሔር እጅ ይህን እንዳደረገ÷

ከእነዚህ ሁሉ ይህን የማያውቅ ማን ነው? ኢዮብ 12÷7 ጀምሮ በሰፊው እንመለከተው።

10 <<ሰማያት ይነግራ ስብሐተ እግዚአብሔር>> ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ÷

የሰማይ ጠፈርም የእጁን ሥራያወራል፣ መዝ. 18÷1

11 ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ታይቶ የማይታወቅ እግዚአብሔር ለፍጥረቱ በስነ ፍጥረቱ ይታወቃል። ሮሜ. 1÷19

እግዚአብሔር በፍጥረቱ እንደሚታወቅ ሲገልጽ ነው።

12 እግዚአብሔር አምላክ ሙሴን በስድስተኛው ቀን ፍጥረቱን ሁሉ ፈጥሮ እንደጨረሰ፣ በሰባተኛይቱ ቀን እንዳረፈ፣ ከዕለታትም ሁሉ እንደለያት፣ ለሥራውም ሁሉ ምልክት አድርጎ እንዳኖራት ጻፍ አለው።

(ስለ ቀዳሚት ሰንበትም ነው)። መጽ. ኩፋሌ 2÷4።

ስለ ስነ ፍጥረት መጽሐፈ ኩፋሌን ከምዕራፍ 2÷1 ጀምሮ እንመልከት።

13 የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው። መዝ. 110÷10, ምሳ. 1÷7።

እግዚአብሔር ማለት የባሕርይ ስም ሆኖ÷ ትርጉሙ የባሕርይ አምላክ፣ የተፈጥሮ ሁሉ ባለቤት፣ ፈጣሪ፣ ገዥ ማለት ነው።

ይኸውም÷እኔ የአባትህ አምላክ÷ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅም አምላክ፣ የያዕቆብም አምላክ ነኝ ብሏል እግዚአብሔር በዘፀ. 3÷6

14 በምንም የማይወሰን ዘለዓለማዊ የሆነ የባሕርይ አምላክ እግዚአብሔር በሁሉ አለ።

ይኸውም÷ ነቢዩ ዳዊት ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ አለህ፣ ወደ ሲኦልም ብወርድ በዚያ አለህ ብሎታል። መዝ. 138÷7

15 እኔ የቅርብ አምላክ ነኝ እንጂ የሩቅ አምላክ አይደለሁም÷ ሰው በስውር ቢሸሸግ አላየውምን? ሰማይንና ምድርን የሞላሁ እኔ አይደለሁምን? ይላል እግዚአብሔር ኤር. 23÷23።

16 አቤቱ ለትውልድ ሁሉ አንተ መጠጊያ ሆንህልን፣ ተራሮች ሳይወለዱ፣ ምድር ዓለምም ሳይሠሩ÷ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም አንተ ነህ። መዝ. 89÷1, ዮሐ 1÷1

አምላካችን እግዚአብሔር ከሁሉም ፍጥረት አስቀድሞ የነበረ መሆኑን ያመሠጥራል።

www.zeyeneta.com

አዎ እግዚአብሔር ከዓለምና ከፍጥረት ሁሉ አስቀድሞ የነበረ፣ ያለ፣ የሚኖር ነው።

17 በእግዚአብሔር ያመኑ ሰዎች ፍራትና ድንጋጤ የለባቸውም። መጽ. መቃ.ሣልስ 7፥1

18 በእግዚአብሔር አምኖ ያፈረ ሰው ማን ነው? ለምኖትስ ቸል ያለው ማን ነው? መጽ. መቃ.ሣልስ 7፥3

19 <<ወንሕነሰ እመነ ወአእመርነ ከመ አንተ ውእቱ ክርስቶስ ወልዱ ለእግዚአብሔር ሕያው>>

በግእዝ ነው።

ትርጉሙም፥ እኛስ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ እንደሆንህ አውቀን አምነናል።

ይህ በትርጓሜው መሠረት ተስተካክሎ የተገለጸው ቅዱስ ጴጥሮስ ለጌታችን የተናገረው ቃል ነው። ዮሐ 6፥67 ጀምሮ፥

20 በእምነታችሁ በሳነትን ጨምሩ። 2ኛ ጴጥ· 1፥5።

እምነትና ምግባር ስለማይለያዩ እምነታችሁን በመልካም ሥራ ግለጹ ማለቱ ነው።

21 እምነት፣ ተስፋና ፍቅር እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ፥ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው። 1ኛ ቆሮ 13፥13።

22 እግዚአብሔር ፍቅር ነውና ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያምንም። 1ኛ ዮሐ 4፥7,8 ጀምሮ

እምነት፣ ተስፋና ፍቅር በምሥጢር አንድ ሲሆኑ ከእነርሱም ደግሞ እውነተኛው ፍቅር የበለጠ መሆኑን ነው የሚያረጋግጥልን።

ጥቅሶቹ አንድ አንድ ማስተካከያና ማብራሪያ እየተደረገላቸው ከልዩ ልዩ ክፍል የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው።

ምዕራፍ 17፥

ሃይማኖት በተለይም ደግሞ የክርስትና እምነት መነሻው፥

የሃይማኖት ምንጭ (መነሻ) በቅዳሳት መጻሕፍት በብዙ ክፍል ከምትጠቀሰው፣ የምድር መካከል በመባልም ከምትታወቀው፥ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ፥ (የእግዚአብሔር ወገኖች) እንደሆኑ በልዩ ልዩ መንፈሳዊና ታሪካዊ መዛግብት የሚነገርላቸው ሕዝበ እስራኤል ከሚኖሩባት በመካከለኛው ምሥራቅ ከምትገኘው ከኢየሩሳሌም እንደሆነ ለሁላችንም ግልጽ ነው።

ምክንያቱም ኢየሩሳሌም ክልደተ ክርስቶስ በፊት፥ ማለትም እግዚአብሔር ከልደቱ በፊት ጀምሮ በምስጋና የሚታወቅባት፣ የእግዚአብሔር የምስጋና ሀገር የምትባል፥ አበውና የእግዚአብሔር መልእክተኞች ቅዱሳን ነቢያት በዙሪያዋ እየተንቀሳቀሱ ሲያስተምሩባት፣ ትንቢት ሲናገሩባት የነበረች፣ ብዙ ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉባት ከመሆኗም በተጨማሪ፥ መዝሙረኛው ነቢይ ዳዊት የዘመረው መዝሙር በግእዙ ሲጠቀስ፥ <<እግዚአብሔርስ ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ ዓለም፥ ወገብረ መድኃኒተ በማዕከለ ምድር>>

ትርጉሙ፥ እግዚአብሔርስ ከዓለም (ከፍጥረት ሁሉ) አስቀድሞ ንጉሥ ነው፣ <<በምድርም መካከል (በኢየሩሳሌም) መድኃኒትን አደረገ>> በማለት በመዝ 73፥12። አስቀድሞ ትንቢቱን በመናገር ምሥጢሩን ያመሠጠረባት፥ በኋላ ጊዜው ሲደርስም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ልዩ ልዩ አምላካዊ ሥራውን ሲሠራባት የነበረ፣ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ለፍጥረቱ ሁሉ ሕይወትን፣ ለመላ ዓለምም ፍጹም ሰላምን ለመስጠት የመረጣት፣ ቅዱሳን ሐዋርያትን ከተለያየ አካባቢ ጠርቶ በከህነታዊ መዓርግ (ሹመት) እየሾመ ለልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎት ያሠማራባት፣ በመጨረሻ ጊዜም የፈጠረውን ፍጥረት የሚያሰናብትባት የምድር መካከል ናት።

አዎ ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር ተከታዮችና አገልጋዮች ሐዋርያት፣ እንዲሁም በእነእርሱ እግር የተተኩ የእነእርሱ ተከታዮች የሆኑ አርድእት፣ (ተማሪዎች) ሊቃውንትም ሁሉ

www.zeyeneta.com

መንፈሳዊ ተልዕኮአችውን የሚጀምሩባት ከሌሎች ሀገሮች ይልቅ በልዩ መልክ የተመረጠች የሕይወት መስጫ፣ የሃይማኖትና የታሪክ ሀገር መሆኗ የታወቀ ነው። መዝ 73÷12 ትርጓሜውንም እንመልከተው። የክርስትና እምነትም ከኢየሩሳሌም ተነሥቶ ነው ከክርስቶስ ዕርገት በኋላ በክርስቶስ ተከታዮች ቅዱሳን ሐዋርያት አማካይነት ለመላ ዓለም የተዳረሰው ቅዱሳን ሐዋርያት ፈጣሪአቸው ኢየሱስ ክርስቶስን እየተከተሉ፣ ከእርሱ በቀጥታ የተቀበሉትን ንጹሕን ቃለ ወንጌል (የወንጌል ትምህርት) የዓለሙን መከራ በመቻል ዓለምን ዙረው ካስተማሩ በኋላ በልዩ ልዩ ተጋድሎ ቢያልፉም÷ ሃይማኖት በተለይም ደግሞ የክርስትና እምነትና ሥርዓቱ ሁሉ በእነእርሱ ተከታዮች አርድእትና (ተማሪዎቻቸው) አበው ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አማካይነት እየተስፋፋና እየተጠናከረ ቀጥሏል።

ክፍል 48÷

እምነት (ሃይማኖት) በኢትዮጵያ÷

የክርስትና ደሴት በመባል የምትታወቀው ኢትዮጵያ ሀገራችን ማንም አስተማሪና ምንም ጽሕፈት ካልነበረበት ጊዜ ጀምራና (በሕገ ልቡና) በዘመነ አሪት÷ (ከክርስቶስ ልደት በፊትም) እግዚአብሔርን የምታመልክ፣ ብሉይ ኪዳንን የተቀበለች የእምነት ሀገር እንደሆነች ቅዱሳት መጻሕፍትና በልዩ ልዩ ምሁራን የተዘገቡት የታሪክ መዛግብት የሚያስረዱ ከመሆናቸውም በተጨማሪ÷ እስከ አሁን ድረስ በሀገራችን ውስጥ እየተካሔደ የሚገኘው ሃይማኖታዊ ሥርዓትና ባህላዊ ልማድም ይህን ይጠቁማል።

ለምሳሌ÷

ሀ በብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት እንዳይበሉ ተለይተው የተከለከሉ እንስሳት÷

ለ ቀዳሚት ሰንበትን ጨምሮ የበዓላትና የታኮታት አከባበር፣

ሐ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት፣

መ የአገልጋዮች አለባበስና ሥነ ሥርዓቱ÷

ሠ ጾም፣ ግዝረትና የመሳሰለው ሁሉ÷

(ፍትሕ መንፈሳዊ { ፍታ ነገሥት} እንመልከት)

እንደዚሁም ደግሞ በግብረ ሐዋርያት (በሐዋርያት ሥራ) 8÷26 ጀምሮ እንደምንመለከተው ሀገሪቱ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥ የነበረ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በ34 ዓመተ ምሕረት ወደ ኢየሩሳሌም የሔደው÷ ቅዱሳት መካናትን ለመሳለም፣ ለመጸለይ፣ ለመስገድ፣ ሃይማኖትን ለማስፋፋት ለመማርና ለመመራመር ስለሆነ ኢትዮጵያ ሀገራችን ከዚያም በፊት የእምነት ሀገር እንደነበረች ያስረዳናል።

ምክንያቱም ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ሃይማኖታዊ በመሆኑ ነው የሃይማኖትን ሥራ ለመሥራት ከሀገሩ ከኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም የሔደው። ግብ ሐዋ (የሐ ሥራ) 8÷26 እንመልከት።

ምዕራፍ 18÷

ክርስትና (ጥምቀተ ክርስትና)

ክርስትና ማለት በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቆ ስመ ክርስትናን መቀበል ክርስቲያናዊ የክርስቶስ ወገን መባል÷ የመንፈስ ቅዱስ ልጅ መሆን ማለት እንደሆነ በቦታው ተገልጿል።

አዎ በዚሁ መጽሐፍ ጥምቀት በሚል ክፍል በሰፊው እንደተገለጸው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ (ከአብራክ መንፈስ ቅዱስ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ) ካልተወለደ÷ ማለትም እኛን ልጅነት የምታሰጠውን ጥምቀት በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም በውሃ ካልተጠመቀ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ልጅ እንደማይባልና ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር (ወደ መንግሥተ ሰማያትም) ፈጽሞ መግባት እንደማይችል÷ ፍጹም ድኅነትና ፍጹም ሕይወትም እንደማይኖረው በማይለወጥ ቃሉ የነገረን ሲሆን÷

በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አምኖ የተጠመቀ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ልጅ ይባላል።

በእግዚአብሔር ማኅበር ገብቶም በክርስቶስ አንድነት ይኖራል ማለት ነው። ማር 16÷16, ዮሐ 3÷5። እንመልከት።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በገላትያ ምዕ 3÷27 መልእክቱ÷

www.zeyeneta.com

በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ስለ ሆናችሁ ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ክርስቶስን ለብሳችኋልና በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁ ማለቱ፥ በካህኑ አማካይነት በመንፈስ ቅዳስ ስም በውሃ የምንጠመቀው ጥምቀት ከማኅፀነ ዮርዳኖስ ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ በሐዲስ ልደት ተወልደን የእግዚአብሔር ልጆች የምንባልበት፥ ስመ ክርስትናን የምናገኝበት፣ የክርስቶስ ወገኖች፣ ክርስቶሳውያን፣ ክርስቲያኖች መሆናችንን የምንታወቅበት ልዩ ስጦታችን መሆኑን ነው የሚያረጋግጥልን።

ክፍል 49፥

ክርስትና (ጥምቀተ ክርስትና) በኢትዮጵያ፥

ቅዳሳት መጻሕፍት፥ በተለይም ደግሞ ከላይ ከፍ ብሎ የተጠቀሰው የሐዋርያት ሥራ 8፥26 እንደሚያስረዳን የክርስትና እምነት ወደ ኢትዮጵያ ሀገራችን የገባው ከልደተ ክርስቶስ በኋላ በ34 ዓ ም መሆኑ ነው። (ጌታችን ባረገ በ14ኛው ዓመቱም ይባላል)

ይኸውም ፊልጶስ ባጠመቀው ከዚህ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ አማካይነት ሲሆን፥ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ የሃይማኖትን ሥርዓት አከናውኖ ከኢየሩሳሌም ወደ ሀገሩ ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሰ ክርስትናን ለሀገሩ ሕዝብ እንዳስተዋወቀና በኋላም ከ328 እስከ 340 ዓ ም አካባቢ በግብፅ ሊቀ ጳጳሳት (ፓትርያርክ) አባ አትናቴዎስ ተሹሞ የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ጳጳስ (አቡን) የሆነው ፍሬ ምናጦስ (አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን የተባለው) ሥርዓት ክርስትናውን ከ350 ዓ ም ጀምሮ በመላዋ የኢትዮጵያ ሀገራችን አካባቢ በትምህርትና በተግባር በይፋ እንዳስፋፋው በብዙ የታሪክ መጻሕፍት ተዘግቦ ይገኛል።

ፍሬ ምናጦስ በአብርሃና አጽብሓ ዘመነ መንግሥት ጊዜ ስለ ሃይማኖት ሥርዓት በግብፅ (እስክንድርያ) ከሃይማኖት መሪዎች ጋር እንዲወያይ ከአኩስም ቤተ መንግሥት የተላከው በ328 ዓ ም ገደማ ሲሆን፥ በ325 ዓ ም ወልድ ፍጡር በመለኮቱ በማለት የተነሣ የመጀመሪያ ከሐዲ አርዮስ አፍሪካውያን (ግብፃውያን) ብፁዓን አባቶች አባ አለእስክንድሮስና አባ አትናቴዎስ በተሾሙበት ክርክር ተረትቶ የተወገዘበት የኒቅያ ጉባኤ በሚካሔድባቸው ዓመታትና ወቅቶች መሆኑ ነው።

ፍሬ ምናጦስ ከአባ አለእስክንድሮስ ሞት በኋላ በምትኩ በተቀመጠው በአባ አትናቴዎስ የጵጵስናን ከህነታዊና አባታዊ መዓርግ ተሹሞ ወደ ኢትዮጵያ በተመለሰ ጊዜ ሥርዓተ ክርስትናን፣ ትምህርተ ወንጌልን፣ ሥርዓተ ቍርባንና ግብረ ክህነትን (የክህነት አገልግሎትን) በመላዋ ኢትዮጵያ እንደ አስፋፋና መንፈሳዊውን እንቅስቃሴ ሁሉ በሚገባ እንዳጠናከረ ይታመቃል።

ዲያቆናትንና ቀሳውስትንም በአንብሮተ እድ እየሾመ በልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎት ላይ መድቧል። ከኢትዮጵያውያን ምሁራን ጋር በመሆን የሳባውያን ፊደላት ለተጠቃሚዎች በሚያመች መልኩ እንዲዘጋጁ፣ ቅዳሳት መጻሕፍትም ከሱርስት፣ ከዕብራይስጥና ከፅርዕ ቋንቋ ወደ ግእዝ ቋንቋ እንዲተረጉሙ አድርጓል። በ350 ዓ ም ገደማ ክርስትና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት ሆነ ማለት ነው።

ስለዚህም ፍሬ ምናጦስ በኢትዮጵያ የነበረውን ልዩ የሆነ መንፈሳዊ ብርሃንን ስለ አንፀባረቀ በመልካም መንፈሳዊ አገልግሎቱና በሃይማኖታዊ አባትነቱ፥ በትጋቱና በሥራው ሁሉ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ትልቅ ተወዳጅነትንና የላቀ ክብርን አግኝቶ፥ <<አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን>> በሚል ስም ሊጠራ ችሏል።

(የሰላም አባት፣ ብርሃንን የሚገልጽ፣ ልዩ የሆነ መንፈሳዊ አባትና ሐዋርያ) ለማለት ነው።

<< ምንጭ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ>>
በብፁዕ አቡነ ጎርጎሬዎስ ሊቀ ጳጳስ

ይህ ሲባል ግን አባ ሰላማ በመንፈሳዊ አባትነቱና በሃይማኖታዊ መሪነቱ መሠረት በሀገራችን የነበረው የክርስትና እምነት በበለጠ እንዲስፋፋ የበኩሉን ጥረት አደረገ ለማለት ነው እንጂ ከላይ በሰፊው እንደተገለጸው ኢትዮጵያ ሀገራችን ከአባ ሰላማ በፊት፣ ከጥንቱም የእምነትና የክርስትና ሀገር ናት።

ስለዚህም መንፈሳዊ ታሪኩ አባ ሰላማ ኢትዮጵያን በሃይማኖት አቀናት ወይም የክርስትናን እምነት ወደ ኢትዮጵያ አመጣ ማለት እንዳልሆነ ሊታወቅ የሚገባው ይመስለኛል።

ትርፍ አስተያየት ነው።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ 19÷

ስለ ክርስትና እና እስልምና በዐጭሩ÷

የክርስትና እምነትና ሥርዓት ከእስልምና እምነትና ሥርዓት ጋር ምንም ግንኙነትም ሆነ ጎብረት የለውም።

ምክንያቱም እስላሞች የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት አያምኑም፣ ሥርዓታችንም ትክክል እንዳልሆነ ነው የሚገምቱ።

ዐላኽ አይወልድም፣ አይወለድም ስለሚሉ፥ ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ቢያውቁም እንኳ እነርሱ ነቢያችን መሓመድ እንደሚሉት ያለ ደግ ሰውና ተራ ፍጡር እንደሆነ ነው የሚያስተምሩ እንጂ የባሕርይ አምላክ፣ ፈጣሪ ወይም በእነእርሱ አጠራር ዐላኽ መሆኑን አምነው አይቀበሉም፣ እንደዚህ ብለውም አያስተምሩም።

ስለሆነም የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ (የእግዚአብሔር ወልድ ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለድ፣ ዓለምን ማዳኑና የባሕርይ አምላክነቱ÷ በአጠቃላይ ክርስቲያናዊ እምነት ለእስላሞች ፈጽሞ አይዋጥላቸውም፤ በእምነቱና በተከታዩ ክርስቲያን ላይም ቢሆን በጎ አመለካከት አላቸው ማለት አይቻልም።

እንዲያውም አንዳንድ የእስልምና እምነት ኃላፊዎችና ተከታዮቻቸው የሚመቻቸውን ወቅትንና ሁኔታዎችን እየተጠቀሙ በክርስትና እምነት ላይ ከፍተኛውን ዘመቻቸው እንደሚያካሒዱ በየጊዜው ከሚፈጸሙ አሳዛኝ የሆኑ ድርጊቶች መገንዘብ ይቻላል።

ለምሳሌም÷ እ.ኤ.አ. በ1443 በቊስጥንጥንያ የነበረው ሁኔታንና የግራኝ አሕመድ ታሪክን፣ እንዲሁም ስለ ቊስጥንጥንያ ታሪክ የሱሌ መልእክት 2ኛ እትም ገጽ 93 እና ሌሎችንም እንመልከት

የእስልምና እምነት በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካባቢ መሓመድ በተባለው የመካ ተወላጅ ተመሥርቶ ከ622 እስከ 630 ዓ ም በከፍተኛ ደረጃ እንደተስፋፋ ይነገራል።

የእምነቱ ዋና መሥራች መሓመድ በ630 ዓ ም መካን ከወረረና 308 የሚያህሉ በመካ ውስጥ የነበሩትንም ጣዖታት ካፈራረሰ በኋላ በ632 ዓ ም ገደማ ቢሞትም እምነቱ በጅሓድ መንፈስ ተጠናክሮ በመላው ዓለም በከፍተኛ ሁኔታ እየተሟሟፈ ይገኛል። የተከታዮቹ ኢኮኖሚያዊ ዐቅምና ሀብትም በቀላሉ የሚገመት አይመስለኝም።

ምዕራፍ 20÷

የክርስትና እምነት ክፍፍል ምክንያት÷

ይህ እንዲገለጽ ያስፈለገበት ምክንያትም እውነተኛው ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ መሠረታዊ ችግሩን በማወቅ ተገቢውን መንፈሳዊ ዝግጅት እንዲያደርግና ምን ጊዜም በጥንቃቄ እንዲኖር ለማስታወስ ታስቦ ነው።

በመሆኑም ቅዱሳን ሐዋርያት ከክርስቶስ በቀጥታ ተረክበው ያስተላለፉልን የክርስትና እምነት በእነእርሱ ተከታዮች አርድእትና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አባቶቻችን እየተመራ ትክክለኛውን ትምህርቱንና ሃይማኖታዊ ሥርዓቱንም ጠብቆ በአንድ መሥመር ሲሔድ የነበረ ሲሆን÷ ከጊዜ በኋላ ግን ከዚህ ቀጥሎ በሚሸው ሁኔታ ሊከፋፈል ችሎአል።

ክፍል 50÷

ጉባኤ ኒቅያ ስለ አርዮስ÷

1ኛ በሰሜን አፍሪካ ሊቢያ የተወለደ የተፋጻሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስ ደቀ መዝሙር የነበረ አርዮስ በመጽሐፈ ምሳሌ ያለውን ጥሬ ንባብ ቊንፅሉ በመውሰድ ወልድ በሥጋዌው÷ ማለትም ሰው በሆነ ጊዜ ባስመዘገበው ጽናትና ታዛዥነት ከአብ (ከእግዚአብሔር አብ ማለቱ ነው) በረከትንና ጸጋን በመቀበሉ ከሌሎች ፍጥረታት በልጦ የአምላክነትን ሱታፌ አገኘ እንጂ የአብ ፍጡርና ልጅ ነው። (ወልድ ፍጡር በመለኮቱ) በማለት በ325 ዓ ም ገደማ ከሕደቱን በአደባባይ ስለ ሰበከ።

በኒቅያ 318 ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንና አባቶች የተገኙበት ጉባኤ ተደርጎ የቅዱስ መጽሐፉን ትክክለኛ ትርጉም መሠረት በማድረግ እግዚአብሔር ወልድ ፍጥረቱን ለማዳን በማይመረመር አምላካዊ ጥበቡ ፍጹም ሰው ቢሆንም የእግዚአብሔር አብ ፍጡር ሳይሆን÷ 318 ሊቃውንት የተናገሩት በግእዝ ቋንቋ ሲጠቀስ÷ ፍ<ዘዕሩይ ምክሩ ምስለ አብ በመለኮቱ>> እንደሚል። ከባሕርይ አባቱ ከእግዚአብሔር አብ ጋር ዕኩል የሆነ ፍጹም የባሕርይ አምላክ፣ እንደ ባሕርይ አባቱ እንደ እግዚአብሔር

www.zeyeneta.com

አብ የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ፣ የአምልኮትና የስግደት ባለቤት መሆኑን በጉባኤው ፊት ተከራክረው ረቱት።

ከሰሕተቱ አልመለሰምስለ አለም አውግዘው ከሃይማኖታዊ ማኅበራቸው ለዩት።

እ.ኤ.ትዮ.አቆ. በ3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በ317 ዓ. ም ይላል።
የሉሴ መልአኩ 2ኛ እትም ገጽ 75።

ክፍል 51፥

ጉባኤ ቊስጥንጥንያ ስለ መቅዶንዮስ፥

2ኛ ከአርዮስ ቀጥሎ መቅዶንዮስ በ381 ዓ ም መንፈስ ቅዱስ ሕጹጽ ነው፥ ማለትም ከሦስቱ አካላት ከአብ፣ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ አንዱ (መንፈስ ቅዱስ) ሕጹጽ ነው (ከአብና ከወልድ ያንሳል) አካል የለውም በማለት በቊስጥንጥኒያ አካባቢ ተነሣ በ150 ሊቃውንት ተረታ።

ይህም ከክሕደቱ አልመለሰ ስለ አለ እንደ አርዮስ ተወገዘ።
እ.ኤ.ትዮ.አቆ. በ3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በ373 ዓ. ም ይላል።
የሉሴ መልአኩ 2ኛ እትም ገጽ 75።

ክፍል 52፥

ጉባኤ ኤፌሶን ስለ ንስጥሮስ፥

3ኛ ከመቅዶንዮስ ቀጥሎ ንስጥሮስ የተባለ የቊስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ የነበረ ሰው በ431 ዓ ም መለኮትንና ሥጋን ነጣጥሎ ባሕርይንና አካልን ከፋፍሎ የሰበከ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ ነው። ማለትም ከእመቤታችን ሥጋን በነሣ ጊዜ አካሉ ሁለት ሆነ።

ይኸውም በአንዱ አካሉ የእግዚአብሔር አብ ልጅ ሲሆን በአንዱ አካሉ ደግሞ የማርያም ልጅ ነው። አምላክ ከሰው ሊወለድ ስለ ማይችል ከድንግል ማርያም የተወለደው ዕሩቅ ብእሲ፥ እንደ እኛ ተራ ፍቡር ሰው ሲሆን በዮርዳኖስ ወንዝ በሚጠመቅበት ጊዜ ቃል ይህ የምወደው ልጄ ነው ብሎ ስለ አደረበት አምላክነትን አገኘ እንጂ ከዚያ በፊትስ አምላክ አልነበረም አለ።

በእርሱ አባባል ድንግል ማርያም የተራ ሰው እንጂ የአምላክ እናት አይደለችም ማለት ነው።

ስለ ሆነም በኤፌሶን ከተማ 200 ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንና አባቶች ሊቃነ ጳጳሳት የተገኙበት ጉባኤ ተደርጎ በውይይቱ አፈረ በክርክሩ ተረታ።

ይህም ተው ተሳስተሃልና ተመለስ ቢባል እንቢ አልመለስም ስለ አለ እንደመሰሉቹ ተወግዞ ከእውነተኛይቱ የሃይማኖት ኅብረት ተለየ።

ምንም እንኳን አንድ አንድ የተለያየ አመለካከት ሊኖር እንደሚችል ቢገመትም ይፋ የሆነ የሃይማኖት ክፍፍል ግን ስለ አልነበረ እስከዚህ ጊዜ ድረስ የመላው ዓለም ቤተ ክርስቲያን በአንድነት እየተጓዘች መምጣቷን ከታሪኩ እንረዳለን ማለት ነው።

እ.ኤ.ትዮ.አቆ. በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በ423 ዓ. ም ይላል።
የሉሴ መልአኩ 2ኛ እትም ገጽ 75።

ክፍል 53፥

ስለ ልዮን፥

4ኛ ከዚህ በኋላ በ451 ዓ ም ገደማ ልዮን የተባለ የሮማው ፓፓ የነበረ መርቅያንና ብርክልያን በተባሉት ኃያላን ገዥዎች ጎን ተጠግቶ ቅድም የተጠቀሰውን ሁለት ባሕርይ የሚለውን የንስጥሮስን ክሕደት በኬልቄዶንና አካባቢዋ እንዲሰፋፋ ጥረት አደረገ።

መልእክተኞችንም ወደ ሃይማኖት ጉባኤው ልኮ ግርግርን አስነሣ።

የነገሥቱን ዳላ የፈሩና አድር ባዮቹ ትምህርቱን ተቀብለው በተግባር ላይ ሲያውሉት እንደ እነዲዮስቆሮስ ያሉት ጠንካራ መንፈስ ያላቸው አባቶች ግን በኤፌሶን ጉባኤ የተካሔደውን ምሥጢር መሠረት በማድረግ የክሕደት ትምህርቱን ነቀፉ።

በአርሜኒያ፣ በሶርያ፣ በህንድና በመሳሰሉት የምሥራቅ ሀገራት አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙት ሊቃውንትና የቤተ ክርስቲያን አባቶችም እነዲዮስቆሮስን በመከተል የልዮንን ክሕደት ተቃወሙ።

የስሕተት ትምህርቱ እንዲታረምም የየበኩላቸውን አስተውጽኦ አደረጉ።

www.zeyeneta.com

ይሁን እንጂ ልዮን ከስሕተቱ የሚመለስ አልሆነም ምክንያቱም ልዮን የሥጋውያን ገዥዎችን ኃይል መከታ በማድረግ በዚሁ አቋሙ መቀጠል እንዳለበት ቆርጧልና።

በመሆኑም የዚህ እውነት ጠንካራ መሪና ዋና ተዋናይ ግብፃዊው (የእስክንድሪያ) ሊቀ ጳጳሳት ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ስለነበር፥ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ በትክክለኛ እምነቱ ጸንቶ እውነተኛይቱን ሃይማኖት መመሥከሩ እንደጥፋት ተቆጥሮበት ባድር ባዮች አሻጥርና፣ በሥጋውያን ገዥዎች ትእዛዝ ጥርሱ እስኪወልቅ ድረስ እንዲገረፍ፣ ጽሕሙም እንዲነጭ ተደርጎ እንደታሠረና በዚያው በዕሥር ቤቱም እንዳረፈ (እንደ ሞተ) መገፋቱና ሃይማኖታዊ ገድሉ ግን ለተከታዮቹ ሁሉ እንዲደርስ እንደ ተደረገ ስለሚታወቅ ሕያው የሆነ (የማይሞት) ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ታሪኩ ሲነገር ይኖራል።

በዚሁም ምክንያት፥ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት፥ ኢትዮጵያን ጨምሮ ማለት ነው እስክንድርያ (ግብጽ) አርመን፣ ህንድና ሶርያ ከዛን ጊዜ ጀምሮ ከሮምና ሮምን ከሚመስሉ ሁሉ ተቆራርጠው በውግዘት ተለያይተው ቀሩ።

አሁንም በኢኮኖሚና በልማት ረገድ ካልሆነ በስተቀር የእምነት፣ የሥርዓተ ሃይማኖትና የመንፈሳዊ አገልግሎት አፈጻጸም ጎብረት የለንም (አንድ ላይም አንቀድስም) ማለት ነው።

ክፍል 54፥

ስለ ማርቲን ሉተር፥

5ኛ ከዚህም በኋላ ማርቲን ሉተር የተባለ የጀርመን ተወላጅ ካቶሊካዊ መነኩሴ በ1483 ዓ ም አካባቢ ከካቶሊክ እምነት አፈንግጦ በመውጣት ከመሰሉቹ ጋር ሆኖ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን እምነትና ሥርዓት ለማሻሻል በሚል መነሻ የምዕራቡን የክርስትና እምነት እንዳነዋወጠው ይታወቃል።

ጀርመናዊው ማርቲን ሉተር ይዟቸው ከተነሣ ዓላማዎች መካከል ምንኩስና አያስፈልግም፣ ገዳማት መዘጋት አለባቸው፣ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ያስፈልጋታል፣ ቅዱሳን ስለማያማልዱ በማንኛውም የጸሎት ጊዜ የቅዱሳንን ስም መጥራት ተገቢ

አይደለም፣ ማንም ሰው መንፈስ ቅዱስን እንደመሰለው ሊተረጕመው ይችላል የሚሉ ይገኙባቸዋል።

በተለይም ማንም ሰው መንፈስ ቅዱስን ለራሱ እንደመሰለው ሊተረጕመው ይችላል የሚለው የጀርመናዊው ማርቲን ሉተር ዓላማ ብዙ ግለ ሰዎች በእየራሳቸው አመለካከት እየተነሡ፥ በመሰላቸውም ትርጉም እየሔዱ እንደ ተራ የሥራ ዕቅድና መስክ በእየአካባቢያቸው ብዙ የጸሎት ቤት እንዲከፍቱና እንዲሠይሙ፣ ከቁጥጥር ውጭ፣ ከቁጥር በላይ የሆኑ የተላያዩ የእምነት ተቋማትንም እንደፈለጉት እንዲያስፋፉና እንዲያራምዱ ብዙ መንገድ ከፍቷል ማለት ይቻላል።

ጀርመናዊው ማርቲን ሉተር በ1546 ዓ ም ገደማ ቢሞትም ከእርሱ ሞት በኋላ በእግሩ የተተካው ጆንክልቪን የተባለው ፈረንሳዊ የማርቲን ሉተር ዓላማን በማንገብ የምዕራቡን እምነት እየከፋፈለ እንደ መሰኖ ውሃ ወደ ፈለገው እንደወሰደውና በበለጠም እንዳንቀሳቀሰው ይነገራል።

(እ.ኤ.አ 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ይላል የሉሌ መልእኩ 2ኛ እትም ገጽ 94)

በተጨማሪም የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም ደረጃና በኢትዮጵያ፥ የብፁዕ አቡነ ጎርጎሬዎስንና የሉሌ መልእኩንም መጻሕፍት በሰፊው እንመልከት።

ክፍል 55፥

ስለ ሔንሪ ስምንተኛ፥

6ኛ የእንግሊዝ መሪ የነበረው ሔንሪ ስምንተኛ የተባለው ደግሞ የሕግ ሚስቱን ፈትቶ ሌላን ለማግባት በፈለገ ጊዜ የሃይማኖት መሪውን በወቅቱ የሮም ፓፓ የነበረውን ቢጠይቀው ሥርዓት አይደለም ስለ አለው በዚህ ምክንያት ተናዶ ከካቶሊክ እምነት አፈንግጦ በመውጣት በ17ኛ መቶ ክፍለ ዘመን የእንግሊካን ቸርች የሚል በሀገሩ በእንግሊዝ ውስጥ እንደ መሠረተ ይነገራል።

ይህ ሔንሪ ስምንተኛ የመሠረተው የእንግሊካን ቸርች ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በተከታዮቹ እየተስፋፋ አሁን ካለበት ደረጃ ላይ ደርሷል።

www.zeyeneta.com

ክፍል 56፦

ስለ አድቨንቲስት፦

7ኛ የአድቨንቲስት እምነትም በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዊልያም ሚለር በተባለው አሜሪካዊ አማካይነት ተመሥርቶ በብዙ አካባቢ እንደ ተስፋፋ ይታወቃል።

አድቨንቲስት ማለት ክርስቶስ ነገ ከነገ ወዲያ ይመጣል እየተባለ የሚሰበክበት አስደንጋጭ እምነት እንደሆነም ይነገራል።

የአድቨንቲስት እምነት በውስጡ ብዙ ክፍፍል አለበት ይባላል።

ከእነአርሱም መካከል ኮንሰርቫቲቭና ኢቫንጀሊካል የሚባሉ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፦ እንደዚሁም ሰንበት ቀዳሚት እንጂ የአይሁድ አይደለችም የሚሉ ዘሰበንዝ ደይ፣ አድቨንቲስት የሚባሉና ሌሎችም ይህን በመቃወም፣ የሰው ነፍስ እስከ ክርስቶስ ምጽአት ድረስ በመቃብር ውስጥ እንደምትቆይ የሚያምኑ እንደሚኖሩበት ይነገራል።

ክፍል 57፦

ስለ ጅሆቫ ዊትነስ (የየሆቫ ምስክሮች ነን ባዮች) {የመጽሐፍ ቅዱስ አጥኒዎች}

8ኛ ጅሆቫ ዊትነስ የተባለው እምነት ደግሞ እ አ አቆጣጠር በ1870 ዓ ም አሜሪካ ውስጥ ቻርልስ ራስል በተባለው አሜሪካዊ እንደ ተቋቋመ ይታወቃል።

ይህ እምነት ከአርዮስና ከመቅደንዮስ የእምነት አመለካከት ጋር ተቀራራቢነት እንዳለውና የእምነቱ ተከታዮችም በኢሳ ምዕራፍ 43፦10 የሚገኘውንና የመሰሰሉትንም የቅዱስ መጽሐፍ ጥራ ቃላትን እየቀነባበሱ እየያዙ የይሖዋ ምስክሮች የተባልን እኛ ነን በማለት ሁለት ሁለት እየሆኑ በእየተቋሙ፣ በየት/ቤቱ፦

በየሥፍራውና በየመንገዱ እየተዘዋወሩ፦ እንደዚሁም የግለ ሰቦችን ቤት እያንኳኩ ጽሑፋቸውን በማሰራጨት ብዙ የዋሆችን

ለማጥመድ እንደሚሞክሩና በእየጊዜው በተለያዩ ቋንቋዎች እያሳተሙም በብዙ ሚልዮን የሚቆጠር የማደናገሪያ ጽሑፋቸውን ለመላው ዓለም እንደሚበትኑ ይታወቃል።

ይህ እንቅስቃሴ አሁንም ለሁላችን እያጋጠመን ያለ በተግባር የምናየው ሐቅ ስለ ሆነ ምንም አያጠያይቅም።

ክፍል 58፦

ስለ በሐሁላ፦

9ኛ መሥራቹ ዓሊ መሐመድ የሚባል ግለ ሰብ እንደሆነ የሚገለጸው፦ የእምነት ቸለልተኝነት አለው (በእምነቱ ቸለልተኛ ነው) የሚባለው በሐሁላ የተባለ የእምነት ድርጅት ደግሞ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ እንደተቋቋመ ይታወቃል።

የዚህን እምነት አራማጆች ስለ እምነት ጥንቃቄን ማድረግ፣ ብዙ ማሰብና መከራከር ተገቢ አይደለም በማለት፣ ለአሁኑ ትውልድ ኢየሱስም ሆነ መሐመድ አላስፈላጊ መሆናቸውን እንደሚገልጹ ይነገራል።

የበሐሁላ እምነት ተከታዮች ከሁሉም የእምነት ዓይነቶች እያዩ ይህ ነው የሚሻል ብለው የሚያምኑበትን ብቻ እንደ አስፈላጊነቱ እያውጣጡ በመውሰድ እንደሚያራምዱትም ይገለጻል።

በሐሁላ ማለት ስብሐተ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር ምስጋና) ማለት ነው።

እንግዲህ እስከ አሁን ድረስ በከፍተኛ እንቅስቃሴአቸው ከታወቁት የእምነት ድርጅቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሲሆኑ፦ አሁን በዐሥሩ ለመግለጽ የማይመቹ በየጊዜው የሚመሠረቱ ከ22 ሺሕ በላይ የሚሆኑ በየበኩላቸው እኛ ብቻ ነን ትክክለኞች የሚሉ የተለያዩ የእምነት ድርጅቶች በዓለም ውስጥ እንዳሉ ይነገራል።

እነዚህ የእምነት ድርጅቶች በየጊዜው በቴክኖሎጂ እድገትና በሳይንሳዊ ፍልስፍና እንቅስቃሴ ላይ እየተመሠረቱ፦ አሁንም በልዩ ልዩ አመለካከት እየተከፋፈሉ በመቀጠል ላይ ስለ ሆኑ

www.zeyeneta.com

መጀመሪያቸው እንጂ ወዴት እንደሚሔዱና የትም እንደሚደርሱ መጨረሻቸው አይታወቅም።

እኛ ኢትዮጵያውያን ግን ከ3 ሺሕ ዓመት ብቻ ሳይሆን፥ ከዚያ በፊት፥ አስቀድሞም ቢሆን እግዚአብሔርን በእምነት ያላወቅንበት፣ ከእግዚአብሔር ተለይተን የኖርንበት ዘመን ስለሌለብንና አዲስ አማኞች ስለ አልሆን ማንም አስተማሪና ምንም መጻሕፍት ባልነበሩበት ዘመንም ፈጣሪአችን እግዚአብሔርን እያመለክንና እያመሰገን የኖርን ነን።

<u>አሞ እኛ ከ34 ዓ ም</u> ጀምሮም ጥምቀተ ክርስትናን የተቀበልን፣ ምን ጊዜም የማይለዋወጥ፣ የማይሸራረፍ በቀደምት አበውና በቅዱሳን ሐዋርያት የተመሠረተ፥ በመልካም ምግባር፥ በሠናይ ሥራ የሚገለጽ ትክክለኛ እምነት ያለን ከመሆናችንም በላይ በክርስቶስ ደም በጸናች አርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሥር የምንገኝ ሕዝበ ክርስቲያን ስለ ሆን፥ አሁን ክርስቶስን ተቀበልን በሚሉ አዲስ አማኞች የማታለያ ዘዴ ልንታለልና ልንደናገር አንችልም።

<u>ግብረ ሐዋርያት (የሐዋርያት ሥራ) 8፥26 እንመልከት።</u>

አሞ እኛ የክርስቶስ ወገኖች እውነተኞች ክርስቲያኖች ነን ስንል በእውነተኛው እምነታችን ጸንተን በቅዱሳን ሐዋርያት አማካይነት በቀጥታ ከጌታችን የተገኘውን በእውነተኞች ቅዱሳን አባቶቻችንና በቅዱሳት መጻሕፍት በትውፊት የተረከብነውን ሃይማኖታችንን ጥንታዊ ሥርዓቱንና መንፈሳዊ ባህሉን በመጠበቅ፣ በማስጠበቅ፤

መልካም ምግባር ሠናይ ሥራ በሚባለው በጸም በጸሎት በምጽዋት በትሕትና፣ በሰላም፣ በርኅራኄ፣ በእንድነትና በፍቅር ስለምንገልጽ ነው።

የሃይማኖት ትርጉሙ መልካም ሥራ እንደመሆኑ መጠን፥ ሃይማኖትን ከምግባር ጋር መያዝ ማለትም ይህ ነው።

ለዚህ እውነተኛ ሃይማኖታችን ማስፈጸሚያ የሚሆንም ቅዱሳት መጻሕፍትን እየጠቀሰ የሚያስረዳ፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት አድርጎ የተመደበ ሃይማኖታዊ ቀኖና አለን።

እዚህ ላይ ግን ከሁሉም በፊት ስለ ሃይማኖትና ስለ ሃይማኖታዊ ቀኖና ምሥጢር በተጣራ መንገድ ሰይቶ ማወቅ ተገቢ ይመስለኛል።

<u>ምዕራፍ 21፥</u>

<u>ሃይማኖት ወይም እምነት በሌላ አጠራርም ደግሞ ማለት፥</u>

<u>አም በዐሥሩ ለማስቀመጥ ሃይማኖት ወይም እምነት በሌላ አጠራርም ደግሞ የሚባለው</u> የእግዚአብሔርን አንድነትንና ሦስትነትን ጠንቅቆ በማወቅ፣ አንድነቱንና ሦስትነቱን ማመን፣ <u>ይኸውም ሥላሴ፥</u> አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ተብለው በመጠራት፥ የስም ሦስትነት ያላቸው፥ <u>ማለትም፥ በስም፣ በግብር፣ በአካል፥</u> ሦስት ሲሆኑ፥ <u>በባሕርይ፣ በመለኮት፣ (በአምላካዊ ሥራ) በሥልጣን፣ በህልውና፣ ፍጥረትን ሁሉ በመፍጠርና በመስለው</u> ግን አንድ ናቸው፣ <u>አሐዱ እግዚእ፥ አንድ ጌታ፣ አንድ እግዚአብሔር።</u>

ፍጹም አምላክ የሆነ ክርስቶስ በሥጋዌው (ፍጹም ሰው በመሆኑ) ምሥጢር፥ አንድ አካል፣ አንድ ባሕርይ፣ አንድ እግዚአብሔር እንደሆነ፥ **<<ዘሠረፀ እምአብ ዘእንበለ እም>>** ተዋሕዶቱ አምላካዊ ባሕርይ የሆነ ክርስቶስ ቅድመ ዓለም (ከዓለም ፍጥረት በፊት) ያለ እናት ከባሕርይ አባቱ፣ ከባሕርይ ሕይወቱ ከእግዚአብሔር አብ እንደተወለደ፥ <u><<ወዘተወልደ እማርያም እምቅድስት ድንግል ዘእንበለ ዘርዓ ብእሲ>></u> በኋላም ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ያለ አባት፣ ያለ ዘርዓ ብእሲ (ካለ ወንድ ዘር) በጎቱም ድንግልና ተፀንሶ፣ በጎቱም ድንግልና የተወለደ፥ ወልደ አብ፣ ወልደ ማርያም (የአብ ልጅ፣ የማርያም ልጅ) ተብሎ በተዋሕዶ የከበረ መሆኑን ማመን፥ <u>እግዚአብሔር የባሕርይ አምላክ፣</u> መሐሪ፣ ይቅር ባይ ስለ ሆነ በደላችንን ሁሉ ይቅር ብሎናል፣ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፣ በቀራንዮ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ አድኖናል ብሎ አምኖ ማሳመን፥ <u>ይህ ጎብስት</u> ጌታችን ሥጋዬን የበላ ደሜንም የጠጣ ለዘለዓለም ሕያው ሆኖ ይኖራል፣ ባለው መሠረት ስለ ዓለም ድኅነት፣ ስለ ስርየተ ኃጢኣት፣ ስለ እኛ ዘለዓለማዊ ሕይወት በቀራንዮ የተፈተተ ቅዱስ ሥጋ ነው።

<u>ወይኑም</u> የእኛን ኃጢኣት ለማስወገድ በቀራንዮ የፈሰሰ የክርስቶስ ክቡር ደም ነው። ፍጹም መድኃኒታችን ነው፤ ከዚህ በስተቀር ፍጹም ድኅነት የለም ብሎ ከልብ አምኖ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር

www.zeyeneta.com

ደሙንም ኃጢኣትን ተናዞ (ንስሓ ገብቶ) ከኃጢኣት ንጹሕ ሆኖ መቀበል ነው። ዮሐ 6÷53 እንደዚሁም ደግሞ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፣ መላእክት፣ ቅዱሳን፣ ጻድቃንና ሰማዕታት የእግዚአብሔር ወዳጆች የሆኑ ሁሉ በሕይወተ ሥጋ እያሉ በልዩ ልዩ ተጋድሎአቸው ከፈጣሪያቸው ከእግዚአብሔር በተቀበሉት የማይሻር አምላካዊ ቃለ ኪዳን (ቃል ኪዳን) መሠረት የሚያማልዱ መሆናቸውን ማመን÷ በቃል ኪዳናቸው፣ በጸሎታቸው፣ በረድኤታቸውና በበረከታቸው መማፀን ነው።

አም ሃይማኖት ወይም እምነት ማለት በዐጭሩ ሲገለጽ ይህ ነው

ክፍል 59÷

ስለ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን÷

ቀኖና ማለት በቀጥታ ሲተረጉም ሥርዓት ማለት ሲሆን÷ ቅዱሳት መጻሕፍትንንና ሃይማኖታችንን መሠረት በማድረግ የወጣ÷ የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ርእስ በሆነ ቅዱስ ሲኖዶስ በሚባል ጉባኤ የበላይ ኃላፊነት የሚጠበቅ የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ማስፈጸሚያ ነው።

ቀኖና ማለት የቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ አገልግሎት መተዳደሪያ ደምብም ነው።

ይኸውም ከ51 ዓ. ም ጀምሮ በቅዱሳን ሐዋርያት የተጀመረና ብዙ መንፈሳዊ ሥራም የተሠራበት እንደሆነ ይታወቃል። የሐዋ ሥራ 16÷4, 15÷1, ቈላስ 3÷5,2ኛ ተሰ 3÷6 እንመልከት

የቀኖና አስፈላጊነትም÷

1ኛ ቤተ ክርስቲያንንና ሕዝበ ክርስቲያንን በመንፈሳዊ ሥርዓት ለመምራት÷

2ኛ ቅዱሳት መጻሕፍትን በየጊዜው ከሚለዋወጡ የመናፍቃን ትምህርትና ጽሑፎች ለመለየት÷

3ኛ የቤተ ክርስቲያንን ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ አገልግሎት ሥርዓት ባለው መንገድ በአግባቡ ለማካሔድ÷

4ኛ መንፈሳዊያን በዐላትንና አጽዋማትን በውሳኔው መሠረት ለመፈጸም፣ ለማስፈጸም እንዲቻል ነው።

የቀኖና የምንጭ መጻሕፍት ከሚባሉ መካከልም÷

ቅዱስ መጽሐፍን መሠረት በማድረግ የተጻፉ÷ ቀኖና ሐዋርያት፣ ሥርዓተ ሐዋርያት፣ ሲኖዶስ ዘሐዋርያት፣ ፍታ ነገሥት፣ (ፍትሕ መንፈሳዊ) መልእክተ አትናቴዎስ የተሰኙት ይጠቡዋቸዋል።

በዚህም መሠረት የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አጠቃላይ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ አገልግሎት እየተከናወነ ይገኛል። ይኸውም ከላይ ከፍ ብሉ እንደተገለጸልን ቅዱሳን ሐዋርያት ለመንፈሳዊ አገልግሎታቸው ሲጠቀሙበት የነበረ÷ ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት አድርጎ የመጣ፣ በመንፈሳዊ ትውፊት የተረከብነው ስለ ሆነ በተገቢው መልክ ልንፈጽመው፣ ልንጠብቀውና ልናስጠብቀው የሚገባን ሃይማኖታዊ ሥርዓታችን ነው።

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታይ የሆነ ሁሉ ስለ ሃይማኖቱና ስለ ሃይማኖታዊ ቀኖናው አፈጻጸም ከእውነተኞች አባቶቻችንና መምህራን ጠይቆ መረዳት መብቱ ነው። የተገለጸለት ጉዳይ ካለም እንደዚህ ቢሆንስ? በማለት ትክክለኛ መስሎ የታየው ሐሳቡን በመጠይቃዊ አስተያየት መልክ÷ በትሕትና ሆኖ ኃላፊነቱ ለሚመለከታቸው አካላት ሊያቀርብ፣ ያልገባውንም ጠይቆ ሊረዳ÷ የተረዳውንም ሊያስረዳ ይችላል።

ነገር ግን ይህ ሃይማኖታዊ ቀኖና ወይም ሥርዓተ ሃይማኖት አሉ በሚባሉ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት እየተጠና እና እየተመረመረ÷ በብዙ አባቶች ጸሎትና ቡራኬ እየተደነገገ የሚጠበቅ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ሕግ ስለ ሆነ የጉባኤው (የሲኖዶሱ) አባላት የሆኑ አባቶች በምልዓተ ጉባኤያቸው በአንድነት በመሆን ተወያይተው፣ አጥንተው፣ አስጠንተው ከሚያሻሽሉት በስተቀር ማንም ሰው በተናጠል (ለብቻው ሆኖ) ወይም የሚፈልጋቸውን ውሑዳን (ጥቂት) ግለ ሰዎችን ሰብስቦ እንደፈለገው ሊቀንስበትም ሆነ ሊጨምርበት ፈጽሞ እንደማይችል የታወቀ ነው።

በእርግጥ ቅዱስ ሲኖዶስ በሚያካሒደው ጉባኤ ሁሉ ጳጳሳት ያልሆኑትንም ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንንና ልዩ ልዩ ምሁራንን ቢያሳትፍ የበለጠውን ውጤት ማምጣት እንደሚቻል ይታመናል።

(ሲኖዶስ ማለት ሃይማኖታዊ ጉባኤው ወይም የሃይማኖት ምክር ቤት ማለት ነው)።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ 22፥

ስለ ታቦትና መሠረታዊ ምሥጢሩ ዐጭር ማብራሪያ

ታቦት ቤተ አደረ ከሚል የግእዝ ግስ የሚገኝ ዘር ነው።

ትርጉሙም ማደሪያ የሚል ሆኖ የእግዚአብሔር ማደሪያ ማለት ነው።

ይኸውም እግዚአበሔር በእርሱ አድሮ የሚመሰገንበት፣ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ የሚፈተትበት፣ የእግዚአብሔር ስም የተጻፈበት ኃይልና ተአምርም የሚገለጽበት ነው።

መሠረታዊ አመጣጡ፣ መንፈሳዊ ምሥጢሩና ትርጉሙም ከዚህ ቀጥሎ በዐጭሩ ተገልጿል።

1ኛ መሠረታዊ አመጣጡ፥

ሀ መጀመሪያ እግዚአብሔር ለሙሴ እንደ ሰጠው፥ በዘፀ 24፥12

ለ ከግራር ዕንጨት እንዲሠራም በእግዚአብሔር የታዘዘ እንደሆነ፥ በዘፀ 25፥5, 37፥1

ሐ ንዋየ ቅድሳቱን የሚሠሩም በእግዚአብሔር የተመረጡ ጠቢባን እንደ ነበሩ፥ በዘፀ 31፥1

መ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን፥ የእግዚአብሔር ሕግና ትእዛዝ ያለባቸው መጀመሪያ በእግዚአብሔር ለሙሴ የተሰጡት ጽላቶች ወይም ታቦት በእግዚአብሔር የተጻፉና የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ እንደሆኑም፥ በዘፀ 24፥12, እና 32፥15 በሰፈው ተጽፏል።

(ጽላት ማለት የእግዚአብሔር ስም የተጻፈበት ቅዱስ ሠሌዳ ማለት ነው)

2ኛ ታቦቱ ሲሰጠው ከነበረው መፈሳዊ አገልግሎት ውስጥም፥

ሀ የሙሴና የእግዚአብሔር፣ የእግዚአብሔርና የእስራኤል መንፈሳዊ መገናኛ እንደ ነበርና፣

ለ ከጥንቱ ጀምሮ የምስጋናና የቃለ ኪዳን ቅዱስ ንዋይ (መሣሪያ) እንደሆነ፥ በዘፀ 25፥21

ሐ እንዲሁም የእግዚአብሔር ስም የተጻፈበትን ጽላት ወይም ቅዱስ ሠሌዳ የሚባለውን በውስጡ ሲይዝ እንደነበረም በዘፀ 40፥20 ተጠቅሷል።

ጠቅላላውን ታሪኩ 10 ቃላት ካሉበት ከዘፀ 20፥1 ጀምሮ እንመልከት፥ የታቦቱ መንፈሳዊ አግልግሎቱን መስጠትና የሙሴ በታቦቱ አማካይነት ከፈጣሪው ጋር መነጋገር በዘኅልቍ 7፥89 ጀምሮም እናገኛዋለን።

ለታቦት መስገድ እንደሚገባ ኢያሱ 7፥6 ለታቦቱ ክብርና አጀብ ማድረግ፥ መንፈሳዊ መዝሙርንም መዘመር ተገቢ እንደሆነም 2ኛ ሳሙ 6፥14 1ኛ ዜና መዋ 13፥8, 15፥28 ያስረዳናል።

የአሁኑ ታቦትን የሚመለከት መንፈሳዊ ሥርዓታችንም ሁሉ መሠረቱ ከዚህ የተወረሰ እንደሆነ ግልጽ ነው።

ስለ ክብሩ ሕዝቡ ከ2 ሺህ ክንድ በላይ ይርቁ ስለነበር አሁንም ታቦቱን መዳፈር አይገባም ኢያሱ 3፥4፣

የሚዳፈሩት እንደሚቀሰፉም 2ኛ ሳሙ 6፥6 1ኛ ዜና መዋ 13፥9 ጀምሮ እንመልከት።

3ኛ ታቦተ እግዚአብሔር ልዩ ልዩ ተአምራትን ያደርጋል።

ለምሳሌ፥ የዮርዳኖስን ባሕር በመክፈል ታይቷል። ኢያሱ 3፥11 ጀምሮ

የኢያርኮን ግንብ በማፍረስም ኃይሉንና ተአምራቱን ገልጿል። ኢያሱ 6፥6 ታቦተ እግዚአብሔር በካህናት ብቻ መያዝ እንደሚገባውም በኢያ 3፥11, 6፥6 ተዘግቧል።

www.zeyeneta.com

የእግዚአብሔር ታቦት ካህናት ተሸክመውት በልዩ ልዩ ዝማሬና በዕልልታ ፈጣሪያቸውን እግዚአብሔርን እያመሰገን ዑደትን ማድረግ ጠቃሚነቱና መሠረታዊ ታሪኩም በኢያሱ 6÷6 እናገኘዋለን።

የእግዚአብሔር ታቦት ከጣዖት የተለየ እንደሆነና በጣዖትም ላይ ኃይልንና ተአምራትን እንደሚያደርግም ተደጋግሞ በተግባር ላይ ታይቷል። 1ኛ ሳሙ 5÷1 ጀምሮ, 2ኛ ቆሮ 6÷16።

የማናቸውንም ምስል ቀርፀህ ለአንተ አታድርግ አትስገድለትም አታምልከውም ተብሎ በእግዚአብሔር የተነገረ ወይም የታዘዘው ደግሞ እግዚአብሔር እንደሆነ ታምኖበት ለሚቀመጥ ምስል÷ ይህ ነው ሁሉን ማድረግ የሚቻለው÷ የባሕርይ አምላክ ተብሎ ለሚመለከው ጣዖት ነው እንጂ እግዚአብሔር ለሚመሰገንበት የእግዚአብሔር ታቦት አይደለም። ዘፀ 20÷4, ዘዳ 4÷15,ኢሳ 40÷18

በጊዜያችን ያለው ታቦትም ምሥጢሩና ሥርዓቱ ከዚህ ተያይዞ የመጣ ሲሆን እንዲሁም እግዚአብሔር የሚመሰገንበት፣ የእግዚአብሔር ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደምም የሚፈተትበት የእግዚአብሔር ስምና ረቂቅ የሆነ ምሥጢራዊ ሥራም ያለበት ነው። ራዕየ ዮሐንስ 1÷17,11÷17።

በሰማይ ያለና በምድር የሚገኘው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስም የሚነፃፀሩ ሲሆኑ ሁለቱ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦትን በውስጣቸው እንደያዙ÷ ራዕየ ዮሐንስ 11÷19። ይገልጻል።
እኛም የፈጣሪያችንን ሕግንና መመሪያን ጠብቀን÷ ትሕትናን፣ የዋህነትን፣ ደግነትንና ይቅር ባይነትን ይዘን በእውነተኛው ፍቅር አንድ ሆነን ለሁሉም ዓለም ሰላም፣ ለእኛ ፍጹም ሕይወት በቀራንዮ በመስቀል ላይ የተፈተተውን የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋንና ክቡር ደምን የተቀበልን በመሆናችን÷ የእግዚአብሔርን አንድነቱንና ሦስትነቱን፣ መሐሪነቱን፣ ፍጹም ሕይወትነቱንና መድኃኒትነቱን እምነን ተጠምቀን የተቀበልነው ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ከእኛ ጋር ስለተዋሐደ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደምንባል የታወቀ ነው። 1ኛ ቆሮ 3÷16, 6÷19, 2ኛ ቆሮ 6÷16, ኤፌ2÷22, 1ኛ ጴጥ 2÷7 እንመልከት።

እንግዲህ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ሃይማኖታችንንና መንፈሳዊ ሥርዓታችን እውነተኛውን የእግዚአብሔር መንገድ ይዞ የመጣ ምንም ሳይበረዝ በዚሁ መልክ የተረከብነው አሁንም ትክክለኛውን መሠረቱ ይዞ፣ ሃይማኖታዊ ሥርዓቱንም ጠብቆ ነው እየሔደ ያለው።

ለዚህ ሁሉ ዋና ምንጭና መሠረት የሆኑት የብሉይ ቅዱሳት መጻሕፍትም እንዳልተሻሩ ራሱ ጌታችን ነግሮናል። ማቴ 5÷17

አዎ ቀደምት የእግዚአብሔር ወዳጆች አባቶቻችን እምነታቸውን በአግባቡ ሲፈጽሙ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት ሲያከብሩና ሲንከባከቡ፣ በታቦቱ አማካይነት የተለያየ ድልን ሲያደርጉ ሕገ እግዚአብሔር ለተጻፈበት፣ ስመ እግዚአብሔር ለተቀረፀበት ለታቦቱ ሲሰግዱ እንደነበሩ÷ እግዚአብሔርም በታቦቱ አድሮ ወይም በታቦቱ አማካይነት ልዩ ልዩ ኃይልንና ተአምራትን ሲያደርግ እንደነበር ቅደም ተከተሉን ጠብቆ በመጣው በትክክለኛው የቅዱስ መጽሐፍ ማስረጃ አይተናል። የቤተ ክርስቲያናችንንም ምሥጢር ተረድተናል።

እኛም ቀደም ሲል ከአበው፣ ቅዱሳን ነቢያት፣ በኋላም ከሐዋርያት ጀምሮ እስካለንበት ዘመን የደረሰውን፣ በመንፈሳዊ ትውፊት የተረከብነውን፣ ምንም ያልተቀላቀለበትን ሃማኖታችንንና መንፈሳዊ ባህላችንን መሠረት በማድረግ ሃይማኖታዊ አገልግሎታችንን፣ ስናከናውን ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን ስናመሰግን እንኖራለን።

እንኳን አማናዊ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ለሚፈተትበት የእግዚአብሔር ታቦት÷ ታቦቱ ለሚያርፍበት የእግዚአብሔር እግር ለቆመበት ስሙ ለሚጠራበት ቅዱስ መካን ስንሰግድ፣ መንፈሳዊ ሥርዓቱንም ስንፈጽም÷ አሁን በየደረጃው እንደተመለከትነው የብሉዩንና የሐዲሱን ቅዱስ መጽሐፍ መሠረት በማድረግ ነው እንጂ መናፍቃን እንደሚሉት ዝም ብለን በልማዳዊና ኋላ ቀርነት ባህል እየተጉተትን አይደለንም።

ንዋየ ቅድሳት በመባል የሚታወቁ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ የሚገኙት የምስጋና መሳሪያዎችም ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር ሲመሰገንባቸው የነበሩ ሲሆኑ ለእያንዳንዳቸው መሠረታዊ ሥጢር አላቸው። መዝ 131÷7,ሕዝ 46÷2 እንመልከት። ታድያ ግን የእምነታችን ተቃዋሚዎች፣ የሥርዓታችን ተጻራሪዎች የሆኑ በተለያየ ሁኔታ በየጊዜው የሚነሡ መናፍቃንና ተከታዮቻቸው ይህን ትክክለኛውን የጽድቅ መንገድ ባይቀበሉት፣ እያወቁም ሊያቃልሉትና ወደ ጎን ሊተዉት ቢሞክሩ የእነርሱ ችግር ስለ ሆነ የሚጐዱት እነርሱ ብቻ ናቸው።

ሆኖም ግን በተለያየ የማሰሳቻ ዘይያቸው እንዳያደናግሩን እኛን መስለው ከውስጣችን ገብተውም እንዳይበርዙን ነቃ ብለን ተገቢውን መንፈሳዊ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልገናል።

እንዲሁም ትክክለኛውን ሃይማኖታችንንና ሃይማኖታዊ ሥርዓታችንን÷ መንፈሳዊ ታሪካችንንና÷ ባህላችንንም ሁሉ ከጥንቱ ጠንቅቀን በማወቅ በተማርነው መሠረት መጽናት ይገባናል።

www.zeyenet.com

በተጨማሪም ከዚህ ቀጥሎው ያሉት ጥቅሶች እንመልከታቸው።

1ኛ እንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ጸንተህ ኑር። 2ኛ ጢሞ 3÷14

2ኛ እንግዲህስ ወንድሞች ሆይ ጸንታችሁ ቁሙ በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ። 2ኛ ተሰ 2÷15

3ኛ የእርሱን ግርማ አይተን እንጂ በብልኻት የተፈጠረውን ተረት ሳንከተል የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ኃይልንና መምጣትን አስታወቅናችሁ። 2ኛ ጴጥ 1÷16

4ኛ ይህን በመጀመሪያ እወቁ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም። 2ኛ ጴጥ 1÷20

5ኛ ከማያምኑ ጋር በማይመች መንገድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና፤ ብርሃንም ከጨለማ ጋር ተካፋይነት አለውን ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው? የእግዚአብሔር ታቦትንስ በጣዖት ቤት ውስጥ የሚያኖር ማን ነው? እኛ የሕያው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነንና። 2ኛ ቆሮ 6÷14÷

6ኛ የሚያናውጡአችሁ፤ የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ አንድ አንዶች አሉ። ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ÷ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን። አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁንም ሁለተኛ እላለሁ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን። ገላ 1÷7።

7ኛ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ÷ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ። ኤፌ 5÷19

8ኛ እርስበርሳችሁ በሰላም ሁኑ÷ ወንድሞች ሆይ እንለምናችኋለን (እንመክራችኋለን) ያለ ሥርዓት የሚሔዱትን ገሥጹላቸው...ሰውን ሁሉ ታገሡ፤ ማንም በሌላው በክፉ ፈንታ ክፉ እንዳይመልስ ተጠንቀቁ፤ ነገር ግን...ሁሉ ጊዜ ለሁሉም መልካሙን ለማድረግ ትጉ ሁሉ ጊዜ ደስ ይበላችሁ፤ ሳታቋርጡ ጸልዩ፤ በሁሉ አመስግኑ። 1ኛ ተሰ 5÷13።

ምዕራፍ 23÷

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ÷

የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ÷ ከልደቷ እስከ ዕርገቷ ያለው ምሥጢር በዐጭሩ ሲገለጽ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ይመስላል።

መግለጫና ማብራሪያ÷

<<ተፈሥሒ ፍሥሕት ኦ ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ>> ምልዕተ ክብር ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና÷ ደስ ይበልሽ። እግዚአብሔር ከሥጋሽ ሥጋን፤ ከነፍስሽም ነፍስን ነሥቶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ይሆናል። (ከአንቺ, ካንቺ ይወለዳል።)

<<ቃሉ ከሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 1÷28 የተወሰደ ሲሆን÷ ምሥጢሩም በአበው ትርጓሜ መሠረት ሲብራራ ነው>>።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ከሌላው ፍጥረት በተለየ መልኩ ከነልዮም ከገቢርም ሁሉ ድንግል፤ ንጽሕት፤ ፍጽምት ናት።

ይኸውም÷ ከሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አባቶቻችንና ከትርጓሜ ቅዳሳት መጻሕፍት ትክክለኛ ምሥጢር እንደምንገነዘበው፤ ከሴቶች መካከል ተለይታ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት ናት።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በአዳምና በሔዋን ከተፈጸመው እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ድርጊትና በዚሁም ምክንያት በላያቸው ላይ ወድቆ ጌታችን በመስቀል ተሰቅሎ እስከ ደመመሰሰው ድረስ ለትውልድ ሲተላለፍ ከነበረው ከፈጣሪ ከእግዚአብሔር አምላክ የሚያስርቅ (ከፈጣሪ ከሚያሸሽ) መርገምም ሆነ÷ በሔዋንና በዘሯ ላይ ከሚታየው ፃዕረ ወሊድ፤ እንዲሁም ሌላው ሥጋዊ ኅልዮ (ሐሳብ) ሥጋዊ ጠባይዕ (ሥጋዊ ባሕርይ) ሁሉ ፈጽማ ንጽሕት ናት፤ ነውርም ሆነ በዘመናችን ጥንተ አብሶ የሚባለው አላገኛትም፤ ፈጽሞም የለባትም።

www.zeyeneta.com

እንደዚሁም ከእግዚአብሔር በተቀበለችው የማይሻር የአማላጅነት ቃለ ኪዳን መሠረት በረከተ ሥጋንና በረከተ ነፍስን እያማለደች የምታሰጥ ናት።

አዎ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር ስለሌለ ዓለም ሳይፈጠር በጎሊና አምላክ (ታስባ)የነበረች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ገና ሳትወለድ ከእናቷ ማኅፀን ሳለች እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ከማንኛውም ነውርና የውርስ ኃጢኣት ጠብቆ ከሌሎች ንጹሓን የተለየች ንጽሕት ልዩ አድርጎ ፈጥሯታል።

ይህ በፍጡር ሊለካ የማይቻል፣ የማይመረመር የእግዚአብሔር አምላካዊ ጥበብና አምላካዊ ሥራ ነው።

ምክንያቱም ሌላው ፍጡር ሁሉ ምንም እንኳ ኃጢኣትን ከመሥራት የታቀበ ከኀቢር (በተግባር ከመፈጸም የተቆጠበ) ንጹሕ ቢሆንም በተፈጥሮአዊ ባሕርዩ እንደእርሷ ስለ አልሆነ ከተፈጥሯዊ ጎልዮ፥ ማለትም በሥጋዊ ጠባይዕ (በሥጋዊ ባሕርዩ) የዓለምን ጊዜያዊ ደስታ ከማሰብ ከቶ ንጹሕ ሊሆን አይችልም።

እርሷ ግን ከጎልዮም ከኀቢርም ማለትም በጎሊና (በልብ) ከማሰብም ሆነ በተግባር ከመፈጸም ሁሉ ንጽሕት ፍጽምት ናት።

ሰው ከመወለዱ በፊት በፈጣሪው በእግዚአብሔር ተመርጦ ለልዩ ልዩ ተግባር ሊመደብ እንደሚችል ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚያስረዱን ሁሉ እመቤታችን ገና ሳትወለድ ከእናቷ ማኅፀን ጀምራ በመንፈስ ቅዱስ ከማንኛውም ነውርና የውርስ ኃጢኣት ተጠብቃ ለአምላክ እናትነት የተመረጠች ናት።

ይኸውም፥ እግዚአብሔር አምላክ ደኃሳች ሰዎችን አስቀድሞ እንደሚያውቅና ለመልካም ተግባርም በብዙ ክፍል ሊመርጣቸው እንደሚችል እንረዳለን።

ለምሳሌ ኤርምያስን በኾድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ፣ ከማኅፀን ሳትወጣም ቀድሼሃለሁ፣ ለአሕዛብም ነቢይን አድርጌሃለሁ ብሎታል። <u>ኤር 1÷4</u> ይህ ቃል ገና ከእናታችን ማኅፀን ሳለን፣ ከመወለዳችን በፊት አስቀድሞ ምን ዓይነት ባሕርይ እንዳለን በፈጣሪአችን በእግዚአብሔር ዘንድ እንደምንታወቅ፣ ፈጣሪአችን ከማንኛውም ኃጢኣት ጠብቆ፣ ባርኮ፣ ቀድሶም ለእርሱ መልካም አገልግሎት፣ ለጽድቅ ሥራ ሊመድበን እንደሚችል ነው የሚያስረዳን።

ነቢዩ ዳዊትም አንተ ግን ከኾድ አውጥተኸኛልና በእናቴ ሳለሁም ባንተ ታመንሁ፣ ከማኅፀን ጀምሮ ባንተ ላይ ተጣልሁ፣ ከእናቴ ኾድ ጀምረህ አንተ አምላኬ ነህ ብሎአል። <u>መዝ 21÷9።</u>

በመዝሙር መቶ ሰላሳ ስምንት ከቍጥር አንድ ጀምሮም <<አቤቱ መረመርኸኝ አወቅኸኝም፣ አንተ መቀመጤንና መነሣቴን አወቅኸ፣ ሓሳቤን ሁሉ ከሩቅ አስተዋልኸ፣ ፍለጋዬን ዕረፍቴን አንተ መረመርኸ፣ መንገዶቼን ሁሉ ቀድመህ አወቅህ ያለ ሲሆን፥

በመዝሙር መቶ ሦስት ከቍጥር ሃያ አራትም አቤቱ ሥራህ እጅግ ነው ሁሉንም በጥበብ አደረግህ>> በማለት የባሕርይ አምላክነቱን በማመሥጠርና በማድነቅ ፈጣሪው እግዚአብሔርን አመስግኗል። <u>መዝ 138÷1, 103÷24።</u>

<u>ነቢይ ዳዊት ስሰ ኃጥኣን ሲገልጽም</u> ኃጥኣን ከማኅፀን ጀምረው ተለዩ፣ ከኾድም ጀምረው ሳቱ፣ ሐሰትንም ተናገሩ፣ ቍጣቸው እንደ እባብ መርዝ ነው ይላል። <u>መዝ 57÷3።</u>

ይህ ደግሞ ኃጥኣን ከእናታቸው ማኅፀን ሳሉ ጀምረው ክፎች እንደሆኑ በፈጣሪአቸው በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቁ መሆናቸውን ነው የሚገልጽልን።

አዎ የክሕደት፣ የክፋትና የተንኰል ተግባር አራማጆች የሆኑ መርዘኞች ሰዎች የኃጢኣትና የዓመፃ ጠበቆች መሆናቸው አስቀድመው በእግዚአብሔር ዘንድ ይታወቃሉ።

ስለሆነም በክፋትና በተንኰል ነፋስ የተሞሉ ሰዎች እግዚአብሔርንና ሰውን ሁሉ ሲያሳዝኑ ይኖራሉ፥ ጥራት ካለውና ጸጥ ብሎ ከሚኖረው ባሕረ መለኮት (እውነተኛው እምነት) እየገቡም፣ የኑፋቄንና የክሕደት ማዕበል እያስነሡ በትክክለኛ መንገድ የሚጓዘውን የእግዚአብሔር ሕዝብ ያውካሉ፣ አሳስፈላጊውን (ተገቢ ያልሆነውን) ነገር በማንቀሳቀስም አንዱን ከአንዱ ጋር ያጋጫሉ፣ ያልሆነውን እንደሆነ፣ ያልተደረገውንም እንደተደረገ አስመስለውእያወሩ፣ እያስወሩም፤ በአንድነትና በፍቅር የሚኖረውን ሕዝበ እግዚአብሔር ያበጣብጣሉ፣ የቤተ ክርስቲያንና የሕዝበ ክርስትያንን ሰላም ያደፈርሳሉ ማለት ነው።

በእግዚአብሔር አስቀድመው የተመረጡ ሕዝበ እግዚአብሔር ግን የእግዚአብሔር ማደሪያዎች፣ የሕይወት መሪዎች ናቸው፥ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ነው፥ እነርሱም ከእግዚአብሔር ጋር ሆነው እግዚአብሔር የሚወደውንና ሁሉም ሰው የሚጠቀምበትን መልካም ሥራ ይሠራሉ፣ ሰላማውያን በመሆናቸው ሁል ጊዜ የሰላምን መልእክት ሲያስተላልፉ ይኖራሉ ማለት ነው።
<u>መዝሙረ ዳዊት 21÷1, 57÷3, 88÷10, ሄኖክ 4÷15, ኤር 1÷4 እንመልከት።</u>

www.zeyeneta.com

በመሆኑም አብርሃምንና ሣራን፣ ዘካርያስንና ኤልሳቤጥን ሌሎችንም ለመልካም ሥራ የመረጠ፣ በዕድሜ ከሸመገሉ በኋላም ደጋጎች ልጆችን እንዲወልዱ ያደረገ እግዚአብሔር የሚሳነው ነገር ስለሌለ እመቤታችንን በድንጋሌ ሥጋ፣ በድንጋሌ ጎሊና ጠብቆ ለዚሁ ደረጃ አብቅቷታል። ዘፍጥ 17÷1, 18÷14 ጀምሮ።

ስለዚህም እመቤታችን አስቀድማ በአምላክ ጎሊና የነበረች፣ ገና ሳትወለድ ከእናቷ ማኅፀን ሳለች እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በአዳምና በሔዋን ምክንያት የመጣውና ለመላው ትውልድ ሲተላለፍ ከነበረው መርገምና የውርስ ኃጢኣት ሁሉ የጠበቃት፥ ሰማይና ምድር የማይችሉትን የባሕርይ አምላክ ባጭር ቁመቷ፣ በጠባብ ደረቷ እንድትሸከም፥ (የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንድትሆን) በአማላጅነቷ ለሚያምን፣ በቃል ኪዳኗም ለሚማፀን ፍጥረት ሁሉ የሕይወት መሠላል፣ ለኃጢኣት መደምሰሻ፣ ለመንግሥተ ሰማይት መውረሻ ድልድይ ሆና የተፈጠረች በልዩ የተመረጠች ፍጥረት ናት።

ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል አምላክን በድንግልና እንደምትወልድ በሚያበሥራት ጊዜ ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና አንቺ ከሴቶች መካከል ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽማለቱም፥ ከተቀደሱ፣ ከከበሩናከተባረኩ ይልቅ አንቺ ቅድስት፣ ንጽሕት፣ ልዩ ነሽ ሲል ነው። ሉቃ 1÷28

ምክንያቱም ከላይ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው በአዳምና በሔዋን የወደቀው የውርስ ኃጢኣትም ሆነ በሌሎች ሴቶች ላይ ያለው መርገምና ሥጋዊ ጠባይዕ (ባሕርይ) ወይም ጎልዮ በእርስዋ ላይ ግን ፈጽሞ የለም።

የመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ብሥራት ልብ ብለን ካስተዋልነው እመቤታችን ከእናቷ ማኅፀን ጀምራ በእግዚአብሔር የተመረጠች፣ ክብርት፣ ልዩ፣ ንጽሕት፣ ቅድስት፣ ቡርክት መሆኗን ነው እንጂ ወደ ፊት እንደምትሆን አይደለም የሚገልጽልን።

በመሆኑም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አምላክን ከመፅነሷ አስቀድማም ከውርስ ኃጢኣትና ከነውር ሁሉ ንጽሕት እንደሆነች በተገቢው መንገድ እንረዳለን።

<<አንጺሖ ኪያሃ፣ ቀዲሶ ሥጋሃ ኃደረ ላዕሌሃ>> (አንጺሖ ሥጋሃ ለማርያም ወረሰያ ድሉተ ለተወክፎ ቃለ አብ) ይላል። የማቴዎስ ወንጌል 1÷18 ትርጒሙ፥ አነጻትም ሲል ነውርና ኃጢኣት ኑሮባት ሳይሆን ጠበቃት (ከነውር ሁሉ ከለከላት) ማለት ነው ብሎ አመሥጥሮታል።

አዎ ሰማይን ያለ ምሰሶ ያቆመ፣ ምድርንም ያለ መሠረት ያፀና፣ እነኤርምያስንና እነዳዊትን ገና ሳይወለዱ ከእናታቸው ማኅፀን ሳሉ ለመልካም ሥራ ያዘጋጀ፣ እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ ስለሚችል ለእርሱ አንዳችም የሚሳነው ነገር የለምና እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ከተመረጡት የተመረጠች፣ ከከበሩት የከበረች ልዩ፣ ንጽሕት፣ ቅድስት ቡርክት አድርጎ ፈጥሯታል።
መዝ 135÷6 ይህን የሚቃወሙ ካሉ እግዚአብሔርን ሁሉን ማድረግ አይችልም እያሉ እንደሆኑ፣ የእግዚአብሔርን ከሃሊነትንና የባሕርይ አምላክነትን እየተቃወሙ መሆናቸውን በመረዳት ከሰሕተታቸው ተመልሰው ንስሓ ሊገቡ ይገባቸዋል።

ምክንያቱም ይህን ያደረገ እግዚአብሔር ስለ ሆነ የእግዚአብሔርን ከሃሊነት፥ ማለትም እግዚአብሔር አምላክ ለእመቤታችንም ሆነ ለሌሎች ቅዱሳን የሰጠውን የማይሻር የአማላጅነት፣ የረድኤት፣ የበረከትና የምሕረት ቃለ ኪዳንን (ቃል ኪዳንን) እንደናቁ፣ የእግዚአብሔርን ዘለዓለማዊ ስጦታ እንዳቃለሉ፣ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ አማላጅነት፣ ፍጹም ቅድስና እና ፍጹም ንጽሕና ላይ እንደቀለዱ፥ በአጠቃላይ በማቴዎስ ወንጌል ያለውን፥ በግእዙ ሲጠቀስ፥ <<ሰማይ ወምድር የኀልፍ ወቃልየሰ ኢየኀልፍ>> ሰማይ ከምድር ጋር (ሰማይና ምድር) ያልፋል ቃሌ ግን አያልፍም የሚለውን የማይሻር የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል ወደ ጎን እንደተው ይቆጠራል።

ዘፍጥ, 48÷16, ዘኅል 20÷16, መጽሐ, ኅበብ 4÷16, ማቴ 24÷35 እንመልከት፥ በሚገባ ካስተዋልን በእነዚህ ቅዱሳት ቃላት ውስጥ አማላጅነትንም የሚመለከት ምሥጢር ማግኘት እንችላለን።

አዎ ይህን የሚቃወሙ አንቺ ከሴቶች መካከል ተለይተሽ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለብሽ፥ በረከተ ሥጋን፣ በረከተ ነፍስን ከልጅሽ ከአየሱስ ክርስቶስ እያማለድሽ የምታሰጪ ነሽ የሚለውን የቅዱስ ወንጌሉን መሠረት አድርጎ በበቁ አበው ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ሲነገር የሚኖረውን ምሥጢረ መለኮትንና፥ ቅድስት ድንግል ማርያም አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና የወለደች ከአዳም ዘር የተላለፈ ኃጢኣት (በዘመናችን ጥንተ አብሶ የሚባለው) ያላገኛት፣ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌሰባት ናት ብሎ እንደ ኢትዮጵያ አቡነጠውር 1988 ዓ ም (1996) እምነት፣ ሥርዓተ አምልኮና የውጭ ግንኙነት በሚል መጽሐፍ ያረጋገጠውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ስላልተቀበሉ በእምነታቸው

www.zeyeneta.com

ከአርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን እምነትና ሥርዓተ አምልኮ ውጭ ናቸው ማለት ነው።

<<እምነት፣ ሥርዓተ አምልኮና የውጭ ግንኙነት ምዕራፍ 7፣ ገጽ 4>>

ክፍል 60፥

የእመቤታችን ሥርዐ ልደት በዐጭሩ ሲገለጽ፥

እመቤታችን በሕጋዊ ሩካቤ ከኢያቄምና ከሐና የተወለደች መሆኗ የታወቀ ነው።

ሥርዐ ልደቷም ከቤተ ክህነትና ከቤተ መንግሥት ነው። መዝ 86፥1 ትርጓሜው,ማቴ 1፥1 እንመልከት።

ይኸውም በሀብታቸው እጅግ ታዋቂነት የነበራቸው ቂክታ እና በጥሪቃ የሚባሉ ቅድመ አያቶቿ መክነው (ልጅ አልባ ሆነው) ሲኖሩ ልጅ እንዲሰጣቸው ፈጣሪአቸው እግዚአብሔርን በጸሎት ይማፀኑት ስለ ነበሩ ደግ ልጅን እንደሚወልዱ፥ እንዲያውም ከፍጡራን ሁሉ በላይ የምትሆን ልጅ (እመቤታችን) ከእነእርሱ ዘር መከከል እንደምትወለድ በራዕይ (በሕልም) አማካይነት አስቀድሞ እንደተጠቆመ ከመንፈሳዊ ታሪኩ መረዳት ይቻላል።

የራዕዩ (የሕልሙ) ሁኔታም፥

ነጭ እንቦሳ ከበረታቸው ስትወጣ፥ እንቦሳይቱ ስድስት እንቦሳዎችን ስትወልድ፣ ስድስተኛይቱም ጨረቃን ስትወልድ፣ ጨረቃ ደግሞ ፀሐይን ስትወልድ አዩና ወደ መፈክረ ሕልም (ወደ ሕልም ፈቺ) ሔደው ቢያስፈቱት (ቢያስተረጕሙት) ሕልም ፈቺው ከፍጡራን ሁሉ በላይ የምትሆን ደግ ልጅን እንደሚወልዱ ጠቆማቸው። የፀሐዩ ነገር ግን ስለ አልተገለጸለት አልተረጐመላቸውምና ጊዜ ይተርጕመው በማለት ወደ ቤታቸው ተመለሱ።

ከዚያም በኋላ ሄኤሜንን እንደ ወለዱና በሰባተኛው ትውልድም የእመቤታችን እናት ሐና እንደተወለደች ይታወቃል። የእመቤታችን እናት ሐና አካለ መጠን ስትደርስ ከይሁዳ

ዘር ለተወለደው በደግነቱ እጅግ ለታወቀው ኢያቄም ለሚባለው ደግ ሰው ብትጋባም በእመቤታችን ቅድመ አያቶች የነበረ ምክነት በኢያቄም እና በሐና ላይም ስለቀጠለ ኢያቄምና ሐና መካኖች (ልጅ አልባ) ሆኑ ማለት ነው።

ስለዚህም በዘመኑ በነበረው ሥርዓት መሠረት እግዚአብሔር የተጣላቸው ርጉማን እንደሆኑ ተቆጥረው ከማንኛውም መንፈሳዊ በረከትና ማኅበራዊ ተሳትፎ እንዲገለሉ ይደረግ ነበር።

የዘመኑ አገልጋዮችም (ካህናተ አሮትም) እግዚአብሔር የመካኖችን መባ ስለማይፈቅድ (ስለ ማይወድ) እናንተ እግዚአብሔር ልጅን የነሣችሁ መካኖች በመሆናችሁ መባችሁን መቀበል እንችልም እያሉ ያሳዝኑዋቸው እንደ ነበር ይነገራል።

በመሆኑም ኢያቄምና ሐና ልጅን እንዲሰጣቸው እግዚአብሔርን ሁል ጊዜ በጎዘንና በልቅሶም ጭምር ይለምኑት ነበር ማለት ነው። በተለይም ከዕለታት አንድ ቀን ወደ ቤተ እግዚአብሔር (ወደ ጸሎት ቤት) በመሔድ ልጅን እንዲሰጣቸው ፈጣሪአቸውን አጥብቀው በጸሎት ተማፅነው የሚወልዱት ልጅ ወንድም ይሁን ሴት የእግዚአብሔር አገልጋይ እንጂ የእነእርሱ አገልጋይ እንዲሆን ፈጽመው እንደማይፈልጉ ቃል በመግባት ወደ ቤታቸው ተመለሱና በሐምሌ ወር (እንደ እኛ ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር ሐምሌ 30 ቀን) ሐና የኢያቄም ማቆሚያ መልካም ፍሬ አፍርታ ፍጥረት ሁሉ ሲመገባት፥ ለእርሱም ፀምር ሲያስታጥቁት በሕልም እንዳየች ለኢያቄም ነገረችው።

(ፀምር ማለት ከልዩ ልዩ እንስሳት፥ በተለይም ደግሞ ከበግ ፀጉር የሚሠራ በክብር ጊዜ የሚለበስ ለስላሳና ምቹ የሆነ ልዩ የሐር ልብስ ነው) (ኢዮብ 31፥20, ሕዝ 34፥3, 44፥17, ራዕ ዮሐ 1፥14 እንመልከት)

ኢያቄምም ነጭ ርግብ ሰባቱን ሰማያት ሰንጥቃ መጥታ በሐና ራስ ላይ ስታርፍ በቀኝ ጆሯ ገብታም በማኅፀኗ ስታድር እንዳየ ለሐና ነገራትና ሁለቱም በዚሁ አስደናቂ ምሥጢር ከተወያዩ በኋላ ወደ መፈክረ ሕልም (ወደ ሕልም ፈቺው) ሔደው ጠየቁት። መፈክረ ሕልም (ሕልም ፈቺውም) ደግ ልጅን እንደሚወልዱ ለመግለጽ ሞከረ። እነርሱም ምንም እንኳን ነግሩን በቀጥታ ባይቀበሉትም ፍጻሜው ግን አልቀረም።

በነሐሴ ወር መልአክ እግዚአብሔር ኢያቄምና ሐና ደግ ልጅን (እመቤታችንን) እንደሚወልዱ ነግሮዋቸው እመቤታችን (እንደ እኛ

www.zeyeneta.com

ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር) ነሐሴ 7 ቀን ተፀንሳ ግንቦት 1 ቀን ተወለደች ማለት ነው።

እመቤታችን ገና ሳትወለድ ከእናቷ ከሐና ማኅፀን እያለች ጀምሮ ብዙ ሕመማን የሐናን አካል (ሰውነት) እየዳሰሱ ከደዌያቸው ይፈወሱ እንደነበር ቅዱስ የሆነ መንፈሳዊ ታሪኩ ይናገራል።

እመቤታችን ሦስት ዓመት ሲሞላት ወላጆቿ ኢያቄምና ሐና በተሳሉት ስዕለት መሠረት ቤተ እግዚአብሔርን እንድታገለግል ከቤታቸው አውጥተው በዘመኑ በነበሩት ካህናት አማካይነት ለቤተ እግዚአብሔር ስለአስረከቧት ሐርንና ወርቅን እያስማማች እየፈተለች፣ እየሠራች፣ ቤተ እግዚአብሔርን እያገለገለች 12 ዓመት በንጽሕና፣ በክብርና በድንግልና ተጠብቃ በቤተ መቅደስ ኖረች።

ከዚህ በኋላም ዮሴፍ በተባለው ደግ የእግዚአብሔር ታማኝ ሰው አማካይነት በክብርና በንጽሕና እንድትጠበቅ ካህናቱና ሕዝብ ስለ ወሰኑ በዚሁ ሁኔታ ላይ እያለች መልአከ እግዚአብሔር ወደ እርሷ መጥቶ (ገብቶ) ደስ ይበልሽ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፣ አንቺ ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ÷ ማለትም እግዚአብሔር ከሥጋሽ ሥጋን ከነፍስሽም ነፍስን ነሥቶ (ተዋሕዶ) አንድ አካል አንድ ባሕርይ ይሆናልና (ከአንቺ ይወለዳልና) በነቢያት ትንቢት በመላእክት ተልእኮ ደስ ያለሽ ምልዕተ ክብር ሆይ፤ <<ተፈሥሒ>> ደስ ይበልሽ ብሎ ባበሠራት መሠረት የፍጥረት ሁሉ መድኃኒት÷ ለታጥላን ተስፋችንና ሕይወታችን የሆነውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በድንግልና ጸንሳ በድንግልና ወለደችልን።

ለሰው ልጆች ሁላችን የይቅርታ ፀወንና የምሕረት መሰላል፣ የመንግሥተ ሰማያት ድልድይ ሆነች ማለት ነው።

ከዚህም በኋላ በስደት መከራና በልዩ ልዩ ጎዘን ቆይታ በ64 ዓመት ዕድሜዋ ጥር 21 ቀን ዓርፋ ወደ ባነት ተወሰደች። በአባቶች ሐዋርያት ጸሎትና ልመና ተመልሳ መጥታም ነሐሴ 15 ቀን ሐዋርያት ቀብሯት ነሐሴ 16 ቀን ከመቃብር ተነሥታ በክብርና በልዩ ልዩ ምስጋና ወደ ሰማይ ዐረገች።

ስድሳ አራት ዕድሜዋ ሲተነተንም÷ በናት በአባቷ 3 ዓመት፣ በቤተ መቅደስ 12 ዓመት፣ በቤተ ዮሴፍ 9 ወር፣ ከልጅዋ ጋር በስደትና በልዩ ልዩ ቦታ 33 ዓመት ከ 3 ወር፣ በቤተ ዮሐንስ (ከዮሐንስ ጋር) 15 ዓመት ጠቅላላ ዕድሜዋ ሲደመር 64 ዓመት ይሆናል ማለት ነው።

ክፍል 61÷

ከዚህ ቀጥሎም ስለ ዕረፍቷ፣ ስለ ትንሣኤዋና ስለ ዕርገቷ÷ መሠረታዊ ዝርዝር በየደረጃው ባጭር ባጭሩ ይብራራል።

የእመቤታችን ዕረፍት÷

ሁል ጊዜ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የጥባኤ መድረክ እንደሚገለጸው እመቤታችን ጥር 21 ቀን ዓርፋ ሐዋርያት ሊቀብሯት ይዟት እየሔዱ እያሉ አይሁድ ከሐዋርያት እጅ ነጥቀው በእሳት ለማቃጠል በመወሰን ስለ ደረሱባቸው ሐዋርያት የአይሁድን ኃይለኛ ግስጋሴ በተመለከቱ ጊዜ ደንግጠው ትቷት ሸሽተው ነበርና በእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ እግዚአብሔር በጌታው እደራ የተባለው ዮሐንስም ከእርሷ ጋር ስለ ነበር ሁለቱን በደመና ነጥቆ በመውሰድ እመቤታችንን በግነት ከዕፀ ሕይወት ሥር እንዳኖራት ቅዱስ ታሪኩ ይገልጻል። ዮሐ 19÷26

ክፍል 62÷

ቀብሯ፣ ትንሣኤዋ፣ ፍልሰቷና ዕርገቷ÷ (ፍልሰታ ለማርያም)።

ሐዋርያት አይሁድ በደረሱባቸው ሰዓት ፈርተው ትቷት በመሔዳቸው አዝነው ከነሐሴ 1 ቀን ጀምረው ለሁለት ሰባት (ለ14 ቀናት ያህል) ሱባኤን በመያዝ ፈጣሪአቸው እግዚአብሔርን ስለ ለመኑ በ15ኛው ቀን እመቤታችንን አግኝተዋት በክብርና በምስጋና ስለቀበሯት በ3ኛው ቀን ከመቃብር ተነሥታ በልዩ ልዩ ምስጋና ወደ ሰማይ ዐረገች።

ከሞት ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት ፈለሰች፣ ተሰደደች ማለት ነው።

ይኸውም እመቤታችን ወደ ሰማይ በምታርግበት ጊዜ በቀብሯ ስነ ሥርዓት ያልተገኘ ቶማስ ሐዋርያ የበቃ ነውና ከሀገረ ስብከቱ በደመና ወደ ሐዋርያት ሲመጣ ከሰማይ ስለ ተገናኙ ደነገጠ። በቀብሯ ስነ ሥርዓት ባለመገኘቱም እጅግ አዘነ።

www.zeyeneta.com

እመቤታችን ግን እነርሱ ያሳዩትን ትንሣኤዎንና ዕርገቱን አንተ ብቻ አይተኻልና አይዞኽ አትዘን ብላ አረጋግታ፥ ማረጓን ለሐዋርያት እንዲነግራቸው፣ ለምልክትና ለበረከት እንዲሆናቸውም ተገንዛበት ከነበረው ሰበን ሰጥታ ሰደደቻው።

ቶማስም ወደ ሐዋርያት በመሔድ ያላወቀና ያላየ መስሎ ስለ እመቤታችን ጉዳይ ሐዋርያትን ጠየቃቸውና እኛስ አግኝተን ቀበርናት አንተ ግን ለዚህ አልታደልኽም አሉት።

እርሱም ይህማ እንደት ይሆናል ያረፈችው በጥር ወር አሁን ቀበርናት የምትሉት በነሐሴ ወር ማንስ በዚሁ ያምናል በማለት ለመከራከር ስለ ሞከረ አንተ ሁል ጊዜ ተጠራጣሪ ነኽ ድሮም ጌታችንን <<የተወጋኽውን ጎንህን ሳላይ አላምንም>> ብልኽው ነበር አሁንስ ለራስህ ተጠራጥረኽ (መናፍቅ ሆነህ) ሌላውንም ስታጠራጥር (ግራ ስታጋባ) ልትኖር ፈልገህ ነውን? በማለት መቃብሩን ከፍተው ሊያሳዩት ቢሞክሩ እመቤታችንን ከመቃብር ውስጥ አጡዋትና ደነገጡ።

ምናልባትም አይሁድ በሌሊት ሰርቀው ወስደዋት ይሆኑ? ብለው በመገመት ሊሆን ይችላል፥ አዘኑ ማለት ነው።

<<ስለ ቶማስ የጌታችንን ጎን መዳሰስ ወንጌለ ዮሐንስ 20፥24>>

ሐዋርያ ቶማስም በሉ አይዛችሁ አትደንግጡ እመቤታችንስ ዐርጋለች እኔ አግኝቻታለሁ ብሎ ምሥጢሩን ሁሉ እንደ ነገራቸው፤ ለምልክትና ለበረከት ይሆናቸው ዘንድ እንዲካፈሉት እመቤታችን የሰጠችውንም ሰበን እንደሰጣቸውና ሁሉም እንደ ተካፈሉት ታሪኩ ይናገራል።

(ሰበን እመቤታችን ተገንዛበት የነበረ ልዩ ልብስ ማለት ነው)

ከዚህ በኋላ ሐዋርያት ቶምስ ትንሣኤሽን አይቶ እኛ ግን ሳናይ ብለው ልክ እንደበፊቱ በነሐሴ 1 ቀን ሱባኤ ይዘው ጌታችንን በጸሎት ስለ ጠየቁ ነሐሴ 16 ቀን እመቤታችን መጥታ በግልጽ አይተዋት፥ ጌታችን እመቤታችንን እንደ መንበር፣ ቅዱስ ጴጥሮስ ሐዋርያን ተራዳዒ ካህን፣ ቅዱስ እስጢፋኖስ ሰማዕትንም ሠራዒ ዲያቆን አድርጎ ራሱ ቀድሶ እንዳቆረባቸው ቅዱስ የሆነ መንፈሳዊ ታሪኩ ያስረዳል።

<<ምንፌጩን ከውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም ትርጉም በስተመጨረሻው እንመልከት>>

ክፍል 63፥

ስለ ፍልሰትና ፍልሰታ ለማርያም መሠረታዊ ዝርዝር፥

በልሳነ ግእዝ (በግእዝ ቋንቋ) <<ፈለሰ>> ብሎ ተሰደደ ይላልና ፍልሰት ለሚለው ዘር ስደት የሚል ትርጉም ነው ሊኖረው የሚችል።

ትንታኔውና ምሥጢራዊ ትርጉሙ ደግሞ ከአንድ ሥፍራ ወደ ሌላ ቦታ መሰደድ ወይም ከሥር ጨርሶ መነቀል፣ መፍለስ፥ ማለት ነው።

ለወንድ ፈላሲ፣ ለሴት ደግሞ ፈላሲት ይባላል።
ትርጉሙ፥ ስደተኛ ማለት ነው።

የትርጉሙ ትንታኔም ፈላሲ ወይም ፈላሲት ማለት፥
ከአንዱ ሥፍራ ወደ ሌላው ሥፍራ በተለያየ ምክንያት የተሰደደ (የተሰደደች) ስደተኛ ማለት ሲሆን፥ ምሥጢሩ ሲራቀቅ ደግሞ ፍልሰት ማለት ከዚሁ ከጊዚያዊው የዓለም ደስታ መሰደድ ማለት ነው።

ፈላሲ ስደተኛ፣ የተሰደደ፥ ከቂም፣ ከበቀልና ከክፋት ሁሉ የራቀ፥ ጥሩ ጥሩን ከመብላት፣ ከመጠጣት መጸምን የመረጠ፣ ከኃጢአት ሥፍራ ወደ ጽድቅ ቦታ የተሰደደ፥ ከሞት ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት የተሸጋገረ፥ ከምድር ወደ ሰማይ ያረገ (የወጣ) ኃጢአትን ከመሥራት ይልቅ ጽድቅን መሥራት የወደደ፤

በአጠቃላይ ገንዘቡንና ንብረቱን ሁሉ ለእግዚአብሔር እንግዶች ለነዳያን መጽውቶ፣ ወይም ለቤተ እግዚአብሔር ሰጥቶ ከዚሁ ከኃላፊው፣ ከጠፊው የዓለም ተድላ ደስታ፥ ከምቾቱም ሁሉ ወደ መከራ የመነነ፥ የሚያስደስተውንና የሚያስጐመጀውን ሁሉ ለመንግሥተ ሰማያት ሲል ፈጽሞ የተወ የክርስቶስን መከራ መስቀል የተሸከመ ማለት ሊሆን ይችላል።

ይኽውም መጽሐፋዊ ምሥጢሩና መንፈሳዊ መልእክቱ ሁላችንንም ስለሚመለከት ብናደርገው መልካም ነው።

ይህን ብናደርግ የማያልፈውን ዘለዓለማዊውን ሕይወት ማግኘት እንችላለን ማለት ነው።

www.zeyeneta.com

ክፍል 64፥

ማጠቃለያ፥

የእመቤታችን ፍልሰተ ሥጋ (ፍልሰቷ) ስንልም ከዚህ በላይ ከመሠረቱ ጀምረን እንደተመለከትነው ከሞት ወደ ሕይወት የፈለሰችበት ከመቃብር ተነሥታ ወደ ሰማይ የወጣችበት፣ (ያረገችበት) ማለታችን ሲሆን፥ እኛ ሕዝበ ክርስቲያን ከእርሷ በረከት ለመሳተፍ፣ በእርሷ አማላጅነት ዘለዓለማዊ ሕይወትን ለማግኘት ስንል በየዓመቱ ከነሐሴ 1 ቀን ጀምሮ እስከ ነሐሴ 15 ቀን ድረስ የሚገኘውን ወቅት፥ ፈጣሪያችንን በማመስገን ለቃል ኪዳን እናታችን፣ ለአማላጃችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ልዩ ልዩ ዝማሬን በማቅረብ ሱባኤ ይዘን ለየት ባለ መልኩ እንጸመዋለን። ኃጢኣታችንን ይቅር እንዲለን ፈጥሪያችንን እንለምንበታለን። ሃይማኖታዊ ሥርዓታችንንና ክርስትያናዊ ግዴታችንንም እንፈጽምበታለን።

አዎ በአጠቃላይ ፍልሰትና በየዓመቱ ከነሐሴ 1 ቀን ጀምሮ ለ15 ቀናት ያህል እውነተኛው ክርስቲያን፣ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ወዳጅ የቃል ኪዳኗ ልጅ የሆነ ሁሉ በጸሎትና በልዩ ሱባኤ የሚጸመው ፍልሰታ (ፍልሰቷ) በመባል የሚታወቀው ትርጉሙና መሠረታዊ ምሥጢሩ በዐጭሩ ሲገለጽ ይህን ይመስላል።

የፍልሰታ ለማርያም ወቅትና ሳምንት ሁሉም እውነተኛው ሕዝበ ክርስቲያን የሚጸመው፥ ከእመቤታችን ጋር ያለውን የቃለ ኪዳን ትስስር በጾም፣ በጸሎትና በልዩ ልዩ ዝማሬ የሚገልጽበት ከሌላው ጊዜ የተለየ የሱባኤና የምስጋና ሳምንት ነው።

ይኸውም ለክርስቲያናዊ እምነታችንና ለሰማያዊ ተስፋችን እውነተኛ መታወቂያ ሲሆን፥ እኛ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ አማላጅነት፣ በእግዚአብሔር የባሕርይ አምላክነትና መሓሪነት የምናምን፥ በመላእክት ተራዳኢነት፣ በጸድቃንና በሰማዕታት በረከት ረድኤት፥እንዲሁም አማላጅነት የምንማፀን የእግዚአብሔር ቤተሰቦች መሆናችንን በተግባር የምናረጋግጥበት ወቅት ነው።

የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ አማላጅነት፣ የመላእክት ተራዳኢነት፣ የቅዱሳን፣ የጸድቃንና የሰማዕታት በረከት፣ ረድኤት፣ እንዲሁም አማላጅነት ሁል ጊዜ አይለየን።

በተጨማሪም ከዚህ ቀጥለው ያሉትን ጥቅሶች እንመልከታቸው፥

ግእዝ 1ኛ <<ኵላንታኪ ሠናይት እንተ ኀቤየ አልብኪ ነውር ወኢምንትኒ ላዕሌኪ>>

ትርጉሙ፥ ወዳጄ ሆይ ሁለንተናሽ ውብ ነው፥ ነውርም የለብሽም ይላል። መሐልየ (መኃልየ) ሰሎሞን 3 (4)፥7

ይህ እመቤታችን ምንም ነውር እንደሌለባት አስቀድሞ የተነገረ ነው።

2ኛ <<ናሁ እምይእዜሰ ያስተበፅዑኒ ኵሉ ትውልድ>> እነሆም ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል። (ከእንግዲህስ ወዲህ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል ይላል በትርጓሜው) ይህ ቅዱስ ቃል እመቤታችን ከእግዚአብሔር በታች በፍጥረት ሁሉ ስትመሰገን የምትኖር መሆኗን ነው የሚያረጋግጥልን። ሉቃ 1፥48

3ኛ ስለ አማላጅነቷም፥ ኢየሱስ እናቱን (ድንግል ማርያምን) ይወደው የነበረው ደቀ መዝሙሩን (ዮሐንስን) ባጠገቡ ቆሞ ባየ ጊዜ እንቺ ሴት እንሆ ልጅሽ አላት፣ ከዚህ በኋላም ደቀ መዝሙሩን እናትህ እነኋት አለው። ዮሐ 19፥26

እኛ ሕዝበ ክርስቲያንም በቃል ኪዳኗ ስለምንማፀን የእመቤታችን የአደራ ልጆች ነን ማለት ነው።

4ኛ <<ነቢይ (ጻድቅ) ነውና ስሰ አንተም ይጸልያል፣ ትድናለህም>> ይህን በልብህ ቅንነት እንዳደረግህ እኔ አወቅሁ፣ እኔ ደግሞ በፊቴ ኃጢኣትን እንዳትሠራ ከለከልሁህ። ዘፍ 20፥6,7

<<ቅዱስ ቃሉ ስለ አማላጅነትና በእግዚአብሔር ሕግ ከገቢረ>> ኃጢኣት (ኃጢኣትን ከማድረግ) ስለ መታቀብ ያስረዳል።

5ኛ ከክፉ ነገር ያዳነኝ መልአክ እርሱ እነዚህን ብላቴኖች ይባርክ። ዘፍ 48፥16,መዝ 33፥7።

6ኛ <<ኤልያስ እርሱ ባለበት ቤት የሞተውን ብላቴና በእግዚአብሔር ኃይል አሥነሣው>> 1ኛ ነገ 17፥22

7ኛ <<ኤልሳዕም ወደ እግዚአብሔር ጸልዮ የሞተውን ሕፃን

www.zeyeneta.com

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዳስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

ስለ ባሕረ ሓሳብ ዐጭር መግለጫ፡

ባሕረ ሓሳብ ማለት ቍጥር ያለው ዘመን ወይም የዘመን መቍጠሪያ ማለት ሲሆን፡ ዘመንን በባሕር መስሎም ሓሳበ ባሕር ይላል።

ሰፊ ባሕር ተቀድቶ እንደማያልቅ ሁሉ የዘመን መጨረሻም በፈጣሪው በእግዚአብሔር ካልሆነ በስተቀር በፍጡር ተቍጥሮ አይታወቅም፣ አያልቅምምና በባሕር ይመሰላል ሁለቱም ይመሳሰላሉ ማለት ነው።

ስለሁለቱ ሲገልጽም፡ <<በመዳልው ደለወ ዓለመ ወበመሥፈርት ሠፈራ ለባሕር>> ይላል፣ ዓለምን በሚዛን መዘነ፣ ባሕርንም በመሥፈርት ሠፈራት፣ በመቍጠሪያ ቍጠራት ለማለት ነው።

ሓሳብን ቍጥር ሲልም <<ኢትትሓሰብዎሙ ወርቆሙ ወብሩሮሙ>> ይላል፣ ገንዘባቸውን አትቍጠሩባቸው ማለት ነው።

<<ካሽሙርህ ጋራ ገንዘብህን በተቍጣጠርህ ጊዜ አትፈር>> ሲራ 42፡3

<<ሰነፍ ሰው ዝም ቢል እንደጠቢብ (እንደ ዓዋቂ) ይቍጠራል>> ምሳሌ 17፡28

<<ወለጽድቅከኒ አልቦቱ ሓሳብ>> ለጽድቅህ ሥፍር ቍጥር የለውም።

<<ብፁዓን እለ ተጎድጎ ሎሙ ኃጢኣቶሙ ወእለ ኢሓሰበ ሎሙ ኵሉ ጌጋዮሙ>>

ኃጢኣቱ የተከደነችለት፣ እግዚአብሔር በደሉን የማይቍጥርበት፣ በመንፈሱም ሽንገላ የሌለበት ሰው ሁሉ ምስጉን ነው ይላል ተራ አማርኛው።

ሲብራራም፡ ኃጢኣታቸው ያልተቍጠረባቸው፣ ማለትም በደላቸው በንስሓ፣ በጥምቀት የተሰረየላቸው ሁሉ ንፁዳን ክቡራን (የተመሰገኑ) ናቸው ማለት ነው። መዝ 31፡1

<<ወሶበ አጎዘ ተህስቦቶሙ አምጽኡ ሎቱ አሐደ ዘይፈድዮ እልፈ መክሊተ>> መጥቶ ሊቍጣጠራቸው በጀመረ ጊዜ የእልፍ ወቄት ባለ ዕዳን አመጡለት ይላል የማቴዎስ ወንጌል 18፡24

ይህ ጌታችን መንግሥተ ሰማያትን በምሳሌ አድርጎ ያስተማረበትን ምሥጢር ያመጣል። ሮሜ 4፡7። 8፡1 ይመልከቱ።

በእግዚአብሔር ኃይል አሥነሣው፡ የቅዳሳን ዓፅምም በረከትና ረድኤት አለው፣ ተአምራትንም ያደርጋል>> 2ኛ ነገ 4፡32, 13፡20, የሐዋ ሥራ 7፡15።

8ኛ <<ከመረጥሁት ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ.....በእውነቴ አልበድልም፣ ኪዳኔንም አላረክስም፣ ከከንፈሬ የወጣውንም አልለውጥም>> መዝ 88፡3, 33

እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፣ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል፣ ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል፣ ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል፡ ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውሃ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋም። የማቴዎስ ወንጌል 10፡41

እነዚህ ጥቅሶች የእግዚአብሔርን እንግዶች ብንቀበል፣ ልክ በአብርሃም ቤት እንደሆነው እግዚአብሔር እምላካችን እንግዳ መስሎ በቤታችን ውስጥ በመገኘት ማዕዳችንን ሊባርክልን እንደሚችል፣ እንዲሁም እንግዳውን መቀበል እርሱን መቀበል ማለት እንደሆነ፣ እርሱን መቀበል ማለትም የላከውን የባሕርይ አባቱ እግዚአብሔር አብን መቀበል ማለት እንደሆነ፡ በእግዚአብሔር፣ በእመቤታችን፣ በቅዳሳን መላእክት፣ በጻድቃንና በሰማዕታት ስም የሚመጻውት ሁሉ ትልቅ ዋጋን እንደሚያገኝ፣ እግዚአብሔር ከወዳጆቹ ጋር ቃለ ኪዳንን (ቃል ኪዳንን) እንደሚያደርግ፣ አንድ ጊዜ የተካሔደው (የተማማለው) ቃለ ኪዳንም (ቃል ኪዳንም) ለዘለዓለም የጸና እንደሆነ፡ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፣ የመላእክት፣ የቅዳሳን፣ የጻድቃንና የሰማዕታት ጸሎትና አማላጅነትም ምን ዓይነት ኃይል፣ በረከትና ረድኤት እንዳለውና እንዴት እንደሚጠቅም፡ ዓፅማቸውም ተአምራትን እንደሚያደርግ የሚያረጋግጡልን ናቸው።

እነሣስቶ ላስጀመረን፣ አስጀምሮም፣ ላስፈጸመን ለልዑል እግዚአብሔር አምላካችን ምስጋና ይድረሰው።

አሜን።

ዋና አዘጋጁ መምህር ሰሎሞን ገብሩ።

www.zeyeneta.com

አስማተኞች ያቃጠሉት የመጽሐፋቸው ዋጋው ቢታሰብ ኃምሳ ሺህ ሆነ ይላል የሐዋ ሥራ 19፥19። ቢታሰብ ማለት ቢቍጠር ማለት ነው።

ይህ ባሕረ ሓሳብ የተባለ የመላ ዘመን፣ የአጽዋማት፣ የበዐላት፣ የመዓልትና የሌሊት መቍጠሪያ (መሥፈሪያ) እነዚህን የተጠቀሱት ሁሉ ቍልጭ አድርጎ ስለሚያሳይ በመስተዋትና በመነፅር የሚመሰል ከዩልዮስ (ዩልያኖስ) በእስክንድርያ ግብፅ የቅዱስ ማርቆስ ሰባኛ ሊቀ ጳጳሳት ሞት በኋላ በቅዱስ ማርቆስ መንፈሳዊ መዓርግና ከሀገረ ወንበር ላይ 12ኛ የእስክንድርያ (የግብፅ) ሊቀ ጳጳሳት በመሆን ያገለገለ ቅዱስ ድሜጥሮስ ፈጣሪው እግዚአብሔር በገለጸለት መሠረት የደረሰው ሲሆን የዘመናት ቍጥር፣ የአጽዋማትና የበዐላት ዕለት በዚህ ነው የሚገኘውና ቍልፉ ብሉም የሚታየው።

ይህ ታሪክ ሰፊ ስለሆነ በሌላ ጊዜ እንድንመለስበት ሆኖ ከዚሁ ይቀጥንና አሁን ስለ እበቅቴና መጥቅዕ በዐጭሩ እንገልጻለን።

መጥቅዕ፦ ማለት ደወል ማለት ሲሆን ደወል ሲደወል ሁሉ ለመንፈሳዊም ሆነ ለልዩ ልዩ ሥራ እንደሚሰበሰብ አጽዋማትና በዐላትም በደወል በሚመሰል በመጥቅዕ ይገኛሉና መጥቅዕ ደወል ይባላል፣ በደወል ይመሰላል ማለት ነው።

መሠረታዊ አመጣጡና መነሻውም ቅዱስ ዲሜጥሮስ በሌሊት 23፣ በቀን 7 ሱባኤ ገብቶ ካገኘው ምሥጢር ሲሆን መቍጠሪያው 7 ዓዕዋዳት ናቸው። (ሱባኤ ማለት ሰባት፣ ሰባተኛ ማለት ነው)

ሰባት ዓዕዋዳትም ዓውደ ዕለት፣ ዓውደ ወርኀ፣ ዓውደ ዓመት፣ ዓውደ አበቅቴ፣ ዓውደ ማኑተም፣ ዓውደ ቀመር፣ ዓውደ ፀሐይ ይባላሉ።

መጥቅዕ፦ ከዕለታት፣ ከበዐላትና ከአጽዋማት ተውሳክ ጋር በመሆን እነዚህ የሚውሉበትን ቀን በትክክል ያስገኛል፣ ዕለታቸውን ያረጋግጣል።

ቍጥሩ ከ15 በላይ የሆነ መጥቅዕ በመስከረም ሲወድቅ፦ ከ2 ጀምሮ እስከ 15 ድረስ ያለው ግን እስከ ጥቅምት ይቀጥላል።

አንድ አንድ ጊዜ መጥቅዕ ይበዛል፣ አበትቴ ያንሳል፣ አንድ አንድ ጊዜም አበቅቴ ይበዛል መጥቅዕ ያንሳል ነገር ግን ሁሉ ጊዜ ሁለቱም ተደምረው 30 ብቻ ይሆናሉ እንጂ ከ30 አይጨምሩም፣ ከ30ም አይቀንሱም።

የዕለታት ተውሳክ በቅዳሜ ይጀምራል፦

ይኸውም፦ የቅዳሜ ተውሳክ 8 ሲሆን የእሑድ 7፣ የሰኞ 6፣ የማክሠኞ 5፣ የረቡዕ 4፣ የሐሙስ 3፣ የዓርብ 2 ነው።

የበዐላትና የአጽዋማት ተውሳክ ደግሞ በዐቢይ ጾም ይጀምራል። ምክንያቱም የነሢዩ ተውሳክ መባቻ ሐመር ስለሆነ ነው።

ስለዚህም የዐቢይ ጾም ተውሳክ 14፣ የደብረ ዘይት 11፣ የሆሳዕና 2፣ የስቅለት 7፣ የትንሣኤ 9፣ የርክበ ካህናት 3፣ የዕርገት 18፣ የጰራቅሊጦስ (የበዐለ መንፈስ ቅዱስ) 28፣ የጾመ ሰኔ (የሐዋርያት ጾም) 29፣ የኃጢኣት ድኅነት 1 ነው።

መጥቅዕ፦ ከእነዚህ ተውሳካት ጋር በመሆን ነው በዐላትንና አጽዋማትን የሚያስገኘው።

ይህ በዚሁ ይቆየንና ቀጥለን ደግሞ ስለ አበቅቴ ትንሽ እናብራራለን።

አበቅቴ፦ ማለት ሥፍር፣ ቍጥር ማለት ሲሆን ከሠርቀ መዓልትና ከሕፀፅ ጋር በመሆን የሌሊትን (የጨረቃን) አቍጣጠር ያስገኛል።

የዚህ መሠረትም እንደ መጥቅዕ ከቅዱስ ዲሜጥሮስ ሱባኤ ነው። የዓመቱ ሕፀፅ ሁሉ ጊዜ 6 ሲሆን 1 ሕፀፅ ለ2 ወር ይሆናል ማለት ነው ሠርቀ ፀሐይና ሠርቀ ወርኀ ደግሞ በሮብ ይጀምራል።

ሠርቅ ሠረቀ ብሎ ወጣ ተወለደ ማለት ሲሆን ሠርቅ ስንል ጥንታዊነቱ፣ መጀመሪያው፣ መሠረቱ ወይም መነሻው ማለታችን ነው።

ስለዚህም ለምሳሌ ያህል ዛሬ መዓልቱና ሌሊቱ ስንት እንደሆነ ለማወቅ ቀኑ እንዳለ የሚነገር ሲሆን ሌሊት ግን ከዕለቱ ከቀኑና ከሕፀፅ ጋር ተደምሮ የተገኘው ቍጥር ሠርቀ ሌሊት ይባላል።

መደበኛ ምሳሌ፦

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

ሃሌ ሉያ በዘንዘክር ሓሳባተ ሕጉ ወዓመታቲሁ ወአዝማናቲሁ ወትእዛዛቲሁ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዘ ሀሎነ በዘመነ ቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ ያብፅሐነ እስከ ዘመነ ቅዱስ ሉቃስ ዜናዊ በሰላመ እግዚአብሔር አሜን።

<<ሰብኣ ምዕት ወአርባዕቱ ምዕት ተሥኣ ወሰመንቱ ዘነ ዓመተ ዓለም>>

(እንደቤተ ክርስቲያናችን አቍጣጠር ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ 7498 ዘመን ብቻ ነው ማለት ነው)

<<ኃምሳ ምዕት ወኃምስቱ ምዕት ዘነ ዓመተ ፍዳ ወኩነኔ>>

www.zeyeneta.com

(ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረው 5500 ዘመን ሁሉ የፍጻ፣ የከኅኔ፣ የጨለማና የችግር ዘመን ነው ማለት ነው)

(አሠርቱ ምዕት ወተሥዓቱ ምዕት ተሥዓ ወተሥዓቱ ክነ ዓመተ ሥጋዌ ወዓመተ ምሕረት)

ከክርስቶስ ልደት ወዲህ ያለው 1998 ዘመን ግን ጌታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በመስቀል ተሰቅሎ ስለ አዳነን የሥጋዊ ወይም የሰው መሆኑ፣ የምሕረትና የይቅርታ ዘመን ይባላል ማለት ነው።

ዮም ሠረቀ ለነ ወርኀ ቡሩክ ሰኔ በዕለተ ሐሙስ ያብፅሐነ እግዚአብሔር እስከ ወርኀ ቡሩክ ሐምሌ ዘይሠርቅ በዕለተ ቀዳሚት በሰላም ወበዳኅና፤ ኃምሱ ሠርቀ መዓልት፣ አሥሩ ወአሚሩ ሠርቀ ሌሊት፣ ሰዱሱ ሠርቀ (ጥንተ ፀሐይ ወወርኀ) ሰኑዩ ጥንተ ዕለት።

የዚህ ዐጭር ትርጉም፦ የጌታችንን አዝማናትንና ጊዜያትን ከዘመነቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ ሆነን ስናስታውሰው ወደ ቅዱስ ሉቃስ ዘመን እንዲያደርሰን እየጸለይን ነው።

ዛሬ ቀኑ እንዳለ 5 ሲባል ሌሊቱ ደግሞ ከላይ ከፍ ብሎ እንደተገለጸው ከአበቅቴ፣ ከዕለቱና ከሕፀፅ ጋር ተደምሮ 11 ይሆናል ማለት ነው።

ሁሉንም ማድረግ የሚቻለው ፈጣሪያችን ልዑል እግዚአብሔር ልባዊ ትሕትናን፣ እውነተኛ ፍቅርን፣ ሰላሙንና አንድነቱን ይስጠን

አሜን።

1998 (2006)

Po.box 41435
Arlington, VA, 22204።

U.S